ግብርና ሚኒስቴር
MINISTRY OF AGRICULTURE

# የግብርና ዘርፍ የመካከለኛ ዘመን የተከለሰ ዕቅድ

# (2016 - 2018 ዓ.ም)

ታህሳስ 2016
አዲስ አበባ

ዜና ሀ/ወልድ
ስትራቴጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

# ማውጫ


I. መግቢያ ........................................................................................................ 1

II. የሦስት ዓመታት (2013-2015 ዓ.ም) የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ............................................ 2

**2.1. የሰብልና ሆርቲካልቸር ምርታማነት ማሻሻል** ................................................................ 2

**2.2. ገበያ ተኮር እንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት** ....................................................................... 8

**2.3. ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም** .................................................................. 12

**2.4. የግብርና ኢንቨስትመንትና ግብይት** ............................................................................ 19

**2.5. የግብርና ቁጥጥር** .................................................................................................. 31

**2.6. የግብርና ትራንስፎርሜሽን** ...................................................................................... 35

**2.7. ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች** .................................................................................................. 40

**2.8. የሶስት ዓመታት የፌደራል ፕሮግራም በጀት አጠቃቀም** ................................................... 49

**2.9. የዘርፉ መሰረታዊ ማነቆዎች** ..................................................................................... 52

III. የመካከለኛ ዘመን (2016-2018) የልማት ዕቅድ እንድምታዎች እና የሚጠበቁ ውጤቶች........53

IV. የመካከለኛ ዘመን (2016-2018) ስትራቴጅክ ዓላማዎች ቁልፍ የውጤት መስኮችና ....ዒላማዎች 53

**3.1. የሰብልና ሆርቲካልቸር ምርታማነት ማሻሻል** .................................................................57
**3.2. ገበያ ተኮር የእንስሳትና ዓሳ ምርታማነት ማሻሻል** ..........................................................66
**3.3. ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም** ..................................................................74
**3.4. የግብርና ኢንቨስትመንትና ግብይት** ............................................................................84
**3.5. የግብርና ቁጥጥር** ..................................................................................................107
**3.6. የግብርና ትራንስፎርሜሽን ማሳለጥ** ..........................................................................110
**3.7. ዘርፈብዙ ጉዳዮች** ..................................................................................................114
**3.8. ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት**..125

V. የግብርና ዘርፍ የመካከለኛ ዘመን ኢንቨስትመንት ...................................................... 126

VI. የአደጋ ስጋት ግምገማ እና ስጋቶችን ለመቀነስ የሚተገበሩ ስትራቴጂዎች........................ 127

VII. የክትትልና ግምገማ ስርዓት ....................................................................................... 127

VIII. የግብርና ሴክተር የሶስት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም (2013-2015 ዓ.ም)........................... 129

XI. የግብርና ሴክተር የሶስት ዓመት ዕቅድ (2016-2018 ዓ.ም)............................................ 144

## I. መግቢያ

ግብርና ሚኒስቴር የግብርና ዘርፍን የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ በማዘጋጀት የግብርናን አማካይ ሀገራዊ ምርት 6 በመቶ በማሳደግ እንደሀገር የተያዘውን "ኢትዮጵያ፤ የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት" የማድረግ ርዕይ ለማሳካት ከሀገራዊ የልማት ዕቅድ ጋር የተሳሰሩና ለኢኮኖሚያዊ መዋቅራዊ ሽግግር መሰረት ለሆኑት ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት መተካት፣ ለኢንዱስትሪዎች የግብርና ምርቶችን ለማቅረብ፣ ኤክስፖርትን ማስፋፋት፣ የምግብና ስርዓተ ምግብ ዋስትና ብሎም የምግብ ሉዓላዊነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ዓላማዎችን በመቅረፅ ከ2013 ጀምሮ ላለፉት ሶስት ዓመታት በርካታ ሥራዎችን በማከናወን አበረታች ውጤት አስመዝግቧል።

የግብርናን አማካይ ሀገራዊ ምርት በ10 ዓመቱ መሪ ዕቅድ መነሻ በ2012 በጀት ዓመት 4.3 በመቶ የነበረ ሲሆን ባለፉት 2 ዓመታት በ2013 እና በ2014 በጀት ዓመት 5.5 እና 6.1 በመቶ በቅደም ተከተል ማሳደግ የተቻለ ሲሆን በ2015 በጀት አመት 6.3 በመቶ እንደሚያድግ ተገምቷል። ለዚህ ዕድገት መመዝገብ የግብርና ምርትና ምርታማነት አጠቃላይ እድገት ማሳየቱ፣ በተመረጡ የእንስሳትና የሰብል ሀገራዊ ፕሮግራሞች በመቅረፅ ወደ ትግበራ በመገባቱ፣ የገበያ መር የግብርና ልማት አሰራርን አጠናክሮ ለመተግበር እንዲያገዝ በገበያ መር ኩታ ገጠር እርሻ ልማት ማስፋት በመቻሉ፣ የዘርፉን የመፈፀም አቅም የሚያሻሽሉ የሪፎርም ሥራዎች ማለትም የገጠር ልማት ፖሊሲዎች፣ የግብርና ግብዓት አቅርቦትን ስርዓት ለማሻሻል የማዳበሪያ ግዥና አቅርቦትን የግዥ ስርዓት ወደ ፎብ (FOB) በመቀየር ከአቅራቢው ወደብ እስከ ክልል ማዕከላዊ መጋዘን በኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት እንዲሰራ መደረጉ፣ ነባሩ አደረጃጀት ያሉበትን ክፍተቶች በመለየት አዲስ አደረጃጀት ተግባራዊ መደረጉ፣ የግብርና ሥራዎችን በቴክኖሎጅ ለመደገፍ የግብርና ዲጅታላይዜሽን ስራዎች እየተከናወኑ መሆኑ በማሳያነት የሚጠቀሱ ናቸው።

አጠቃላይ ሀገራዊ የስንዴ ምርትን ከፍ ለማድረግ ሀገራዊ የስንዴ ምርት ማሻሻል ፕሮግራም ተቀርፆ ወደ ተግባር መገባቱና አበረታች ውጤት ማስመዝገብ መቻሉ ወደ ሌላ ከውጪ የሚገቡ የግብርና ምርቶችን በሀገር ውስጥ መተካት የሚያስችሉ የቅባት እህሎች እና ሩዝ ምርት ማሻሻያ ስራ ማስፋት እንዲሁም የእንስሳት ምርቶችን (በተለይም ወተት እና የዶሮ ስጋ) ማስጀመር እንደሚቻል የሚያመላክት ውጤት ተመዝግቧል።

የግብርና ወጪ ንግድ አፈፃፀም ለማሻሻል ከግሉ ዘርፍ እና ከሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች ጋር በመቀናጀት ማነቆዎችን በመለየትና የመፍትሄ ሃሳቦችን በማቅረብ ስራዎች ተሰርተዋል። በዚህም ምክንያት ከግብርና የወጭ ምርት የሚገኝ ገቢ በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ መጥቷል።

ያለፉት ሶስት ዓመታት አፈፃፀም ውስጣዊና ውጫዊ ተግዳሮቶችን በመቋቋም በተተገበረው ልክ ዉጤት ያረጋገጠ፣ በርካታ ልምዶች የተገኙበትና በዚሁ ላይ በመመስረት ትራንስፎርሜሽን ለማረጋገጥ የሚያስችል ቀጣይ ሥራ መስራት እንደሚጠይቅ ግንዛቤ የተያዘበትም ነው። በመሆኑም ባለፉት ሶስት ዓመታት ትግበራ በተገኙ ውጤቶች ላይ በመመስረትና ከመጀመሪያ ዙር ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ፖሊሲ ማሻሻያን አፈፃፀም

ዜና ሀ/ወልድ
ስትራተጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

የተገኙ ልምዶችንና የሁለተኛ ዙር ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ፖሊሲ ማሻሻያ የትኩረት መስኮች መሰረት ያደረገ እንዲሁም የግብርና ዘርፍ ማሻሻያ (ሪፎርም) እርምጃዎች በማስቀጠል የግብርና ዘርፍ የሶስት ዓመት (2016-2018 ዓ.ም) የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ እንዲዘጋጅ ተደርጓል።

መሪ ዕቅዱም ቁልፍ የውጤት መስኮች፣ በየውጤት መስኮች በተመረጡ ቁልፍ አመልካቾች ዒላማዎችን በማስቀመጥ፣ ዒላማዎችን ለማሳካት ሊፈፀሙ የሚገባቸው ተግባራት፣ ለዕቅዱ ማስፈፀሚያ የሚያስፈልገውን የኢንቨስትመንት መጠን፣ የሰው ኃይል፣ የማስፈፀሚያ ስልቶችንና ከሌሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች የግብርና ዘርፍ የሚፈልጋቸው ግብዓቶችን በዝርዝር እንዲያካትት ተደርጎ ተዘጋጅቷል።

## II. የሦስት ዓመታት (2013-2015 ዓ.ም) የልማት ዕቅድ አፈጻጸም

### 2.1. የሰብልና ሆርቲካልቸር ምርታማነት ማሻሻል

#### 2.1.1. ሰብል ልማት

**ሀ) በአነስተኛ አርሶ አደር የእህል ሰብል በመኸር**

ከ2013 - 2015 በነበሩት የመካከለኛ እቅድ ዘመን የመኸር ምርት የአነስተኛ ይዞታ እርሻ በ2012 ከነበረበት በመሬት ከ13,049.07 ሺህ ሄ/ር ወደ 13,390.95 ሺህ ሄ/ር፣ በምርት ከ339,073.48 ሺህ ኩ/ል ወደ 393,868.4 ሺህ ኩ/ል ለማሳደግ ታቅዶ በሶስት ዓመቱ መጨረሻ ዓመት መሬት 14,034.42 ሺህ ሄ/ር በማረስ ምርት ደግሞ 393,298.93 ሺህ ኩ/ል ማምረት ተችሏል። አፈፃፀሙም በመሬት 2.62 በመቶ እና በምርት 16 በመቶ ማሳደግ ተችሏል። የተቀመጠውን ሀገራዊ ግብ ለማሳካት በየደረጃው ተግባር ተኮር ስልጠናዎች፣ጠንካራ የድጋፍና ክትትልና ግብረ-መልስ በመዘርጋት ክልሎችን የመደገፍ ተግባራት የተከናወኑ ሲሆን ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆነ የሰብል ልማት ስርዓቶችን (ፈረቃ፣ በተለያየ ኮምፖስት በማዘጋጀትና በመጠቀም፣ ጥብቅ የሰብል ልማት ወዘተ) በማስተዋወቅና እንዲተገበሩ ድጋፍ ተደርጓል።

**ለ) የበልግ ወቅት**

በበልግ በ2012 ሰብሎች 169.29 ሺህ ሄ/ር በማልማት እና 24,465.20 ሺህ ኩ/ል ምርት ከነበረበት በ2015 2700.75 ሺህ ሄ/ር እና 48,052 ሺህ ኩ/ል ምርት መድረስ ተችሏል። በበልግ በ2012 ብዕርና አገዳ 52.29 ሺህ ሄ/ር በማልማት እና 9,250 ሺህ ኩ/ል ምርት ከነበረበት በ2015 በጀት ዓመት 2,137.86 ሺህ ሄ/ር በማልማት እና 40,812 ሺህ ኩ/ል ምርት መድረስ ተችሏል። በበልግ በ2012 በጀት ዓመት የቅባት እህሎች 117.04 ሺህ ሄ/ር በማልማት እና 15,215.20 ሺህ ኩ/ል ምርት ከነበረበት በ2015 በጀት ዓመት 63.12 ሺህ ሄ/ር እና 435 ሺህ ኩ/ል ምርት መድረስ ተችሏል።

**ሐ) በመስኖ የለማ መሬት**

በመስኖ በ2012 የበጋ ስንዴ 160.60 ሺህ ሄ/ር በማልማት እና 6.56 ሺህ ኩ/ል ምርት ከነበረበት በ2015 ወደ 1,374 ሺህ ሄ/ር እና 52,130 ሺህ ኩ/ል ማሳደግ ተችሏል።

### መ) በሰፋፊ እርሻ በመኸር የእህል ምርት

በ2012 በጀት ዓመት በሰፋፊ እርሻ በመኸር ሰብሎች 169.29 ሺ.ህ ሄ/ር በማልማት እና 24,465.20 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት ከነበረበት በ2015 በጀት ዓመት 774.53 ሺ.ህ ሄ/ር እና 21,583.65 ሺ.ህ ኩ/ል ም.ርት መድረስ ተችሏል። በ2012 በጀት ዓመት ብርዕና አገዳ 52.29 ሺ.ህ ሄ/ር በማልማት እና 9,250 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት ከነበረበት በ2015 በጀት ዓመት 291.90 ሺ.ህ ሄ/ር በማልማት እና 11,715.57 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት መድረስ ተችሏል። በ2012 በጀት ዓመት የቅባት እህሎች 117.04 ሺ.ህ ሄ/ር በማልማት እና 15,215.20 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት ከነበረበት በ2015 በጀት ዓመት 482.63 ሺ.ህ ሄ/ር እና 9,868.08 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት መድረስ ተችሏል።

## 2.1.2. የጥጥ ልማት

ባለፉት ሶስት ዓመታት ለጥጥ ልማት ከተቀመጡ ግቦች አንዱ በአነስተኛ አርሶ አደር መኸር በጥጥ ሰብል የሚሸፈነውን መሬት በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 13.9 ሺ.ህ ሄ/ር በ2015 ምርት ዘመን ወደ 39.8 ሺ.ህ ሄ/ር ለማድረስ ታቅዶ 24.85 ሺ.ህ ሄ/ር (61.9%) መሬት በጥጥ ተሸፍኗል። ለአፈጻጸሙ መቀነስ ለጥጥ ኢንቨስትመንት የተላለፉ ሰፋፊ መሬቶች በተለያዩ ምክንያቶች አለመልማታቸው፣ የግብዓት አቅርቦት ውስንነት፣ በወሳኝ የእርሻ ወቅት የጉልበት ሰራተኛ አቅርቦት እጥረት፣ ግልፅ ቀልጣፋና ተደራሽ የሆነ የተዳመጠ እና የጥሬ ጥጥ ግብይት ስርዓት አለመዘርጋቱ፣ አዳዲስ በጥጥ ኢንቨስትመንት መስክ ለመሰማራት ያለው ፍላጎት ዝቅተኛ መሆን፣ የአየር ንብረት ለውጥ ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸው።

በጥጥ ልማት ዘርፍ የተፈጠረ አጠቃላይ የሥራ ዕድል በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 50 ሺ.ህ ወደ 1,323 ሺ.ህ ለማድረስ ታቅዶ ለ137 ሺ.ህ (10.6%) ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል። ለዚህም ከላይ በመሬት ሽፋን ዕቅድ አፈፃጸም ግምገማ ዝቅተኛ መሆን በተጠቀሱ ምክንያቶች የጥጥ ልማት ዘርፍ በታቀደው ልክ የሰው ሃይል መቅጠር ባለመቻሉ ለአፈጻፀም ዝቅተኛ ለመሆን አስተዋፅኦ አድርጓል። በተጨማሪም ላለፉት ዓመታት በነበረው የፀጥታ ችግር ሰራተኞች በነፃነት ተንቀሳቅሰው ለመስራት ከፍተኛ ስጋት ስለነበረ በዘርፉ የስራ ዕድል ፈጠራ ላይ ከፍተኛ ተግዳሮት ሆኖ ቆይቷል።

## 2.1.3. የሆርቲካልቸር ምርትና ምርታማነት ማሳደግ

### ሀ) የመኸር ወቅት

በመኸር በ2012 በጀት ዓመት በአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ሰብሎች 427 ሺ.ህ ሄ/ር በማልማት እና 90,790 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት ከነበረበት በ2015 በጀት ዓመት 702.95 ሺ.ህ ሄ/ር በማልማት እና 230,226.92 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት መድረስ ተችሏል። በመኸር በ2012 በጀት ዓመት በአትክልት ሰብሎች 127 ሺ.ህ ሄ/ር በማልማት እና 15,064 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት ከነበረበት በ2015 በጀት ዓመት 143.76 ሺ.ህ ሄ/ር እና 23,524.72 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት መድረስ ተችሏል። በመኸር በ2012 በጀት ዓመት ፍራፍሬ ሰብሎች 119 ሺ.ህ ሄ/ር በማልማት እና 434,374 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት ከነበረበት በ2015 በጀት ዓመት 272 ሺ.ህ ሄ/ር እና 32,463 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት መድረስ ተችሏል። በመኸር በ2012 በጀት ዓመት ስራስር ሰብሎች 181 ሺ.ህ

ሄ/ር በማልማት እና 41,348 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት ከነበረበት በ2015 ዓ.ም 287.19 ሺ.ህ ሄ/ር እና 174,239.20 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት መድረስ ተችሏል።

### ለ) የበልግ ወቅት

በበልግ በ2012 በጀት ዓመት በሆርቲካልቸር ሰብሎች 169.29 ሺ.ህ ሄ/ር በማልማት እና 24,465.20 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት ከነበረበት በ2015 ዓ.ም 405.63 ሺ.ህ ሄ/ር እና 54,398.70 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት መድረስ ተችሏል። በበልግ በ2012 በጀት ዓመት በአትክልት ሰብሎች 52.29 ሺ.ህ ሄ/ር በማልማት እና 9,250 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት ከነበረበት በ2015 ዓ.ም 119.69 ሺ.ህ ሄ/ር እና 10,078 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት መድረስ ተችሏል። በበልግ በ2012 በጀት ዓመት በሥራስር ሰብሎች 117.04 ሺ.ህ ሄ/ር  እና 15215.20 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት ከነበረበት በ2015 ዓ.ም 285.94 ሺ.ህ ሄ/ር እና 44320.70 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት መድረስ ተችሏል።

### ሐ) በመስኖ የለማ መሬት

በመስኖ በ2012 በጀጥ ዓመት የሆርቲካልቸር ሰብሎች 404.62 ሺ.ህ ሄ/ር በማልማት እና 68,888.99 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት ከነበረበት በ2015 ዓ.ም ወደ 503.65 ሺ.ህ ሄ/ር እና 92,634.31 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት መድረስ ተችሏል። በመስኖ በ2012 በጀት ዓመት በአትክልት ሰብሎች 276.14 ሺ.ህ ሄ/ር በማልማት እና 45,483.44 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት ከነበረበት ወደ 250.71 ሺ.ህ ሄ/ር እና 43,983.77 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት መድረስ ተችሏል። በመስኖ በ2012 በጀት ዓመት በስራስር ሰብሎች 117 ሺ.ህ ሄ/ር በማልማት እና 22,544.88 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት ከነበረበት ወደ 86.04 ሺ.ህ ሄ/ር እና 21,511.40 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት መድረስ ተችሏል። በመስኖ በ2012 በጀት ዓመት የፍራፍሬ ሰብሎች 11.4 ሺ.ህ ሄ/ር በማልማት እና 860.67 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት ከነበረበት ወደ 166.9 ሺ.ህ ሄ/ር እና 27,139.14 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት መድረስ ተችሏል።

### መ) በሰፋፊ እርሻ የለማ አበባ፣ አትክልት፣ እጸ-ጣዕም እና ፍራፍሬ ሰብሎች

አበባ ልማትን በተመለከተ በ2012 የነበረዉ መነሻ 3.20 ሺ.ህ ሄ/ር በ2015 ዓ.ም መጨረሻ 2.50 ሺ.ህ ሄ/ር ሲሆን በምርት ረገድም በ2012 ዓ.ም ከነበረዉ መነሻ 113.53 ሺ.ህ ቶን የተመረተ ሲሆን፣ በ2015 ዓ.ም ደግሞ 112.99 ሺ.ህ ቶን ማምረት ተችሏል።

የአትክልትና እፀ-ጣእም የለማ መሬት የ2012 ዓ.ም ወደ 424.09 ሺ.ህ ሄር የለማ ሲሆን በ2015 ዓ.ም ወደ 469 ሺ.ህ ሄ/ር መሬት ማልማት ተችሏል። ያለፉት ሶስት አመታት አፈፃፀም ስንመለከት ወደ 1,246 ሺ.ህ ሄ/ር በአትክልት እፀ-ጣእም ሰብሎች የለማ ሲሆን ይህዉም የእቅዱን 91 በመቶ ማሳካት ተችሏል።

የፍራፍሬ ልማትን ስንመለከት ይህ ሪፖርት እስከተዘጋጀበት ድረስ ያለፉትን ሶስት ዓመታት (የአስር አመቱ) እቅድ ላይ የሚለማ መሬት ባለመታቀዱ ምክንያት ሪፖርቱ በመሬት ሽፋን መግለፅ አልተቻለም። ሆኖም የ2015 ዓ.ም ወደ 6.024 ሺ.ህ ሄ/ር መሬት በባለሃብቶች የፍራፍሬ ልማት (ስትሮዉቤሪ፣ አቮካዶ እና ሙዝ) ማልማት እንደተቻለ መረጃዎች ያሳያሉ።

2.1.4. ቡና ሻይና ቅመማ ቅመም

**የቡና ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ**

በ2012 በጀት ዓመት የቡና ምርት ከነበረበት 559,933 ቶን ወደ 761,478 ቶን ለማድረስ እንዲሁም ምርት የሚሰጥ መሬት ከነበረበት 861.43 ሺህ ሄ/ር ወደ 1,062 ሺህ ሄ/ር ለማሳደግ እና ምርታማነትን ከ6.38 ኩ/ል ወደ 7.6 ኩ/ል በሄክታር ለማድረስ የታቀደ ሲሆን ምርት የሚሰጥ መሬት 1,062.03 ሺህ ሄር (100%)፣ ምርት 7,615 ሺህ ኩ/ል (94%) እንዲሁም ምርታማነት 7.17 ኩ/ል/ በሄ/ር (94.3%) ተገኝቷል፡፡ አፈጻጸሙ ከ2012 በጀት ዓመት ዕቅድ ጋር ሲነጻጸር የ201,545 ቶን የምርት ጭማሪ ያሳያል፡፡

**የሻይ ምርትና ምርታማነት ማሳደግ**

በሻይ ልማቱ በአልሚ ባለሃብትና በአውት ግሮወርስ በሚታቀፉ የሻይ አልሚ አርሶ አደሮች የመሬት ሽፋን በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 3,196 ሄ/ር በ2015 ወደ 3,340 ሄ/ር፣ ምርታማነት ከ35.6 ኩ/ል/ሄ/ር ወደ 36.1 ኩ/ል/ሄ/ር እና ምርት ከ11,154 ቶን ወደ 9,280 ቶን መፈፀም ተችሏል፡፡

**የቅመማ ቅመም ምርትና ምርታማነት ማሳደግ**

**የቅመማ ቅመም ልማት፡-** ጠቅላላ ቅመማ ቅመም በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 388.15 ሺህ ሄ/ር በ2015 ወደ 443.86 ሺህ ሄ/ር ምርት ማድረስ ምርት 634.74 ሺህ ቶን በ2015 ወደ 7,900 ሺህ ኩ/ል ማድረስ ተችሏል፡፡ በዕቅድ ዘመኑ የቅመማ ቅመም ምርት ከዕቅድ አፈጻጸም አንጻር ጭማሪ እንደተመዘገበ የሚያሳይ ሲሆን ዝርዝር የቅመማ ቅመም አይነቶችን በተለይም በተመረጡት ስድስት ዋና ዋና ቅመማ ቅመም ሰብሎች ማለትም በርበሬ፤ አዝሙድ፤ ዝንጅብል፤ ኮረሪማ ፤ እርድ እና አብሽ ያካትታል፡፡

**የቡና ሻይና ቅ/ቅመም የወጪ ንግድ በመጠንና በገቢ ማሳደግ**

**ቡና**

የቡና ኤክስፖርት መጠን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 270,840 ቶን በ2015 በጀት ዓመት ወደ 240.37 ሺህ ቶን የተፈፀመ ሲሆን በገቢ ደግሞ በ2012 ከነበረበት 855.84 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ወደ 1,331 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር መፈፀም ተችሏል፡፡

**ሻይ**

የሻይ ኤክስፖርት መጠን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 1,770 ቶን በ2015 በጀት ዓመት ወደ 0.90 ሺህ ቶን የተደረሰበትና በገቢ በ2012 ከነበረበት 2.65 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ወደ 2.02 ሚ/ን. የአሜሪካን ዶላር መፈፀም ተችሏል፡፡

**ቅመማ ቅመም**

የቅመማ ቅመም ኤክስፖርት መጠን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 11.9 ሺህ ቶን በ2015 በጀት ዓመት 6.32 ሺህ ቶን ወደ ውጪ በመላክ እና በገቢ በ2012 ከነበረበት 16.02 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ወደ 10.48 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ማግኘት ተችሏል።

## 2.1.5. የእርሻና ሆርቲካልቸር ኤክስቴንሽን

### ሀ) የኤክስቴንሽን ተጠቃሚ ቁጥርን ማሳደግ

በሦስት ዓመታት 12.77 ሚ/ን የኤክስቴንሽን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 12.19 ሚ/ን (95%) ለማድረስ ተችሏል። የኤክስቴንሽን ተጠቃሚ ቁጥር ከ9.36 ሚ/ን ወደ 12.19 ማድረስ ተችሏል። የተሰበሰበው መረጃ እንደሚያሳየው የአርብቶና ከፊል አርብቶ አደር ኤክስቴንሽን ተጠቃሚ ቁጥር ዝቅተኛ ሲሆን በአንጻራዊነት የአርሶ አደር የኤክስቴንሽን ተጠቃሚ ቁጥር የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል።

### ለ) የሙሉ ፓኬጅ ተጠቃሚ

ባለፈው ሦስት ዓመታት 8.61 ሚ/ን የሙሉ ፓኬጅ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 5.84 (67.9%) ማድረስ ተችሏል። በዚህም ሂደት መገንዘብ የተቻለው የፌደራልም ይሁን የክልል የፓኬጅ ጥንቅርን ማለትም ከመሬት ዝግጅት ጀምሮ እስከ ድህረ ምርት አያያዝ አልፎም እስከ ገበያ ያለውን ወስዶ ተግባራዊ ማድረግ ቀላሉና ተገቢው መንገድ ሲሆን በክልሎችና በአንዳንድ ባለድርሻ አካላት በኩል ያለው አረዳድ ግን ከምክረ-ሀሳቡ መካከል ቢያንስ ሶስቱን ማለትም ምርጥ ዘር መጠቀም፣ በመስመር መዝራት፣ ማዳበሪያን መጨመር የመሳሰሉትን ካሟላ በሚል ተገቢ ያልሆነ አረዳድና ምክረ ሀሳብ የተጠቃሚውን ሕብረተሰብ አረዳድ የተዛነፈ እንዲሆን አድርጎታል።

### ሐ) ሞዴል አ/አ/አደር

ሞዴል አ/አ/አደር ከመፍጠር አንጻር በ2012 ዓ.ም (መነሻ) ከነበረበት 2.37 ሚ/ን ቁጥር በ2015 ዓ.ም ወደ 3.69 ማድረስ ተችሏል። ባለፉት ሦስት አመታት 3.83 ሚ/ን ሞዴል አ/አ/አደር ለመፍጠር ታቅዶ 3.69 ሚ/ን (96.3%) ለማድረስ ተችሏል።

### መ) የግብርና ልማት አካላት ግንኙነት አማካሪ ካውንስል

የባለድርሻ አካላት መካከል የተቀናጀ አሰራር ለማስፈን በ12 የክልል ፌደራልን ጨምሮ የምክክር መድረኮችን ለማጠናከር ታቅዶ 10 (83%) ሲከናወን፣ የዞን መድረኮችን በተመለከተ 68 ለማቋቋምና ለማጠናከር ታቅዶ 58 (85%) ተከናውኗል፣ የወረዳ አማካሪ ካውንስል 713 ለማቋቋምና ለማጠናከር ታቅዶ 516 (72%) ተከናውኗል። የልማት አካላት ያላቋቋሙ አዳዲሶቹ 2 ክልሎች ማለትም ሲዳማ እና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ናቸው። በቀጣይ ለማቋቋም በዝግጅት ላይ ናቸው። ይህንንም ጥናት ታሳቢ በማድረግ የልማት አካላት አማካሪ ካውንስል መመሪያ ተከልሶ ታትሟል።

### ሠ) የብዙ ተዋናዮች (Pluralistic) የኤክስቴንሽን የምክር አገልግሎት

አሁን በሥራ ላይ ያለውን የግብርና ኤክስቴሽን አገልግሎት ያለበትን የአቅም እና የአፈጻጸም ውስንነት ለመቅረፍ እና ብቃትን ለማሳደግ፣ ባልተቀናጀ እና ባልተመዘገበ ሁኔታ በተለያዩ ተዋንያን እየተሰጠ ያለውን የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት አቀናጅቶ ለመምራት፣ ደረጃውን የጠበቀ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ፣ ተወዳዳሪ እና ተጠያቂነትን ያሰፈነ የብዙ ተዋንያን የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት ለመዘርጋት በማስፈለጉ የብዙ ተዋናዮች (Pluralistic) የኤክስቴንሽን የምክር አገልግሎት አሰጣጥ የሚመለከት ረቂቅ አዋጅ እና ደንብ ተዘጋጅቷል። በተዘጋጀው አዋጅ ላይ በፌደራል እና በክልል ደረጃ ለሚመለከታቸው አካለት በማቅረብ ግብረ መልስ ለማሰባሰብ ተችሏል።

### ረ) የዲጂታል ኤክስቴንሽን አገልግሎት

በዲጂታል ኤክስቴንሽን የምክር አገልግሎት በ2015 በጀት ዓመት የባለድርሻ አካላትን ቅንጅትና መናበብ ሊያጠናክር የሚችል አንድ የምክክር መድረክ በግብርና ልማት አካላት አማካሪ ካውንስል የምክክር መድረክ ሥር ለማቋቋም፣ አንድ ፍኖተ ካርታ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተዘጋጅቷል። በተጨማሪም በዲጅታል ኮሙዩኒኬሽን ለ350 ክልል፣ ለዞን እና ለወረዳ ባለሙያዎች ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ205 (58.6%) ሲሆን የ60,000 ቀበሌ ግብርና ባለሙያዎችን መረጃ ዲጂታላይዝ ለማድረግ ታቅዶ 43,000 (71.6%) ተሰብስቧል።

### 2.1.6. የእፀዋት ጥበቃ

በ2013 በጀት ዓመት የነበረው ምቹ የአየር ሁኔታ እየቀነሰ በመምጣቱ በሀገር ውስጥና በአጎራባች ሀገሮች የነበረው የአንበጣ መንጋ እየቀነሰና በመጨረሻም በመጥፋቱ ምክንያት የአሰሳና መከላከል ስራው ወደ 250 ወረዳዎች ቀንሷል። የመደበኛ ተባይ አሰሳና መከላከል በ2012 ከነበረበት በ193 ወረዳ የአሰሳ ስራ የተከናወነ ሲሆን ከ2013 በጀት ዓመት፣ በ2014 በጀት ዓመትና በ2015 በጀት ዓመት በ183 ፣ በ312 እና በ358 ወረዳዎች በቅደም ተከተል የአሰሳና መከላከል ስራ ተከናውኗል። የግሪሳ ወፍ አሰሳና መከላከል በ2012 በጀት አመት ከነበረበት 23 ማደሪያ ቦታዎች ላይ 2,962 የማደሪያ ስፍራዎች ላይ 223 ሚ/ን የሚገመት የግሪሳ ወፍ መንጋ አሰሳና መከላከል ስራ ተሰርቷል። የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት መስፋፋት ጋር ተያይዞ በቂ ምግብ በመኖሩ ምቹ በሆኑ ቆላማ አካባቢዎች በስፋት በመራባቱና ከአጎራባች ሀገራት ወደ ኢትዮጵያ በመዛመቱ ምክንያት በየአመቱ የሚደረገው የመከላከል ስራ እንዲጨምር አድርጎታል።

በአጠቃላይ የተዛማች ወራሪ ተባዮች አሰሳና መካከል በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 445 ወረዳዎች የአሰሳና መከላከል ስራ በ2013 ከፍተኛ የበረሃ አንበጣ ወረርሽኝ ምክንያት የአሰሳና መካለከል ስራው 448 ወረዳዎች የደረሰ ሲሆን በ2014 እና 2015 በጀት ዓመት ለበረሃ አንበጣ መኖርና መራባት አየር ሁኔታ ምቹ ባለመሆኑ የበረሃ አንበጣ ክስተት በሀገራችንና በአጎራባች አገራት እየቀነሰ በመምጣቱ 420 እና 408 ወረዳዎች በቅደም ተከተል የአሰሳና መከላከል ስራ ተከናውኗል። የመደበኛና መጤ አረሞችን በ2012 ከነበረበት በ28 ወረዳዎች የአሰሳና መከላከል ስራ በሶስት አመት 191 ወረዳዎች ላይ የአሰሳና መከላከል ስራ ተከናውኗል።

በኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን የተደገፈ የመደበኛ ተምች ማህበረሰብ ተኮር ስራዎችን በዘላቂነት ለማስቀጠል 1,200 ፌርሞን ትራፕና 3,600 የፌርሞን ካፕሱል ለሁሉም ክልሎች በማሰራጨት ግንባር ቀደም በሆኑ ወረዳዎች (Frontline Districts) እንዲጠመዱ በማድረግና 515 ፌርሞንትራፕ ወጥመድ እና 2,620 ካፕሱል በማሰራጨትና የተሰበሰቡ መረጃዎችን በማሰባሰብና በመተንተን 14 ትንበያና ቅድመ ማስጠንቀቂያ ለክልሎች ተሰራጭቷል። ለተዛማች ወራሪ ተባዮች መከላከል የሚውል የፀረ-ተባይ ኬሚካል ከነበረበት 335,215 ሊትር በ2013 በጀት ዓመት እየጨመረ የመጣውን የበረሃ አንበጣ ክስትት (Upsurge) ለመከላከል 937,659 ሊትር ግዥ የተፈጸመ ቢሆንም ከ2014 ጀምሮ ክስተቱ እየቀነሰ በመምጣቱ የፀረ ተባይ ግዥ መጠን ቀንሷል። በ2015 በጀት አመት ለግሪሳ ወፍ መከላከል የሚውል 10,000 ሊትር የፀረ-ተባይ ኬሚካል ግዥ ተፈጽሟል።

## 2.2. ገበያ ተኮር እንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት

### 2.2.1. የእንስሳትና ዓሳ ምርትና ምርታማነት

#### የወተት ምርትና ምርታማነት

የአነስተኛ እንስሳት እርባታ በወተት ምርት በዳልጋ ከብት፣ ፍየል እና ግመል ልማት ላይ ትኩረት ተደርጎ የሚሰራ ሲሆን የተለያዩ የአመራረት ስርዓቶችን ታሳቢ በማድረግ ከላም ከግመልና ፍየል አጠቃላይ የወተት ምርት በ2012 ከነበረበት 4.37 ቢሊየን ሊትር በ2015 ዓ.ም መጨረሻ ላይ 8.69 ቢሊየን ሊትር ማድረስ ተችሏል። የዳልጋ ከብት (የላም) ወተት ልማት ሶስት የአመራረት ስርዓቶችን የሚከተል ሲሆን አብዛኛው (86 በመቶ) የሚሆነውን የወተት ምርት ሽፋን ይይዛል። የወተት ምርታማነት በሶስት ዓመታት በአማካይ ከሀገረሰብ ላም 1.6፣ ከተሻሻለ የወተት ላም ዝርያ 6.8፣ የውጪ ደም ካላቸው የወተት ላሞች 13.8፣ ከፍየል 0.5 እና ከግመል በቀን አማካይ 3 ሊትር ታቅዶ ከሀገረሰብ ላም 1.7፣ ከተሻሻሉት 7.7፣ የውጪ ደም ካላቸው 14.3፣ ከፍየል 0.6 እና ከግመል በቀን አማካይ 4 ሊትር በአያያዝና በተለያ በተደረገላቸው እንክብካቤ ምርታማነታቸው ሊሻሻል ችሏል።

#### የቀይ ሥጋ ምርትና ምርታማነት

የቀይ ስጋ ምርት ከዳልጋ ከብት፣ በግ፣ ፍየል እና ግመል ልማት ላይ ትኩረት ተደርጎ የሚሰራ ሲሆን የተለያዩ የአመራረት ስርዓቶችን ታሳቢ በማድረግ በ2012 መጨረሻ ከተደረሰበት 295 ሺህ ቶን በ2015 መጨረሻ ላይ 491.35 ሺህ ቶን ለማድረስ ተችሏል። ይህ ምርት በአብዛኛው ከአነስተኛ አርሶና አርብቶ አደር የእንስሳት ልማት ይሆናል። የቀይ ስጋ ምርታማነት በሶስት ዓመታት በአማካይ የዳልጋ ከብት 112፣ በግ 10.8፣ ፍየል 8.7 እና ግመል 255.4 ለማድረስ ታቅዶ የዳልጋ ከብት 112፣ የበግ 10.8፣ የፍየል 8.8 እና የግመል 255.4 ኪ/ግ/ በእንስሳ ማድረስ ተችሏል።

#### የቆዳና ሌጦ ምርት

ከስጋ ምርት ጋር በተያያዘ ቆዳና ሌጦ ዋነኛው ተዋፅዖ ሲሆን በ2012 ከተደረሰበት 15.95 ሚ/ን የቆዳ እና የሌጦ ምርት በ2015 ዓ.ም 19.02 ሚ/ን ደርሷል።

ለዘ ሀብታሙ ዋና ሥራ አስፈጻሚ

### የዶሮ ስጋና እንቁላል ምርትና ምርታማነት

የዶሮ ሥጋና እንቁላል ምርት ከማሻሻል አንጻር የእንቁላል ምርትን በ2012 መጨረሻ ከነበረዉ 2,854 ሚ/ን እንቁላል በ2015 መጨረሻ ላይ ወደ 3,918 ሚ/ን እንቁላል ማድረስ የተቻለ ሲሆን የዶሮ ስጋ ምርትን በ2012 መጨረሻ ከደረሰበት 48 ሺህ ቶን በ2015 መጨረሻ ላይ ወደ 112 ሺህ ቶን አድጓል። የዶሮ ስጋ ምርታማነት በሶስት ዓመቱ በአማካይ ከስፔሻላይዝድ 2.07፣ ከተሻሻለ ቤተሰብ 1.57 እና ከባህላዊ 1.4 ኪ/ግ በዶሮ ለማድረስ ታቅዶ ከስፔሻላይዝድ 1.9፣ ከተሻሻለ ቤተሰብ 1.5 እና ከባህላዊ 1.3 ማድረስ ተችሏል። በተመሳሳይ የዶሮ እንቁላል ምርታማነት ከስፔሻላይዝድ 260፣ ከተሻሻለ ቤተሰብ 192 እና ከባህላዊ 75 በዶሮ በዓመት ለማድረስ ታቅዶ ከስፔሻላይዝድ 230፣ ከተሻሻለ የቤተሰብ 204 እና ከባህላዊ 67 ማድረስ ተችሏል።

### የዓሣ ምርት እና ምርታማነትን ማሳደግ

የዓሳ ምርትን ለማሳደግና የሀገር ውስጥ የምግብና ስነ-ምግብ ፍላጎትን ለማሟላት ከሀይቆች፣ ግድቦች፣ ወንዞችና ሌሎች ትንንሽ የውሃ አካላት እንዲሁም አኳካልቸር በ2012 መጨረሻ ከተደረሰበት 101.36 ሺህ ቶን በ2015 መጨረሻ ወደ 214.36 ሺህ ቶን ለማድረስ ተችሏል።

### የማር ምርትና ምርታማነት

የማር ምርትን ለማሳደግና ለሀገር ውስጥ ፍላጎት እና ለኤክስፖርት የማር ምርት በ2012 መጨረሻ ከደረሰበት 59 ሺህ ቶን በ2015 መጨረሻ 194 ሺህ ቶን አድጓል። በተመሳሳይ በ2012 መጨረሻ ከደረሰበት የሰም ምርት 6 ሺህ ቶን በ2015 መጨረሻ 13.13 ሺህ ቶን ለማድረስ ተችሏል። ይህን ለማሳካት ስነምህዳርን መሰረት በማድረግ የማርና የሰም ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በመጠቀም ጥረት በመደረጉ ነው። የደረቅ የሐር ኩብኩባ ምርት በ2015 41 ቶን ማምረት ተችሏል።

## 2.2.2. የእንስሳት ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት

የአርሶ/አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሮችን የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚነት እና ተደራሽነት በተመለከተ የኤክስቴንሽን ተጠቃሚ ቁጥር በ2015 ዓ.ም 12.19 ሚ/ን መድረስ ተችሏል። የሙሉ ፓኬጅ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ ከነበረው 2 ሚ/ን ማድረስ ተችሏል። ሞዴል አ/አ/አደር ከመፍጠር ከነበረበት በ2015 ዓ.ም ወደ 600 ሺህ ማድረስ ተችሏል። በተመሳሳይ በአርብቶ አደር አካባቢ ለ668 ሺህ አርብቶ አደሮች የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ484 ሺህ (73%) አርብቶ አደሮች የኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት ተችሏል። ለ300 ሺህ የቆዳና ሌጦ ኤክስቴንሽን ተጠቃሚዎች የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ197 ሺህ (66%) ተጠቃሚዎች የኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት ተችሏል። ለ103 የሐር ልማት ኤክስቴንሽን ተጠቃሚዎችን የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ47 ሺህ (46%) ተጠቃሚዎች የኤክስቴንሽን አገልግሎት ተሰጥቷል።

### 2.2.3. የመኖ ልማት

ባለፉት ሶስት ዓመታት በሁሉም የእንስሳት መኖ ምንጮች (የተፈጥሮ ግጦሽ፣ የሰብል ተረፈ ምርት፣ ከተሻሻለ የመኖ ዕፅዋት ልማት፣ ከኢንዱስትሪ ተረፈ ምርት እና ከወልና ከግል የግጦሽ መሬት ልማት) በ455 ሚ/ን ቶን ድርቆ መኖ ለማምረት ታቅዶ 438 ሚ/ን ቶን (96%) ድርቆ መኖ ማምረት ተችሏል:: ከዚህም 165.04 ሚ/ን በ2015 ታቅዶ የተሰራ ነው።

በቆላማዉ አርብቶ አደር አካባቢ የሚገኘዉ የተፈጥሮ ግጦሽ /Rangeland/ ምርት በዕቅዱ መሰረት ያልተፈፀመዉ በሀገራችን በተደጋጋሚ እየተፈጠረ ባለዉ የአየር ንብረት ለዉጥ ለተከታታይ አመታት የዝናብ እጥረት ምክንት ድርቅ በመከሰቱ እና በቆላማዉ የአርብቶ አደር የግጦሽ ማሻሻል ትግበራ ለቴክኖሎጂና ግብዓት አቅርቦት ከፍተኛ ኢንቨስትመንት የሚያስፈልግ በመሆኑ ነው።

### 2.2.4. የእንስሳት ጤና አገልግሎት

በሶስት ዓመታት በክሊኒክ ላይ የተመሰረተ የእንስሳት ጤና አገልግሎት ተደራሽነትን በአማካይ 86 በመቶ ማድረስ ተችሏል:: 410 ሚ/ን ዶዝ የድንበር ዘለል በሽታዎች ክትባት ለማሰራጨት ታቅዶ 268 ሚ/ን ዶዝ ክትባት ማሰራጨት ተችሏል። በተመሳሳይ ለድንበር ዘለል በሽታ 410 ሚ/ን እንስሳቶችን ለመከተብ ታቅዶ 268 ሚ/ን (65.4%) እንስሳት መከተብ ተችሏል። ለሀገር አቀፍ የበጎችና ፍየሎች ደስታ መሰል በሽታ (PPR) ቁጥጥር ፕሮግራም 35 ሚ/ን በግና ፍየሎችን ለመከተብ ታቅዶ ለ32 ሚ/ን (94%) በግና ፍየሎችን መከተብ ተችሏል።

ባለፉት ሶስት ዓመታት ከቆላ ዝንብ 208,102 ስኩየር ካሬ መሬት ነፃ ለማድረግ 210,000 (100+%) ስኩየር ካሬ መሬት ነፃ ማድረግ ተችሏል። በተመሳሳይ ከቆላ ዝንብ ዳግም ወረራ 289,413 ስኩየር ካሬ መሬት ነፃ ለማድረግ 221,578 (76.5%) ስኩየር ካሬ መሬት ነፃ ማድረግ ተችሏል።

### 2.2.5. የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል

**የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል**

የእንስሳት ዝርያን ከማሻሻል አንጻር በሦስት አመታት ውስጥ በኢንስቲትዩቱ እና በክልሎች 4.31 ሚ/ን ዶዝ አባለዘር ለማምረት ታቅዶ 3.74 ሚ/ን ዶዝ (87%) አባለዘር ማምረት ተችሏል። 1.12 ሚ/ን ሊትር ፈሳሽ ናይትሮጅን ለማምረት ታቅዶ 1.07 ሚ/ን ሊትር (96%) ፈሳሽ ናይትሮጅን ማምረት ተችሏል። ጾታው የተለየ 32,420 ዶዝ አባለዘር ከውጪ ሀገር በማስገባት ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል። በተመሳሳይ መልኩ 72,770 ዶዝ ሆርሞን ከውጪ ሀገር በማስገባት ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ እና ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል። የተመረተውን አባለዘር ወደ ላሚቷ ማህጸን ውስጥ በማድረስ እርግዝና እንዲፈጠር የሚያደርጉ ባለፉት ሶስት ዓመታት ውስጥ 750 አዳቃይ ቴክኒሽያኖችን ለማሰልጠን ታቅዶ 1,204 አዳቃይ ቴክኒያኖችን ለማሰልጠን ተችሏል። ይህም የዕቅዱን 160 በመቶ ሆኗል። ዝርያቸው የተሸሻሉ 57,750 ፍየሎችን አዘጋጅቶ ለማሰራጨት ታቅዶ 45,038 ፍየሎች የዕቅዱን 78 በመቶ ለማሰራጨት ተችሏል።

ዜና ሀ/ወልድ
ሪከርድና ቶማቲክ ጉዳዮች
ዳይሬክተር

### የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎች እና ስርጭት

ባለፉት ሶስት አመታት 40 ታዳጊ ኮርማዎች ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ታቅዶ 40 (100%) ታዳጊ ኮርማዎች ማስገባት ተችሏል፡፡ በዘርፉ የተሻሻሉ ዝርያዎችን በማሳደግ የአርሶ/አርብቶ አደሩን ተጠቃሚነት ለማሳደግ 57,750 አውራ ፍየሎች ለማሰራጨት ታቅዶ 45,038 (78%) አውራ ፍየሎች ለማሰራጨት ተችሏል፡፡

### የዝርያ ማሻሻል ብዜት ማዕከላት

ባለፉት ሶስት ዓመታት 4 ነባር የዝርያ ማሻሻል የብዜት ማዕከላት ለመደገፍ እና ለማጠናከር ታቅዶ 7 (100$^{+}$%) ነባር የዝርያ ማሻሻል የብዜት ማዕከላት መደገፍ እና ማጠናከር ተችሏል፡፡ በነባር እና አዳዲስ ብዜት ማዕከላት የቦረና ጊደሮች እና የፎገራ ዝርዎችን የተመረጡ የቦረና ጊደሮች እና 1,304 የፎገራ ዝርያዎችን በማስገባት ያታው በተለየ አባለዘር እንዲጠቁ በማድረግ 50% የደም መጠን ያላቸው 100 እንስሳት ጥጃዎችን ማግኘት ተችሏል፡፡ ይህ የሚበረታታ ጅምር ስራ የዘርፉን የምርምር ስራ የሚያሻሽል ከመሆኑም በላይ በማዕከላት የሚባዙ ዝርያቸው የተሻሻሉ ጊደሮችን ለአርሶ/አርብቶ አደሩ በማሰራጨት ምርት እና ምርታማነትን ለማሳደግ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል፡፡

### የእንስሳት ዝርያ ኢንፎርሜሽን ማሳደግ

በእንስሳት ምርታማነት ምዝገባና ግብረመልስ የእንስሳት ምርታማነት ከማሳደግ አኳያ 2,200 አዲስ እርባታዎችን በመመዝገብ ወደ መረጃ ቋት ማስገባት ታቅዶ 2,240 (100$^{+}$%) እርባታዎች በመመዝገብ ወደ መረጃ ቋት በማስገባት የእቅዱን 100$^{+}$% ማከናወን ተችሏል፡፡ እንዲሁም 340,000 የወተት ከብት ምርታማነት ለመመዝገብ ታቅዶ 400,000 (100$^{+}$%) የወተት ምርታማነት ምዝገባ በማካሄድ ወደ መረጃ ቋት በማስገባት በመረጃ ቋት ለተመዘገበላቸው አርብቶ/አርሶ አደር መረጃውን በመተንተን እንዲሁም አጠቃላይ ምክረ-ሀሳብ ስለወተት ከብት እርባታ አያያዝና እንክብካቤ በሞባይል አጭር የጹሁፍ መልዕክት 260 አጭር የጹሁፍ መልዕክት (ግብረ-መልስ) ለመስጠት ታቅዶ 347 (100$^{+}$%) አጭር የጹሁፍ መልዕክት (ግብረመልስ) ለተመዘገቡ አርቢዎች ተደራሽ ማድረግ ተችሏል፡፡

### 2.2.6. የወጪ ንግድ አፈጻጸም

የወጪ ንግድ ገቢን በተመለከተ ከ2013-2015 ባሉት ሶስት አመታት ተቀነባብረው ወደ ውጪ ከተላኩ 82,815 ቶን የእንስሳት ምርትና ውጤቶች 343.14 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር የወጪ ንግድ ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 68,447 ቶን በመላክ 295 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር (86%) ማግኘት ተችሏል፡፡ በሦስቱ አመታት የተገኘው ገቢ በምርት አይነት ሲቃኝም 57,898 ቶን ሥጋ በመላክ 306.35 የአሜሪካን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 42,120 ቶን (73%) በመላክ 257.25 (84%) ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር የተገኘ ሲሆን፤ 10,760 ቶን የእርድ ተረፈ-ምረት በመላክ 25.56 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 12,053 ቶን (100$^{+}$%) በመላክ 30.28 (100$^{+}$%) የአሜሪካን ዶላር ተገኝቷል፡፡

በተመሳሳይ 695 ቶን የማር ምርት በመላክ 1.86 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 108 ቶን (16%) በመላክ 0.52 (28%) ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር የተገኘ ሲሆን 737 ቶን የሰም ምርት በመላክ 6.06 ሚ/ን የአሜሪካ ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 526 ቶን (71%) በመላክ 4.03 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር (67%) ማግኘት ተችሏል። በተጨማሪም 5,776 ሺህ ሊትር ወተት በመላክ 0.67 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 3,039 (53%) ሚ/ን ሊትር ወተት በመላክ 0.38 (56%) ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ተገኝቷል። ከዚህ ሌላ 6,949 ቶን መኖ በመላክ 1.63 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 10,600 ቶን (100⁺%) መኖ ወደ ውጪ ተልኮ 2.54 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር (100⁺%) ተገኝቷል። ጠቅላላ ከተገኘው 295 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር የወጪ ንግድ ገቢ 287.53 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር (97.5%) ከቀይ ሥጋና ዕርድ ተረፈ ምርት የተገኘ ሲሆን ይህም የወጪ ንግዳችን በተወሰኑ ምርቶች ላይ መወሰኑን ያመላክታል።

በአጠቃላይ የወጪ ንግዱ ካሉበት በርካታ ችግሮች አንጻር ባለፉት ሦስት አመታት መልካም አፈጻጸም የተመዘገበበት ቢሆንም በተወሰኑ የምርት አይነቶች ደግሞ ዝቅተኛ አፈጻጸም አሳይቷል። ዝቅተኛ አፈጻጸም የታየባቸው ምርቶች ዋና ዋና ምክንያቶችም የእንስሳት እና የእንስሳት ምርቶች አቅርቦት በጥራትና በብዛት ዝቅተኛ መሆን፣ በሀገር ውስጥ የእንስሳትና የእንስሳት ምርት ውጤቶች ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ መምጣቱ፣ ለወጪ ንግድ ምርቶቻችን ውስን ገበያዎች ላይ ብቻ ማተኮራችን ዋንኞቹ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ከጥራት ጉድለትና ከኮረና ወረርሽኝ ጋር በተያያዘ የማርና ዓሣ አቅርቦት ማነሱና ምርቶቹን ወደ ውጭ የመላክ ሁኔታ በከፍተኛ ሁኔታ መቀነሱ እንዲሁም የዓሣ ምርት መዳረሻ ገበያ ከሆነችው ሱዳን ጋር እና የማር ምርት ምንጭ ከሆነው ከሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ጋር ተያይዞ የነበረው የፀጥታ ሁኔታም የራሱ አስተዋፅኦ የነበረው ሲሆን በአርብቶ አደር አካባቢዎች የተከሰተው ድርቅም በእንስሳትና ወተት አቅርቦት ላይ ተፅእኖው ቀላል የሚባል አይደለም።

## 2.3. ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም

ተፋሰስንና አረንጓዴ አሻራ ልማትን መሠረት ያደረገ የተቀናጀ የተፈጥሮ ሀብት ልማት አጠባበቅና አጠቃቀም፣ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም፣ የአፈር ሀብት ጤንነትና ለምነት ማሻሻያ እና የአነስተኛ ይዞታ መስኖ ልማት ፕሮግራም መስኮች ያከናወናቸው ተግባራትና ያስገኛቸው ውጤቶች ተገምግሞ በየፕሮግራሙ እንሚከተለው ተተንትኗል።

### 2.3.1. ተፋሰስ ልማት እና አግሮ ፎረስትሪ

በሦስት ዓመታት ውስጥም 1.04 ሚ/ን ቀያሽ አርሶ አደሮችን በመለየትና በማሰልጠን የቅየሳ (Layout)፣ ዕለታዊ ሥራን በማስረከብ ጥራቱን የመቆጣጠር እና ለክቶ የመረከብ ሥራ ላይ ለማስማራት ታቅዶ 1.1 ሚ/ን ሰዎች ማሳተፍ ተችሏል። የአፈርና ውሃ ጥበቃ እና የጥምር ደን-እርሻ (አረንጓዴ አሻራ) ሥራዎች የሚሰሩት በኅብረተሰብ ተሳትፎ በመሆኑ በየዓመቱ በአማካይ እስከ 16 ሚ/ን አርሶ አደሮች በዓመት ከ30-40 ቀናት ነጻ የጉልበት አስተዋጽኦ በማድረግ በሥነ-አካለዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ ላይ ተሳታፊ ሆነዋል።

ዜና ሀ/ወልድ
የስትራቴጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

የልኬትና የቁፋሮ መሳሪያዎችን ከማሟላት አኳያ 2.045 ሚ/ን የቅየሳ መሳሪያዎች (ውሃ ልክ፣ ጂፒኤስ፣ ጃሎ፣ ክሊኖሜትር) እና 37.785 ሚ/ን የልማት ሥራ መሳሪያዎች (ዶማ፣ አካፋ፣ ገሶ፣ ደንገራ፣ ድጅኖ፣ መራጃ) በስራ ላይ ማዋል ተችሏል። ለ3,000 የማኅበረሰብ ተፋሰሶች ሁሉን አቀፍ የተፋሰስ ስትራቴጂክ ዕቅድ ለማዘጋጀት ታቅዶ ለ3,418 ተፋሰሶች በዚህ ደረጃ ማዘጋጀት ተችሏል።

በዕቅድ ዘመኑ ሦስት ዓመታት 5 ሚ/ን ሄ/ር የተጎዳ መሬትን በአዳዲስ የሥነ-አካላዊ የአ/ው/ጥ ቴክኖሎጂዎች ለመሸፈን እና 1 ሚ/ን ሄ/ር የተጎዱና የተራቆቱ አካባቢዎችን በመከለል ከንክኪ ነጻ ለማድረግ ታቅዶ 6.3 ሚ/ን ሄ/ር (100⁺%) መሬትን በአዳዲስ የሥነ-አካላዊ የአ/ው/ጥ ቴክኖሎጂዎች መሸፈን እንዲሁም 1.45 ሚ/ን ሄ/ር (100⁺%) የተጎዱና የተራቆቱ አካባቢዎችን በመከለል ከንክኪ ነጻ ማድረግ ተችሏል።

በዕቅድ ዘመኑ 17 ቢ/ን ችግኞችን አዘጋጅቶ ለመትከል ታቅዶ 19.9 ቢ/ን (117%) ችግኞች ተተክሏል። ለዚህም 28,677 ኩ/ል ዘር ለማቅረብ ታቅዶ 35,951 ኩ/ል የዛፍ፣ የቀርከሃ፣ የጥምር-ደን እርሻ እና የፍራፍሬ ዛፍ ዘሮች የቀረቡ ሲሆን አፈፃፀሙም 125.36% ነው። ችግኞቹም የተዘጋጁት በተለያዩ ሥነ-ምህዳሮች ውስጥ በሚገኙ 121,985 ችግኝ ጣቢያዎች ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 61,810 ችግኝ ጣቢያዎች የጂኦግራፊ መገኛ ቦታቸው ተለይቶ ካርታ ተዘጋጅቶላቸዋል። ከተተከሉት 19.9 ቢ/ን ችግኞች ውስጥ በ2013 "ኢትዮጵያን እናልብሳት" እና በ2014 "አሻራችን ለትውልዳችን" በሚል መሪ ቃል በተካሄደው የአረንጓዴ አሻራ መርሀ-ግብር 10.965 ቢ/ን የሚሆኑት የግብርና ሚ/ር በቀጥታ የሚተገብራቸው ዘርፈ-ብዙ ጥቅም የሚሰጡ የጥምር ደን እርሻ፣ የፍራፍሬ፣ የሥነ-ሕይወታዊ እና የመኖ ዕፅዋት ችግኞች ናቸው።

የፍራፍሬ ችግኞች ዘርፈ-ብዙ ጠቀሜታ ካላቸው ዕፅዋት ውስጥ ለምግብነት በመዋልና ለኤክስፖርት በመዋል በአጠረ ጊዜ ውጤት የሚያሳዩ በመሆኑ በ2013 እና በ2014 የተከላ ዘመን ብቻ 887.32 ሚ/ን ችግኞች በዋናነት በግለሰብ ማሳዎች ላይ መትከል ተችሏል። በሦስቱ ዓመታት 6.1 ሚ/ን ሄ/ር መሬት በጥምር ደን-እርሻ ለመሸፈን ታቅዶ 6.2 (101.6%) ሚ/ን ሄ/ር መሬት መሸፈን ተችሏል።

በጎረቤት አገራት ለሚደረግ ተከላ ከውጨ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ከየአገራቱ ኤምባሲዎችና ቆንስላ ጽ/ቤቶች ጋር በመወያየት ወደ ሥራ የተገባ ሲሆን አገራት እንደየአካባቢያቸው ሥነ-ምህዳር የሚመረጡ ችግኞች ተለይተው በምድር እና በዓየር ትራንስፖርት እንዲደርሱ ተደርጓል። በዚሁ መሠረት ለጂቡቲ (102,000) ፤ ለኤርትራ (80,000) ፤ ለሶማሊላንድ (20,000) ፤ ለፑንትላንድ ሶማሊያ (20,000) ፤ ለሶማሊያ (500) እና ለደቡብ ሱዳን (500) በድምሩ 223,000 የተለያዩ ችግኞች ተልኳል።

በአፈርና ውሃ ጥበቃ ቴክኖሎጂዎች ከተሸፈኑ እና ከንክኪ ነጻ ከተደረጉ ተፋሰሶች ውስጥ ለ3,000 የማኅበረሰብ ተፋሰሶች ላይ የተፋሰስ ተጠቃሚዎች ማኅበራት ለማደራጀት ታቅዶ 3,418 የተፋሰስ ማኅበራትን በማቋቋም በኢትዮጵያ የኅ/ሥራ ኮሚሽን በኩል የህጋዊ ዕውቅና ሰርቲፊኬት እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን አፈፃፀሙም 113.93% ነው።

በተጨማሪም የለሙ ተፋሰሶች መረጃን በአግባቡ ለመያዝ፣ የዕቅድ እና የሪፖርት ግንኙነቱ ያጠረ ጊዜ የሚወስድና ወረቀት አልባ በማድረግ የተሳለጠ የመረጃ ክምችትና ልውውጥ እንዲኖር በጂአ-ስፓሻል



ለክ ዜና ሀ/ወልድ
የስትራተጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

ቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ ቋት እና የመረጃ ሠንሠለትን ተዘርግቶ አጠቃቀሙን የማስረጽና የተፋሰስ መረጃዎችን የማስገባት ሥራ እየተሰራ ይገኛል። እስከአሁን ወደ 3,000 የሚጠጉ ተፋሰሶች እንዲገቡ ተደርጓል። በተመሳሳይም የአረንጓዴ አሻራ ሥራዎች መረጃ (የተተከሉ ችግኞች ብዛት በክልል፣ የተሳተፈ የሰው ኃይል፣ የተከናወኑ መርሀ-ግብሮች) ለኅብረተሰቡ ተደራሽ የሚሆንበት ድረ-ገጽ ተዘጋጅቶ ወደሥራ ገብቷል።

የሥነ-አካላዊ እና የሥነ-ሕይወታዊ የተፋሰስ ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ሥራዎች በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ላይ ይደረስባቸዋል ተብሎ የተቀመጡ ግቦችን: - የአፈር ክለትን ከ20.5 ወደ 15.84 ቶን/ሄር/ዓመት ለመቀነስ፣ **የህይወት ክቡድ** (ባዮማስ) መጠንን ከ27 ወደ 75.2 ሚ/ን ቶን ካርበን/ሄ/ር በዓመት ለማሳደግ የሚያስችል አዝማሚያን ያሳያል። የእነዚህ ግቦች ውጤት የሚለካው በ10 ዓመቱ መሪ ዕቅድ በተቀመጠው መሠረት በ4ኛው እና በ9ኛው ዓመት ውስጥ ስለሆነ በቀጣይ ጥናት ተካሂዶ ሪፖርት የሚደረግ ይሆናል።

በአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ በለሙ ተፋሰሶች ላይ ንብ በማንባት፣ በማደለብ፣ ፍራፍሬ አልምተው ለገበያ በማቅረብ፣ ዘር በመሰብሰብና በማቅረብ፣ ችግኝ አዘጋጅቶ በመሸጥ፣ በችግኝ ጣቢያዎች ውስጥ ተቀጥሮ በመስራት 93,600 የሥራ ዕድሎችን ለወጣቶች/ሴቶች ለመፍጠር ታቅዶ 138,500 የሥራ ዕድሎች ለወጣቶችና ለሴቶች የተፈጠረ ሲሆን አፈፃፀሙም 147.97% ነው። ከተፈጠረው የሥራ ዕድል ውስጥ አብዛኛው በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ምክንያት የተፈጠረ ነው።

### 2.3.2. የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም

የሁለተኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጥና የይዞታ የምስክር ወረቀት የመስጠት ተግባራት አፈፃፀምን አስመልክቶ ለ7.3 ሚ/ን ያህል ማሳዎች የይዞታ ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዶ ለ5.66 ሚ/ን ማሳዎች የተሰጠ ሲሆን አፈፃፀሙም 77.5% መሆኑን ያመላክታል። በተመሳሳይ መልኩ በተጠቃሚ ደረጃ ለ2.1 ሚ/ን ያህል ተጠቃሚዎች (1.5 ሚ/ን አባወራ እና 0.62 ሚ/ን እማወራ) ለመስጠት ታቅዶ ለ1.51 ሚ/ን (1.06 ሚ/ን አባወራ እና 0.45 ሚ/ን እማወራ) (72.5 %) የይዞታ ማረጋገጫ ሠርተፊኬት ተሰጥቷል።

የሁለተኛ ደረጃ የመሬት ይዞታ ሠርተፍኬት ለተሰጠባቸው 262 ወረዳዎች የብሄራዊ የገጠር መሬት አስተዳደር የመረጃ ስርዓት ለመዘርጋት ታቅዶ በ271 ወረዳዎች (100+%) መተግበር ተችሏል። የመሬት መጠቀም መብታቸውን በመጠቀምና የመሬት ይዞታ ሠርተፍኬታቸውን በዋስትና በማስያዝ በብድር እስከ 1.4 ቢ/ን ብር ከአሥር (10) አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ከ252 ቅርንጫፎች አገልግሎት ማግኘት አስችሎቸዋል። የዚህ የብድር ተጠቃሚዎች 35% ያህሉ እማወራዎች ናቸው።

ህብረተሰቡን ያሳተፈ የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ ሰነድ ለ2,242 ቀበሌዎች ለማዘጋጀት ታቅዶ ከ2013-2015 ዓ.ም ድረስ ለ1,232 ቀበሌዎች (55%) ተዘጋጅቷል። ለአፈፃጸሙ ዝቅተኛ መሆን ባለፉት ዓመታት በክልሎች ያለው ነባራዊ ሁኔታ (አለመረጋጋት፣ በቂ በጀት ለዕቅዱ አለመመደብና ትኩረት አለመስጠት) በዋናነት ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህ የተጠቀሱት ችግሮች የአሳታፊ የገጠር መሬት አጠቃቀም ትግበራውንም በዕቅድ ዘመኑ ውስጥ 1,772 ለማድረስ የታቀደ ቢሆንም የተከናወነው ግን 59.2% ብቻ እንዲሆን አስተዋጽኦ አድርገዋል።

የአሳታፊ መሬት አጠቃቀም እቅድ ዝግጅት ሥራን ዘመናዊ ለማድረግና ትንተናውን ለማቃለል የሞባይል መተግበሪያ LandPKS app መስራት እንዲቻል በሦስት ክልሎች (በአማራ፣ ኦሮሚያና ደቡብ) በስድስት ቀበሌዎች የሙከራ ትግበራ ተከናውኖ የመጀመሪያው ማንዋል ተዘጋጅቷል።

### 2.3.3. የአፈር ሀብት ልማት ተግባራት አፈፃፀምን በተመለከተ

በ2012 በጀት ዓመት 246 ሺህ ቶን የግብርና ኖራ በመጠቀም ከታከመው 82,000 ሄ/ር አሲዳማ አፈር መነሻ ላይ 710,000 ሄ/ር አሲዳማ አፈር በማከም 792,000 ሄ/ር ለማድረስ ታቅዶ 38,369 (5.4%) ሄ/ር ብቻ በማከም እስከአሁን ያለውን አፈፃፀም 120,369 ሄ/ር ብቻ ማድረስ ተችሏል። በ2012 ከቀረበው 246 ሺህ ቶን የግብርና ኖራ ላይ ተጨማሪ 2.13 ሚ/ን ቶን በማቅረብ አቅርቦቱን 2.376 ሚ/ን ቶን ለማድረስ የታቀደ ቢሆንም 0.1151 ሚ/ን ቶን (5.4%) ብቻ በማቅረብ ጠቅላላ አፈፃፀሙን 0.3611 ሚ/ን ቶን ማድረስ ተችሏል። ለዚህም ዝቅተኛ አፈፃፀም ዋናው ምክንያት መንግሥት የግብርና ኖራን እንደ አንድ የግብርና ግብአት በመዉሰድ ለ2013/14 ምርት ዘመን 875 ሚ/ን ብር የመደበ ቢሆንም ከችግሩ ስፋት አንጻር የተመደበው በጀት አነስተኛ ከመሆኑም ባሻገር ከሩሲያ-ዩክሬን ጦርነት ጋር ተያይዞ የኬሚካል ማዳበሪያ ዋጋ በከፍተኛ መጠን በመጨመሩ ለግብርና ኖራ የተመደበዉ በጀት ራሱ ወደ ኬሚካል ማዳበሪያ ግዥ እንዲዞር ስለተደረገ በኖራ አቅርቦት ላይ ከፍተኛ የበጀት እጥረት የፈጠረ ሲሆን የዕቅድ አፈፃፀሙንም በዚህ ደረጃ ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጎታል። አማራጭ የአሲዳማ አፈር ማከሚያ ቴክኖሎጂዎችን ለመሞከር ታሳቢ ተደርጎ ከኦሲፒ የማዳበሪያ ካምፓኒ ጋር በመተባበር ካልሲየም ኦክሳይድ (CaO) የማዳበሪያ ምጥን በ520 የሰርቶ ማሳያዎች ላይ ተካሂዶ ውጤቱ በአሁኑ ጊዜ በምርምር ባለሙያዎች በመተንተን ላይ ይገኛል።

ጨዋማ አፈር ባለባቸው ቆላማ አካባቢዎች በተለይም በመካከለኛዉ የአዋሽ ሸለቆ ባዮሳላይን አማራጭ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም በ2012 መነሻ ዓመት ከተደረሰበት 10 ሄ/ር የታከመ ጨዋማ መሬት 43.2 ሄ/ር ጨዋማ መሬትን በማከም 53.2 ሄ/ር ለማድረስ ታቅዶ 37.24 ሄ/ር (70%) በማልማት 47.24 ሄ/ር ማድረስ ተችሏል። በተጨማሪም የጂኦስፓሻል ቴክኖሎጂን በመጠቀም ለ13 ወረዳዎች የአፈር ጨዋማነት ካርታ ተዘጋጅቷል። የዘርና የፋይናንስ አቅርቦት ችግር አፈጻጸሙ ዝቅ እንዲል ያደረገ ቢሆንም ጨዋማነትን የሚቋቋሙ የመኖ እና የሰብል ዝርያዎች እንዲያለማ በማድረግ ከፊል አርብአደሩ ተጠቃሚ እንዲሆን ተደርጓል።

የኮትቻ አፈር ለማልማት በ2012 መነሻ ዓመት ከተደረሰበት 6.99 ሚ/ን ሄ/ር መነሻ በማድረግ 1.7 ሚ/ን ሄ/ር የኮትቻ አፈርን በማልማት 8.69 ሚ/ን ሄ/ር ለማድረስ ታቅዶ 1.9 ሚ/ን ሄ/ር (100%) በማልማት ወደ 8.89 ሚ/ን ሄ/ር ማድረስ ተችሏል። የጂኦስፓሻል ቴክኖሎጂን በመጠቀም ለ171 ወረዳዎች የኮትቻ አፈር ካርታ ተዘጋጅቷል። የተፈጥሮ ማዳበሪያዎች አጠቃቀምን በተመለከተ 9.2 ሚ/ን ሄ/ር አፈር ለማልማት ታቅዶ 12.9 ሚ/ን ሄ/ር (139.99%) ማልማት ተችሏል።

ካካ ዜና ሀ/ወልድ ስትራተጂክ ጉዳዮች ሥራ አስፈጻሚ

የማዕድን ማዳበሪያዎች አጠቃቀምን በተመለከተ እስከአሁን በስፋት ባልተዋወቁባቸው የአገራችን አካባቢዎች ወደ 1,950 ሰርቶ ማሳያዎችን ለማስተዋወቅ ታቅዶ 1,858 (95.28%) የሚሆኑ ሰርቶ ማሳያዎችን ማስተዋወቅ ተችሏል። በዚህ ዘርፍ ከሰርቶ ማሳያዎች በተጨማሪ የማዳበሪያ ጥራት ቁጥጥር መዋቅራዊ አደረጃጀት ሀገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ የዳሰሳ ጥናት የማካሄድ እና የማዳበሪያ የአፈር ጤንነት ማሻሻያ ግብአቶች ማምረት፣ አያያዝ፣ ንግድና ስርጭት ረቂቅ አዋጅ የማዘጋጀት ስራዎች ተሰርተዋል።

የአፈር ዓይነት ካርታ ዝግጅት በተመለከተ ለ144 ወረዳዎች የአፈር ሀብት ዓይነት ካርታ ለማዘጋጀት ታቅዶ በ17,133 የተሰበሰቡ ውርስ (Legacy) የአፈር ናሙና መረጃዎችን በማጥራትና በማጣጣም በዕቅዱ የተያዙትን 144 ወረዳዎች ጨምሮ በአገር-አቀፍ ደረጃ 18 የአፈር ዓይነቶችን የያዘ የአፈር ሀብት ካርታ ለማዘጋጀት ተችሏል። በዚህም ከአራት አስርት-ዓመታት በፊት በ2 ሚ/ን ስኬል ተዘጋጅቶ ጥቅም ላይ ሲውል የነበረውን የአፈር ዓይነት ካርታ በመከለስ እንዲሻሻል ተደርጓል።

### 2.3.4. የአነስተኛ ይዞታ መስኖ ልማት

የመስኖ መሬት ማስፋፋትን በተመለከተ የመስኖ አውታሮችን በመገንባት፣ ፓምፖችን በስፋት በማቅረብ 82,000 ሄ/ር መሬት ለመስኖ ልማት ዝግጁ ለማድረግ ታቅዶ 140,890 ሄ/ር (172%) ተከናውኗል። በዚህም ዝናብን ብቻ ጠብቀው ያመርቱ የነበሩ 368,910 አርሶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮችን ተጠቃሚ ያደረገ ሲሆን አፈፃፀሙም 69.08% ለማድረስ ተችሏል።

የመስኖ አውታሮችን ገንብቶ አርሶ አደሮች በጋራ እንዲጠቀሙ ለማድረግ በቁጥር 591 አነስተኛ የመስኖ አውታሮች ግንባታ እንዲጠናቀቅ ታቅዶ 477 (81%) ተፈጽሟል። እነዚህ ግንባታዎች በልማት አጋር አካላት እና በመንግስት መደበኛ የበጀት ድጋፍ የተከናወኑ ሲሆን በግንባታ ሂደትም የግንባታ ዕቃ (ሲሚንቶ) እጥረትና የዋጋ ንረት አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድረዋል። እንዲሁም የመስኖ ውሀ እና የመሬት አቅም ያላቸው አርሶ አደሮች የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም በቤተሰብ ደረጃ የመስኖ ውሀ አቅርቦት እንዲኖራቸው ከማድረግ አኳያ በቁጥር 156,329 የውሀ አማራጮች (የአነስተኛ ፓምፕ፣ ውሀ ማሰባሰብ፣ የቅርብ ከርሰ-ምድረ ጉድጓድ ውሀ አቅርቦት) በግለሰብ አርሶ አደር ደረጃ የተዘጋጀ ሲሆን በቁጥር 615 ትላልቅ ፓምፖችም ስራ ላይ ውለዋል።

የተገነቡ የመስኖ አውታሮች ዘላቂ እንዲሆኑ፣ የጥገና ስራዎች በአርሶ አደሩ እንዲከናወኑና የውሀ አጠቃቀምን ለማሻሻል እንዲቻል 591 የውሀ ተጠቃሚ ማህበራትን ዕውቅና ለመስጠት ታቅዶ 445 (75.3%) የተከናወነ ሲሆን ለዚህም ዝቅተኛ አፈፃፀም እንደ ዋንኛ ምክንያት የሚጠቀሰው ዕውቅናውን የሚሰጠው ከግብርና ውጭ የሆነ አካል በመሆኑ ነው። በዚህም መሰረት በተከለሰው የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ ላይ በተመላከተው መሰረት አዋጁ የሚሻሻልበት ወይም ከግብርና ዕቅድ ላይ እንዲወጣ መደረግ አለበት።

በመስኖ ልማት በስፋት አርሶ አደሩን ተጠቃሚ ለማድረግ 482 ሄ/ር ማልማት የሚችሉ በፀሐይ ሀይል የሚሰሩ የመስኖ ውሀ መሳቢያ ፓምፖች ለአርሶ አደሩ እንዲሰራጩ ተደርገዋል። እንዲሁም የውሀ አጠቃቀምን ለማሻሻል ሲባል ቴክኖሎጂዎችን ከመተግበር አንጻር የጠብታ እና የርጭት መስኖዎችን

ዜና ሀ/ወልድ
ስትራተጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ



Federal Democratic Republic Ministry of Agriculture

በተለያዩ አካባቢዎች ላይ ሙከራ ለማድረግ 68 ሄ/ር ማልማት የሚችሉ የጠብታ መስኖ ቴክኖሎጂዎች ለአርሶ አደሩ በመሠራጨት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል።

### 2.3.5. ደን ልማት

የደን ሀብት በርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ጥቅሞችና ግልጋሎቶች አሉት። ይህንን ግልጋሎት ከማሳደግ አንፃር በ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል።

ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት የሚጠበቁ ውጤቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመፈፀም እንዲያስችል በየበጀት ዓመቱ ያለፈውን ዓመት አፈፃፀም በማዕከላትና በዋናው መስሪያ ቤት በሚገኙ አመራሮችና በክልል ባለድርሻ አካላት እንዲገመገም በማድረግና አስፈላጊ ግብዓቶች በመውሰድ በየዓመቱ ዕቅድ ዝግጅት ላይ ግብዓቱ እንዲካተት በማድረግ የተዘጋጀውን ዕቅድ በማኔጅመንት እንዲሁም በባለድርሻ አካላት እንዲገመገምና ለሰራተኞች ተዋውቆ ወደ ስራ እንዲገባ ተደርጓል። ከዚህም በተጨማሪ ለስራው አስፈላጊ ግብዓቶችን የማሟላት፣ ስራዎችን የሚያሳልጡ የአሰራር ስርዓቶችን የመዘርጋትና የማጠናከር እንዲሁም የተቋም አደረጃጀት ተከትሎ በመስራት ላይ ያለውን የመስሪያ ቤቱን መዋቅር ከዳር ለማድረስ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል።

ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት ድረስ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ለደን ልማት እና ምርምር እንዲሁም ለአቅም ግንባታ ስራዎች 468.63 ሚ/ን USD ከተለያዩ አጋር አካላት ማግኘት ተችሏል።

በተደረገው የደን ልማትና ጥበቃ ስራ ከደን ዘርፍ 15 ሚ/ን ቶን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ለመቀነስ ታቅዶ 13.1756 ሚ/ን ቶን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት መቀነስ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ87.8% በላይ ሆኗል።

በደን ልማት፣ በደን ፖሊሲ እና ስትራቴጂ እንዲሁም በደን ጥበቃ እና አጠቃቀም ህጎች ዙሪያ ለ4.55 ሚሊየን የማህበረሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ለመስጠት ታቅዶ ለ5.38 ሚሊየን የማህበረሰብ ክፍሎች በስልጠናና በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ሆኗል።

2.4 ሚ/ን ሄ/ር የተከላ መሬት ለመለየት ታቅዶ በ2.2358 ሚ/ን ሄ/ር ከ93.2% በላይ መለየት ተችሏል፣ 11 ቢሊዮን ደረጃቸውን የጠበቁ ችግኞች ለማዘጋጀትና ለመትከል ታቅዶ 14.359 ቢሊዮን (100%) ማከናወን ተችሏል፣ የቀርከሃ ደን ሽፋን 0.06 ሚ/ሄ/ር ለማድረስ ታቅዶ 0.16 ሚ/ሄ/ር ማድረስ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ነው። አፈጻጸሙ ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት ለቀርከሀ ልማት የተሰጠው ትኩረት ከፍተኛ በመሆኑና ከመደበኛ በተጨማሪ የፕሮጀክቶችና የተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተሳትፎ ከፍተኛ በመሆኑ ነው።

ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት 2.85 ሚ/ን ሄ/ር የተራቆቱ የደን መሬቶችን በመለየት እንዲያገግሙ ለማስቻል ታቅዶ 2.098 ሚ/ን ሄ/ር የተራቆቱ የደን መሬቶችን በመለየት እንዲያገግሙ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 73.6% ሆኗል።

በየበጀት ዓመቱ 19.2 ሚ/ን ሄ/ር ነባር የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ደኖችን ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብና በዘላቂነት ለመጠቀም የሚያስችል ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ በየዓመቱ 18.68 ሚ/ን ሄ/ር ነባር የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ደኖችን ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብና በዘላቂነት ለመጠቀም የሚያስችል ክትትልና ድጋፍ የተደረገ ሲሆን አፈፃፀሙም 97.3% ሆኗል። 2.28 ሚ/ን ሄ/ር የተፈጥሮ ደን በአሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓትን እንዲታቀፉ ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት ተከናውኗል።

ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት ከሮያሊቲ እና ከተወረሱ የደን ምርት ውጤቶች ሽያጭ 650 ሚሊየን ብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች በተሰራው ስራ 880 ሚሊየን ብር የተሰበሰበ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ሆኗል። ከእቅድ በላይ የተከናወነበት ምክንያት የተሻለ ክትትልና ድጋፍ በመደረጉ እና ክልሎችም ትኩረት ስለሰጡት ነው።

ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት ለ1 ሚ/ን ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ በደን ጥበቃ፣ የደን ምርቶችን በመጫን፣ በማጓጓዝና በማውረድ፣ በችግኝ ተከላና እንክብካቤ፣ በእንጨት ኢንዱስትሪ፣ ኢንተርፕራይዞችና ማህበራትን በማደራጀት፣ የደን ምርት ውጤቶችን በማቅረብ፣ በመቸርቸርና በመላክ ፣ በከሰል ማክሰል (አማራ ክልል) እና የመሳሰሉት የስራ መስኮችን በአጠቃላይ ለ1.1 ሚ/ን ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 100% ነው።

ከ2013 እስከ 2015 ዓመት ድረስ 2.38 ሚልዮን ቶን የደን ምርት ውጤቶች ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያ ለማቅረብ በዕቅድ ተይዞ ክንውን 5.038 ሚልዮን ቶን (ከዚህ ውስጥ 25,000 ቶን ለውጭ ገበያ የቀረበ) የቀረበ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ነው። አፈፃፀሙ ከዕቅድ በላይ የሆነበት ምክንያት በዘርፉ የደን ውጤት ምርት ፍላጎት እና አቅርቦት እየጨመረ በመምጣቱ ነው።

ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት ድረስ ተቋሙ በምርምር ዘርፍ የደን ሽፋን ለመጨመር ፣ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ የደን ውጤቶችን ምርታማነት ለማሳደግ፣ እሴት ለመጨመርና የገበያ ስርዓትን ለመዘርጋት፣ እና ስርዓተ-ምህዳሩን ለማሻሻል የሚያስችሉ በሰዉ ሰራሽ ደን፣ በደን ዉጤቶች ኢኖቬሽን፣ በፖሊሲና ሶሺዮ-ኢኮኖሚክስ፣ በተፈጥሮ ደን እና በአየር ንብረት ለወጥ የተለያዩ የምርምር ፕሮጀክቶችን ነድፎ መረጃና ቴክኖሎጂዎችን በማዉጣት የበኩሉን ሀገራዊ ሃላፊነት ሲወጣ ቆይቷል። በዚህም መሰረት ከ2013 እስከ 2015 በጀት አመት ድረስ በሰው ሰራሽ ደን ምርምር 34 መረጃና ቴክኖሎጂ ለማዉጣት ታቅዶ 21 ማዉጣት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 61.8%፣ በተፈጥሮ ደን እና አየር ንብረት ለዉጥ 43 መረጃና ቴክኖሎጂ ለማዉጣት ታቅዶ 47 ማዉጣት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 100% በላይ የደን ውጤቶች ኢኖቬሽን ምርምር 32 መረጃና ቴክኖሎጂ ለማዉጣት ታቅዶ 27 ማዉጣት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 84.4% እና በፖሊሲና ሶሺዮ-ኢኮኖሚክስ ምርምር 11 መረጃ ለማዉጣት ታቅዶ 10 ማዉጣት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 90.9% ነዉ። በአጠቃላይ ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት ስንመለከት በምርምሩ ዘርፍ 120 የምርምር ውጤቶችን (100 መረጃዎች 20 ቴክኖሎጂዎች) ለማውጣት ታቅዶ 105 የምርምር ውጤቶችን (95 መረጃዎች 10 ቴክኖሎጂዎች) ለማውጣት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 87.5% ነው። የቴክኖሎጂ ቅድመ ማስፋትን በተመለከተ ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት ድረስ 470 ከተለያዩ አካላት ለተዉጣጡ

የቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ466 ተጠቃሚዎች ማሰልጠን የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 99.1% ነዉ::

በአጠቃላይ 2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት ድረስ በተሰሩ ስራዎች የፊዚካል ስራዎች አፈፃፀም 93.3% ሲሆን፣ ለተቋሙ ከተለቀቀው መደበኛ በጀት 749,840,583.40 ብር ውስጥ 574,567,617.85 ብር ጥቅም ላይ ለማዋል የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 76.6% ነው:: አፈፃፀሙም ያነሰበት ምክንያት በዋናነት በሃገር ደረጃ በተከሰተው የግንባታ ማቴሪያል የዋጋ መናር እና በገበያ ላይ የግንባታ ማቴሪያል እጥረት ሳቢያ የሁለቱ ላቦራቶሪዎች የግንባታ ስራዎች በመዘግየታቸው ነው:: ይህንም ችግር ለመቅረፍ ከተቋራጭ ድርጅቶቹ ሃላፊዎች፣ ከአማካሪው ድርጅት አመራሮች፣ ከግንባታ ቁጥጥር ባለስልጣን ባለሙያዎች፣ የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን አመራሮች ጋር በመነጋገር የዋጋ ለውጥ በግንባታ ላይ ያስከተለውን ችግር እንዴት መቅረፍ እንደሚቻል ውይይት ተደርጓል:: ለመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ ቀርቦ ተቀባይነት ያገኘ በመሆኑ በቀጣይ የግንባታው ስራ እንዲፋጠን ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል::

#### 2.3.6. ብዝሀ ሕይወት ጥበቃና አጠቃቀም

አሰሳና ቅኝት ማካሄድን አስመልክቶ አሰሳ ቅኝት የተደረገባቸዉ 41ቦታዎች 9 ዝርያ 16 ጥናት ታቅዶ 41 ቦታዎች / 10 ዝርያዎች/ እና 16 ጥናት አሰሳ ቅኝት ተደርጓል:: ከብዝሀ ሕይወት ጋር ተያያዥ የሆነ የማህበረሰብ እውቀት ምዝገባ ጥናት 3 ታቅዶ 3 (100%) ተከናውኗል:: የተሰበሰበ በዘቦታና በኢዘቦታ የተነበሩ 417 ዝርያ 8,090 ናሙና ታቅዶ 442 ዝርያ እና 8,803 ናሙና በዘቦታና በኢዘቦታ ተሰብስቦል:: ከወራሪ መጤ ዝርያዎች ነፃ የተደረጉ ቦታዎች ሽፋን በሄክታር 60,000 ታቅዶ 67,578 (100%) በላይ ተከናውኗል፤ ለቀጣይ ምርምር፣ ልማትና መልሶ ለመተካት የተሰራጩ ናሙናዎችና/አባላዘር/ቀሰም 30,651/3,000 ታቅዶ 46,730/1,500 ተከናውኗል፤ የአርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት አፈፃፀም ክፍተቶች ጥናት ዘገባ፣ ለምርምር ዓላማ የአርክቦት ፈቃድ ለመስጠት 347 ታቅዶ 410 በላይ ተከናውኗል::

## 2.4. የግብርና ኢንቨስትመንትና ግብይት

### 2.4.1. የግብርና ግብዓት አቅርቦትና ስርጭት

#### ሀ) የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት

በ2012/13 ምርት ዘመን እንደ መነሻ 16.1 ሚ/ን ኩንታል የቀረበ ሲሆን በ2013፣ 2014 እና 2015 ምርት ዘመን የክረመን ጨምሮ 19.90 ሚ/ኩ/ል (95.86%) ፣ 15.71 ሚ/ኩ/ል (71.64 %) እና 16.2 ሚ/ኩ/ል (61.96%) በቅደም ተከተል ከፍላጎቱ አንጻር ቀርቧል:: ከፍተኛ መጠን ያለው አፈር ማዳበሪያ የቀረበው በ2013/14 ምርት ዘመን ሲሆን በ2014/15 እና 15/16 ምርት ዘመናት የአፈር ማዳበሪያ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ በመጨመሩ ምክንያት ብሄራዊ ባንክ ለግብርና ግብዓቶች መግዣ በሚል በመደበልን በጀት ልክ በመገዛቱ ክልሎች ካቀረቡት ፍላጎት በታች ሊገዛ ተችሏል:: የተለያዩ መጠን እና ዓይነት ያላቸው የአፈር ማዳበሪያዎች በ2012/13 ምርት ዘመን 14.08 ሚ/ኩ/ል፣ በ2013/14 ምርት ዘመን 15.39 ሚ/ኩ/ል (ከቀረበው 77.33%) ፣ በ2014/15 ም/ዘመን 13.47 ሚ/ኩ/ል (ከቀረበው 85.74 %) እና በ2015/16 ም/ዘመን 16.2 ሚ/ኩ/ል ከቀረበው ሙሉ በሙሉ ማሰራጨት ተችሏል::



ዜና ሀ/ወልድ
የስትራተጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

በ2012 ምርት ዘመን 29.2 ቢ/ን ብር እና 503 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር የተፈቀደና ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን በ2013 ምርት ዘመን 30 ቢ/ን ብር እና 650 ሚ/ን ዶላር እንዲሁም በ2014 ምርት ዘመን 48 ቢ/ን ብር እና 1 ቢ/ን ዶላር እና በ2015 ምርት ዘመን 62.9 ቢ/ን ብር እና 1.1 ቢ/ን ዶላር ብሄራዊ ባንክ በማስፈቀድ ጥቅም ላይ ውሏል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ በተለያዩ ምክንያቶች የአፈር ማዳበሪያ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ በመጨመሩ ምክንያት የአርሶ እና ከፊል አርብቶ አደሩን የመግዛት አቅም እንዳያሳጣ እና በምርት እና ምርታማነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳያመጣ ባለፉት ሦስት ዓመታት ውስጥ በመንግስት ደረጃ ድጎማ ተደርጓል። በ2012/13 ምርት ዘመን ከጅቡቲ እስከ መዳረሻ ጣቢያዎች ድረስ የነበረውን ጠቅላላ ዋጋ 4.3 ቢ/ን ብር፣ በ2014 ምርት ዘመን 15 ቢ/ን ብር ይህ ማለት በአንድ ኩ/ል የአፈር ማዳበሪያ ዋጋ ላይ 1,100 ብር ቅናሽ እንዲኖር በማስቻል እና በ2015 ም/ዘመን ደግሞ የአፈ.ር ማዳበሪያ መግዣ ዋጋ በአንጻራዊነት ከ2014/15 ም/ዘመን የተወሰነ ቅናሽ የታየበት የነበረ ቢሆንም የሃገር ውስጥ ማጓጓዣ በከፍተኛ ደረጃ በመጨመሩ መንግስት 21 ቢ/ን ብር ድጎማ በማድረግ ይህም በአንድ ኩ/ል 1,566 ብር የዋጋ ቅናሽ እንዲኖር አስችሏል።

### ለ) የአግሮ ኬሚካል አቅርቦት

የአግሮ ኬሚካልን በተመለከተ በ2013/14 ምርት ዘመን 1,692,313 ሊ/ር/ኪ/ግ ለማቅረብና ለማሰራጨት ታቅዶ 818,561 ሊ/ር/ ኪ/ግ የተሰራጨ ሲሆን በ2014/15 ም/ዘመን 2,202,992 ሊ/ር/ኪ/ግ በማቅረብ 99,998 ሊ/ር/ኪ/ግ ተሰራጭቷል። በ2015/16 ም/ዘመን 1,000,000 ሊ/ር/ኪ/ግ በማቅረብ የከረመ ጨምሮ 1,320,000 ሊ/ር/ኪ/ግ (100%) ተሰራጭቷል። በኬሚካል አቅርቦትና ስርጭት ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችም በየዓመቱ ወደ ሃገር ውስጥ የሚገቡ ኬሚካሎች በውል አለመታወቅ፣ በተወሰኑ አስመዝጋቢዎች ብቻ መያዝ፣ በየምርት ዘመኑ የሚያስፈልግ ኬሚካል መጠንና ዓይነት ቢለይም በማን ምን ያህል የሚለው ሳይለይ ማስገባት ናቸው።

### ሐ) የኖራ አቅርቦትና ስርጭት

ከ2013 እስከ 2015 ባሉት ሦስት ተከታታይ ምርት ዘመን 1,757,395 ኩ/ል ኖራ ለመቅረብ ታቅዶ 822,862 ኩ/ል (46.82%) ቀርቧል። ይህ ማለት በአማካኝ በአንድ ሄ/ር ላይ 30 ኩ/ል ኖራ እንደሚጨመር ታሳቢ በማድረግ በሦስት ምርት ዘመን 27,428.73 ሄ/ር መሬት ብቻ አከምን ማለት ነው። በኖራ አቅርቦትና ስርጭት ሂደት የተለዩት ዋና ዋና ችግሮች በክልሎች በቂ የኖራ ፋብሪካዎች አለመኖር፤ ለአንድ ሄ/ር የሚያስፈልግ የኖራ መጠን ከፍተኛ መሆን፤ የማጓጓዣ ዋጋ ከፍተኛ መሆን እና በክልሎች ያለ የበጀት እጥረት ዝቅተኛ አፈፃፀም እንዲመዘገብ አድርገዋል።

### መ) የምርጥ ዘር አቅርቦት

ባለፉት ሦስት ተከታታይ ምርት ዘመን 3.81 ሚ/ኩ/ል ለማቅረብ ታቅዶ 2.79 ሚ/ኩ/ል (73.2%) በማቅረብ 2.65 ሚ/ኩ/ል ተሰራጭቷል። በዘር ዘርፉ ላይ ዋነኛው ተግዳሮት የመሬት አቅርቦት እና የመነሻ ዘር አቅርቦት በዓይነትና በመጠን ከፍላጎቱ ጋር አለመጣጣም ሲሆን የጥራት ችግሮችም በሰፊው ዘርፉን እየፈተኑ ያሉ ችግሮች ናቸው።

### ሠ) የእንስሳትና ዓሳ ሃብት ግብዓት አቅርቦት

ባለፉት ሦስት ዓመታት 71.9 ሚ/ን የአንድ ቀን ጫጩቶችን ለተጠቃሚው በማቅረብ ለማሰራጨት ታቅዶ 87.2 ሚ/ን (100+%) ጫጩቶችን ማሰራጨት ተችሏል። የመኖ አቅርቦት እና ስርጭትን በተመለከተ 58,592 ኩ/ል በማቅረብ ለማሰራጨት ታቅዶ 71,078 ኩ/ል መኖ በማቅረብ ማሰራጨት ተችሏል። ለእንስሳት ምርቶች መወደድ ዋነው ምክንያት የመኖ አቅርቦት ሰንሰለት መብዛትና ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ አለመሆኑ ነው።

## 2.4.2. የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት

ባለፉት ሦስት በጀት ዓመታት 38,000 የተለያዩ የፈረስ ጉልበት ያላቸውን ትራክተሮች ከነመለዋወጫቸው በግል ባለሃብቶችና ህብረት ስራ ማህበራት በኩል ለማቅረብ ታቅዶ 34,630 ተፈጽሟል። የኮምባይነር (አጭዶ መውቂያ) አቅርቦት አፈጻጸም በሚመለከት 14,000 ለማቅረብ ታቅዶ 10,686 ኮምባይነር ማቅረብ ተችሏል። በተመሳሳይ ባለሞተር መውቂያና መፈልፈያ አቅርቦት አፈጻጸም ሲታይ ባለፉት ሦስት በጀት ዓመታት 17,006 ባለሞተር መውቂያና መፈልፈያ ለማቅረብ ታቅዶ 13,200 ማቅረብ ተችሏል። በተጨማሪም የነፍስ ወከፍ መርጫና መለዋወጫ አቅርቦት በተመለከተ በሦስቱ በጀት ዓመት 302,500 የነፍስ ወከፍ መርጫ ከነመለዋወጫቸው ለማቅረብ ታቅዶ 911,449 (100+%) ማቅረብ ተችሏል። የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ላይ ያለውን የክህሎት ችግር ለመፍታትና ለተጠቃሚዎች በቅርበት ተገቢውን ድጋፍ ለመስጠት የተለያዩ ማሰልጠኛ ማዕከላትን በማቋቋም የአጫጭርና የደረጃ ስልጠናዎችን ለመስጠት እየተሰራ ሲሆን 2 በደረጃ (ሌቭል) የሚያሰለጥኑ ማዕከላት ለማቋቋም ታቅዶ 2 ማዕከላትን ማቋቋምና አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ተደርጓል። በጨማሪም አጫጭር ስልጠናዎች ለመስጠት የሚያስችሉ የስልጠና ማዕከላትን በሚመለከት 20 ለማቋቋም ታቅዶ 5 ማዕከላትን በማቋቋም አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ተችሏል። በተጨማሪም 2 የተመረጡ የአርብቶ/ አርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት የተሟላ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ተደርጓል።

በኦሮሚያ አማራና ደቡብ ክልሎች በተለያዩ አካላት የተጀመሩትንም የማሻሻል እና የማሳደግ አላማ ለማሳካት በሚያስችል መልኩ በተመረጡ 15 የህብረት ስራ ዩኒየኖች የግብርና ሜካናይዜሽን ጽንሰ ሃሳብ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል። አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና አሰራሮችን ለማስተዋወቅ አላማ ባደረገ መልኩ ለተመረጡ 5 ዩኒየኖች በፕሮጀክት የተገዙ ትራክተር እና የተሟላ የቅድመ ምርት እና ድህረ ምርት ቴክኖሎጂዎች የማሸነሪ ድጋፍ ተደርጓል። ለግብርና አገልግሎት የሚውሉ የግብርና ሜካናይዜሽን ማሽነሪዎች፣ ቴክኖሎጂዎች እና እቃዎች የቀረጥ እና ታክስ ነጻ ማረጋገጫ ለ1,092 አስመጪዎችና ግለሰቦች (በተደጋጋሚ አገልግሎት የወሰዱትን ጨምሮ) በመስጠት በድምሩ 1,197,421 የተለያዩ የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎች /በቁጥር 70,718 የተለያዩ መለዋወጫዎች/ ወደ ሃገር ውስጥ ገብተው ስራ ላይ እንዲውሉ ድጋፍ የተደረገ ሲሆን በተጨማሪም ለ10 የተለያዩ የጸረ ሰብል ኬሚካል መርጫ እና መለዋወጫ አስመጪዎች የቴክኒክ ምርመራ ድጋፍ በመስጠት አጠቃላይ የኬሚካል መርጫዎችና መለዋወጫዎች በቁጥር 348,503 የተለያዩ የሰብል ጸረ-ተባይ ኬሚካል መርጫ መሳሪያዎች ከነመለዋወጫዎቻቸው ወደ ሀገር ውስጥ ገብቷል።

ዜና ሀ/ወልድ
ስ/ ... ትራተጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

### የግብርና ሜካናይዜሽን የአጠቃቀም ክህሎትን ማሳደግ

የግብርና ሜካናይዜሽን የቴኒክኒክ ትምህርት ስልጠና ኮሌጆች በሌቭል ስልጠና የሞያ ደረጃ እና ማሻሻል እና ካሪኩለም ዝግጅት ቀደም ሲል ከ5 ዓመት በፊት የተዘጋጀውን የሞያ ደረጃና ስርዓተ ትምህርት ለማሻሻል ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎች ኦፕሬሽን እና ጥገና ባለሞያዎችን ለማሰልጠን ከሌቭል 1-4 የሙያ ደረጃ (OS) እንዲሻሻልና እና ካሪኩለም (Curriculum) በአዲስ መልክ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

ከኮሪያ መንግስት በተገኘው የገንዘብ ድጋፍ ሀንድ ሀገር አቀፍ የግብርና ሜካናይዜሽን ልህቀት ማእከል እና አምስት በክልል ደረጃ የግብርና ሜካናይዜሽን ልህቀት ማእከል ለማቋቋም የሚያስችል ፕሮጀክት ለመተግበር የሚያስችል የአፈፃፃም ማንዋል እንዲዘጋጅ፣ ማእከላቶቹን ለመገንባት የሚሆኑ ቦታ በቃሊቲ ቅጥር ግቢ ውስጥ እንዲዘጋጅ በማድረግ ሌሎች ዲዛይን እና የግንባታ ፈቃድ ማስጨረስ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ ከሰላም ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ለጋምቤላ እና ቤኒሻንጉል ክልሎች በቁጥር 42 የሚሆኑ ባለ2 ኢንች የውሃ ፓምፖች ግዢ የጥራት ፍተሻ እና ስርጭት እንዲካሄድ ቴክኒካል ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በLRLP ፕሮጀክት የተገዙ ትራክተሮች እና ተቀጽላ መሳሪያዎች እና SDR ፕሮጀክት የተገዙ በቁጥር አራት በትራክተር የሚሰሩ የዛፍ ችግኝ መትከያ እና የሳር ዘር መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ግዢ የጥራት ፍተሻ እና ስርጭት እንዲካሄድ ቴክኒካል ድጋፍ ተደርጓል፣ በኦሮሚያ 81 ትራክተሮች፣ 10,828 የውሀ ፓምፖች፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል 25 ትራክተሮች እና እና በሶማሊ ክልል የተገዙ በቁጥር 162 ትራክተሮች ግዢ የጥራት ፍተሻ እና ስርጭት እንዲካሄድ ቴክኒካል ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በቁጥር ሰላሳ /30/ የሚሆኑ ከዚህ በፊት ለፍተሻ መጥተው ተከማችተው የቆዩ ናፕሳክ እስፕሬየሮች ለአቃቂ ክፍለ ከተማ ድጋፍ በማድረግ ለአገልግሎት እንዲውሉ ተደርጓል፡፡

### 2.4.3. የግብርና ኢንቨስትመንትና ምርት ግብይት

### ሀ) የሰፋፊ እርሻ ኢንቨስትመንት ማስፋፊያ

በሰፋፊ እርሻ ኢንቨስትመንት በተሰማሩ ባለሀብቶች በመኸርና በመስኖ በዋና ዋና ሰብሎች በ2012 ምርት ዘመን በሄ/ር በተለያዩ ሰብሎች የለማውን 800.84 ሺህ ሄ/ር መሬት በ2015 ወደ 980 (14.9%) ሺህ ሄ/ር መሬት በሰብል እንዲለማ ተደርጓል፡፡ ምርትን በተመለከተ በ2012 ከነበረበት 17.36 ሚ/ን ኩንታል ወደ 31.76 ሚ/ን ማሳደግ ተችሏል፡፡

### የመሬት ልማት

በ2013 ምርት ዘመን 856.44 ሺህ ሄ/ር መሬት ለማልማት ታቅዶ 863.671 ሺህ ሄ/ር (100.8%) ማልማት ተችሏል፡፡ በበጀት ዓመቱ 110,245 ሄ/ር መሬት ለማስተላለፍ ታቅዶ 99,221 ሄ/ር (90%) መሬት ለ2015 ለአዳዲስ ባለሀብቶች በክልሎች በኩል እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ በ2014 ምርት ዘመን 999.459 ሺህ ሄ/ር መሬት በሰብል እንደሚሸፈን እቅድ የተያዘ ሲሆን አፈጻጸሙ በመሬት ልማት 806.308 ሺ.ህ ሄ/ር (80.67%) ነው፡፡ ለባለሀብት መሬት ማስተላለፍ ጋር በተያያዘ ለ362 ባለሀብቶች 130,541.4 ሄ/ር (94.52%) መሬት ተላልፏል፡፡ በ2015 በጀት ዓመት 1,157.74 ሺህ ሄ/ር በተለያዩ ሰብሎች እንዲለማ



ከአ ዜና ሀ/ወልድ የስትራቴጂክ ጉዳዮች ሥራ አስፈጻሚ

ለማድረግ የታቀደ ሲሆን በተለያዩ ምክንያቶች ከክልሎች የመሬት ልማት የተገኘ መረጃ ተሰብስቦ ባይጠናቀቅም ከባለፉት አመታት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በመነሳት የለማ የመሬት 920.51 ሺህ ሄ/ር (79.55%) እንደሚደርስ ይገመታል። ለአፈጻጸሙ ማነስ የተለዩ መሰረታዊ ተግዳሮቶች በትግራይ ክልል 159,114 ሄ/ር መሬት ለማልማት በዕቅድ ተይዞ በክልሉ በነበረው የፀጥታ ችግር ምክንያት በቂ መረጃ አለመኖር፣ በተመሳሳይ በቤኒሻንጉል-ጉሙዝ (መተከልና ካማሽ ዞኖች) እና አፋር ክልሎች በተከሰተው የፀጥታ ችግር ለባለሀብት የተላለፈው መሬት በብዛት ወደ ልማት መግባት አለመቻል፣ በዝናብ ለሚለማው መሬት ብድር አቅርቦት አለመኖር የተነሳ በርካታ እርሻ ኩባንያዎች ወደ ልማት አለመግባት፣ ለባለሀብቶች ከተላለፈው መሬት በተገባው ውል ወደ ልማት ያልገባውን መሬት በመለየትና ውሳኔ በመስጠት ለሌላ ባለሀብት ማስተላለፍ አለመቻል፣ የግብዓት አቅርቦት ውስንነት እና አልፎ አልፎ የመሰረተ ልማት አለመሟላት ከሚጠቀሱ ምክንያቶች ዋና ዋናዎች ናቸው።

### ለ) የሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንትና ወጪ ንግድ

ባለፉት ሶስት ዓመታት የሆርቲካልቸር ግብርና ምርቶች የወጪ ንግድ አጠቃላይ አፈፃፀም (በአበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት ዘርፍ) በድምሩ 1,176 ሺህ ቶን ለማቅረብ ታቅዶ 935.2 ሺህ ቶን (79.5%) ምርትን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ተችሏል። ከወጪ ምንዛሬ ግኝት አንጻር ከንኡስ ዘርፉ በድምሩ 2,018.32 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 1,818.22 ሚ/ን (90%) የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ተችሏል።

### ሐ) የግብርና ምርት ውል (ኮንትራት እርሻ) እቅድ አፈጻጸም

የግብርና ምርት ውል (Contract Farming) ለማስተዋወቅ በተዘጋጀ መድረክ ላይ ከክልል 16፣ ከፌደራልና ከባለድርሻ አካላት 52፣ መስኩን ከሚደግፉ መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት 5 እና ትስስር ፈጥረው እየሰሩ ከሚገኙ ባለሀብቶች 9 ጋር በተደረገ ውይይት በጠቅላላው 82 ተሳታፊዎች ተገኝተዋል። በውይይቱም ስድስት ጥናታዊ ጹፎች ቀርበው በርካታ ቁምነገር ተገኝቶበታል። በክልሎች በተደረገው የመስክ ዳሰሳ በአጠቃላይ 17 ድርጅቶች ከ 12,977 (2,595 ሴቶች) አርሶ አደሮች ጋር ትስስር ፈጥረው እየሰሩ ሲሆን በዚህም ትስስር 9,586.12 ሄ/ር መሬት በማልማት 36,148 ኩ/ል ዘር ብዜትና የቢራ ገብስ፣ 118,929.53 ኩ/ል ቀይ ቡና፣ 500 ኩ/ል ማር እና 3,500 ሊትር ወተት/ቀን ማግኘት የተቻለ ሲሆን ከስራ ዕድል ፈጠራ አኳያም ለ250 (75 ሴት) ቋሚና ለ2,346 (1,899 ሴት) ዜጎች የስራ ዕድል በመፍጠር ትልቅ አስተዋፅኦ ማበርከት እንደሚችል ለማየት ተችሏል።

**ለባለሀብቶች የክትትልና ድጋፍ ስራ መስራት፡-** በክልሎች በመስክ በመገኘት ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ በተያዘው እቅድ መሰረት በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች እንቅስቃሴ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ መረጃው ለማሰባሰብ ተችሏል። ከክልልና ዞን ግብርና ቢሮዎች ጋር በመቀናጀት በግብርና ምርት ውል ላይ የተሰማሩ 9 ድርጅቶችን መረጃ ማለትም በትስስሩ የለማ መሬት (40,265 ሄ/ር) ፣ የተገኘ ምርት 459,930.36 ኩ/ል፣ በትስስሩ የታቀፉ አርሶ አደሮች ብዛት (13,579) እና 351 መሰረታዊ ማህበራት ሲሆኑ በትስስሩ የተፈጠረ

ኣካ ዜና ሀ/ወልድ የስትራቴጂክ ጉዳዮች ሥራ አስፈጻሚ

የስራ ዕድል ደግሞ (454 ቋሚና 910 ጊዜያዊ) መሆኑንና በልማቱ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ዙሪያ አስፈላጊው ውይይት ተደርጓል።

**የውጭ ምንዛሬ ማሳደግና የአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦትን ማሳደግ፡-** የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነትን ለመወሰን የተዘጋጀውን ረቂቅ አዋጅ ከህግ ክፍል እና ኤ.ቲ.አይ ጋር በመቀናጀት ሰነዱን በማዳበር በተቋሙ በኩል ለተወካዮች ምክር ቤት ተልኳል።

**የግብይት የህግ ማዕቀፎች እንዲዘጋጁና እንዲጸድቁ ማድረግ፡-** የህብረ-ንብና የንብ ውጤቶች እንዲሁም የወተትና የወተት ተዋጽኦ የግብይት ህግ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ እንዲዘጋጅ ተደርጓል። በመንግስትና የግል አጋርነት ዘርፍ የቁም እንስሳት ኳራንቲ አገልግሎት የአሰራር ማኑዋል ተዘጋጅቷል።

**የግብርና ምርት ግብይት ደረጃዎችን ማዘጋጀት፡-** የወተትና የወተት ተዋጽዖ ደረጃዎች እንዲሁም የእንስሳት መኖ ልማት ብሔራዊ ደረጃ የማዘጋጀት ስራ ተከናውኗል። የዶሮ ሀብት ልማትና ግብይት እንዲሁም የማርና ሰም ሀብት ልማትና ግብይት የህግ ማዕቀፍ ረቂቅ ተዘጋጅቷል።

**የገበያ ትስስር ስራዎች ማጠናከር፡-** የገበያ ትስስርን በሚመለከት አርብቶ አደሮችና ኤክስፖርት ቄራዎች መካከል የበጎችና ፍየሎች የገበያ ትስስር እንዲያደርጉ ድጋፍ ተደርጓል። በልማት ባንክ እና 10 የግል ንግድ ባንኮች ለግብርና ዘርፍ ስራዎች የሰጡት ብድርን በተመለከተ በተደረገው ክትትል በድምሩ ለ857 ተጠቃሚዎች ብር 14,757,178,260.24 ተሰጥቷል።

### 2.4.4. የግብርና የስራ ዕድል ፈጠራና የከተማ ግብርና ልማት

**የግብርና ስራ ዕድል ፈጠራ**

በሀገር ደረጃ ባለፉት 3 ዓመታት በግብርናው ዘርፍ 2,964,000 ለሚሆኑ ዜጎች የስራ እድል ለመፈጠር ታቅዶ ለ3,200,605 (100⁺%) ስራ ፈላጊዎች በግብርና ዘርፍ ቋሚና ጊዜያዊ የስራ እድል ተፈጥሯል። ለስራ እድል ምቹ የሆኑ የስራ ዘርፎች ማለትም እንስሳት ሀብት ልማት እና አትክልትና ፍራፍሬ የተፈጠረው ስራ እድል ዝቅተኛ ነው። ለግብርና የስራ እድል ፈጠራ የመሬት አቅርቦት እቅድ 319,530 ሄክታር ክንውን 129,357.62 ሄክታር (40.48%)፣ ብድር አቅርቦት ብር 17 ቢሊየን ለማቅረብ ታቅዶ ብር 2.3 ቢሊየን የቀረበ ሲሆን አፈጻጸሙ 13.5% ነው። ለመስርያና ለመሸጫ አገልግሎት የሚውል 10,519 ሼድ ለማቅረብ ታቅዶ 1,889 (17.96%) ቀርቧል። በመሆኑም የሚደረጉ ድጋፎች በጣም ዝቅተኛ መሆኑ ያሳያል። ለአብነት መንግስት ለተዘዋዋሪ ብድር የመደበው ብድር በአግባቡ አለመመለሱና ተጨማሪ ተዘዋዋሪ ብድር አለመፈቀዱ ከጊዜ ወደ ጊዜ ብድር አቅርቦት እየቀነሰ እንዲሄድ አድርጎታል።

በሌላ በኩል የግብርና ስራ እድል ፈጠራ በተፈለገው ደረጃ እና ስፋት ለማስፋፋት በፌዴራል ደረጃ የተፈጠው አደረጃጀት ክክልልና ከተማ አስተዳደር ጀምሮ ባለው መንግስታዊ መዋቅር የተናበበ አደረጃጀት ባለመኖሩ በቂ ክትትልና ድጋፍ ለመስጠት አልተቻለም። በተጨማሪም የግብርና ሙያ በቴክኖሎጂ ባለመደገፉ በሙያው ለመሰማራት ያለው ፍላጎት አነስተኛ መሆን፣ በክልሎች ያለው ትስስር አነስተኛ መሆን፣ የስልጠናና ቴክኖሎጂ ልማት አለመስፋፋት፣ የገበያ አቅርቦትና ትስስር ማነስ፣ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት መጨመር፣ የተጠናከረ የአሰራር ስርዓት አለመኖር፣ በየደረጃው ያለ ፈፃሚና አስፈፃሚ

ዜና ሀ/ወልድ
ዳይሬክቶሬት ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

Federal Democratic Republic ... Ministry of Agriculture

አካላት የአቅም ውስንነት እንዲሁም በግብርናው የስራ ዘርፍ ለመስራት የወጣቶች የአመለካከት ችግሮች ትኩረት የሚሹ ዋና ዋና ዎቹ ተግዳሮቶች ናቸው።

**የአግሪ ቢዝነስ ስራዎችን ማስፋፋት**

የእሴት ሰንሰለት መሰረት ያደረገ የአግሪቢዝነስ ስራዎች ለማስፋፋት ገበያ ተኮር ምርቶችን የሚያመርቱ አርሶ/አርብቶ አደሮች፣ የንግድ ስራ ፈቃድ በማውጣት በግል በአግሪቢዝነስ የሚሰማሩ አካላት እንዲሁም በኢንተርፕራይዝ እና በህብረት ስራ ማህበራት በመደራጀት 155,600 አካላት የአግሪቢዝነስ ስራ ላይ ለማሰማራት እቅድ ተይዞ በበጀት አመቱ መጨረሻ ላይ 83,000 (53.4%) ስራ ላይ ተሰማርተዋል። በአግሪቢዝነስ ለሚሰማሩ 156,800 አካላት የድጋፍ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ በ2015 በጀት አመት መጨረሻ ላይ 217,000 (100+%) አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያገኙ ተደርጓል።

**የከተማ ግብርና ልማት**

የባለፉት ሦስት አመታት በከተማ ግብርና የተካሄደው የእንስሳት ሀብት ልማት አፈጻጸም ስንመለከት በወተት ልማት 24,924 ሚ/ን ሊትር ለማምረት ታቅዶ 23,436 ሚ/ን ሊትር (94%) ወተት ተመርቷል። የስጋ ምርት 15,309,000 ቶን የበሬ ስጋ፣ 7,494,000 ቶን የበግና ፍየል፣ 260,000 ቶን የዶሮ ስጋ ላመምረት ታቅዶ በቅደም ተከተል መሰረት 18,325,000 ቶን (100+%) ፣ 15,259,000 ቶን (100+%) ፣ እና 361,000 ቶን (100+%) ተከናውኗል። የእንቁላል ምርት እቅድ 43,406 ሚ/ን ሲሆን ክንውን 43,200 ሚ/ን ነው። የማር ምርት 1,218 ቶን እቅድ የተያዘ ቢሆንም ክንውኑ 1,418 ቶን ነው። በከተማ ግብርና በመኖ ማቀነባበር 100 ቶን እንዲመረት ታቅዶ 98 ቶን ተከናውኗል። በከተማ ግብርና የአሳ ማስገር፣ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል፣ የቴክኖሎጂና ግብዓት አቅርቦት እና የከተማ ግብርና ኤክስቴንሽን ሽፋን ለማሻሻል በባለፉት በጀት አመታት የታቀደ ስራ ባይኖርም ከከተማ አስተዳደሮች የሚሰበሰብ መረጃ ለወደፊት ስራ እንደሚፈልግ ያሳያል።

የከተማ ግብርና ልማት ለማስፋፋት የህብረተሰቡን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ 213,365 ተሳታፊዎች በዶሮ እርባታ፣ በወተት ሀብት ልማት፣ በዳልጋ ከብት ድለባና በግና ፍየል ማድለብ፣ በንብ ማነብ እና በመኖ ማቀነባበር የስራ ዘርፎች እንዲሰማሩ ለማድረግ ታቅዶ 141,639 (66.4%) ተሳታፊዎች ተሰማርተዋል። የከተሞች የውሃ አጠቃቀም ፖሊሲ ለከተማ ግብርና ልማት የሚሆን የከርሰ ምድር ውሃ በማውጣት ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ የበጀት እጥረት መኖሩ፣ በስራ ዘርፉ ልምድና ክህሎት ያላቸው ባለሙያዎች እጥረት በመኖሩ የከተማ ግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ በሚፈለገው ደረጃ ተደራሽ አለመሆን፣ የከተማ ግብርና አደረጃጀት ወጥ አለመሆን እና ጠንካራ የአሰራር ስርአት አለመዘርጋት ለአገልግሎት አሰጣጥ እና ለመረጃ ቅብብሎሽ ላይ ማነቆ እየሆኑ ነው።

### 2.4.5. የኅብረት ሥራ ማህበራት

የኅብረት ሥራ ሴክተሩን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር ከተቀመጡ ስትራቴጅካዊ የትኩረት መስኮች መካከል የኅብረት ስራ ማህበራትን ማጠናከር አንዱና ዋነኛው እንደመሆኑ ኅብረት ስራ ማህበራት ከአገር ዓቀፍ እና ዓለም ዓቀፍ የኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ለውጥ እና ዘመን ጋር አደረጃጀታቸውን፣ አመራራቸውን፣

ዜና ሀ/ወልድ
ከ ስትራቴጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

አሰራራቸውን እና አገልግሎት አሰጣጣቸውን በማዘመን ዘመናዊ ቴክኖሎጅዎችን በመጠቀምና በማስፋፋት ነባርና አዳዲስ ኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባሎቻቸው የሚሰጡት አገልግሎት ጥራት ያለው፣ ተደራሽ እንዲሆንና አባላት ያሉባቸውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቻቸውን ለመፍታት የሚያስችል እና መሪነታቸውን፣ ባለቤትነታቸውን፣ ተጠቃሚነታቸውን እና አመኔታቸውን ማሳደግ እንዲችሉ ወጥ የሆነ የማጠናከሪያ የአሰራር ስርዓት ሰነድ በማዘጋጀት ላለፉት አመታት ሲተገበር ቆይቷል። በዚህም በአምስት ዓመት እቅድ ዘመኑ ለሦስት አመት ለትግበራ ከታቀደዉ አንፃር እንደሚተለዉ ተተንትኗል።

**ኅብረት ሥራ ማኅበራትን ማጠናከር፣**

ነባር የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባሎቻቸው የሚሠጡትን አገልግሎት ጥራት ያለውና ተደራሽ እንዲሆንና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቻቸውን እንዲቀርፉ ለማድረግ በአምስት ዓመት እቅድ ዘመኑ ለሦስት አመት ለትግበራ ከታቀደዉ 59,001 መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት፤ 379 የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች እና 4ቱን የኅብረት ሥራ ፌዴሬሽኖች ለማጠናከር ታቅዶ በየዓመቱ በማጠናከር ስራዎችን በድግግሞሽ 79,174 መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን፤ 543 የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖችን እና 3ቱን የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽኖችን በአደረጃጀት፣ በአመዘጋገብ፤ በስራ አመራር፣ በአሰራር ስርዓት ዝርጋታ፤ መልካም አስተዳደርን በማስፈን፤ በተግባራት አፈፃፀም፣ በፋይናንስና ንብረት አስተዳደር እና በአባላት ተሳትፎና ተጠቃሚነት እንዲሁም በተቋማዊ መሰረት ልማት ግንባታና አስተዳደር ያሉባቸውን ችግሮች ለመፍታት አቅማቸውን መገንባት፤ የአፈፃፀም ብቃታቸውን ማሳደግ እና የተቋቋሙለትን ዓላማ ማሳካት የሚያስችሉ የማጠናከር ሥራ ተከናውኗል።

**ኅብረት ሥራ ማህበራትን ማደራጀት፣**

በኅብረተሰቡ ጥያቄ መሰረት በተጠኑና በተመረጡ የሥራ መስኮች በአምስት ዓመት እቅድ ዘመኑ ለሦስት አመት ለትግበራ ከታቀደዉ 3,000 አዳዲስ መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት እና 9 የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች ለማደራጀት ታቅዶ፤ 17,829 መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት፤ 12 የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች እና 2 ፌደሬሽን ለማደራጀት ተችሏል።

**በመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት አዳዲስ አባላትን ማፍራት፣**

አዳዲስ አባላትን በማፍራት የአባላትን ቁጥር ለመጨመር፤ የአባላትን ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ አዳዲስ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን ማደራጀት እና ነባሮችን በማጠናከር ጠንካራ አባላትን ማፍራት በአምስት ዓመት እቅድ ዘመኑ ለሦስት አመት ለትግበራ ከታቀደዉ 4,600,000 (ወንድ 2,300,000 ሴት 2,300,000 ወጣት 1,380,000) ታቅዶ ክንዉን 5,981,972 (ወንድ 3,798,756 ሴት 2,183,226 ወጣት 746,241) ክንዉኑ ከሦስት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ሲነፃፀር ከ100% በላዩን ማሳካት ሲቻል አፈፃፀሙ በአባላት ተሳትፎ በወንድ 63.5%፣ በሴት አባላት ተሳትፎ 36.5% ማከናወን ተችሏል።

**መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን የዩኒየን አባል ማድረግ**

የኅብረት ሥራ ማህበራት ጠንካራ መሰረትና አቋም እንዲኖራቸዉ ዩኒየኖች በስራቸው የሚያቅፏቸውን ኅብረት ስራ ማህበራት ቁጥር ለማሳደግ በአምስት ዓመት እቅድ ዘመኑ ለሦስት አመት ለትግበራ ከታቀደዉ 6,383 መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን የዩኒዬን አባል ለማድረግ ታቅዶ 4,160 መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን በዩኒየኖች አባል ለማድረግ ተችሏል። በዚህም የመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራትን

ለአ ዜና ሀ/ወልድ
... ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

የዩኒዬን አባል ማድረግ የዕቅዱን ከ65.2%ን መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት የዩኒዬን አባል ማድረግ ተችሏል። አፈፃፀሙ ሲታይ ዝቅተኛ በመሆኑ በእቅድ ክለሳ ወቅት የማካካሻ ስራዉን በእቅድ በማካተት ለቀጣይ በትኩረት ሊተገበር የሚገባ ስራ ነዉ።

**አጠቃላይ የኅብረት ስራ ማህበራትን ካፒታል ማሳደግ**

በአጠቃላይ የኅብረት ሥራ ማህበራትን በተሰማሩበት ዘርፍ ጠንካራ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የውስጥ የካፒታል አቅማቸዉን ለማሳደግ የማጠናከር ሥራ በመስራት እንዲሁም አዳዲስ ኅብረት ሥራ ማህበራት በጠንካራ የካፒታል አቅም ለማቋቋም በአምስት ዓመት እቅድ ዘመኑ ለሦስት አመት ለትግበራ ከታቀደዉ ብር 6,84 ቢ/ን ለማሳደግ ታቅዶ በክንዉኑ በብር 13.9 ቢ/ን የካፒታል አቅማቸዉን ማሳደግ ተችሏል። የዕቅዱ አፈጻጸምም ከ100% በላዩን ማከናወን ተችሏል።

**የኅብረት ሥራ ማህበራትን አቅም በመገንባት**

በጥናት ላይ የተመሰረተ እና ወቅታዊ የሆነ ስልጠና ለሁሉም የኅብረት ሥራ ፈጻሚና አስፈጻሚ አካላት በየዓመቱ በማዘጋጀት እና የተጀመረውን የሥራ ላይ ስልጠና አጠናክሮ በማስቀጠል በአምስት ዓመት እቅድ ዘመኑ ለሦስት አመት ለትግበራ ከታቀደዉ 24,000 የኅብረት ሥራ ማስፋፊያ ባለሙያዎችን፣ 240,000 የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራሮችን፣ 36,000 የኅብረት ሥራ ማህበራት ቅጥር ሰራተኞችን እና 11,640,000 የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት በድምሩም 11,940,000 የዘርፉን ተዋንያን በማብቃት እና የስልጠናውን ውጤታማነት ለማሳደግ ታቅዶ በአፈፃፀም ረገድ ለ43,435 የኅብረት ሥራ ማህበራት ባለሙያዎች፤ ለ431,552፤ የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራር አካላት ለ49,907 የኅብረት ሥራ ማህበራት ቅጥር ሠራተኞች እና ለ9,948,740 በድምሩም 10,473,634 የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የአቅም ግንባታ ስልጠና በመስጠት በዕውቀት፣ በክህሎት እና በአመለካከት ረገድ የነበረባቸውን ክፍተት መሙላት መቻሉን በተካሄዱ የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት እና የስልጠና ውጤታማነት ጥናት ማረጋገጥ ተችሏል።

**የኅብረት ሥራ ማህበራትን የግብይት ድርሻ ማሳደግ**

**የኅብረት ሥራ ማህበራት የሃገር ዉስጥ ግብይት**

በሃገር ዉስጥ ግብይት በአምስት ዓመት እቅድ ዘመኑ ለሦስት አመት ለትግበራ ከታቀደዉ የሀገር ዉስጥ ግብይት አንጻር የብርዕና የአገዳ ሰብል ግብይት 1,939,146.41 ቶን ለማቅረብ ታቅዶ ክንዉን 1,348,109.94 ቶን የብርዕና የአገዳ ሰብል ግብይት ተካሂዷል። የዕቅዱን 69.5% ማከናወን ተችሏል። የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት 258,960 ቶን ለማቅረብ ታቅዶ ክንዉን 113,671.80 ቶን የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ተካሂዷል። የዕቅዱን 43.9% ማከናወን ተችሏል። የቅባት እህሎች ግብይት 291,174 ቶን ለማቅረብ ታቅዶ ክንዉን 38,854.33 ቶን የቅባት እህሎች ግብይት ተካሂዷል። የዕቅዱን 13.3% ማከናወን ተችሏል። አትክልትና ፍራፍሬ ግብይት 2,164,837 ቶን ለማቅረብ ታቅዶ ክንዉን 1,921,207.27 ቶን አትክልትና ፍራፍሬ ግብይት ተካሂዷል። የዕቅዱን 88.7% ማከናወን ተችሏል። ቅመማ ቅመም ግብይት 9,120 ቶን ለማቅረብ ታቅዶ ክንዉን 109,357.18 ቶን ቅመማ ቅመም ግብይት ተካሂዷል። የዕቅዱን 100% በላይ ማከናወን ተችሏል። ቡና ግብይት 142,281 ቶን ለማቅረብ ታቅዶ ክንዉን 46,231.97 ቶን ቡና ግብይት ተካሂዷል።

ከኣ ዜና ሀ/ወልድ የስትራተጂክ ጉዳዮች ሥራ አስፈጻሚ



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

የዕቅዱን 32.5% ማከናወን ተችሏል፡፡ የእንስሳት ተዋፅዖ ግብይት 234,482 ቶን ለማቅረብ ታቅዶ ክንዉን 766,004.77 ቶን የእንስሳት ተዋፅዖ ግብይት ተካሂዷል፡፡ የዕቅዱን 100% በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ የግብርና ምርቶችን ለአገር ውስጥ ገበያ ማቅረብ በአምስት ዓመት እቅድ ዘመኑ ለሦስት አመት ለትግበራ ከታቀደዉ 5,040,000 ቶን ለማቅረብ ታቅዶ በክንዉኑም 5,065,776 ቶን ምርት ለሀገር ዉስጥ ግብይት ቀርቧል፡፡ በአፈፃፀም ረገድ የዕቅዱን ከ100% በላዩን ማከናወን ተችሏል፡፡ በአገር ውስጥ የቁም እንስሳት ግብይት በቁጥር 555,566 ተካሂዷል፡፡

በተጨማሪም በዕቅድ ያልተያዙ እጣን እና ሙጫ ግብይት 956.10 ቶን ማር ግብይት 9,788.40 ቶን ጨዉና አሞሌ ጨዉ ግብይት 719,231.60 ቶን በድምሩ 729,976.10 ቶን በኅብረት ሥራ ማህበራቱ ግብይት ተካሂዷል፡፡

**በቅድመ እና ድህረ ምርት የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት**

የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት በግብርና ቅድመ ምርት እና ድህረ ምርት ተግባራት ላይ የተለያዩ የግብርና ምርታማነትን ሊያሳድጉ የሚችሉ የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ በአገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ ብቁ ተወዳዳሪ እየሆኑ የግብይት ተሳትፎን በማሳደግ የአባለትን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነትን በማሳደግ ከፍተኛ ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ፡

**የቅድመ ምርት መካናይዜሽን አገልግሎት አፈፃፀም አንፃር**

የግብርና ቅድመ ምርት ሜካናይዜሽን አገልግሎት የሚሰጡ አዳዲስ የመካናይዜሽን መሳሪያዎች በማስገባት ህብረት ሥራ ማህበራቱ ለአባሎቻቸዉ አገልግሎት እንዲሰጡ በአምስት ዓመት እቅድ ዘመኑ ለሦስት አመት ለትግበራ 210 ታቅዶ 989 ማከናወን ተችሏል፡፡

**የድህረ ምርት መካናይዜሽን አገልግሎት አፈፃፀም**

ኅብረት ሥራ ማህበራት የድህረ ምርት መካናይዜሽን አገልግሎት ለአባሎቻቸዉ እና በዙሪያቸዉ ለሚገኙ አርሶ አደሮች እና ለግብርናዉ ክፍለ ኢኮኖሚ የበኩላቸዉን ማበርከት እንዲችሉ በአምስት ዓመት እቅድ ዘመኑ ለሦስት አመት ለትግበራ 90 ታቅዶ 511 የተለያዩ የግብርና ድህረ ምርት መካናይዜሽን ማሽነሪዎች ቀርበዉ ለአባላቱ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡

**የኅብረት ሥራ ማህበራት የዉጭ ግብይት**

ኅብረት ሥራ ማህበራት በሀገር ውስጥና በውጭ ግብይት ላይ ብቁ ተወዳደሪ እንዲሆኑና የሀገር ውስጥ የገበያ ድርሻቸውን እንዲሰፋ በማድረግ አምራቹንና ሸማቹን ቀጥታ በማገናኘት ተጠቃሚ እንዲሆኑና ለሀገር ኢኮኖሚ ግንባታም የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ለማስቻል በአምስት ዓመት እቅድ ዘመኑ ለሦስት አመት ለትግበራ ከታቀደዉ ቡና ግብይት 70,099 ቶን፣ የቅባት እህል ግብይት 14,924 ቶን፣ ጥራጥሬ ግብይት 2,192 ቶን፣ ማር ግብይት 204 ቶን፣ እጣን እና ሙጫ ግብይት 163 ቶን፣ አትክልት እና ፍራፍሬ ግብይት 202 ቶን ቅመማ ቅመም ግብይት 2,216 ቶን በድምሩም 90,000 ቶን የተለያዩ የግብርና ምርቶች በማቅረብ 469,235,294 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ

በክንዉን ደረጃ ቡና 32,286.45 (46.1%) ቶን የቅባት እህል ግብይት 1,599 (11%) ቶን እና በጥራጥሬ (ቦሎቄና አኩሪ አተር) ግብይት 4,767 (100% በላይ) ቶን ማር ግብይት 1 ቶን በድምሩ 38,653.45 ቶን (42.9%) ወደ ተለያዩ አገራት በመላክና ግብይት በማካሄድ 202,326,024.65 ሚ/ን (43.1%) የአሜሪካን



ለአ ዘነበ ሀ/ወልድ
የስትራቴጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

ዶላር ተገኝቷል። በአፈፃፀም ረገድ በአራት አይነት የግብርና ምርቶች በመሳተፍ በመጠን ከዕቅዱ አንፃር 42.9% ሲከናወን ከዶላር ግኝት አንፃር 43.1% ማከናወን ተችሏል።

**የአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ውጤታማነትን ማሳደግ እና ማስፋፋት**

የኅብረት ሥራ ማህበራት በአባላት ምርቶች ላይ እሴት በመጨመር አባላት ከምርታቸው የተሻለ የገበያ ዋጋ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያደርግ አሰራር እንዲከተሉ በማድረግና የኅብረት ሥራ ማህበራት የተለያዩ ዓይነት አግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎችን በማቋቋም የአባላት ምርቶችን በማቀነባበር፣ በማሸግ እና ልዩ ምልክት በመስጠት ለገበያ እንዲያቀርቡ ትኩረት በመስጠት የአካባቢያቸውን ፀጋ መሠረት በማድረግ የሚያቋቁሟቸውን የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ስራዎችን ለአምስት ዓመት እቅድ ዘመኑ ለሦስት አመት ለትግበራ ከታቀደዉ 204 ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች ማቋቋም አፈጻጸም በተለያዩ አይነት 234 ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች ተቋቁመዋል። አፈፃፀሙ ከዕቅዱ ሲነፃፀር ከ100% በላይ ማከናወን ተችሏል።

**ቁጠባን ማሰባሰብ/ማሣደግ**

የኅብረት ስራ ማህበራት በገጠርም ሆነ በከተማ የሚኖረውን የህብረተሰብ ክፍል የቁጠባ ባህል እንዲዳብርና የአባላቱ ገቢ እንዲጨምርም ሆነ የአገር ኢኮኖሚ ግንባታ እንዲያድግ የሚያደርጉት አስተዋጽኦ ክፍተኛ ነው። በዚህም በፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰበሰበው የቁጠባ መጠን ማሳደግ ስራዎችን በአምስት ዓመት እቅድ ዘመኑ ለሦስት አመት ብር 10 ቢ/ን ለመቆጠብ ታቅዶ ብር 30.2 ቢ/ን በመሰብሰብ ከዕቅድ በላይ ማከናወን ተችሏል ።

**ብድር ሥርጭት/መስጠት**

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የመጨረሻቸው ግብ ቁጠባ ማሰባሰብ ብቻ ሳይሆን ቆጥቦ በማበደር ለኢንቨስትመንት ማዋል እንዲችሉ ማድረግ እንደመሆኑ ለአምስት ዓመት እቅድ ዘመኑ ለሦስት አመት ብር 12 ቢ/ን ለማሰራጨት ታቅዶ በክንዉን ደረጃ ብር 38.3 ቢ/ን ከዕቅድ በላይ ማከናወን ተችሏል። በዚህም ለ2,012,286 (ወንድ 851,265 ሴት 1,161,021 (57.7%)) አባላት ብድር አሰራጭተው በተለያዩ የልማት ሥራዎች ላይ ውሏል፡

**የሥራ ዕድል ፈጠራ**

በነባርና በአዲስ ኅብረት ስራ ማህበራት በአምስት ዓመት እቅድ ዘመኑ ለሦስት አመት ለትግበራ ከታቀደዉ 3,090,000 የስራ ዕድል 135,700 በቋሚና 2,954,300 በጊዜያዊ ለመፍጠር ታቅዶ ክንዉን ከ2,191,362 በላይ የስራ ዕድል 103,007 በቋሚነትና 2,088,355 በጊዜያዊነት ለመፍጠር የተቻለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የሴቶች ድርሻ 42.2 በመቶ በላይ መድረሱን በኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን በኩል ከክልሎችና ከተማ አስተዳደር ማስፋፊያ አካላት የተሰበሰበዉ ሪፖርት ያመለክታል።

### 2.4.6. ግብርና ምርምር

የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የግብርናውን ዘርፍ ለማዘመንና ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድጉ ቴክኖሎጂዎችን (የምርምር ውጤቶችን) በማቅረብ ለምግብ ዋስትና፣ ለውጭ ገበያ፣ ለአግሮ ኢንዱስትሪ ግብዓትና ለተፈጥሮ ሃብት አያያዝ አስተዋፅኦ ለማድረግ በ2013 እና በ2015 በጀት ዓመት በመልካም አስተዳደር የቁልፍ ስራዎች በመታገዝ በርካታ የምርምር ውጤቶችን አፍልቋል።

በእነዚህ ሶስት የበጀት ዓመታት የታቀዱ የምርምር ስራዎችን ለማካሄድ በመደበኛ ፕሮግራም ከተመደበው ውስጥ ብር 2,777 ሚ/ን (የዕቅዱ 96 በመቶ) ስራ ላይ የዋለ ሲሆን 1,348 (333 ቴክኖሎጂዎችና 1,015 መረጃዎች) የምርምር ውጤቶች ፈልቀዋል። አፈጻጸሙ በምርምር ፕሮግራሞች ሲተነተን በሰብል ምርምር 254 የምርምር ውጤቶች የተገኙ ሲሆን 514.7 ሚ/ን ብር (የዕቅዱ 96 በመቶ) ስራ ላይ ውሏል፤

በእንስሳት ምርምር 295 የምርምር ውጤቶች የተገኙ ሲሆን 310.6 ሚ/ን ብር (የዕቅዱ 97 በመቶ) ስራ ላይ ውሏል፤ በተፈጥሮ ሃብት አያያዝ ምርምር 149 የምርምር ውጤቶች የተገኙ ሲሆን 291.2 ሚ/ን ብር (የዕቅዱ 94 በመቶ) ስራ ላይ ውሏል።

በእጽዋት ጥበቃ ምርምር 195 የምርምር ውጤቶች የተገኙ ሲሆን 144.414 ሚ/ን ብር (የዕቅዱ 98 በመቶ) ስራ ላይ ውሏል፤ በግብርና ባዮቴክኖሎጂ ምርምር 90 የምርምር ውጤቶች የተገኙ ሲሆን 138.4 ሚ/ን ብር (የዕቅዱ 96 በመቶ) ስራ ላይ ውሏል፤

በግብርና ምህንድስና ምርምር 48 የምርምር ውጤቶች የተገኙ ሲሆን 47.7 ሚ/ን ብር (የዕቅዱ 99 በመቶ) ስራ ላይ ውሏል፤ በምግብ ሳይንስና ስነ-ምግብ ምርምር ላብራቶሪ 76 የምርምር ውጤቶች የተገኙ ሲሆን 72.6 ሚ/ን ብር (የዕቅዱ 99 በመቶ) ስራ ላይ ውሏል፤ በአየር ፀባይና ጂኦስፓሻል ምርምር 92 የምርምር ውጤቶች የተገኙ ሲሆን 28.5 ሚ/ን ብር (የዕቅዱ 95 በመቶ) ስራ ላይ ውሏል፤ በግብርና ኢኮኖሚክስ ምርምር 70 የጥናት ውጤቶች የተገኙ ሲሆን 65 ሚ/ን ብር (የዕቅዱ 98 በመቶ) ስራ ላይ ውሏል፤ በክትትልና ግምገማ ምርምር 3 የጥናት ውጤት የተገኘ ሲሆን 31 ሚ/ን ብር (የዕቅዱ 94 በመቶ) ስራ ላይ ውሏል፤ በተቀናጀ የግብርና ምርምር 57 የምርምር ውጤቶች የተገኙ ሲሆን 48.7 ሚ/ን ብር (የዕቅዱ 99 በመቶ) ስራ ላይ ውሏል፤ በቴክኖሎጂ ብዜትና የዘር ምርምር 29 የምርምር ውጤቶች የተገኙ ሲሆን 185.8 ሚ/ን ብር (የዕቅዱ 99 በመቶ) ስራ ላይ ውሏል፤ በግብርና ስርፀትና ኮሜርሻላይዜሽን 21 የጥናት ውጤቶች የተገኙ ሲሆን 102.6 ሚ/ን ብር (የዕቅዱ 97 በመቶ) ስራ ላይ ውሏል፤ በአርብቶ አደር፣ ከፊል አርብቶ አደርና ልዩ ድጋፍ የሚሹ ክልሎች ምርምር 31 የምርምር ውጤቶች የተገኙ ሲሆን 23.8 ሚ/ን ብር (የዕቅዱ 99 በመቶ) ስራ ላይ ውሏል። በማዕከል ልማትና ምህንድስና ፕሮግራም የታቀዱት ግንባታዎች ሲከናወኑ የነበረ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ የአስራ ሁለት ሕንጻዎች ግንባታ ሙሉ በሙሉ በመጠናቀቁ የመጨረሻ ርክክብ የተደረገ ሲሆን 134.9 ሚ/ን ብር (የዕቅዱ 81 በመቶ) ስራ ላይ ውሏል።

በሌላ በኩልም በምርምር የፈለቁ ቴክኖሎጂዎችን ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ለማድረግ ለ95,204 የልማት ተሳታፊ አካላት የማስተዋወቅ እና ለ84,898 የልማት ተሳታፊ አካላት የማስፋት እንዲሁም የተለያዩ የምርምር ጽሁፎችን አዘጋጅቶ የማሰራጨት ስራዎች ተከናውነዋል። የቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎችን ክህሎት

ለማሳደግ ለ124,518 አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮች፣ ከፊል አርብቶ አደሮች፣ የልማት ጣቢያ ሠራተኞች፣ የግብርና ባለሙያዎች፣ የዘር አባዦች፣ የግል ባለሀብቶች እና ከተለያዩ የልማት ድርጅቶች ለተውጣጡ አካላት የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል።

ይሁን እንጂ በአፈፃፀም ሂደት ለምርምር ማከናወኛ የሚመደበው በጀት አነስተኛ መሆን፣ የበጀት መልቀቂያ ጊዜ ከምርምር የስራ ወቅት ጋር አለመጣጣም እንዲሁም የላቦራቶሪ መሳሪያዎች፣ የተሽከርካሪና የእርሻ መሳሪያዎች እርጅናና እጥረት በመከሰቱ ሥራዎችን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመስራት እንቅፋት የሆነ ሲሆን የምርምር መገልገያ መሳሪያዎችን በመከራየትና ነባር ተሽከርካሪዎችና የእርሻ መሳሪያዎችን በመጠገን እንዲሁም ልዩ ልዩ አስተዳደራዊ አማራጮችን በመውሰድ የታቀዱ ስራዎች እንዲከናወኑ ጥረት የተደረገ ሲሆን ወደፊት የምርምር ስራውን በተፈለገው ዕቅድ መሰረት ለማከናወን ከላይ የተጠቀሱት ወሳኝ ችግሮች በጥናት የሚሻሻሉበት፣ ተሽከርካሪዎችና የእርሻ መሳሪያዎችን ለመግዛት የሚያስፈልገው በጀት የሚመደብበትና የግዥ ሂደቱም የሚፋጠንበት ሁኔታ ሊፈጠር ይገባል። አገራዊ የግብርና ምርምር ሥርዓቱን የማስተባበርና የማጠናከር ሥራዎች አፈፃፀም በአገር አቀፍ ደረጃ የግብርና ምርምር ሥራዎችን በማቀናጀት ውጤታማነትን ለማሳደግ እና ምርምሩን ለማዘመን በማስተባበር ረገድ የተሰሩ ዋና ዋና ስራዎች የሚከተሉት ናቸው።

## 2.5. የግብርና ቁጥጥር

### ፕሮግራም 1. የዕጽዋት ሬጉላቶሪ የግብዓት ቴክኖሎጅ አገልግሎትና ምርት ጥራት ቁጥጥር

በዚህ ፕሮግራም ውስጥ በቁልፍ አመልካችነት የተያዙት ሶስት ሲሆኑ እነዚህም በግብዓት ቁጥጥር ፣ በምርትና ቴክኖሎጂ የትኩረት መስኮች የታቀፉ ናቸው ። እነዚህን ወደ ስኬት ለማድረስ የተከናወኑ በርካታ ዝርዝር ተግባራት የሚገኙ ሲሆን በዚህ የሶስት ዓመታት የአፈጻጸም ትንተና ቁልፍ የሆኑ አመልካቾችን ብቻ መሠረት ያደረገ ትንተና እንደሚከተለው ቀርቧል።

### ውጤት 1. ውጤታማ ጥራቱና ደህንነቱ የተጠበቀ ፀረተባይና ማዳበሪያ

በዚህ ውጤት ውስጥ ስድስት ቁልፍ አመልካቾችና እነዚህን ወደ ስኬት ለማድረስ የተከናወኑ በርካታ ዝርዝር ተግባራት የሚገኙ ሲሆን በነዚህ ቁልፍ አመልካቾች የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው የዕጽዋት ምርት ግብዓቶች በተለይም ጸረ-ተባይና ማዳበሪያ ጥራትና ደህንነትን ለመጠበቅ ከተከናወኑ ተግባራት መካከል በ2012 የነበረውን መነሻ ለንጽጽር ሲወሰድ የሶስት አመታት አጠቃላይ አፈጻጸም በ62.61% መጨመር ተችሏል።

ከቁልፍ አመልካቾች አንጻር በዝርዝር ሲታይ ለሙከራ ምርምር ፈቃድ የተሰጣቸው ፀረ-ተባይና ማዳበሪያዎች በሶስት ዓመቱ ለ524 ታቅዶ ለ471 የተሰጠ ሲሆን የዚህ ቁልፍ አመልካች የሶስት ዓመት አፈጻጸም 90% ነው። በ2012 ከነበረው አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር የ3.5% ብቻ ልዩነት አሳይቷል። ተገምግመው የተመዘገቡ በሶስት ዓመት ውስጥ 564 የፀረ-ተባይ እና የአፈር ማዳበሪያዎችን ሰነድ በመገምገም ለመመዝገብ ታቅዶ 642 ሰነዶችን በመገምገም ለመመዝገብ ተችሏል። ከዕቅድና ክንውን አንጻር 113.8% አፈጻጸምና በ2012 ከነበረው ደግሞ የ150% ብልጫ አሳይቷል። ይህ የሚያመለክተው ባለፉት



ስለ ዜና ሀ/ወልድ
የስትራቴጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

ሶስት የበጀት ዓመታት በምዝገባና በግምገማ ሂደት የሚያልፉ የጸረ-ተባይና ማዳበሪያ ምርቶች መጨመራቸውን ነው። የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው እና እድሳት የተደረገላቸው ፀረ-ተባይ እና የአፈር ማዳበሪያ ተቋማትን ቁጥር በ2015 በጀት ዓመት 121 ማድረስ የተቻለ ሲሆን ባለፉት ሶስት ዓመታት ለ6,930 ቶን የፀረ ተባይና የአፈር ማዳበሪያዎችን የሀገር ውስጥ ኢንስፔክሽን ተደርጎላቸው የመልቀቂያ ፈቃድ እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ 6,255 ቶን የፀረ ተባይና የአፈር ማዳበሪያዎችን ወይም የዕቅዱን 90.1% ለመፈጸም ተችሏል። በ2012 ዓ.ም ከነበረው ጋር ሲነጻጸር የሀገር ውስጥ ኢንስፔክሽን ተደርጎላቸው የመልቀቂያ ፈቃድ እንዲያገኙ የተደረጉ ጸረ ተባይና ማዳበሪያዎችን መጠን በ32.1% ለመጨመር ተችሏል።

### ውጤት 2. ወደ ውጭ ለሚላኩና ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ የእጽዋት ምርቶች የተሰጠ የጤና ማረጋገጫ

በአጠቃላይ በወጪ የዕጽዋት ምርቶች ላይ የተደረጉ የቁጥጥር ስራዎች አፈጻጸም በቀጥታ ከኤክስፖርቱ ጋር ተያያዥ ናቸው። ይህ ማለት ከዕቅድ ክንውን አንጻር የተገኘው ውጤት መቀነሱ የሚያሳየው ለኤክስፖርት የቀረቡ ምርቶች መቀነሳቸውን ነው። በዚህ መሠረት ባለፉት ሶስት ዓመታት ለ4,020 ሜትሪክ ቶን የዕጽዋት ምርቶች የጤናና የጥራት ምርመራ ተደርጎላቸው እንዲላኩ የቁጥጥር ስራዎችን ለመስራት ታቅዶ ለ2,237 ሜትሪክ ቶን ምርቶች በቁጥጥር ስርዓት ውስጥ እንዲያልፉ ለማድረግ በመቻሉ ከዕቅድ አንጻር አፈጻጸሙ 55.6% ነው። በ2012 ዓ.ም ከነበረው ክንውን ጋር ሲነጻጸር ወደ ውጭ የሚላኩ የእጽዋት ምርቶች በ59% ቀንሰው ታይተዋል። ባለፉት ሶስት ዓመታት ለ197,000 ሜትሪክ ቶን ወደ ውጭ ለሚላኩ የእጽዋት ምርቶች የጤና ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመስጠት ታቅዶ 109,551 የጤና ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የተሰጠ በመሆኑ አፈጻጸሙ 55.6% ሆኗል። በ2012 ከተከናወነው አንጻር ክንውኑ በ69% ቀንሷል። ባለፉት ሶስት ዓመታት ለውጭ ገበያ በሚቀርቡ 1,020,000 ሜትሪክ ቶን የተመረጡ የዕጽዋት ምርቶች ላይ የማዕጠንት /Fumigation/ ክትትል ለማድረግ ታቅዶ በ583,676 ሜትሪክ ቶን የተመረጡ የዕጽዋት ምርቶች ላይ የማዕጠንት /Fumigation/ ክትትል ለማድረግ ተችሏል። ይህም የዕቅዱ 57.22% ሲሆን በ2012 ከነበረው ጋር ሲነጻጸር ክንውኑ በ76.1% ቀንሶ ታይቷል። በ6,400 ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕፅዋቶች፣ የእጽዋት ምርቶች፣ የዕፅዋት ውጤቶች እና ግብአቶች ጥራት እና ደህንነታቸውን ጠብቀው እንዲገቡ የላብራቶሪ ምርመራ ለማከናወን ታቅዶ 6,407 ላይ ለማከናወን በመቻሉ ዕቅዱ 100% ተፈጽሟል። በ2012 ከነበረው ጋር በንጽጽር ሲታይ ክንውኑ በ2015 የ55.5% ጭማሪ አሳይቷል።

### ውጤት 3. በቁጥጥር ሰንሰለት ውስጥ ያለፈ ጥራት ያለው ዘር

በዚህ ውጤት ውስጥ በሁለት የትኩረት መስኮችን ቁልፍ አመልካቾች ማለትም የቴክኖሎጂ ቁጥጥርና የዕጽዋት ግብዐት አንዱ በሆነው የዕጽዋት ዘር ቁጥጥርን አስመልክቶ የተከናወኑ ስራዎች ይታያሉ። ክክንውም አንጻር በ2012 ከነበረው ጋር ሲነጻጸር የ68.7% ብልጫ አሳይቷል ዝርዝር አፈጻጸሙ እንደሚከተለው ቀርቧል።

የቴክኖሎጂ ቁጥጥርን በተመለከተ በሶስት ዓመታት ውስጥ 320 ከተለያዩ የምርምር ተቋም ዩኒቨርስቲዎች የግል ኩባንያዎች የቀረቡ ዝርያዎችን በመስክ እንዲገመገሙ ለማስተባበር እና ለመገምገም ታቅዶ 338 (105%) ለማከናወን ተችሏል። በ2012 ከነበረው የ96 ዝርያዎች ክንውን ጋር ሲነጻር በ2015 የ119

ዜና ሀ/ወልድ
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር
ሥራ አስፈጻሚ

ዝርያዎች ክንውን ስላለ በ24% ለማሳደግ እንደተቻለ ያሳያል። ከግብዓት ቁጥጥር ጋር በተያያዘ ለ65 ጥያቄ ለሚያቀርቡ ዘር አስመጪዎች አምራቾችና አዘጋጆዎች የብቃት ማረጋገጫ መስጠትና ለማደስ ታቅዶ ለ65 ተከናውኗል። አፈጻጸሙ 93.5% ሲሆን ክንውኑ በንጽጽር በ2012 ከነበረበት 10 ወደ 25 ዘር አስመጪዎች አምራቾች ከፍ ስላለ በመቶኛ 150% ብልጫ አሳይቷል። በተመሳሳይ ለ770 ናሙናዎች በላቦራቶሪ የዘር ጥራት ፍተሻ እንዲደረግባቸው ታቅዶ ለ607 የዘርና ሙናዎች የጥራት ፍተሽ በመከናወኑ አፈጻሙ78.3% ሆኗል። በንጽጽር በ2012 ከነበረው የ176 ክንውን በ2015 180 ለማድረስ በመቻሉ ከክንውን አንጻር የ2.3% የብልጫ ልዩነት ታይቷል።

## ፕሮግራም 2 የእንስሳትና ዓሳ የግብዓት ቴክኖሎጅ አገልግሎትና ምርት ጥራት ቁጥጥር

በዚህ ፕሮግራም ውስጥ በውጤት ደረጃ የተያዙ አራት ሲሆኑ እነዚህም በእንስሳት ግብዓት ቁጥጥር እንዲሁም የእንስሳት ውጤቶች (ስጋ፣ ወተት፣ ማርና ሰም) የኤክስፖርት ቁም እንስሳት ቁጥጥርን የተመለከቱ የትኩረት መስኮች ስር የታቀፉ ናቸው። እነዚህን ወደ ስኬት ለማድረስ የተከናወኑ በርካታ ዝርዝር ተግባራት የሚገኙ ሲሆን በዚህ የሶስት ዓመታት የአፈጻጸም ትንተና ቁልፍ የሆኑ አመልካቾችን ብቻ መሠረት ያደረገ ትንተና እንደሚከተለው ቀርቧል።

### ደህንነቱና ጥራቱ ተረጋግጦ ለውጭ ገበያ የተላከ የእንስሳት ምርትና የቁም እንስሳት

### የኤክስፖርት ስጋና ተረፈ ስጋ ኢንስፔክሽን እና ሰርቲፊኬሽን

ከኢትዮጵያ ወደ ተለያዩ የውጭ አገራት የሚላክ ሥጋና ተረፈ ስጋ ምርት አመራረት፣አያያዝ እና አጓጓዝን በቅርብ በመከታተል እና የኢንስፔክሽን አገልግሎት በመስጠት የሚላከው ሥጋና ተረፈ ሥጋ ጤነኛ፣ ደህንነቱና ጥራቱ የተጠበቀ የአገራችንን እና የተቀባይ አገሮችን መስፈርቶች ያሟላ ስለመሆኑ የጤና ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በመስጠት የአገሪቱን የሥጋና ተረፈ ሥጋ ምርት ኤክስፖርት እንዲደረግ ማድረግ ነው።

በአጠቃላይ በዚህ ሶስት አመት ውስጥ ለ6,895,487 እንስሳት የቅድመ እርድ ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ በ5,918,070 የእርድ እንስሳት ላይ የቅድመ እርድ ምርመራ ተካሂዷል። ይህም የዕቅዱን 85.83% ሲሆን ከተመረመሩት ውስጥ በቁጥር 546,333 እንስሳት በምርመራ ሂደት የሚፈለገውን ደረጃ እና ጥራት አሟልተው ባለመገኘታቸው ለእርድ ሳይቀርቡ ውድቅ ተደርገዋል። እንዲሁም ወደ ውጭ ገበያ ለመላክ ከቀረበው የ6,797,070 የታረዱ እንስሳት ስጋ እና ተረፈ ስጋ ውስጥ 5,490,432.00 (80.1%) ለመመርመር የተቻለ ሲሆን እና ተረፈ ስጋ 279,400 ከደረጃ እና ከሚፈለገው ጥራት በታች በመሆናቸው ኤክስፖርት ሳይደረጉ ቀርተዋል። ለተላከው ስጋ እና ተረፈ ስጋም 24,200 የምርት ጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለመስጠት ታቅዶ ለ23,527.00 (97.22%) ለመስጠት ተችሏል።

### የኳራንቲን አገልግሎት ተሰጥቶት ወደ ውጭ የተላከ የቁም እንስሳት

**ባለፉት ስስት ዓመታት በቁጥር** 1,202,000 የቁም እንስሳት ኳረንቲን ስርዓት አልፈውና ቁጥጥር ተደርጎባቸው ወደ ውጭ እንዲላኩ ታቅዶ በ435,115 የቁም እንስሳት ላይ ለማከናወን የተቻለ ሲሆን ይህም የዕቅዱን 36.2% ነው። ክንውኑ በንጽጽር በ2012 ከነበረው የ406,000 ክንውን በ2015 18,815 (95.5%)

ዜና ሀ/ወልድ
ስለ የእንስሳት ሪጉላቶሪ ጉዳዮች ሥራ አስፈጻሚ

ዝቅ ብሏል። ለዚህ እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው የሰላም መታጣት የምንዛሪ እንደ ልብ አለመገኘትና ይህንን ተከትሎም የህገ ወጥ ግብይት መስፋት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

**በኳራንቲን የቁጥጥር ስርአት ውስጥ አልፎ የቨተርነሪ ሳኒተሪ ሰርተፍኬት የተሰጠው ማርና ሰም**

**ባለፉት ሶስት ዓመታት በቁጥር** ለ442 ቶን የማር ምርት በኳራንቲን የቁጥጥር ስርአት ውስጥ አልፎና የቨተርነሪ ሳኒተሪ ሰተፍኬት ተሰጥቶት እንዲያልፍ ታቅዶ ቁጥጥር ተደርጎባቸው ወደ ውጭ እንዲላኩ ታቅዶ ለ481 ቶን ማር ለማከናወን የተቻለ ሲሆን ይህም የዕቅዱን108.8% ነው። ክንውኑ በንጽጽር በ2012 ከነበረው የ147 ቶን ክንውን በ2015 179 ቶን ማድረስ ስለተቻለ (21.7%) ጭማሪ አሳይቷል። በተመሳሳይ **ባለፉት ሶስት ዓመታት በቁጥር** ለ439 ቶን ሰም ምርት በኳራንቲን የቁጥጥር ስርአት ውስጥ አልፎና የቨተርነሪ ሳኒተሪ ሰተፍኬት ተሰጥቶት እንዲያልፍ ታቅዶ ለ662 ቶን ሰም ለማከናወን የተቻለ ሲሆን ይህም የዕቅዱን 150.8% ነው። ክንውኑ በንጽጽር በ2012 ከነበረው የ159 ቶን ክንውን በ2015 357 ቶን የሰም ምርት ማድረስ ስለተቻለ (124.8%) ጭማሪ አሳይቷል።

በላቦራቶሪ ምርመራ ጥራትና ደህንነታቸው የተረጋገጠ የእንስሳት ምርት ናሙናዎች (ስጋ ወተት ማር) **ባለፉት ሶስት ዓመታት በቁጥር** ለ1,740 የእንስሳት ምርት ናሙናዎች የላቦራቶሪ የጥራትና ደህንነት ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ በ2,147 ናሙናዎች ላይ ማከናወን የተቻለ ሲሆን ይህም የዕቅዱን 123.4% ሲሆን ክንውኑ በንጽጽር በ2012 ከነበረው የ256 ናሙና ወደ በ2015 ወደ 570 ናሙናዎች ለማሳደግ ስለተቻለ ክንውኑ የ (122.65%) ጭማሪ አሳይቷል።

**ጥራቱ ደህንነቱና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድሃኒት**

**ባለፉት ሶስት ዓመታት በቁጥር** የ179 የእንስሳት መድኃኒትና የህክምና መሳሪያዎች ምዝገባ ሰነዶችን ለመገምገም ታቅዶ 201 የምዝገባ ሰነዶችን መገምገም ተችሏል። ይህም የዕቅዱ 100+% ሲሆን ክንውኑ በንጽጽር በ2012 ከነበረው የ185 ሰነዶች ብልጫ ያለው ነው። 407 የእንስሳት ክትባት ምዝገባ ሰነዶችን ገምግሞ ለመመዝገብ ታቅዶ 627 የእንስሳት ክትባት ምዝገባ ሰነዶችን ለመገምገም ተችሏል። አፈጻጸሙ 100+% ሲሆን በንጽጽር በ2012 ከነበረው የ329 ሰነዶች በ2015 ወደ 7 የግምገማ ሰነዶች ዝቅ በማለቱ የእንስሳት ክትባት ሰነዶች ግምገማ አፈጻጸም እየቀነሰ መምጣቱን ያሳያል። ለ912 የእንስሳት መድኃኒት ተቋማት የብቃት ማረጋጋጫ ለመስጠት ወይም ለማደስ ታቅዶ 1,364 ማከናወን በመቻሉ ከዕቅዱ 100+% አፈጻጸም አሳይቷል። ክንውኑ በንጽጽር በ2012 ከነበረው የ231 ክንውን በ2015 331 ማድረስ በመቻሉ ክንውኑ 43.3% ጭማሪ አሳይቷል።

የእንስሳት መድሃኒት የቅድመ ማስገቢያ ፈቃድ በተመለከተ 919 ታቅዶ 1,222 ማከናወን ተችሏል። አፈጻጸሙ 100+% ሲሆን ክንውኑ በንጽጽር በ2012 ከነበረው 237 በ2015 500 ማድረስ በመቻሉ ክንውኑ 100+% ጭማሪ አሳይቷል። በእንስሳት መድሃኒት ተቋማት ላይ የተደረገ የኢንስፔክሽን ስራዎችን በተመለከተ በ591 ተቋማት ላይ ለማድረግ ታቅዶ በ688 ተቋማት ላይ ኢንስፔክሽን ማድረግ በመቻሉ የዕቅዱን 100+% መፈጸም ተችሏል።

426 የእንስሳት መድሃኒት ናሙናዎችን ለቅድመ ምዝገባ፣ ከኮንሳይንመንት እና ከድህረ ገበያ ለምርመራ ለመላክ ታቅዶ 370 ማከናወን ተችሏል። ይህም የዕቅዱን 77.46% ሲሆን በ2012 ከነበረው በ2015 150 ጭማሪ አሳይቷል። 284 የእንስሳት ናሙናዎች በላቦራቶሪ ምርመራ ጥራትና ደህንታቸው የማረጋገጥ ስራ ለማከናወን ታቅዶ 754 የእንስሳት መድሃኒት ናሙናዎች መመርመር ተችሏል። ይህም የዕቅዱን 100+% አፈጻጸም አለው።

### ጥራቱ ደህንነቱና የተረጋገጠ የእንስሳት መኖ

ለ755 የእንስሳት መኖ ንግድ ተቋማትና ባለሙያዎች የብቃት ማረጋገጫ መስጠትና ለማደስ ታቅዶ ለ708 የእንስሳት መኖ ንግድ ተቋማትና ባለሙያዎች የብቃት ማረጋገጫ መስጠትና ለማደስ ተችሏል። አፈጻጸሙ 93.7% ነው፡ ለ5,654 ቶን የመኖና መኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮች የግዥና ማስገቢያ ፈቃድ በአንድ መስኮት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ10,325 ቶን የመኖና መኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮች የግዥና ማስገቢያ ፈቃድ በአንድ መስኮት አገልግሎት ለመስጠት ተችሏል። አፈጻጸሙ 100+% ነው። በ741 ናሙናዎች ላይ የመኖ የላቦራቶሪ ጥራትና ደህንነት ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ 1,633 ናሙናዎች ላይ ለማከናወን በመቻሉ የዕቅዱን 100+% ለመፈጸም ተችሏል።

## 2.6. የግብርና ትራንስፎርሜሽን

### የግብርና ሴክተር ላይ ያሉ ሥርዓታዊ ተግዳሮቶች እና የፖሊሲ ክፍተቶችን መለየትና የመፍትሄ ሀሳቦችን መጠቆም

አብዛኛው የግ.ት.ኢ. ጥናቶች የሚከናወኑት በትንተና (Analytics) ቡድን ስር ሲሆን፤ ባለፉት ሶስት አመታት 105 ጥናቶች ተካሂደዋል። ከነዚህም ጥናቶች 38% የሚሆኑት የፕሮጀክት ዲዛይን ጥናቶች ሲሆኑ 34% የሚሆኑት ደግሞ የግብርና ዘርፍ ስትራቴጂዎች ላይ ያተኮሩ ናቸው። በተጨማሪም 19% የሚሆኑት ጥናቶች የግ.ት.ኢ. ውስጣዊ አሰራር ግምገማና ማሻሻል ላይ ያተኮሩ ሲሆኑ የተቀሩት 9% የሚሆኑት ጥናቶች የትምህርታዊ (የተሞክሮ) ጥናቶች ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ በግ.ት.ኢ. ድጋፍ ከዘር ምርት መብቶችና ቁጥጥር ጋር የተያያዙ 4 የፖሊሲ ሰነዶች ተዘጋጅተዋል።

### ሥርዓታዊ ችግሮችን የሚፈቱ አዳዲስ ፕሮጀክቶችን መንደፍ፤ ስርቶ ማሳየትና ማስረከብ

ግ.ት.ኢ. ባለፉት ሶስት አመታት የተለያዩ የአሰራር ተግዳሮቶችን ለመፍታት ያለሙ አጠቃላይ 23 ፕሮጀክቶችን የተገበረ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ሶስቱ ፕሮጀክቶች በ2014 ዓ.ም የተጀመሩ አዳዲስ ፕሮጀክቶች ናቸው። ስምንት ፕሮጀክቶች ደግሞ በሙከራ ጊዜቸው ጥሩ ውጤት አሳይተው ለሴክተር ተቋማት የተላለፉ ወይም በተለያየ ምክንያት የተዘጉ ፕሮጀክቶች ናቸው።

### በፈጠራ የታገዙ አዳዲስ ስርቶ ማሳያ ፕሮጀክቶች ብዛት

**የታዳሽ ኃይል መስኖና ዘርፈ-ብዙ ልማት (DREAM Irrigation) ፕሮጀክት**

በአራት ክልሎች (ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደ/ብ/ብ/ሕ እና ሲዳማ) ለ3 ዓመታት ከኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት በራቁ 9 የሙከራ መንደሮች በሃይል ዘርፍ የተሰማሩ ኢንቨስተሮችን በማሳተፍ በአካባቢዉ ማህበረሰብ

በግብርና ኮሜርሻላዜሽን ክላስተር ፕሮግራም የሚደገፉ 5 ሆርቲካልቸር ተክሎች (አቮካዶ፣ሙዝ፣ማንጎ፣ ቲማቲምና ሽንኩርት) የግብርና ምርትና ምርታማነት እንዲያሳድጉ የሚያደርግ የፀሃይ ሃይል (ሶላር ኢኔርጂ) የሚጠቀም የሚኒ-ግሪድ መስኖና ኤሌክትሪክ ሃይል ልማት ስርቆ ማሳያ ፕሮጀክት እየተተገበረ ይገኛል።

## የኢትዮጵያ የዘር ስርዓት ተቋማዊ ድጋፍ ፕሮጀክት (ISSSE)

ፕሮጀክቱ አርሶ አደሩ ጥራቱ የተመሰከረለት ዘር በተመጣጣኝ ዋጋና በተፈለገ ጊዜ ተደራሽ የሚሆንበትን የዘመነ የዘር ስርዓት እንዲፈጠር ከሚረዱ ሁኔታዎች የመጀመሪያው የመነሻ ዘር በዓይነት፣ በጥራትና በተፈለገው መጠን በማምረት፣ ባልተማከለ ገበያ መር ግብይት ስርዓት ተከትሎ ለተጠቃሚው እንዲደርሰው ማገዝ ላይ ያተኮረ ነው።

እንዲሁም የሀገሪቱ የዘር ጥራት ቁጥጥር ተቋማትን አቅም በማሳደግ ለሁሉም ዘር አምራቾች የሚያረካ አገልግሎት እንዲሰጡ ማብቃት ነው። በመጨረሻም ለሁሉም የዘር አምራቾች እና ተዋናዮች አመቺ ሁኔታዎችን እንዲኖር እና የዘመነ የዘር ስርዓት እንዲፈጠር የሚያስችል የፖሊሲና ህግ ስርዓት እንዲዘረጋ ማገዝ ነው።

## የአፈር ጤንነት እና ለምነት ማሻሻያ ፕሮጀክት

ለግብርና ምርታማነት አስፈላጊ የሆነውን የአፈር ለምነትን በዘላቂነት ማስጠበቅን አላማ ያደረገ የፕሮጀክት ንድፍና የትግበራ እቅድ ተዘጋጅቷል። ከነዚህም ስራዎች መካከል የኖራ ስርጭት አሰራር ሂደትን መቅረፅ ይገኝበታል። ምንም እንኳን ፕሮጀክቱ ለግብርና ምርታማነት ወሳኝ ቢሆንም፤ በወቅቱ ባጋጠመው የበጀት እጥረት ምክንያት የፕሮጀክቱ ትግበራ እንዲቆም ተገዷል።

## በሙከራ ጊዜአቸው ጥሩ ውጤት አሳይተው ለሴክተር ተቋማት የተላለፉ/ያለቁ ፕሮጀክቶች

## የኢትዮጵያ የአፈር ሃብት መረጃ ስርዓት ፕሮጀክት

በኢትዮጵያ የአፈር ሀብት መረጃ ስርአት ፕሮጀክት ስር የወጡ የማዳበሪያ አይነት ምክረ ሃሳቦችን በ300 ወረዳዎች ላይ የሙከራ ሥራ ከኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩትና ከክልል ግብርና ምርምር ጋር ተሰርቷል። በኢትዮጵያ የአፈር ሀብት መረጃ ስርአት ፕሮጀክት ከሁሉም የሀገሪቱ ክፍል የተሰበሰቡና የንጥረ ነገር ትንተናቸዉ የተጠናቀቀ ናሙናዎችን ሙሉ በሙሉ ወደ የአፈር ቤተ-መዘክር ገብቷል።

## የግብርና ኢንቨስትመንት ካርታ ፕሮጀክት

በአማራ (51)፣ በኦሮሚያ (46) እና በደቡብ (47) የተመዘገቡ በድምሩ 144 የሚደርሱ የግብርና እንቨስትመት ፕሮጀክቶች መረጃ፤ እንዲሁም በፌደራል ደረጃ የተመዘገቡ 29 የግብርና እንቨስትመት ፕሮጀክቶች መረጃ፤ በጠቅላላው 173 የግብርና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች መረጃ ወደ የግብርና ኢንቨስትመንት የአካባቢ ልየታ መተግበሪያ ስርአት ተካቷል። የግብርና ኢንቨስትመንት ካርታ ስርዓትን ወደ ግብርና ሚኒስቴር የማዘዋወር ስራ ከተጠናቀቀ በኋላ ሲስተሙን ማስተዳደር የሚያስችል አስፈላጊው የቴክኒክ ድጋፍ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መስጠት ተችሏል።

ከከ ዜና ሀ/ወልድ
የስትራተጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

### የቀጥታ ዘር ግብይት ፕሮጀክት

የቀጥታ ዘር ግብይት ክትትልና ግምገማ ተከናውኖ ፕሮጀክቱ በጥሩ የአፈጻጸም ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ስለታወቀ አስፈላጊዉ የሙያ ድጋፍ በመስጠት ለክልል ግብርና ቢሮዎች እና የግብዓት ቁጥጥር ባለስልጣናት የቀጥታ ዘር ግብይት ተግባራት እና የሚያስፈልገዉን በጀት በእቅዳቸዉ ዉስጥ እንዲያካትቱ ተደርጓል።

### የዕጽዋት አዳቃይ መብት አዋጅ

የዕጽዋት አዳቃይ መብት አዋጅን ለማስፈጸም የሚረዳው ረቂቅ የሚኒስቴር መስሪያ ቤት መመሪያ ሰነድ፤ የዕጽዋት አዳቃይ መብት መመሪያ 769/2013 በሚል ፀድቋል።

### የንብ ማነብ የእሴት ሰንሰለት ልማት ፕሮጀክት

የ18 የንብ ጋጣ ግንባታዎች (4 በኦሮሚያ፤ 3 በአማራ፣ 4 በደቡብ ብ/ብ/ሕ እና 7 በትግራይ ክልሎች) ተጠናቋል። በማርና ሰም ግብይት ማሳለጥ ረገድ ለፕሮጀክት ወረዳዎች መድረክ በማዘጋጀትና ገዥና ሻጭን በማገናኘት 4,164 ኩንታል ማር በብር 33.5 ሚ/ን እንዲገበያዩ ተደርጓል።

### የአርሶ አደሮች ምርት ክላስተር ዲጂታይዜሽን ቅድመ ፓይለት ፕሮጀክት/ክሮፒን

በ2013/14 የምርት ዘመን በአርሶ አደሮች የምርት ክላስተር ዲጂታይዝ የማድረግ እና መረጃ የመሰብሰብ ስራ ከ6,935 በላይ ለሆኑ በአርሶ አደሮች ምርት ክላስተር ስር ያሉ የኩታ ገጠም መረጃዎች ተሰብስበዋል። ፕሮጀክቱን በስፋት ለመተግበር ከፍተኛ የሆነ መዋዕለ-ነዋይ የሚጠይቅ ሆኖ ስለተገኘ፤ እንዲሁም በወቅቱ ባጋጠመው የበጀት ችግር የፕሮጀክቱ ትግበራ እንዲቆም ተገዷል።

### የንግድ ስልጠናዎች በገበሬ ማሰልጠኛ ማዕከላት ፕሮጀክት

አርሶ አደሮች ግብርናን እንደ አንድ የአዋጪነት ስራ እንዲቀጥሩና እንዲተገብሩ የሚያስችል የግብርና ቢዝነስ ስልጠናዎች በገበሬ ማሰልጠኛ ማዕከላት እንዲሰጡ ተደርጓል፤ አስፈላጊው የቴክኒክ እገዛና ክትትል ለአራቱም ክልሎች ተደርጓል።

## ትግበራ ላይ የቆዩ ነባር ፕሮጀክቶች

### የአርሶ አደር ምርት ክላስተር - በሰብል ምርት

ባጠቃላይ ከ2.2 ሚ/ን በላይ አርሶ አደሮችን እና ከ80 በላይ ክላስተሮችን ለመመዝግብ ተችሏል። ከ1.6 ሚ/ን ሄክታር በላይ መሬት የግብርና ኩታ-ገጠም እርሻ በምርት ተሸፍኗል። አርሶ አደሮች የተሻለ የተሻሻለ ዘር፣ ማዳበሪያ እና ኬሚካሎች፣ የብድር፣ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት፣ የገበያ ትስስር፣ የምክር አገልግሎት እና የተሻሻለ የድህረ ምርት አገልግሎት አቅርቦት እና አጠቃቀም እንዲሻሻል ድጋፍ ተደርጓል።

### የአርሶ አደር ምርት ክላስተር - በአትክልትና ፍራፍሬ ምርት

ባጠቃላይ ከ66 ሺህ በላይ አርሶ አደሮችን እና ከ1 ሺህ በላይ ክላስተሮችን ለመመዝግብ ተችሏል። ከ11.5 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት የግብርና ኩታ-ገጠም እርሻ በምርት ተሸፍኗል። አርሶ አደሮች የተሻሻለ ዘር፣ ማዳበሪያ እና ኬሚካሎች፣ የብድር፣ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት፣ የገበያ ትስስር፣ የምክር አገልግሎት እና የተሻሻለ የድህረ ምርት አገልግሎት አቅርቦት እና አጠቃቀም እንዲሻሻል ድጋፍ ተደርጓል።

ዜና ሀብተወልድ
የስትራቴጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

**የግብርና ግብዓትና አገልግሎት ፕሮጀክት**

በባለፉት ሶስት አመታት 242 የግብርና ግብዓትና አገልግሎት ማዕከላት ተቋቁሟል። 108.4 ቢሊየን ብር የሚያወጣ የግብዐት ግብይት ተካሂዷል። በዚህም 5,451,877 አርሶ አደሮች ተጠቃሚ ሆነዋል። በተጨማሪም ለ2,554 ሰዎች የስራ ዕድል ተፈጥሯል።

**የኅብረት ስራ ማህበራት አቀፍ ዘር ብዜት ፕሮጀክት**

ባጠቃላይ ከ407 ሺህ በላይ ኩንታል የተሻሻለ ዘርን በማምረት እና በማሰራጨት ከ940 ሺህ በላይ የሚሆኑ አርሶ አደር አባላትን ተጠቃሚ በማድረግ የሰብል ምርትና ምርታማነት ለመጨመር ተችሏል። በተጨማሪም 1,283 ለሚሆኑ ሰዎች ቋሚና ግዜያዊ የሥራ ዕድል ተፈጥሯል።

**የተቀናጀና ጥልቅ ያልሆነ የከርሰ ምድር ውኃ መስኖ ልማት ፕሮጀክት**

በአነስተኛ ወጪ በፀሐይ ኃይል የሚሰሩ ፓምፖችና የጠብታ መስኖ ቴክኖሎጂ ከ110 በላይ ለሆኑ አርሶ አደሮች ተደራሽ ለማድረግ ተችሏል።

**አግሪ ሃብ**

ባለፉት ሶስት ዓመታት ለአንድ መስኮት ግብርና ግብአት አገልግሎት፣ ለሜካናይዜሽን ማእከል፣ ለማህበረሰብ አቀፍ ዘር ብዜት፣ ለቀጥታ ዘር ግብይት፣ ለአትክልትና ፍራፍሬ ዘር አምራቾች፣ ሌሎችም ጥቃቅን እና አነስተኛ ማህበራት የንግድ ክህሎት ስልጠና በተለያዩ ጊዜያት ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል። ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፐራይዞች (4 Accelerator and 8 Capability Booster) ትርፋማ እንዲሆኑ እና ንግዳቸውን ለማስቀጠል የምክር አገልግሎት ተሰጥቷል። የብድር ፋይናንስ ትስስር ለማቅረብ ከተለያዩ የፋይናንስ ተቋማት ጋር በመስራት ለኢንተርፕረራይዞች ድጋፍ ተደርጓል።

**የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ማዕከላት የሙከራ ፕሮጀክት**

አዳዲስ የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎችን ለአርሶ አደሮች የማስተዋወቅ ተግባራት ሲከናወኑ ቆይቷል። በተጨማሪም ውጤታማ ለሆኑ የአርሶአደር ምርት ክላስተሮች የተለያዩ መዝሪያዎችን፣ ማጨጃዎችን፣ የመርጫ መሳሪያዎችንና ሌሎች ቴክኖሎጂዎችን በሽልማት መልክ በመስጠት በሜካናይዜሽን አጠቃቀም ለውጥ ለማምጣት ጥረት እየተደረገ ይገኛል። ትራክተርና ኮምባይነር ኦፕሬተሮችን እና መካኒክ ቴክኒሻያኖችን በማሰልጠን ወደስራ እንዲገቡ ተደርጓል። ለማዕከላት ሰራተኞችና አመራሮች ባለፉት 3 ዓመታት በፋይናንስና በስራ አመራር የአቅም ግምባታ ስልጠናዎች ለመስጠት ተችሏል።

**የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ፕሮጀክት**

206 የእንስሳትና የአሳ ሀብት አምራቾች የመስክ ትምህርት ቤቶች ብዛት ተቋቁመዋል። ለ618 አስተባባሪዎችና ለ40 አሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል።

**የንግድ እና ኢንቨስትመንት ማስፋፍያ ፕሮጀክት**

የምግብና መጠጥ ምርቶች ማቀነባበሪያና የአባሪ ኢንዱስትሪ ስትራቴጂን ተግባራዊ በማድረግ ለአርሶ/አደሮች ብር 50 ሚ/ን ዋጋ ያለው የገበያ ትስስር ተፈጥሯል። በጠቅላላው 1 ቢሊዮን ብር የሚገመቱ የሀገር ወስጥ እና የዉጪ የግብርና ምርት ማቀነባበርያ ኢንቨስትመንት ውጥኖችን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንዲሆኑ ታግዟል።

ከኢ ሮዛ ሀ/ወልድ
የስትራቴጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

### የ8028 የድምፅ ቅብብሎሽ ምላሽ ፕሮጀክት

በግብርና ሰብሎች ለአርሶ አደሮች/ለልማት ጣቢያ ሰራተኞች ዓመቱን ሙሉ የኤክስቴንሽን ምክር አገልግሎት እንዲሁም የግብርና ምርጥ ተሞክሮዎችና የተሻሻሉ ተሞክሮዎችን (ማለትም የኤክስቴንሽን ፓኬጆችን ስልጠና፣ ለሚቀርቡ ጥቄዎች ምላሽ መስጠት፣ የቅድመ ማስጠንቀቂያ መልእክት ማሰራጨት እና በቴሌፎን የዳሰሳ ጥናቶች) በተንቀሳቃሽ ስልካቸው መረጃን በቀጥታ ያደርሳል:: በባለፉት ሶስት አመታት ከ42 ሚ/ን በላይ ጥሪዎችን በማስተናገድ የ9 ሚ/ን አርሶአደር ተመዝጋቢዎች የመረጃ ፍላጎት ለሟሟላት ጥረት ተደርጓል::

### ሀገር አቀፍ የገበያ መረጃ ስርዓት ፕሮጀክት

በሀገር አቀፍ ደረጃ በተመረጡ 5 የግብርና ምርቶች ላይ ወቅታዊ እና ትክክለኛ የገበያ መረጃ ለሁሉም ተጠቃሚዎች ያደርሳል:: በባለፉት ሶስት አመታት ከ42 የገበያ ቦታዎች በተለያዩ የተመረጡ ምርቶች 202,110 በላይ የተረጋገጡ ሳምንታዊ የገበያ መረጃዎችን በማሰበሰብና ወደ የገበያ ስርአቱ በማስገባት ከ1.7 ሚሊየን በላይ አዲስ የተመዘገቡ ተጠቃሚዎች መረጃው እንዲደርሳቸው ማድረግ ተችሏል::

### የግብርና ግብዓት የኩፖን ሽያጭ ሥርዓት ፕሮጀክት

ከ798 ሺህ አርሶአደሮች በላይ የብድር አቅርቦት ማግኘት ችለዋል:: 6,700 በላይ ሰራተኞች ቋሚ የስራ ዕድል ተፈጥሯል::

### የገ/ቁ/ብ/ኀ/ሥ/ማ የዓቅም ግንባታ ፕሮጀክት

ባለፉት ሶስት ዓመታት ለህብረት ስራ ማህበራት የአቅም ክፍተት ልየታና ምዘና ስራ እና ለክልል ማህበራት ኤጀንሲ ባለሙያዎች፣ ለዞንና ለወረዳ ባለሙያዎች እና ለገጠር ገንዘብ ቁጠባና ብድር ዩኒየን ሰራተኞች በተለዩት ክፍተቶች ዙሪያ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ተሰጥቷል:: ለገጠር ገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበር ቦርድ አባላት በተሻሻለ አመራር እና የፋይናንስ አስተዳደር ላይ ስልጠና ተሰጥቷል::

### የማስፈፀም (የትግበራ) ድጋፍ

በግብርና ሚኒስቴር በሌሎች የሴክተሩ ተቋማት 41 የሚሆኑ የዴሊቨሪ ዩኒት ከፍተኛ ባለሙያዎች ተቀጥረው ለባለፉት ሶስት አመታት የአፈፃፀም ድጋፍ የዕቅድ፣ የቴክኒክ ድጋፍ፣ የአቅም ግንባታ፣ የክትትልና ሪፖርት ድጋፍ ስራዎችን ሲሰሩ ቆይተዋል::

### ትስስርና ቅንጅት

የኢትዮጵያ የምግብ ስርዓት ፕሮግራም እና የዲጂታል ግብርና የኤክስቴንሽን እና ምክር አገልግሎት ፕሮግራም አፈፃፀም ውጤታማ እንዲሆን የትስስር ስራዎችን እየሰራ ይገኛል:: ይህም በዋናነት የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት በአስፈፃሚ አካላት መካከል ቅንጅት እንዲኖር ተደርጓል:: የፌደራል ስትሪንግ ኮሚቴ እና የክልል ትራንስፎርሜሽን ካውንስል መድረኮች እየተካሄዱ ይገኛሉ::

## 2.7. ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች

### 2.7.1. ምግብ ዋስትና

በልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራም የታቀፉ ተጠቃሚዎች ቁጥር: - የልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራም ከ2013-2015 በየበጀት ዓመቱ ለ7.9 ሚ/ን የሚሆኑ በገጠር የሚኖሩና በፅኑ ድህነት ውስጥ የሚገኙ እንዲሁም ለተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን በፕሮግራሙ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ የነበረ ሲሆን በ2013 በጀት አመት የዕቅዱን 131 በመቶ አሳክቷል። በውቅቱ በአገራችን ተከስቶ በነበረው የኮቪድ-19 ወረርሽን ምክንያት 2.5 ሚ/ን ተጨማሪ ተጠቃሚዎች ድጋፍ መደረጉ ከእቅዱ የበጀት ዓመቱን አፈጻጸም ከፍ ድርጎታል። በ2014 በጀት ዓመት ደግሞ ከመደበኛ የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች 7.9 ሚ/ን በተጨማሪ በሀገራችን በተለይም በኦሮሚያ፣ ሶማሌ፣ ደቡብና ደቡብ ምዕራብ በ111 ወረዳዎች ለሚገኙ 2.74 ሚ/ን ተጠቃሚዎች የተከሰተውን ድርቅ መቋቋም እንዲቻል ለሶስት ወራት ድጋፍ እንዲያገኙ በማድረግ በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ 10.6 ሚ/ን ተጠቃሚዎችን መድረስ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙን 134% ከፍ አድርጎታል። በ2015 በጀት ዓመትም በተመሳሳይ 7.9 ሚ/ን ተጠቃሚዎችን በፕሮግራሙ ለመደገፍ በእቅድ የተያዘ ሲሆን ሪፖርቱ እስከተጠናቀረበት (መጋቢት 2015) ድረስ በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ማለትም አማራ፣ኦሮሚያ፣ደቡብ፣ ሲዳማ እንዲሁም ደቡብ ምእራብ ኢትዮጲያ የተከሰተውን ድርቅ መሰረት በማድረግ 3.9 ሚ/ን ተጨማሪ ተጠቃሚዎች የአደጋ ምላሽ ድጋፍ በመደረጉ በድምሩ 10.9 ሚ/ን ጠቃሚዎችን መደገፍ ተችሏል። ይህም አፈጻጸሙን 138% አድርሶታል። በአጠቃላይ ከ2013 እስከ 2015 ግማሽ ዓመት አፈፃፀም ስንገመግም የተጠቃሚዎች ቁጥር ጨምሮ ታይቷል። ምክንያቱም ከ2013ቱ የኮቪድ 19 ወረርሽ በተጨማሪ በተከታታይ ሁለት ዓመታት (2014-2015 በጀት ዓመት) በተከሰተው ድርቅ ምክንያት ፕሮግራሙ በሚተገበርባቸው ወረዳዎች ተጨማሪ ድጋፍ በማስፈለጉ ሲሆን በድምሩ 6.6 በአደጋ ምላሽ ድጋፍ ተደረሽ ሆነዋል።

ለፕሮግራም ማስፈፀሚያ ለክልሎች የተላለፈ ገንዘብ: - የገጠር ልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራም ከሚይዘው ዓመታዊ በጀት ውስጥ ከሰማንያ በመቶ በላይ የሚሆነው በጀት በተለያዩ የበጀት አርዕስቶች ስር ፕሮግራሙ በሚተገበርባቸው ክልሎች የሚላክ ሲሆን በአስር ዓመት እቅድ መሰረት የመጀመሪያ ሶስት ዓመታት አፈፃፀም ማለትም ከ2013 በጀት ዓመት እስከ 2015 በአጠቃላይ በብር 38.25 ቢ/ን በጀት ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን በዝርዝር ሲታይም በ2013 በጀት ዓመተ 14.38 ቢ/ን፣ በ2014 በጀት አመት የድርቅ ምላሽ በጀትን ጨምሮ ብር 16.54 ቢ/ን እንዲሁም በ2015 በጀት ዓመት የስድስት ወር አፈፃፀም 5.41 ቢ/ን ወደ ክልል ተላልፎ አፈፃፀሙም ክትትል ተደርጎበታል።

ባለፉት ሶስት የትግበራ ዓመታት ለፕሮግራሙ ጥቅም ለይ የዋለው በጀት 57.89 ቢ/ን ሲሆን በፕሮግራሙ ዲዛይን ከተቀመጠው ዕቅድ ጋር ሲነጻጸር አፈፃፀሙ በ25 በመቶ አንሶ ታይቷል። ለአብነት ያህልም ካሳለፋናቸው ዓመታት ውስጥ ሙሉ የበጀት ዓመት ትግበራ ያለውን የ2014 በጀት ዓመት ስናይ ለበጀት ዓመቱ በፕሮግራም ዲዛይን መሰረት ብር 24.7 ቢ/ን የታቀደ ቢሆንም ተገኝቶ ጥቅም ላይ የዋለው በጀት ግን 18.46 ቢ/ን (75 በመቶ) ብቻ ነው። ፕሮግራሙ ላጋጠመዉ የበጀት እጥረት የሰሜኑ የሃገራችን ክፍል የነበረው ጦርነት በዋናነት የሚጠቀስ ሲሆን በዚሁ ምክንያት ለጋሽ የፕሮግራሙ ለጋሽ አካላት

በፕሮግራም ዲዛይን ላይ ቃል በገቡት መሰረት ገንዘቡን ገቢ አለማድረግ እንዲሁም ማዘግየት ችግር በሰፊው ተስተውሏል፡፡ ይህ የበጀት ክፍተት የፕሮግራሙን ልማታዊ ባህሪ ሚያጠናክሩ ንዑስ ፕሮግራሞችን ማለትም የማህበረሰብ ስራ እና የቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ ስራዎችን በታቀደላቸው ልክ መስራት ባለማስቻሉ በፕሮግራሙ አፈፃፀም ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳደረና የፕሮግራሙን ዓላማ ከማሳካት አንጻር (በገጠር የድህነት መጠንን መቀነስ) ከፍተኛ ተግዳሮት እየሆነ ይገኛል፡፡

### 2.7.2. ምግብና ስርዓተ ምግብ

የምግብና ሥርዓተ ምግብ ጽ/ቤት ባለፉት ሶስት ዓመታት የተሰባጠረ አመጋገብን ማሻሻል እንደ ዋና ውጤት በማስቀመጥ ይህንን ለማሳካት ደህንነቱ የተጠበቀ እና በምግብ ንጥረ ነገር ይዘቱ የበለፀገ ምርትን ለማሳደግ፣ የአርሶ/አርብቶ አደሩን ገቢ ለማሳደግ እና የሴቶች ውሳኔ ሰጭነት ለማሻሻል የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ የምግብና ሥርዓተ ምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ከፍተኛ ድርሻ ያለውን መዋቅራዊ አደረጃጀት እንዲፈጠር በማድረግ እና በከፍተኛ አመራሩ ትኩረት እንዲያገኝ በማድረግ ረገድ በፌደራል እና በክልሎች በርካታ የአድቮኬሲ እና ሎቢ ስራዎች የተሰሩ ሲሆን በሦስት ዓመቱ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር ተመላክተዋል፡፡

#### የምግብና ሥርዓተ ምግብ መዋቅራዊ አደረጃጀት

በፌደራል ደረጃ የተቋቋመውን የምግብና ሥርዓተ ምግብ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ደረጃውን በማሻሻል የባለሙያዎችን ስብጥር እና ቁጥር ከፍ በማድረግ በጽ/ቤት ደረጃ እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡ ጽ/ቤቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ ተደርጎ በሁለት ዴስክ የተደራጀ ሲሆን በሶስት ክልሎች ማለትም አፋር፣ ኦሮሚያ እና ሶማሊ የምግብና ሥርዓተ ምግብ አደረጃጀት በዳይሬክቶሬት ደረጃ እንዲዋቀር ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት በሶስቱ ክልሎች ራሱን የቻለ የምግብና ስርዓተ ምግብ መዋቅራዊ አደረጃጀት የተፈጠረ ሲሆን በሰው ሀይል የማሟላት ስራ ተሰርቷል፡፡ በአማራ ክልል መዋቅሩ የተፈቀደ ሲሆን በሰው ሀይል የማሟላት ስራ በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

#### የአቅም ግንባታ ሥልጠና

ከግብርና ሚኒስቴር ጀምሮ እስከታችኛው መዋቅር ድረስ ላሉ 730 ባለሙያዎች የሥ/ም/ተ ግብርናን በማስመልከት በተዘጋጀው የማሰልጠኛ ማኑዋል በመጠቀም ለ550 (91 ሴት) (75%) ሰልጣኞች ስልጠና በምግብ ንጥረ ነገር ይዘቱ የበለፀገ ምርት ድህረ ምርት አያያዝ፣ ምግብ ደህንነትና ጥራት፤ የምግብ አዘገጃጀት መመሪያ ላይ፤ በተዘጋጀው በምግብ ንጥረ ነገር ይዘታቸው የበለፀጉ ሰብሎች ፓኬጅ፤ በዲጂታል የግብርና መረጃ አያያዝ እና የሥርዓተ ምግብ መረጃ ዙሪያ ላይ፤ ለባለሙያዎች እና በማህበር ለተደራጁ ሴቶች እሴት መጨመር ላይ፤ መዋቅራዊ አደረጃጀትን ለመፍጠር እና የምግብና ሥርዓተ ምግብ ጉዳይ በአመራሩ ትኩረት እንዲያገኝ ለማድረግ እና ለምግብና ሥርዓተ ምግብ ማስፈጸሚያ በጀት ለማስመደብ የሚጠቅም የአድቮኬሲ እና ሎቢይንግ ለ786 የፌዴራል እና የክልል ተሳታፊዎች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ742 (68 ሴት) (94.4%) የስራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ አዲስ በተዘጋጀው የሥ/ም/ተ ግብርና ሞዴል መንደር በሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ሞዴል መንደር አመሰራረት ዙሪያ እና

በተለያየ ርዕሰ ጉዳይ ለ339 የወረዳ እና የቀበሌ ባለሙያዎችን እና የመንደሮች ነዋሪዎች ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ335 (167 ሴት) (99%) ስልጠና መስጠት ተችሏል። የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና የአሰልጣኞች ስልጠና እና ለሥርዓተ ምግብ ትግበራ ማዋል የሚያስችል የመሰረታዊ የንግድ ክህሎት ሥልጠና ለክፍሉ ባለሙያዎች፣ የሥ/ም/ተ/ግብርና ሞዴል መንደር በሚመሰረትባቸው ወረዳዎች ለ354 (126 ሴት) ሰልጣኞችን ማሰልጠን ተችሏል። ለ52 (16 ሴት) በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት እና ለግብርና ሚኒስቴር የስራ ኃላፊዎች መሰረታዊ የሥርዓተ ምግብ ጽንሰ ሐሳብ እና ምግብን መሰረት ያደረገ የአመጋገብ መመሪያ፣ የግብርናና የሥርዓተ ምግብ ትስስር፣ ድህረ ምርት እና የምግብ ደህንነት እንዲሁም የኢትዮጵያ የምግብ ሥርዓት ላይ የግንዛቤ ማሳደጊያ ስልጠና ተሰጥቷል።

### የዳሰሳ ጥናቶች

ዝቅተኛ የተሰባጠረ አመጋገብ (Minimum Dietary Diversity Score) ዳሰሳ ጥናት፣ የምግብና ሥርዓተ ምግብ የሰው ሀይል ፍላጎት ጥናት፣ የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ስትራቴጅ (2016-2020) አፈጻጸም ግምገማ፣ የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና የማበረታቻ ሥርዓት የዳሰሳ ጥናት፣ የምግብ ደህንነት መመሪያዎች እና የህግ ማዕቀፍ የዳሰሳ ጥናት እና በምግብ ንጥረ ነገር ይዘታቸው የበለፀጉ የግብርና ምርቶች ድህረ ምርት አያያዝ የዳሰሳ ጥናት ስራ ለማካሄድ ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት ተከናውኗል።

### የሰነድ ዝግጅት

### የስልጠና ማኑዋሎች

ለከፊል አርብቶ አደር እና አርብቶ አደር አካባቢ የሚሆን የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ማሰልጠኛ ማኑዋል የማዘጋጀት ስራ ተሰርቷል። እንዲሁም ለአርሶ አደሮች የሚሆን የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ማሰልጠኛ ማኑዋል ማዘጋጀት ተችሏል።

### ስትራቴጂዎች

የኢትዮጵያ የምግብና ሥርዓተ ምግብ ፖሊሲን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀው የኢትዮጵያ የምግብና ሥርዓተ ምግብ ስትራቴጂ፣ የተቀዳሚ የግብርና ምርቶች ደህንነትና ጥራት ስትራቴጂ፣ የተቀናጀ የድህረ ምርት አያያዝ ስትራቴጂ ለማዘጋጀት ታቅዶ ስትራቴጂዎቹን የማዘጋጀት ስራ ተሰርቷል፤ የኢትዮጵያ የምግብ ሥርዓተ ትራንስፎርሜሽን ፍኖተ ካርታ ተዘጋጅቷል። የተከለሰው ረቂቅ የግብርና ፖሊሲ ሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርናን ባካተተ መልኩ እንዲዘጋጅ ተደርጓል። የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ስትራቴጂ የመከለስ ስራም እየተከናወነ ይገኛል።

### ፓኬጅ ዝግጅት

በምግብ ንጥረ ነገር ይዘታቸው የበለፀጉ ሰብሎች (አሉማ፣ ኬንዋ፣ ካሚሊና እና የምግብ ሲናር) ፓኬጅ ከሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ጋር ተዘጋጅቷል።

## መመሪያዎች

ደረጃውን የጠበቀ የምግብ አዘገጃጀት፣ የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና የተግባቦት፣ የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ሞዴል መንደር የአመሰራረት እና የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ሰርቶ ማሳያ ማዕከል (Nutrition Demonstration Corner/NDC) መመሪያ ተዘጋጅቷል።

## የምግብ ሰርቶ ማሳያ

የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ሞዴል መንደር በሚመሰረትባቸው ሁለት መንደሮች እና ከጃይካ ጋር በመተባበር የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ማሳያ በተሞከረበት አርሶ አደር ላይ በድምሩ አራት የምግብ ሰርቶ ማሳያ ተካሄዷል። ከዚህ በተጨማሪ ባዮፎርቲፋይድ የሆኑ ሰብሎች ላይ ማለትም ብርቱካናማ ስኳር ድንች እና በብረትና በዚንክ የበለፀገ ቦሎቄ የምግብ አዘገጃጀት ሰርቶ ማሳያ ሁለት ጊዜ ተካሄዷል።

## የሥ/ም/ተ ግብርና ሞዴል መንደር መመስረት

የተቀናጀ የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ተግባራትን ለማከናወን እና ለሌሎች አካባቢዎች ለማስተማር የሚያስችል የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ሞዴል መንደር ለመፍጠር ታቅዶ ለማሳያ የሚሆኑ ሦስት መንደሮች (በአማራ፣ ኦሮሚያና አፋር ክልሎች) በመመስረት ላይ ናቸው።

## የምግብና ሥርዓተ ምግብ ማስፈጸሚያ ፕሮግራም/ፕሮጀክት መቅረጽ

የምግብና ሥርዓተ ምግብ ተግባራትን ለመፈጸም ፕሮግራሞችን/ፕሮጀክቶችን መቅረጽ ዕቅድ ተይዞ ከጃፓን መንግስት ጋር በመተባበር "የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ሞዴል መንደር ምስረታ" የሚል ፕሮጀክት ተቀርጾ ፕሮጀክቱ ወደ ተግባር እንዲገባ ተደርጓል።

## በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና መልእክቶችን ማስተላለፍ

የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ግንዛቤን ለማሳደግና የተሰባጠረ አመጋገብን ለማሻሻል ከተለያዩ ሚዲያዎች ጋር ሥርዓተ ምግብ ተኮር ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ እና መልእክቶችን ለማስተላለፍ ታቅዶ በሦስቱ ዓመት በድምሩ 14 መልእክቶችን በህዝብ ሚዲያዎች ማስተላለፍ ተችሏል።

## ምግብን መሰረት ያደረገ የአመጋገብ መመሪያን መተግበር

በሀገር አቀፍ የጸደቀውን ምግብን መሰረት ያደረገ የአመጋገብ መመሪያ (Food Based Dietary Guideline) በተመረጡ ወረዳዎች ከአለም የግብርናና ምግብ ድርጅት እና ከኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር ለመተግበር የሦስት ወረዳዎች ልየታ፣ የትግበራ ዕቅድ ማቀድ እና የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት ተከናውኗል።

## በሰቆጣ ስምምነት ወረዳዎች የተከናወኑ ተግባራት

በሰቆጣ ስምምነት ወረዳዎች በከፍተኛ ሁኔታ የሚታየውን የስርዓተ ምግብ መጓዳል ችግር ሊቀንሱ የሚችሉ ሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ አስፈላጊ በመሆኑ በተመረጡ ወረዳዎች ለነፍሰጡር እና ከ2 ዓመት በታች ህጻናት ላላቸው ቤተሰቦች የተለያዩ የግብአት አቅርቦት

ኪኪ ዜና ሀ/ወልዴ የስትራተጂክ ጉዳዮች ሥራ አስፈጻሚ

የማካሄድ ስራ ተሰርቷል። የተሰራጩ የግብአት አቅርቦቱም በምግብ ንጥረ ይዘት የበለጸጉ የግብርና ግብአቶች (የወተት ፍየል፣ እንቁላል ጣይ ዶሮዎች፣ የጓሮ አትክልት ዘር፣ የፍራፍሬ ችግኝ፣ የብርቱካንማ ስኳር ድንች ቁርጥራጭ፣ በብረት የበለጸገ ቦሎቄ እና ገንቢ በቆሎ እና የመሳሰሉት ስርጭት)፣ በማንኛውም ጊዜ ማምረት የሚያስችል የመስኖ፣ የግሪን ሀውስ እና የተግባር ስልጠና በቀላሉ ሊያገኙበት የሚችሉበትን የስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ሰርቶ ማሳያ ማእከል ግንባታ ስራዎች የማከናወን ስራ ተሰርቷል።

## ከልማታዊ ሴፍቲኔት ጋር በመተባበር የተከናወኑ ተግባራት

ከምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ጋር በመተባበር በአራተኛው እና በአምስተኛው ልማታዊ ሴፍቲኔት ተጠቃሚ የሆኑ ታላሚ ቤተሰቦችን የሥ/ምተ ግብርና ተግባራዊ እንዲያደርጉ እና የሥርዓተ ምግብ ሁኔታቸውን እንዲሻሻል ለማድረግ ታቅዶ በአራት ወረዳዎች 200 ተጠቃሚዎች እና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል። ስልጠና ከተሰጠ በኋላ ለታላሚዎች የተለያየ ግብዓት ለአንድ ቤተሰብ ቢያንስ ሶስት ግብዓቶችን በማድረግ (ዶሮ፣ የወተት ፍየል፣ ፍራፍሬ ችግኝ፣ የአትክልት ዘር እና ጥራጥሬ ዘር) እንዲሰራጭ ተደርጓል።

## ክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ እና ቅንጅታዊ አሰራር

የምግብና ሥርዓተ ምግብ ተግባራትን በክልሎች በወረዳ እና በቀበሌ ደረጃ ድጋፍና ክትትል 25 ዙር ለማካሄድ ታቅዶ በአጠቃላይ 25 ጊዜ ድጋፍና ክትትል ተካሂዷል። ቅንጅታዊ አሰራርን ለማጠናከር የምግብና የስርዓተ-ምግብ አጋር አካላት የጋራ መድረክ (Platform) ለመፍጠር ታቅዶ ብሄራዊ የሥርዓተ ምግብ ተኮር የአጋር አካላት ፎረም ተቋቁሟል። በሶስት ክልሎችም የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና የአጋር አካላት የጋራ መድረክ እንዲደራጅ ተደርጓል።

በኦሮሚያ እና አማራ ክልሎች በሚገኙ ሁለት ወረዳዎች የግብርና መረጃ ሥርዓትን በመጠቀም የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና መረጃ አጠቃቀምን ለማሳደግ ታቅዶ በሁለቱም ወረዳዎች በሙከራ ደረጃ እየተተገበረ ይገኛል።

በየዓመቱ ክልሎች፣ የምርምር ተቋማት፣ ዩኒቨርሲቲዎች እና አጋር አካላት በተገኙበት የጋራ የምግብ ስርዓተ ምግብ የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ የአፈፃፀም ግምገማ ለማካሄድ ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት የተከናወነ ሲሆን በአውደ ጥናቱም 151 (28 ሴት) ከየተቋማቱ የተውጣጡ አካላት ተሳትፈዋል። በምግብና ስርዓተ ምግብ የአቅም ግንባታ ፕሮጀክት አስተባባሪነት አስራ ስድስት የስራ ኃላፊዎችን ያሳተፈ (10 ከፌደራል እና 6 ከአማራ፣ ኦሮሚያ እና ሶማሊ ክልሎች) (2 ሴት) የምግብና ስርዓተ ምግብ ትግበራ ላይ የልምድ ልውውጥ በብራዚል ሀገር ተካሂዷል።

## በምግብ ንጥረ ነገር ይዘታቸው የበለጸጉ ሰብሎች ዘር ብዜት

ከህጻናት አድን (Save the Children) ድርጅት በተገኘ የበጀት ድጋፍ በብር 209,271 280 ከ/ል የተለያዩ በምግብ ንጥረ ይዘታቸው የበለጸጉ የጥራጥሬ ሰብሎች (Mung Bean, Cow Pea, Chick Pea, Peagon Pea, Quality Protein Maize) ዘርና እና ሌሎች የግብርና ግብአቶች ግዥ በመፈጸም ከመልካሳ ግብርና ምርምር ማዕከል ጋር በመተባበር የማባዛት ስራ ተሰርቶ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል።



ከላ ዜና ሀ/ወልድ
የስትራተጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

### 2.7.3. የአካባቢ እና አየር ንብረት ለውጥ

በግብርናው ሴክተር ይህንን ግብ ለማሳከት ከሰብል ልማት ዘርፍ ዝቅተኛ የካርበን ልቀት ያላቸው ቴክኖሎጂዎች የተተገበረበት የእርሻ ማሳዎች ላይ እስከ 2015 ዓ/ም 11.01 ሚ/ን ሜ/ቶን Co2e የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ለመቀነስ ታቅዶ ባለፉት ሦስት አመታት በተከናወኑት ስራዎች ከዘርፉ 7.11 ሚ/ን ሜ/ቶን Co2e የሙቀት አማቂ ለመቀነስ ተችሏል። ይህም ከእቅዱ ጋር ሲነፃፀር 64.58 በመቶ ሲሆን ከተፈጥሮ ሀብት ልማት ዘርፍ እስከ 2015 ዓ/ም 8.1 ሚ/ን ሜ/ቶን Co2e የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ለመቀነስ ታቅዶ ባለፉት ሦስት አመታት በተከናወኑት የተቀናጀ የተፈጥሮ ሀብት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ስራዎች ከዘርፉ 5.25 ሚ/ን ሜ/ቶን Co2e የሙቀት አማቂ ለመቀነስ ተችሏል። ይህም ከእቅዱ ጋር ሲነፃፀር 64.81 በመቶ ነው። ከእንስሳት ሀብት ልማት ዘርፍ እስከ 2015 ዓ/ም 12.94 ሚ/ን ሜ/ቶን Co2e የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ለመቀነስ ታቅዶ ባለፉት ሦስት አመታት በተከናወኑት ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተጣጣሙ፣ የእንስሳትን ምርትና ምርታማነትን የሚጨምሩ ስራዎችን በማጎልበት ከዘርፉ 8.34 ሚ/ን ሜ/ቶን Co2e የሙቀት አማቂ መቀነስ ተችሏል።

ይህም ከእቅዱ ጋር ሲነፃፀር 64.45 በመቶ መቀነስ ተችሏል። በአጠቃላይ ባለፉት ሦስት አመታት 32.05 ሚ/ን ሜ/ቶን Co2e የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ለመቀነስ ታቅዶ በየዘርፉ በተከናወኑ የማጣጣሚያና ማስተሰሪያ ስራዎች 20.7 ሚ/ን ሜ/ቶን Co2e የሙቀት አማቂ ጋዝ መቀነስ የተቻለ ሲሆን ይህም ከእቅዱ ጋር ሲነፃፀር 64.58 በመቶ መቀነስ ተችሏል። አፈፃፀሙ ከዕቅዱ በታች የሆነበት ምክንያት በአገራችን ያለው የመረጃ ቅብብሎሽ ስርዓት ያልተጠናከረ መሆኑ፣ ለዚህ ስራ ሊያግዝ በሚችል መልኩ መረጃን ከማደራጀትና ከማጠናከር አንፃር ክፍተት መኖሩ፣ በየደረጃው የተናበበና የተደራጀ አደረጃጀት አለመኖር፣ እንዲሁም የመረጃ መንጭ የሆኑ መ/ቤቶች በሚፈለገው ሁኔታና ጊዜ መረጃ ማቅረብ ባለመቻለቸው ትንታኔ ውስጥ ባለመካተቱ ነው። በመሆኑም የግብርና ሴክተር የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ልኬት ስራን በሚ/መ/ቤታችን ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ለማከናዎን የልኬት፣ ዘገባና ማረጋገጥ ስርዓት (MRV System) ተቋሙን በሚመጥን ደረጃ ማጠናከርና ስራውን የሚመጥን አደረጃጀት የመፍጠርና የሰው ኃይሉን የማብቃት ስራ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው።

በተቋሙ ስር የሚገኙ የተለያዩ የስራ ክፍሎችና ፕሮግራሞች ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታን ለማጎልበት የሚያስችሉ ስራዎችን በዓመታዊ ዕቅዳቸው ውስጥ በማካተት እንዲተገበሩ የማድረግ ስራ ባለፉት ሶስት ዓመታት በሶስቱ ዘርፎች (በሰብል፣ተፈጥሮ ሃብትና እንስሳት) ስር በሚገኙ በስምንት የስራ ክፍሎች እና በአምስት የማካተት ስራ ተሰርቷል። የግብርና ዘርፍን ለአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭነትን ለመቀነስ የሚያስችሉ ተግባራትን ለመተግበር የሚያስችል የሃብት ግኝትን ለማሳደግና ሃብት ለማፈላለግ አምስት ፕሮፓዛሎችን ለማዘጋጀትና ሃብት ለማግኘት ታቅዶ አምስቱም ፕሮፓዛሎች ከተለያዩ የልማት አጋራት ጋር በመተባበር ተዘጋጅተዋል። በዚህም መሰረት ከGIZ-RGIL በተገኘ ፋይናንስ ለግብርና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት አንፃር ስራ የድጋፍ፣ የክትትልና የአቅም ግንባታ ስራ ተሰርቷል። እንዲሁም የተቀሩት አራት ፕሮፓዛሎች በ"Global Green Growth Institute (GGGI)" አስተባባሪነት በአለም አቀፍ ደረጃ የአየር ንብረት ለውጥን ለመደገፍ ለተቋቋመው የፋይናንስ ተቋም



ዜና ሀ/ወልድ
የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

ለGreen Climate Fund (GCF) በማቅረብ የተቋሙን የምዝና መስፈርት ያሟሉ ሁለት (2) ፕሮፖዛሎች ተቀባይነት አግኝተዋል። የቀሩትን ሁለት ፕሮፖዛሎች በቀጣይ የአየር ንብረት ለውጥን ለመደገፍ ፍላጎት ላላቸው የፋይናንስ ተቋማት ለማቅረብ ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

ባለፉት ሶስት ዓመታት በአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ስትራቴጂ በግብርናው ዘርፍ እንዲተገበሩ ለተለዩ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያና ማስተሰረያ ስራዎችና አሰራሮች፤ እንዲሁም የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት ማረጋገጥ ስራዎችን ለመተግበር መደላድል መፍጠር የሚያስችሉ ስራዎች ለማከናወን ተችሏል።

ከAlliance Biodiversity and CIAT ጋር በመተባበር አገራዊ ከአየር ንብረት ጋር የተስተጋበረ የግብርና ልማት ፍኖታ ካርታ ተዘጋጅቶ ወደ ትግበራ እንዲገባ ተደርጓል። ከClimate Change Agriculture and Food Security (CCAFS) ጋር በመተባበር የእንስሳት ዘርፍ ሙቀት አማቂ ጋዝ ልኬት፣ዘገባና ማረጋገጥ (MRV) ስራን በደረጃ II (በ Tier II") ለመስራት የሚያስችል አሰራር ማዘጋጀትና መተግበር ተችሏል። በግብርና ሚኒስቴር፣ በተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም (UNDP) እና ከዓለም ምግብና እርሻ ድርጅት (FAO) በጋራ ከሚተገበረው Scaling up Climate Ambition on Land Use and Agriculture through NDCs and NAPs (SCALA) Ethiopia Programe ጋር በመተባበር በሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ልኬት፣ ዘገባና ማረጋገጥ (MRV) ፅንስ ሀሳብ እና መሰረታዊ አተገባበር ዙሪያ ከዓለም ምግብና እርሻ ድርጅት ዋና መ/ቤት በመጡ አለም አቀፍ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች በአራት ዙር ተግባር ተኮር ስልጠናዎች ለፌደራል፣ ለክልል ግብርናና ሌሎች የሚመለከታቸው ባለሙያዎች ተሰጥቷል።

በGreen Climate Fund (GCF) ድጋፍ የሚተገበረው ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ፕሮጀክት በሚተገበርባቸው አስራ ስምንት ወረዳዎች እየተተገበረ ያለውን የማጣጣሚያና የማስተሰርያ ስራዎችን በሚፈለገው ደረጃ መተግበራቸውን የማጣጣሚያና የማስተሰርያ መርሆዎችን መሰረት በማድረግ ተደጋጋሚ የክትትል፣ ድጋፍና የአቅም ግንባታ ስራዎች ተሰርቷል። በግብርና ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮጀክቶች አለምአቀፍና ሀገር አቀፍ የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት ስታንዳርድን መሰረት በማድረግ የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት እንዲያረጋግጡ ለማስቻል በጋምቤላ ክልል አኙዋክና መጃንግ ዞን፣ በአማራ ክልል በምስራቅ ጎጃም፣ በሰሜን ሸዋ እና በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሸዋ በመስክ ላይ በመገኘት በሆርቲካልቸር፣ በጥጥ፣ በሰሊጥ፣ በቡናና እንስሳት ልማት ላይ ለተሰማሩ የግብርና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ተከታታይ የድጋፍ፣ ክትትልና የአቅም ግንባታ ስራ ተከናውኗል። በግብርና ልማት ዘርፍ ላይ ለተሰማሩ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት ጉዳዮች ዙሪያ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት በማድረግና ስራዎቹን በመገምገም አስፈላጊውን ግብረ-መልስ የመስጠት ስራ ተከናውኗል። በFarm Africaና GIZ-S2RAI ድጋፍ በመስሪያ ቤታችን የተዘጋጀውን ኃላፊነት የተሞላበት የግብርና ኢንቨስትመንት ዕውን ለማድረግ የሚያስችል የማህበራዊና አካባቢ የስነምግባር ደንብ ሰነድ የአማርኛ ትርጉም ከ6,000 ኮፒ በላይ ለሁሉም ለክልሎችና የግብርና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የማሰራጨትና ግንዛቤ መፍጠር ስራዎች ተከናውኗል።

### 2.7.4. ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች

**የአቅም ግንባታ ስራዎች**

ከፌደራል፣ ከክልል እስከ ቀበሌ ለተዉጣጡ ፈፃሚዎችና አስፈፃሚዎች፣ ለፕሮጀክቶች/ ፕሮግራሞ ፈፃሚዎችና አስተባባሪዎችና ባለድርሻ አካላት እንዲሁም ለተጠሪ ተቋማት ፈፃሚዎች በስርዓተ-ፆታ ፅንሰ ሀሳብ፣ ስርዓተ-ፆታን አካቶ መስራት ዙሪያ ለ4,824 (ሴት 3,124) ፈፃሚና አስፈፃሚ አካላት የስልጠና/የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ለመስራት ታቅዶ (ሴት 2,937) በአጠቃላይ **ለ4,535 (94%)** አካላት መስጠት ተችሏል። የሚ/ር መ/ቤቱ የሴት ሠራተኞች ፎረምን የማደራጀትና የማጠናከር ስራ በመስራት የአባላቱ ቁጥር 526 ማድረስ የተቻለ ሲሆን፤ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ችግር ለማሻሻል፣ በዝቅተኛና መካከለኛ አመራርነት ደረጃ ያላቸዉን ዝቅተኛ ተሳትፎ ለማሳደግ ያስችል ዘንድ በዶሮና በዓሳ እርባታ/አያያዝ፣ በራስ-መተማመን ፅንሰ ሀሳብ፣ በስርዓተ-ፆታ ፅንሰ ሀሳብ እና በኤች.አይ.ቪ. ዙሪያ ቀጣይነት ያለዉ የአቅም ግንባታ ስራዎች ተሰርቷል።

**የክትትል፣ ድጋፍና የዳሰሳ ጥናት ስራዎችን ማጠናከር**

አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ደቡብ፣ ሲዳማ፣ ድሬደዋ፣ ሀረሪ ክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎችና ቀበሌዎች፣ ከአርብቶ አደር አካባቢዎች ለሶማሌ፣ በጋንቤላ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በደቡብ ለደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ክትትልና ሙያዊ ድጋፍ ተደርጓል።

**የመልካም ተሞክሮ ስራዎችን ማጠናከር**

ልምድ ልውውጥን በሚመለከት በደቡብ ክልል ጉራጌ ዞን መስቃን ወረዳ በሴቶችና ወጣቶች የተገኙ ዉጤታማ ስራዎችን ለማስፋት ከተቋሙ፣ ከክልልና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን አሳታፊ ያደረገ የልምድ ልዉዉጥ መድረክ ተካሄዷል። በኦሮሚያ ክልል ደቡብ ምዕራብ ዞን ወሊሶና ጎሮ ወረዳ የኩታ ገጠም እርሻ ተሳታፊና ተጠቃሚ የሆኑ ሴት አርሶአደሮች በጤፍና በበቆሎ ልማት ያለሙትን በመስክ የመጎብኘትና ተሞክሮዎችን የመቀመር ስራ ተሰርቷል። በአማራ፣ ደቡብና በኦሮሚያ ክልሎች በስርዓተ ጾታ ሞዴል ቤተሰቦች ላይ መረጃ በማሰባሰብ ምርጥ ተሞክሮ በመቀመር ወደ ሌሎች አካባቢዎች የማስፋት ስራ እየተሰራ ይገኛል። በሴቶችና ወጣቶች የተገኙ ዉጤታማ ስራዎችን ለማስፋት የዶክመንተሪ ስራዎች ተሰርቷል።

**የግብርና ቴክኖሎጂዎች አቅርቦትና ዉጤታማነት ስርዓትን ማሻሻል**

በወተት ሀብት ልማት ዙሪያ ለሴቶች ምቹ፣ ጊዜ፣ ጉልበት ቆጣቢ እና እሴት የሚጨምሩ የወተት ማለቢያና ማጣሪያ ቴክኖሎጂዎች ለአማራ፣ ኦሮሚያና ደቡብ ክልሎች ለእያንዳንዳቸዉ 70 በአጠቃላይ 280 ግብዓቶችን ድጋፍ ማድረግ ታቅዶ 210 (75%) ድጋፍ ማድረግ ተችሏል፤ የሴቶችን ጊዜና ጉልበት ለመቆጠብ የሚያስችሉ 200 ግብዓቶችን ድጋፍ ማድረግ ታቅዶ 150 (75%) የጓሮ አትክልት ግብዓቶች ለኦሮሚያ፣ አማራና ደቡብ ክልሎች ድጋፍ ተደርጓል። እንዲሁም ከዓሳ ሀብት ዳ/ት ጋር በመቀናጀት በሀረሪ ክልልና በደቡብ ክልል አርባ ምንጭ ዙሪያ ለሚገኙ ሴቶች በዓሳ ሀብት ልማት ዙሪያ ለ80 ተሳታፊዎች ተግባር ተኮር ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ70 (88%) ተሰጥቷል። በሀረሪ ክልል ለሚገኙ

ዜና ሀ/ወልድ
የስርዓተ-ፆታ ጉዳዮች
ስራ አስፈጻሚ

የሴት የልማት ቡድን አደረጃጀቶች በመስኖ ስራዎች ተሰማርተዉ ሁለንተናዊ ተጠቃሚነታቸዉን ለማሳደግ የሚያስችል ለመስኖ ስራ የሚዉሉ ድጋፍ ተደርጓል፣

**የአሰራር ስርዓትን ማሳደግ**

ከUN-WOMEN ፕሮጀክት ጋር በመቀናጀት የግብርናዉን ሴክተር መዕከል ያደረገ የስርዓተ-ፆታ የስልጠና ማንዋል ተዘጋጅቷል፣ የማህበረሰብ ተፋሰስ አጠቃቀምና አስተዳደር መመሪያ እንዲሁም የዶሮ ሃብት ልማትና ግብይት ረቂቅ አዋጅ ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር አብሮ በመሆን ከስርዓተ ጾታ እና ከማህበራዊ ጉዳይ አኳያ እንዲታይ የግብዓት ማሰባሰቢያ የውይይት መድረክ በማካሄድ በመመሪያዉ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ግብርና ሚ/ር ከCARE ETHIOPIA ጋር በመሆን የስርዓተ ፆታ ኦዲት በፌደራል እና በክልል ደረጃ (አማራ እና ሲዳማ ክልል) በአማካሪ ተጠንቷል፡፡ በዚህ መስረት በግኝቱ መሰረት የድርጊት መርሀ ግብር ተዘጋጅቶ ወደ ስራ ተግብቶዋል፡፡ የግብርና ሴክተር የስርዓተ-ፆታ እኩልነት ስትራቴጂ የክለሳ ስራ የመግቢያ ሪፖርት የሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላትን አሳታፊ ያደረገ መድረክ በመፍጠር ሰነዱን የማዳበር ስራ ተሰርቷል፡፡

**የበጎ አድራጎትና የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎችን ማሻሻል**

ተስፋ አዲስ ፓረንትስ ቻይልድ ሁድ የካንሰር ህሙማን ድርጅት እንዲሁም ደብረ-ሊባኖስ የሴቶች ህፃናትና ወጣቶች አዕምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል ከብር 41,725 በላይ የሚያወጡ የምግብና የትምህርት መርጃ ቁሳቁስ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች ወላጆቻቸዉን ላጡ ህፃናት (አካል ጉዳተኞችም ይገኙበታል) የተለያዩ አልሚ ምግቦችን እንዲሁም ለንጽህና መስጫ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን በመግዛት ድጋፍ ተደርጓል፣ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተፈጠረዉ ጦርነት ሳቢያ ለተፈናቀሉ ወገኖቻችን ከብር መቶ ሺህ በላይ በማሰባሰብ የምግብ፣ የህፃናት ሞዲስና ሌሎችም ልዩ ልዩ ድጋፎች ተደርጓል፡፡ ለሰዋሰዉ ገነት የአረጋዊያን፣ ሴቶችና ህፃናት የእርዳታ ድርጅት የአልባሳትና የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁስ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ ለኦሮሚያ፣ አማራና ደቡብ ክልሎች ከሁለት ሚሊየን ብር በላይ የሚያወጡ የአልባሳት ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በመስሪያ ቤቱ ድጋፍ ለሚደረግላቸው ወላጆቻቸውን በሞት ላጡ 7 ህጻናት የትምህርት መርጃ ቁሳቁስ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ 200,000 ብር የሚገመት የምግብ እህሎች እና የአልባሳት ድጋፍ ለሰዋሰው አዕምሮ ህሙማን መርጃ እና በኤች አይቪ/ኤድስ ወላጆቻችውን ላጡ ህጻነት ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በአማራ እና በደቡብ ምዕራብ ክልሎች 10 የአቅመ ደካማ ማህበረሰብ የመኖሪያ ቤቶችን በመገንባት ድጋፍ ተደርጓል፡፡

ዓለም አቀፋዊና ሀገር አቀፍ ኩነቶችን ማክበርን በተመለከተ፡- የሚ/ር መ/ቤቱ፣ የተጠሪ ተቋማት እና የክልል ፈፃሚዎችና አስፈፃሚዎችን አሳታፊ ያደረገ የግንዛቤና የምክክር መድረክ ተካሄዷል፣ በጉራጌ ዞን እነሞር ወረዳ ተርሆኜ ቀበሌ ከፌደራል እስከ ቀበሌ የሚገኙ አመራሮች፣ ፈፃሚዎች፣ አስተባባሪዎች/አስፈፃሚዎች፣ ተፅዕኖ ፈጣሪ አካላት፣ በልዩ ልዩ የግብርና ልማት ስራዎችን በማከናወን ዉጤታማ የሆኑ 80 የስርዓተ-ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ተመራቂዎችንና ባለድርሻ አካላትን በአጠቃላይ 400 አካላትን ለማሳተፍ ታቅደ 350 አካላትን አሳታፊ በማድረግ ዉጤት ተኮር በሆነ መንገድ/መልካም ተሞክሮዎችን ለማስፋት በሚያስችል መልኩ ተከብሯል፡፡ በሲዳማ ክልል ሸበዲኖ ወረዳ በአማራ ክልል

በሚጫ ወረዳ በልዩ ልዩ የግብርና ልማት ስራዎች ዉጤታማ የሆኑ የስርዓተ-ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ተመራቂዎችንና ሴት ሞዴል አርሶ አደሮች ማሳ ከፌደራል እስከ ቀበሌ የሚገኙ አመራሮች፣ ፈፃሚዎች፣ አስተባባሪዎች/አስፈፃሚዎች፣ ባለድርሻ አካላትን አሳታፊ በማድረግ መልካም ተሞክሮዎችን ለማስፋት በሚያስችል መልኩ ተከብሯል፡፡

## 2.8. የሶስት ዓመታት የፌደራል ፕሮግራም በጀት አጠቃቀም

### ግብርና ሚኒስቴር እና ተጠሪ መ/ቤቶች

ባለፉት ሁለት ዓመት ተከ‍ል ለግብርና ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት (50.2 ቢሊዮን) ብር እንዲመደብ ተደርጓል፡፡ የተመሳሳይ ጊዜ አፈፃፀም ሲታይ (62.9 ቢሊዮን) ብር ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የበጀት አፈፃፀም ሲታይ 125 በመቶ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

### 2.8.1. ግብርና ሚኒስቴር

ለግብርና ሚኒስቴር በመደበኛ በጀት 2.19 ቢሊዮን ብር የተመደበ ሲሆን በካፒታል በጀት 32.1 ሚ/ን ብር በድምሩ 34.28 ቢሊዮን ብር እንዲመደብ ተደርጓል፡፡ የተመሳሳይ ጊዜ አፈፃፀም ሲታይ በመደበኛ 3.54 ቢሊዮን ብር እንዲሁም በካፒታል 59.52 ቢሊዮን ብር በድምሩ 63.07 ቢሊዮን ብር ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

የበጀት አፈፃፀም በመቶኛ ሲታይ በመደበኛ፣ በካፒታል እና በአጠቃላይ በጀት ሲታይ 162 በመቶ፣ 185 እና 184 በተከታታይ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ይኸ የበጀት አጠቃቀም በ2013 በጀት ዓመትና በ2014 በጀት ዓመት የተወሰኑ ወራት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስር የነበሩና በመ/ቤቱ የአደረጃጀት ለውጥ ምክንያት በአሁኑ ወቅት ወደ ተጠሪ ተቋማት እና ከግብርና ሴክተር ውጪ ወደ ሌላ አካል ተዛውረው ያሉ የስራ ክፍሎችን በጀት አያካትትም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተመሳሳይ ምክንያት በመ/ቤቱ ስር በሚገኙ ፕሮግራሞች የተዋቀሩ ስራ አስፈፃሚዎች በጀትና አጠቃቀማቸው በአዲሱ አደረጃጀት መሰረት መረጃዎቹ እንዲያዙ ተደርገዋል፡፡

ከላይ የተገለፀው የበጀት አፈፃፀም ልዩነት በዋናነት የመነጨው በመደበኛ በጀት አስተዳደር ስርዓት መሰረት በግብርናው ሴክተር በተከሰቱ አስገዳጅ ሁኔታዎች ምክንያት በተጨማሪ በጀት የተፈቀደ እና ጥቅም ላይ የዋለ በጀት በመኖሩ ምክንያት ሲሆን በመ/ቤቱ የተፈቀደ በጀት ላይ ተፅዕኖ ባያሳድርም በተወሰነ ደረጃ በመ/ቤቱ ስር በሚገኙ ፕሮግራሞች መካካልና በአንድ ፕሮግራም ስር በሚገኙ ንዑስ ፕሮግራሞች መካከል የተደረጉ የበጀት ዝውውሮች በንዑስ ፕሮግራሞች ደረጃ ለተከሰቱ የመደበኛ በጀት ከፍተኛ አፈፃፀሞች ምክንያት እንደሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡

በካፒታል በጀት አፈፃፀም ላይ ለታየው የአፈፃፀም ብልጫ አንዱ ምክንያት የዕርዳታ የበጀት ምንጭ ያላቸው ፕሮጀክቶች በአጠቃላይ ስምምነት የተደረሰበትን የበጀት መጠን ሳያፋልስ በየዓመቱ ለፕሮጀክቶቹ ስራ ማስፈፀሚያ ከበጀት ውጪ በሚመደበው ተጨማሪ ገንዘብ ምክንያት የመጣ ልዩነት እንደሆነ መታወቅ አለበት፡፡

ለ/ አ/ ዜና ሀ/ወልድ
የስትራቴጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

በአጠቃላይ በሚ/ር መ/ቤቱ የበጀት አፈፃፀም ላይ ለታዩት ልዩነቶች እንደሚከተለው በአምስቱ ዋና ዋና ፕሮግራሞች ስር ለማብራራት ተሞክሯል።

## የበጀት ዕቅድ አፈፃፀም እና ማብራሪያ በአምስቱ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮግራሞች

### ፕሮግራም 1. ስራ አመራርና አስተዳደር

ይኸ ፕሮግራም በስሩ በመደበኛ በጀት ስራቸውን የሚያከናውኑ 17 ስራ አስፈፃሚዎችን (17 ተግባራት በፕሮግራም በጀት አገላለፅ) እና በክልል የሚተገበሩትን የሰቆጣ ቃል ኪዳን ስምምነት የስርዓተ-ምግብ ተግባራትን እንዲሁም በካፒታል በጀት የሚሸፈን አንድ የአዳራሽ ግንባታ ፕሮጀክትን የሚይዝ ሲሆን በመደበኛ በጀት 772.1 ሚ/ን ብር እና በካፒታል በጀት 83.41 ሚ/ን ብር በድምሩ 855.51 ሚ/ን ብር ልዩ ልዩ የድጋፍ አገልግሎቶችን ለማከናወን በጀት የተመደበ ሲሆን በተመሳሳይ ጊዜ 820.1 ሚ/ን ብር (106%) በመደበኛ 47.1 ሚ/ን (57%) በካፒታል በጀት በድምሩ 867.55 ሚ/ን ብር (101%) ለታቀዱ ስራዎች ማስፈፀሚያ ስራ ላይ ውሏል።

በበጀት አጠቃቀም ረገድ በፕሮግራም ደረጃ ሲታይ በሁለቱ የበጀት ዓይነቶች 35.95 (11.08%) ሚ/ን ብር ጥቅም ላይ ያልዋለ በጀት እንደነበረ የሚያሳይ ሲሆን ይህ ልዩነት በተለይ ለአዳራሽ ግንባታ የተመደበው በጀትና የሰቆጣ ቃል ኪዳንን ለማስፈጸም የተመደበው በጀት አጠቃቀም ዝቅተኛ በመሆኑ ምክንያት የመጣ ልዩነት ነው። በሌላ በኩል ለ17ቱ አገልግሎት ሰጭ ስራ አስፈፃሚዎች ከተመደበው የመደበኛ በጀት በላይ 48 ሚ/ን ብር ጥቅም ላይ እንደዋለ መገንዘብ የተቻለ ሲሆን ለዚህም ምክንያቱ በተወሰኑ የፕሮግራሙ የስራ ክፍሎቹ ላይ የበጀት ዕጥረት በማጋጠሙ ምክንያት በመንግስት የበጀት ዝውውር አስተዳደር ስርዓት መሰረት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚገኙ ሌሎች ፕሮግራሞች በተከናወነ የበጀት ዝውውር ዕጥረቱ እንዲሟላ በመደረጉ የተፈጠረ ልዩነት ነው።

### ፕሮግራም 2፡ የእርሻና ሆርቲካልቸር ልማት

ይኸ ፕሮግራም በስሩ በመደበኛ በጀት ስራቸውን የሚያከናውኑ 4 ንዑስ ፕሮግራሞችን/ስራ አስፈፃሚዎችንና 3 የካፒታል ፕሮጀክቶችን የሚይዝ ሲሆን በመደበኛ በጀት 484.54 ሚ/ን ብር እና በካፒታል በጀት 4,733.41 ሚ/ን ብር በድምሩ 5,217.95 ሚ/ን ብር የተመደበ ሲሆን በተመሳሳይ ጊዜ 1,803.83 ሚ/ን ብር (372%) በመደበኛ 4,714.25 ሚ/ን ብር (99.6%) በካፒታል በድምሩ 6,518.08 ሚ/ን ብር (125%) በፕሮግራሙ ለታቀዱ መደበኛ ተግባራትና ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ ስራ ላይ ውሏል። በአጠቃቀም በኩል በመደበኛ በጀት ለታየው 1,319.29 ሚ/ን ብር ብልጫ ዋናው ምክንያት ለእፀዋት ጥበቃ አገልግሎት የድሮንና የአውሮፕላን ግገር በመንግስት የበጀት ዝውውር ስርዓት መሰረት ተጨማሪ በጀት ተፈቅዶ ስራ ላይ እንዲውል በመደረጉ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ በካፒታል በጀት በ19.16 ሚ/ን ብር አፈፃፀሙ በማነስ ይታያል።

ለኩ ሀብታሙ ሀ/ወልድ
የስትራቴጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

### ፕሮግራም 3. የተፈጥሮ ሀብት ልማት

በዚህ ፕሮግራም ስር የመደበኛ በጀት በሚመደብላቸው 4 ንዑስ ፕሮግራሞችን/ስራ አስፈፃሚዎችና 4 የካፒታል ፕሮጀክቶችን የሚይዝ ሲሆን በመደበኛ በጀት 111.46 ሚ/ን ብር እና በካፒታል በጀት 22,514.99 ሚ/ን ብር በድምሩ 22,626.45 ሚ/ን ብር የተመደበ ሲሆን በተመሳሳይ ጊዜ 235.54 ሚ/ን ብር (211%) በመደበኛ 50,456.72 ሚ/ን ብር (224%) በካፒታል በድምሩ 50,692.26 ሚ/ን ብር (224%) በፕሮግራሙ ለታቀዱ መደበኛ ተግባራትና ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ ስራ ላይ ውሏል። የበጀት አፈፃፀሙ ሲታይ በፕሮግራም ደረጃ በመደበኛ በጀት የ124 ሚ/ን ብር ከፍ ያለበት ምክንያት ለአረንጓዴ አሻራ የሚሆን ተጨማሪ በጀት በመገኘቱ ነው። የፕሮግራሙ የካፒታል በጀት አጠቃቀም ከፍ ብሎ የታየበት ምክንያት በየዓመቱ በፕሮግራሙ ስር ለሚገኙና በተለይ ከልማት አጋራት ከሚገኝ የዕርዳታ ገንዘብ ምንጮች ስራቸውን የሚያከናውኑ ፕሮጀክቶች አጠቃላይ ስምምነት የተደረገበትን የገንዘብ መጠን መሰረት ባደረገ ሁኔታ ጥቅም ላይ የዋለ ተጨማሪ የገንዘብ መጠን በመኖሩ ነው።

### ፕሮግራም 4. የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት

ይኽ ፕሮግራም በስሩ በመደበኛ በጀት ስራቸውን የሚያከናውኑ 4 ንዑስ ፕሮግራሞችን/ስራ አስፈፃሚዎችንና 7 የካፒታል ፕሮጀክቶችን የሚይዝ ሲሆን በመደበኛ በጀት 254.41 ሚ/ን ብር እና በካፒታል በጀት 4,739.32 ሚ/ን በድምሩ 4,993.64 ሚ/ን ብር የተመደበለት ሲሆን በተመሳሳይ ጊዜ 268.39 ሚ/ን ብር (105%) በመደበኛ 4,296.46 ሚ/ን ብር (91%) በካፒታል በድምሩ 4564.85 ሚ/ን ብር (91%) በፕሮግራሙ ለታቀዱ መደበኛ ተግባራትና ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ ስራ ላይ ውሏል። በአጠቃቀም ረገድ በመደበኛ በጀት ለታየው 13 ሚ/ን ብር ብልጫ ዋናው ምክንያት ለእንስሳት ድንበር ዘለል በሽታዎች ክትባት ለሚውል የመድሀኒት ግዢ በየዓመቱ የሚመደበው በጀት በቂ ባለመሆኑ ምክንያት በመንግስት የተጨማሪ በጀት አስተዳደር ስርዓት በየዓመቱ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ እየተጠየቀ የሚፈቀድና ጥቅም ላይ የሚውል በጀት በመኖሩ ምክንያት ነው።

### ፕሮግራም 5. የኢንቨስትመንትና ግብዓትና ግብይት

በዚህ ፕሮግራም ስር በመደበኛ በጀት ስራቸውን የሚያከናውኑ 4 ንዑስ ፕሮግራሞችን/ስራ አስፈፃሚዎችን የያዘ ሲሆን በካፒታል በጀት የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች የሉትም። በዚሁ መሰረት በመደበኛ በጀት 72.19 ሚ/ን ብር የተመደበ ሲሆን በተመሳሳይ ጊዜ 58.53 ሚ/ን ብር (81%) በፕሮግራሙ ለታቀዱ መደበኛ ተግባራትና ስራ ላይ ውሏል።

### ፕሮግራም 6. የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና

በዚህ ፕሮግራም ስር በመደበኛ በጀትና ካፒታል በጀት ለሚከናወኑ ተግባራት በመደበኛ በጀት 496.65 ሚ/ን ብር፣ በካፒታል 22.72 በድምሩ 519.37 የተመደበ ሲሆን በመደበኛ በጀት 359.28 (72%) በካፒታል 10::14 (95%) በድምሩ 369.42 (71) በፕሮግራሙ ለታቀዱ መደበኛ ተግባራትና ስራ ላይ ውሏል።

### 2.8.2. ተጠሪ ተቋም

ባለፉት ሁለት ዓመት ተከል ተጠሪ ተቋማት (6.2 ቢሊዮን) ብር እንዲመደብ ተደርጓል። በየተመሳሳይ ጊዜ አፈፃፀም ሲታይ (5.4 ቢሊዮን) ብር ጥቅም ላይ ውሏል። ሶስት ዓመት ጊዜ የበጀት አፈፃፀም ሲታይ 87 በመቶ እንደሆነ መረዳት ይቻላል።

## 2.9. የዘርፉ መሰረታዊ ማነቆዎች

ባለፉት ሶስት ዓመታት የግብርና ትራንስፎርሜሽንን ለማረጋገጥና ግብርና ለሀገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት የሚጠበቅበትን አስተዋፅኦ ለማበርከት በሚደረገው ጥረት የሚከተሉት ጉዳዮች የዘርፉ መሰረታዊ ማነቆ ሆነው ተለይተዋል። የግብዓትና ቴክኖሎጂ አቅርቦት ስርዓት ውስንነት፤ የፋይናንስ ተደራሽነት፤ ያልተስተካከለ የግብርና ግብይት ስርዓት፤ በቂ ያልሆነ መሰረተ ልማትና ኢንቨስትመንት፤ ተቋማዊ የማስፈፀም አቅም እና የአየር ንብረት ለውጥ ናቸው። በየንዑስ ዘርፎች የሚከተሉት ተግዳሮቶች ተለይተዋል

**በሰብልና ሆርቲካልቸር ልማት፡** የቅድመ እና ድህረምርት ሜካናያዜሽን መሳሪያዎች አቅርቦት፣ በሽታን የሚቋቋሙ የሰብል ቴክኖለጂዎች ያለመኖር፣ ከእፀዋት በሽታ ሀገራዊ ችግር መስፋፋት ጋር የተጣጣመ በአደረጃጀት፣ በሰው ሀይል፣ በሎጂስቲክስ የተጠናቀረ መዋቅር በክልሎች ያለመኖር ዋና ዋና ተግዳሮቶች ናቸው።

**በእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት፡** የዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት፣የፈሳሽ ናይትሮጂን አምራች ማሽኖች፣ የዶሮ ማባዣ ማዕከላት፣ ላብራቶሪዎች፤ የዶሮ ዝርያ አማራጮች አለመኖርና የቅድመ መስራች የዶሮ ዝርያ ማዕከል በሀገራችን ባለመኖሩ፤ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ አነስተኛ መሆን፤ የእንስሳት መኖ ዋጋ በየጊዜዉ እየጨመረ መምጣቱ፤ የወተት ላም ዝርያ ማባዣ ማዕከላት በበቂ አለመኖር ዋና ዋና ተግዳሮቶች ናቸው።

**በተፈጥሮ ሀብት ልማት፡** የመሬት አሲዳማነት ለመከላከል በቂ የኖራ አቅርቦት አለመኖር፤ ለመስኖ አውታር ግንባታ የግንባታ ግብዓት አቅርቦት እጥረትና የዋጋ መናር ፤ ነባር የስነ-አካላዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች ጥገና፣ እድሳት እና ደረጃ ማሳደግ ተግባራት ላይ በክልሎች በኩል ትኩረት ማነስ፣ የተሻሻለው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ረቂቅ አዋጅ በሚኒስትሮች ም/ቤት ታይቶ አለመፅደቅ ዋና ዋና ተግዳሮቶች ናቸው።

**በግብርና ኢንቨስትመንትና ግብርና ግብይት፡** የማዳበሪያ የመግዣ ዋጋዉ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ መምጣቱ የመጣ፤ የአርሶ አደር ምርጥ ዘር ፍላጎትና አቅርቦት አለመቀራረብ፤ ለግብርና ኢንቨስትመንት የመሬት አቅርቦት አሰጣጥ በፌደራልና ክልሎች ግልፅ የአሰራር ስርዓት አለመኖር፤ የአበባ እርሻዎች በየአመቱ በጎርፍ መጠቃትና የመሰረተ ልማት በሚፈለገዉ ደረጃ አለመሟላት (የመብራት ፤ ውሃና መንገድ)፤ በግብርና ግብይት እና በሜካናይዜሽን ላይ የፋይናንስ አቅርቦት ችግር ዋና ዋና ተግዳሮቶች ናቸው።

## III. የመካከለኛ ዘመን (2016-2018) የልማት ዕቅድ እንድምታዎች እና የሚጠበቁ ውጤቶች

### ርዕይ

በ2022 የተሸጋገረ ግብርና በመፍጠር በውስጣዊ ሽግግር ግብርናን ምርታማና ተወዳዳሪ በማድረግ የአርሶና አርብቶ አደሩን ገቢ ማሳደግና ከድህነት ማላቀቅ፤ ለሀገራዊ ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ደግሞ ሀገራዊ ምግብና ስርዓተ ምግብ ፍልጎት ያሟላ፣ ለኢንዱስትሪ ግብዓትና ለወጪ ንግድ በቂ ምርት ያቀረብ ፣ ወደ እሴት ጭመራ የተራመደ እና በገጠር በቂ ስራ እድል የፈጠረ ዘርፍ ማድረግ ይሆናል።

### ግብርና ለሀገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት የሚኖረው አስተዋፅኦ

የግብርና ዘርፍ ዕቅድ ግብ ከሀገራዊ ኢኮኖሚው አስተዋፅኦ ማበርከት ሲሆን በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት ግብርናን ምርታማና ተወዳዳሪ በማድረግ አማካይ ዓመታዊ የግብርናን አጠቃላይ ሀገራዊ ምርት 6 በመቶ በማሳደግ የአርሶና አርብቶ አደሩን ገቢ ማሳደግ፣ የምግብና ስርዓተ ምግብ ዋስትና ማረጋገጥ እና ለመዋቅራዊ ሽግግር አስተዋፅኦ ማድረግ ሲሆን ለሀገራዊ ኢኮኖሚያዊ ትራንስፎርሜሽን በሚከተሉት መስኮች ላይ የራሱን አስተዋፅኦ ያበረክታል። ግብርና ለጠቅላላ ምርት ያለው አስተዋፅኦ፣ አነስተኛ መጠን የተሰባጠረ የምግብ ምድቦችን መመገብ የቻሉ የአርሶ/አርበቶ አደሮች ቁጥር ማሳደግ፣ የምርት ስብጥር ደረጃ ማሻሻል፣ የግብርና ምርት የወጪና ገቢ ምርት ሚዛን ማሻሻል፣ የግብርና-ኢንዱስትሪ ትስስር ማጠናከር፣ በግብርና የሚተዳደር የህብረተሰብ ክፍል እየቀነሰ እንዲሄድ ማስቻል፣ ከግብርና ልማት የሚለቀቀውን የሙቀት አማቂ ጋዝ መጠን መቀነስ ናቸው።

## IV. የመካከለኛ ዘመን (2016-2018) ስትራቴጅክ ዓላማዎች ቁልፍ የውጤት መስኮችና ዒላማዎች

### የእቅዱ መነሻ

### የግብርና ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት

ለሶስት ዓመት መካከለኛ ዘመን ዕቅድ እንደ አንድ መነሻ የተወሰደ ሲሆን በሚከተሉት ዋና ጉዳየች ላይ ያተኩራል። የሰብል፣ እንስሳትና ዓሳ ምርታማነትን ማሻሻል፣ የተፈጥሮ ሀብት በዘላቂነት እንዲለማና ጥቅም ላይ እንዲውል እና ጥምር ግብርና ማስፋፋት፣ የግብርና ቴክኖሎጂ አቅርቦትና ስርጭት ስርዓትን ማሻሻል፣ የግብርና ምርት ጥራት ቁጥጥር፣ የገበያ ትስስር፣ የምግብና ስርዓተ ምግብ ዋስትና፣ የከተማ ግብርና እና የገጠር ስራ ዕድል ፈጠራ ያካትታል።

### የማክሮ ኢኮኖሚክ ማዕቀፍ

ግብርና ዘርፍ በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት የሚኖሩትን ስትራቴጅክ ምሰሶዎችንና የትኩረት መስኮችን በዝርዝር ያስቀመጠ ሲሆን በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት የዘርፉን አማካይ እድገት 6 በመቶ በማድረስ ከጠቅላላ ምርት ያለውን ድርሻ እየቀነሰ እንደሚሄድ ተቀምጧል። የሌሎች ዘርፎች የምርት ፍላጎት ግምት ውስጥ ገብቷል። አህጉራዊ ማዕቀፎች በአጀንዳ 2063 የበለጸገች አፍሪካ የማየት ርዕይ፣ በአጠቃላይ የአፍሪካ ግብርና ልማት ፕሮግራም ማዕቀፍ የተደረሱ ስምምነቶች ማለትም ግብርና ዋናው የእድገት አምጭ መሆኑ፣ እ.ኤ.አ በ2025 አካታች የግብርና ልማት በማከሄድ ድህነትን በግማሽ የመቀነስ፣ ለዚሁም

በየዓመቱ ለግብርና ዘርፍ ከ10 በመቶ በላይ በጀት መመደብ እንዲሁም ከ6 በመቶ በላይ እድገት ማስመዘገብ ወዘተ እንደመነሻ ተወስዷል፡፡ በተጨማሪም የአጀንዳ 2030 ዘላቂ የልማት ግቦች (SDG) በታሳቢነት ተወስዷል፡፡

### ያለፉት ሶስት ዓመታት አፈፃፀም

ያለፉት ሶስት ዓመታት የአፈፃፀም ግምገማ የተለዩ መሰረታዊ ማነቆዎችና መልካም ተሞክሮዎች ለመካከለኛ ዘመን ዕቅድ እንደመነሻ ተወስደው ማነቆዎችን ሊፈቱ የሚችሉ የፖሊሲ ሪፎርም አጀንዳዎች፣ ፕሮግራሞችና ሀገራዊ ኢንሼቲቮች በዕቅዱ ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

### ስትራቴጂክ አቅጣጫዎች

**የመስኖ አቅምን በማጎልበት የግብርናን ዘርፍ ከዝናብ ጥገኝነት ማላቀቅ፡-** የሀገራችን ምርት በዝናብ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ምክንያት ለምርታማነት ዝቅተኛነት የተጋለጠ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከዓመት ዓመት የምርት መጠን ከዝናብ መጠን መለያየት ጋር ታያይዞ ከፍተኛ ልዩነቶች ይታዩበታል፡፡ ይህ አካሄድ የሚጠበቀውን የግብርና ትራንፎርሜሽን ለማምጣት በቂ ስላልሆነ መንግስት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የመስኖ ልማት ላይ ኢንቨስትመንት ማድረግ አለበት፡፡ ይህም ያሉንን የምርት ወቅቶች ከ3 እና 4 ጊዜ በማድረስ የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ በላይ ለኢንዱስትሪና ለወጪ ንግድ በቂ ምርት ከማቅረብ አኳያ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያመጣል፡፡ የምንከተለው የመስኖ ልማት አካሄድ በሁለት ይከፈላል፤ ይህም የአነስተኛ መስኖ ልማትና መካከለኛና ትላልቅ መስኖ ልማት ሲሆን የምንተገብረውም ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ይሆናል፡፡ የመስኖ ልማት ስራችን በተለያዩ ተዋንያኖች የሚፈፀምበትን ሁኔታ በማመቻቸት ለምሳሌ በመንግስት፣ በልማት አጋሮች፣ በግሉ ዘርፍ እንደዚሁም በማህበረሰብ ተሳትፎ የሚሰራ መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡ የመስኖ ኢንቨስትመንት ቅደም ተከተል በሚሰጡት ጥቅምና በመረጃ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በመስኖ ስራ ላይ ትኩረት መስጠት በቤተሰብ ደረጃ የውሃን ተደራሽነት ከማረጋገጥ ባሻገር ተያያዥ ለሆኑ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች መጎልበት የራሱን አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

**የሜካናይዜሽን አገልግሎትን ማስፋፋት፡-** የሜካናይዜሽን አገልግሎት ማስፋፋት ግብርናን ለማዘመንና የምርት ጥራትን ለማረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ለሀገራችን መልከዓ ምድርና አግሮ ኢኮሎጂ ተስማሚ የሆኑ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀምና ተደራሽነትን ለአርሶ/አርብቶ አደር በማረጋገጥና አጠቃቀም ላይ የተመሰረተና የአርሶአደሩን አቅም ያገናዘበ ሀገር-በቀል የሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎች ፈጠራ፣ ማኑፋክቸሪንግና ስርጭት ስርዓት በማስፋፋት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የአርሶአደሩን ገቢ ትርጉም ባለው መልኩ ማሳደግ ይቻላል፡፡ ዘርፉ የሚጠቀማቸውን ማናቸውም የቴክኖሎጂ ግብዓትና ማሽነሪዎች ከግብር ነጻ በማድረግና የሊዝ ፋይናንሲንግ የብድር ስርዓት በመገንባት ግብርናን ለማዘመን ትኩረት ተሰጥቷል፡፡ በዚህም የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለመቋቋም ከፍተኛ ዕገዛ ይኖረዋል፡፡ ምርታማነትና የምርት ጥራት በማሻሻል እንዲሁም አዳዲስ የስራ እድል በመፍጠር ወጣቱን ትውልድ ወደ ግብርና መሳብ ያስችላል፡፡ የሜካናይዜሽን አገልግሎት ዋና ምሶሶ የግሉ ዘርፍ መሆኑ ቢታወቅም የግብርና ዘርፍ ከአጋሮቹ ጋር በመሆን የቁጥጥርና ፍተሻ እንዲሁም ክትትል ስራዎችን

ይሰራል። የግሉን ዘርፍ ለማሳተፍ በሚደረገው ሽግግር መንግስት የተለያዩ የማበረታቻ ስልቶች ይጠቀማል።

**አሲዳማ መሬቶችን ወደ ምርት ማስገባት፡** ጠቅላላ በሰብል ከሚለማው መሬት ውስጥ 4 ሚሊየን ሄ/ር በአሲዳማነት የተጠቃ ሲሆን በሶስት ዓመት ለማሳካት የታቀደው ምርትና ምርታማነት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ የሚያሳድር በመሆኑ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት በትኩረት የሚሰራ ይሆናል።

**በከፍተኛ ምርታማነታቸው የሚታወቁ አነስተኛ አርሶ አደሮችን** ቀስ በቀስ ወደ ኢንቨስትመንት እንዲገቡ ማድረግ፦ የኢትዮጵያን እርሻ ለማዘመን በሚደረገው ጥረት እንደ ዋና ተግዳሮቶች ከሚታዩት መካከል የአርሶ አደሮች የመሬት ይዞታ እጅግ አነስተኛ፣ የተበጣጠሰና በተለያዩ ቦታዎች ተበታትነው የሚገኙ መሆናቸው ነው። በዚህ ሁኔታ አርሶ አደሮች የእርሻ ሜካናይዜሽንንና ሌሎች የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም አዋጭ ካለመሆኑም በላይ የድህረ-ምርት ማሰባሰብና ጥራት ቁጥጥር ስራዎችን ለመስራትም አዳጋች አድርጎታል። ይህንን ችግር በዘላቂነት ለመፍታትና ዘርፉን ለማዘመን አርሶ አደሮች በመሬታቸው የመጠቀም መብትን በማይነካ ሁኔታና አሰራሩ አዋጭ በሆነባቸው አካባቢዎች ኩታ-ገጠም መሬቶችን አንድ ላይ በማሰባሰብ (Land Consolidation) የኩታ-ገጠም ይዞታ አሠራር ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል። በመሆኑም በረቂቅ የመሬት አጠቃቀም አዋጁ ላይ የተጠቀሱትን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የገጠር መሬት የኩታ-ገጠም ይዞታ አሠራርን የማሻሻል ስራ በስፋት ይሰራል። በተጨማሪም የአነስተኛ አርሶአዳሮችን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ በቀጣይ አስር ዓመታት የኮንትራት እርሻ አሰራር ትኩረት የሚሰጥ ይሆናል።

**ከእንስሳት ሃብት ልማቱን ማዘመን፦** የእንስሳት ሃብት ልማትን መደገፍ የአረባብ ስርዓትን ከማሻሻልና ገበያ መር ከማድረግ ይጀምራል። በተጨማሪም በእንስሳት ጤና አገልግሎት ውስጥ የግሉን ዘርፍ ሚና ማሳደግ፣ የመኖ ምርትን ማስፋፋትና የግብይት ማዕከላትን ማጠናከር ዋና ዋና ትኩረት የሚደረግባቸው ጉዳዮች ናቸው። የወጪ ንግድ አፈፃፀምን ከማሻሻል አኳያ የኳራንቲን ማዕከላትን አጠናክሮ ወደ ስራ ማስገባትና ሌሎች ከግብይት ጋር የተያያዙ መሰረተ ልማቶችን በመንግስት-ግል ዘርፍ ሽርክና ማሟላት ትኩረት ሊደረግባቸው ይገባል። የወጪ ንግዳችንን የሚያነቃቁና ወደ አዳዲስ ገበያዎች እንድንገባ የሚያደርጉ ዘመናዊ የምርት ዱካ ስርዓት መተግበር ፣ የፋይናንስና ኢንሹራንስ ስርዓቶችን ማሻሻል፣ የአርብቶ አደር አከባቢዎችን እንደ FMD ካሉ ከበሽታዎች የፀዱ ማድረግና ህገወጥ ንግድን ትርጉም ባለው መልኩ መቆጣጠር በሰፊው ሊሰራባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው። ከዚህ ጋር ተያይዞ የእሴት ጭመራን ለማቀላጠፍ በኤክስፖርት ቄራዎችና በአርቢዎች መካከል ቀጥታ የምርት-ግብዓት ግንኙነቶችን ማዳበር ትኩረት ሊደረግበት ይገባል።

**ሆርቲካልቸር ልማት ማስፋፋት፦** የሆርቲካልቸር ልማት ዋና ምሰሶዎች የሚሆኑት በክላስተር የተደራጁ አነስተኛ አርሶ አደሮችና ትላልቅ የግል አምራቾች ይሆናሉ ተብለው ይጠበቃል። በዘርፉ የምርት ስፔሺያላይዜሽን ቢበረታታም የሀገር ውስጥ ፍላጎትን መሰረት ያደረገና የዋጋ ግሽበትን የሚያረጋጋ ስትራቴጂ የምንከተል ይሆናል። ለምሳሌ የአቮካዶ የወጪ ንግድ፣ የፍራፍሬ ምርቶች ወደ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ አበባ ምርት ኤክስፖርት ማስፋፋት። የሆርቲካልቸር ዋና ስትራቴጂ የሚሆነው ግብዓት

አቅርቦት ስርዓቱን ማዘመን ነው፤ ይህም ማለት ገበያ ተኮር የሆነና የገበያውን ፍላጎት የሚያሟሉና ከፍተኛ ምርታማነት ያላቸው ዝርያዎችን ማፍለቅና ማስራጨት፣ የግሉ ዘርፍ ተሳታፊነቱን አሁን ካለበት ማስፋፋትና ተመሳሳይ ስራዎችን ያጠቃልላል። የዘመናዊ ነርሰሪ ልማት ስትራቴጂያዊ በሆኑ ቦታዎች ላይ ማጠናከር፣ የግብይት ማዕከላትን ለአርሶ አደሩ ቅርበት ባለባቸው አከባቢዎች ማደራጀት፣ የኮልድ ቼይን መሰረተ ልማት ከግሉ ዘርፍ ጋር በመሆን ማመቻቸት ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል። የገበያ ትስስርን በተመለከተ በትላልቅ የሆርቲካልቸር ምርት ሰብሳቢዎችና በአርሶአደሮች መካከል ቅርበት ፈጥሮ የሀገር ውስጥ የዋጋ ግሽበትን ለመከላከል የሚያመቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፣ በሌላ በኩል የኤክስፖርት ገበያዎች ወስጥ ያለንን ድርሻ ማጠናከር በሰፊው ይሰራባቸዋል።

**በግብርና ልማት የባለሀብቱን ተሳትፎ ማሳደግ፦** ባለሃብቱ በዘርፉ ላይ ያለውን ተሳትፎ ለማሳደግ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል። ይህም በምርምር፣ በኤክስቴንሽን፣ በፋይናንስና ኢንሹራንስ አቅርቦት፣ በግብዓት አቅርቦት፣ በግብርና ምርት፣ በግብይት መሰረተ ልማት ላይ የተሻሉ ድጋፍና ማበረታቻዎችን በመስጠት ዘርፉ ውስጥ መሰረታዊ ለውጥ ማምጣት ይቻላል። ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ መንግስት ከሀገር በቀልና አለማቀፍ ባለሃብቶች ጋር በጥምረት የሚሰራ ይሆናል። በተጨማሪም ባለሃብቱን የእሴት ጭመራ ስራዎች ላይ ለማሳተፍ በተለይም አግሮ ኢንዱስትሪዎችን መሰረት ያደረገ የእሴት ሰንሰለት ማጠናከር ስራ የሚሰራ ይሆናል።

**የግብርና ግብይት ስርዓትን ማሻሻል፡** አሁን የሚታየውን የተዛባ የግብርና ግብይት ስርዓት በማሻሻልና አርሶ አደሩ ከገበያ ጋር እንዲተሳሰር በማድረግ አምራቹ ዋጋ ወሳጅ (Price Taker) ሳይሆን ዋጋ ወሳኝ (Price Maker) እንዲሆን ለማድረግ ይሰራል።

**የግብርና ኤክስቴንሽን ስርዓቱን ማሻሻል፡** አሁን ያለውን የግብርና ኤክስቴንሽን አሰራር አርስ አደሩ የገበያን ፍላጎት መሰረት በማድረግ ማምረት እንዲችል፣ የስርዓት ምግብ ችግሮችን ሊፈቱ የሚችሉ ምርቶች ላይ ትኩረት አድርጎ እንዲሰራ የሚቃኝ ይሆናል።

**ተቋማዊ የማስፈፀም አቅምን መገንባት፦** የ10 ዓመቱን እቅድ ለማሳካት ዋናው መሰረት የዘርፉን የማስፈፀም አቅምና ክህሎት ማሳደግ የግድ ይላል። በዚህም ረገድ በፌደራል ግብርና ሚኒስቴር ደረጃ ስር-ነቀል የሰው ሃብት ሪፎርም እየተሰራ ይገኛል። ይህ ስራ የአገልግሎት ጥራትና ጊዜን የሚያፋጥን ሲሆን የወሳኔ አሰጣጥን የሚያቀላጥፍ ነው። በክልል፤ በዞንና በወረዳ የኤች አይቪ ኤድስ ባለሙያ እንዲመድቡ ማድረግ በ2030 ሀገራችን የያዘችውን አዲስ በኤች አይቪ መያዝ ዜሮ የማድረግ እቅድ ለማሳካት ይረዳል። ይህ ጅማሮ በክልል በዞንና በወረዳ መውረድ እንዳለበት ሲታመን፣ የተቋማዊ መስተጋብር ጎን ለጎን መቀናጀት አለበት። እነዚህም የቅንጅት ስራዎች አብሮ በማቀድ፣ አብሮ ችግሮችን በመፍታት፣ ተደጋጋሚ ግንኙነቶችን በማድረግ፣ ሀገራዊ የሆነ የስራ ድግግሞሽን ፣ የሃብት አጠቃቀም ጉድለትን የሚቀንስ ሲሆን እንደዚሁም ያለውን የቴክኒክ አቅም በሀገር ደረጃ እንድንጠቀምበት ያደርጋል።

**የሥራ ዕድል መፍጠር፦** በገጠር የሚኖሩ ስራ ፈላጊ ዜጎች ፍትሃዊ፣ ዘላቂና ውጤታማ የስራ እድል ተፈጥሮላቸው የልማቱ ተሳታፊ እና ተጠቃሚ በማድረግ ለሃገር እድገት እና ትራንስፎርሜሽን

የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል። በተለይም የተማረ አርሶና አርብቶ አደር ለመፍጠር እንዲያግዝ በትኩረት የሚሰራ ሲሆን በሜካናይዜሽን አገልግሎትና በመጀመሪያ ደረጃ እሴት ጭመራ ስራዎች ላይ ወጣት የተማረ የግብርና አግልግሎት ሰጪዎችን በመፍጠር የተሻገረ ግብርና እውን ለማደረግ አስተዋፆ ይኖረዋል።

**ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ዘላቂ ግብርና ልማት ማካሄድ፡** የግብርና ምርት በአማካይ በዓመት 6 በመቶ እያደገ የኤክስፖርት ምርቶችን በበቂ በማቅረብ የግብርና ምርት የወጪና ገቢ ምርት ሚዛን ያሻሽላል፣ ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን ግብዓት ያሟላል፤ ሀገራዊ የምግብ ፍጆታ ክፍተትን ያሟላል። የምርት ስብጥር ደረጃ በማሻሻል አርሶ/አርበቶ አደሮች አነስተኛ መጠን የተሰባጠረ የምግብ ምድቦችን መመገብ እንዲችሉ ያደርጋል። የግብርና ልማትን ዘላቂነት በማረጋገጥ ከግብርና ልማት የሚወጣውን የሙቀት አማቂ ጋዝ መጠን መቀነስ ይሆናል።

## 3.1. የሰብልና ሆርቲካልቸር ምርታማነት ማሻሻል

### 3.1.1. የሰብል ልማት

### የአነስተኛ ይዞታ መኸር እህል የሰብል ልማት

የሰብል ልማት በሀገራችን ግብርና ልማት ዘርፍ የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ፣ የኤክስፖርት ግኝታችን ለማሳደግና የኢንዱስትሪ ግብዓት ፍላጎትን ለማሟላት ካለው ጉልህ ሚና አንፃር ከ2016 እስከ 2018 ባሉት የመካከለኛ ዘመን እቅድ ዓመታት በተገቢው ትኩረት የሚፈፀም ይሆናል። በመካከለኛ ዘመን እቅድ በአነስተኛ አርሶ አደር በመኸር ወቅት የሚለማውን የአዝዕርት ሰብሎች በ2015 በጀት አመት 14,034.42 ሺህ ሄ/ር ከነበረበት በመሬት በ2018 ወደ 18,306.89 ሺህ ሄ/ር ፤ አጠቃላይ ምርቱን በ2015 ምርት ዘመን ከነበረበት 393,298.93 ሺህ ኩ/ል ወደ 574,470.33 ሺህ ኩ/ል (46 ፐርሰንት በላይ በማሳደግ) ለማድረስ ታቅዷል። ከዚህም ውስጥ በአገዳና ብዕር ሰብል 11,037.98 ሺህ ሄ/ር ከነበረበት በ2018 ወደ 13,509.84 ሺህ ሄ/ር ፣ ምርቱን ከነበረበት 348,710.24 ሺህ ኩ/ል በ2018 498,088.30 ሺህ ኩ/ል፣ የጥራጥሬ ሰብል 2,026.01 ሺህ ሄ/ር ከነበረበት በ2018 ወደ 2,177.42 ሺህ ሄ/ር እና ምርቱን በመነሻዉ ዓመት ከነበረበት 36,604.26 ሺህ ኩ/ል ወደ 36,849.36 ሺህ ኩ/ል ማድረስ፣ በቅባት ሰብሎች በ2015 በጀት አመት ከተደረሰበት 970.43 ሺህ ሄ/ር መሬት በ2018 ወደ 2,619.63 ሺህ ሄ/ር እንዲሁም ምርቱን በመነሻዉ ዓመት ከተገኘው 7,984.43 ሺህ ኩ/ል ወደ 39,532.68 ሺህ ኩ/ል ለማድረስ ታቅዷል። ከላይ የጠቀመጡትን እቅዶች ለማሳካት የተለያዩ ፕሮጀክቶችንና ፕሮግራሞችን እንዲሁም ልዩ ልዩ ኢኒሼቲቮችን በመቅረፅና በሀገር ደረጃ ልዩ ትኩረት የተሰጣቸውን እና የተለዩ የሰብል ምርቶች ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠትና የተጠናከረ የሰብል ኤክስቴንሽን ድጋፍ፤ ስልጠና እና ድጋፍ እንዲሁም ከዚህ በፊት የነበሩ ምርጥና መልካ ተሞክሮዎችን አጠናክሮ በማስቀጠልና በማስፋት እቅዶችን ለማሳካት ታሳቢ ተደርጓል።

ላላ ዜና ሀ/ወልድ
የስትራተጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

## የሰፋፊ እርሻ መኸር እህል ሰብል ልማት

በመካከለኛ ዘመን እቅድ በሰፋፊ እርሻ በመኸር የአዝዕርት ሰብሎች በ2015 በጀት አመት 774.53 ሺህ ሄ/ር ከተደረሰበት በመሬት በ2018 ወደ 1,921.18 ሺህ ሄ/ር (በ148 በመቶኛ ጭማሪ ) ለማድረስ የታቀደ ሲሆን ከዚህ በፊት ወደ ልማት ያልገቡ ሰፋፊ መሬት በተለይም በቆላማ አካባቢዎች ያለሙ መሬቶችን በስፋት ወደልማት ለማስገባት ትኩረት በማድረግ የታቀደ ሲሆን ፣አጠቃላይ ምርቱን በመነሻዉ ዓመት ከነበረበት 21,583.65 ሄ/ር ኩ/ል ወደ 59,592.44 ሺህ ኩ/ል ለማድረስ ፣በብርዕና አገዳ ሰብሎች በ2015 በጀት አመት ከነበረበት 291.90 ሺህ ሄ/ር መሬት በ2018 ወደ 547.19 ሺህ ሄ/ር (87 በመቶኛ ጭማሪ ) እና ምርቱን በመነሻዉ ዓመት ከነበረበት 11,715.57 ሺህ ኩ/ል ወደ 28,181.90 ሺህ ኩ/ል ፤ በቅባት ሰብሎች በ2015 በጀት አመት 482.63 ሺህ ሄ/ር ከተደረሰበት በ2018 ወደ 1,373.99 ሺህ ሄ/ር (185 በመቶኛ ጭማሪ) ለማድረስ እና ምርቱንም በመነሻዉ ዓመት ከነበረበት 9,868.08 ሺህ ኩ/ል ወደ 31,410.54 ሺህ ኩ/ል (218 በመቶኛ ጭማሪ) ለማድረስ የታቀደ ሲሆን ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስፈልጉ ቴክኖሎጅዎችና አሰራሮች በተሻለ ሁኔታ ይጠቀማሉ ተብሎ ታሳቢ ተደርጓል።

## የአነስተኛ ይዞታ የበልግ እህል የሰብል ልማት

በአነስተኛ እርሻ በበልግ የሰብል ልማት በመካከለኛ ዘመን እቅድ በ2015 በጀት አመት 2,700.75 ሺህ ሄ/ር የመሬት ሽፋን የተደረሰ ቢሆንም የበልግ ዝናብ የሚያገኙ አካባቢዎች ውስን ስለሆኑና አሁን እያጋጠመ ካለው የአየር ንብረት ተፅዕኖ አኳያ በ2018 ከዚህ በፊት የተደረሰበትን 2,700.75 ሺህ ሄ/ር መሬት እንዳለ እንዲለማ በማድረግ በ2015 ከነበረው 48,052 ሺህ ኩ/ል በ2018 በጀት አመት ከዚህ በፊት ያለውን ምርታማነትን የሚያሳድጉ የግብዓትናቴክኖሎጅ አጠቃቀምና አሰራር በማሻሻልና እንዲተገበር በማድረግ ምርታማነትን በማሳደግ በጥቅሉ 63,710.35 ሺህ ኩ/ል (33 ፐርሰንት በማሳደግ) ምርት ለማምረት ታቅዷል። በዝርዝር ሲታይ በአገዳና ብርዕ ሰብሎች ከነበረበት 40,812 ሺህ ኩ/ል ምርት በ2018 በጀት አመት 56,247.9 ሺህ ኩ/ል፣ በጥራጥሬ ሰብሎች 6,805 ሺህ ኩ/ል ከነበረበት ምርት በ2018 ወደ 6,957.11 ሺህ ኩ/ል፣ የቅባት ሰብሎች ምርት በ2015 በጀት አመት ከተደረሰበት 435 ሺህ ኩ/ል በ2018 ወደ 504.74 ሺህ ኩ/ል ምርት (16 በመቶኛ) ለማድረስ ታቅዷል።

## በመስኖ የስንዴ ልማት

በመስኖ ስንዴ መካከለኛ ዘመን እቅድ የአዝዕርት ሰብሎች በአነስተኛ አርሶ አደሮችና ሰፋፊ እርሻ መስኖ ልማት በ2015 በጀት አመት ከተደረሰበት 1,374 ሺህ ሄ/ር የመሬት ሽፍን በ2018 ከዚህ በፊት ወደ ልማት ያልገቡ መሬቶችን እና ከዚህ በፊት እየለማ ያለውን መሬት የሰብል አመራረት ስርዓትን በመከተል በማሰቀጠል ወደ 3,307.50 ሺህ ሄ/ር (141 ፐርሰንት) በማሳደግ አጠቃላይ ምርቱን በመነሻዉ ዓመት ከነበረበት 52,130 ሺህ ኩ/ል ወደ 137,592 ሺህ ኩ/ል (160 ፐርሰነት) ምርት ለማድረስ የታቀደ ሲሆን መንግስት ከሰጠው ልዩ ትኩረት አኳያ የመስኖ ስንዴን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ እና የታቀደውን እቅድ ለማሳካት ሀገራዊ የስንዴ ፕሮጀክትና ፕሮግራም በመንደፍ ወደ ስራ እንደሚገባ ታሳቢ ተወስዶ ታቅዷል።

### 3.1.2. የጥጥ ልማት

የአነስተኛ አርሶ አደር በመኸር ጥጥ ልማት

በመካከለኛ ዘመን የሶስት ዓመት እቅድ በአነስተኛ አርሶ አደር በመኸር ጥጥ በ2015 በጀት አመት 24.85 ሺ.ህ ሄ/ር ከተደረሰበት የመሬት ሽፋን በ2018 ወደ 51.79 ሺ.ህ ሄ/ር (108 ፐርሰነት ጭማሪ) አጠቃላይ ምርቱን በመነሻዉ ዓመት ከነበረበት 341 ሺ.ህ ኩ/ል ወደ 932.20 ሺ.ህ ኩ/ል ለማድረስ (173 ፐርሰነት ጭማሪ) ለማድረስ የተሻሻሉ ቴክሎጅዎችን፣አሰራሮችና የተጠናከረ ኤክስቴሽን ድጋፍ በማድረግ የተያዘውን ግብ ለማሳካት ታቅዷል።

የሰፋፊ እርሻ በመኸር ጥጥ ልማት

በመካከለኛ ዘመን እቅድ በሰፋፊ እርሻ በመኸር ጥጥ ልማት በ2015 በጀት አመት 24.65 ሺ.ህ ሄ/ር ከነበረበት የመሬት ሽፋን በ2018 ወደ 89.63 ሺ.ህ ሄ/ር (264 ፐርሰነት) በማሳደግ አጠቃላይ ምርቱን በመነሻዉ ዓመት ከነበረበት 397 ሺ.ህ ኩ/ል ወደ 1,703 ሺ.ህ ኩ/ል) ለማድረስ (329 ፐርሰንት እድገት) ታቅዷል።

**የአነስተኛ አርሶ አደርና የሰፋፊ እርሻ በመስኖ ጥጥ ልማት**

በመካከለኛ ዘመን እቅድ የአነስተኛ አርሶ አደርና የሰፋፊ እርሻ በመስኖ ጥጥ በ2015 በጀት አመት 12.35 ሺ.ህ ሄ/ር ከነበረበት የመሬት ሽፋን በ2018 ወደ 37.75 ሺ.ህ ሄ/ር ሽፋን (200 በመቶኛ) ለማሳደግና በአጠቃላይ ምርቱን በመነሻዉ ዓመት ከነበረበት 325 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት ወደ 1,246.80 ሺ.ህ ኩ/ል (284 በመቶኛ) ለማድረስ ታቅዷል።

### 3.1.3. የሆርቲካልቸር ሰብል ልማት

**በአነስተኛ ይዞታ መኸር የሆርቲካልቸር ሰብል ልማት**

በአነስተኛ አርሶ አደር በመኸር የአትክልት ሰብሎች የመካከለኛ ዘመን እቅድ በ2015 በጀት አመት 143.76 ሺ.ህ ሄ/ር ከተደረሰበት የመሬት ሽፋን በ2018 ወደ 147.99 ሺ.ህ ሄ/ር አጠቃላይ ምርቱን በመነሻዉ ዓመት ከነበረበት 23,524.72 ሺ.ህ ኩ/ል ወደ 26,836.85 ሺ.ህ ኩ/ል ማድረስ (14 በመቶኛ ጭማሪ)፣ የስራስር ሰብል በ2015 በጀት አመት 287.19 ሺ.ህ ሄ/ር የመሬት ሽፋን በ2018 ወደ 299.23 ሺ.ህ ሄ/ር (4 በመቶኛ ጭማሪ) አጠቃላይ ምርቱን በመነሻዉ ዓመት ከነበረበት 174,239.2 ሺ.ህ ኩ/ል ወደ 203,982.39 ሺ.ህ ኩ/ል ማድረስ (17 በመቶኛ ጭማሪ)፣ በፍራፍሬ ሰብሎች በ2015 በጀት አመት 272 ሺ.ህ ሄ/ር ከነበረበት በመሬት በ2018 ወደ 280.74 ሺ.ህ ሄ/ር አጠቃላይ ምርቱን በመነሻዉ ዓመት ከነበረበት 32,463 ሺ. ኩ/ል ወደ 37,145.88 ሺ.ህ ኩ/ል ለማድረስ ታቅዷል።

**በሰፋፊ እርሻ መኸር የሆርቲካልቸር ሰብል ልማት**

በመካከለኛ ዘመን እቅድ በሰፋፊ እርሻ በመኸር የአትክልት ሰብሎች በ2015 በጀት አመት ከተደረሰበት 3.20 ሺ.ህ ሄ/ር መሬት ሽፋን በ2018 ወደ 3.80 ሺ.ህ ሄ/ር (18 በመቶኛ ጭማሪ) በአጠቃላይ ምርቱን በመነሻዉ ዓመት ከተገኘው 1,077.30 ሺ.ህ ኩ/ል በ14 ፐርሰነት በማሳደግ ወደ 1,226.07 ሺ.ህ ኩ/ል ለማድረስ፣ በፍራፍሬ ሰብሎች በ2015 በጀት አመት 6.60 ሺ.ህ ሄ/ር ከነበረበት የመሬት ሽፋን በ2018 ወደ 8.35 ሺ.ህ ሄ/ር (27 በመቶኛ ጭማሪ) አጠቃላይ የፍራፍሬ ምርቱን በመነሻዉ ዓመት 2015 ከነበረበት 728.20 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት ወደ በ 40 በመቶኛ ምርት ጭማሪ በማምጣት 984.05 ሺ.ህ ኩ/ል ለማምረት ታቅዷል።

**በአነስተኛ ይዞታ የበልግ የሆርቲካልቸር ሰብል ልማት**

በመካከለኛ ዘመን እቅድ በአነስተኛ አርሶ አደር በበልግ የአትክልት ሰብሎች ልማት በ2015 በጀት አመት ከነበረበት 119.69 ሺህ ሄ/ር የመሬት ሽፋን በ2018 ወደ 120.84 ሺህ ሄ/ር ለማድረስና አጠቃላይ የአትክልት ምርቱን በመነሻዉ ዓመት ከነበረበት 10,078 ሺህ ኩ/ል ወደ 11,892.07 ሺህ ኩ/ል ለማድረስ ታቅዷል። በበልግ ስራስር ሰብሎች በ2015 በጀት አመት 285.94 ሺህ ሄ/ር ከነበረበት መሬት ሽፋን በ2018 ወደ 287.66 ሺህ ሄ/ር ለማድረስና አጠቃላይ ምርቱን በመነሻዉ ዓመት ከተገኘው 44320.70 ሺህ ኩ/ል ወደ 56630.56 ሺህ ኩ/ል ለማድረስ የታቀደ ሲሆን የበልግ ዝናብ በሀገራችን የተወሰኑ አካባቢዎች ውስን ስለሆነ በመካከለኛ ዘመኑ እቅድ ሰፊ ለውጥ የማይኖረው ሲሆን የተለያዩ ምርትን የሚያሳድጉ ግብዓቶች እና አሰራሮችን እዲተገበሩ በማድረግ በተወሰነ መጠን ምርቱን ለመጨመር ታቅዷል።

**በመስኖ የሆርቲካልቸር ሰብል ልማት**

በመካከለኛ ዘመን እቅዱ በመስኖ የአትክልት ሰብሎች ልማት በ2015 በጀት አመት የተደረሰበትን 250.71 ሺህ ሄ/ር የመሬት ሽፋን በ2.3 በመቶኛ ጭማሪ በማሳደግ በ2018 ወደ 309.09 ሺህ ሄ/ር ለማልማት የታቀደ ሲሆን ከዚህም አጠቃላይ ምርቱን በመነሻዉ ዓመት ከነበረበት 43,983.77 ሺህ ኩ/ል የአትክልት ምርት ወደ 50,402.30 ሺህ ኩ/ል ለማድረስ (በ15 በመቶኛ ጭማሪ) ፣ የስራስር ሰብሎች ልማት በ2015 በጀት አመት ከተደረሰበት 86.04 ሺህ ሄ/ር የመሬት ሽፋን በ2018 63 በመቶኛ ጭማሪ ወደ 140.57 ሺህ ሄ/ር የመሬት ሽፋን ለማድረስና አጠቃላይ ምርቱን በመነሻዉ ዓመት ከነበረበት 21,511.40 ሺህ ኩ/ል ወደ 24,172.01 ሺህ ኩ/ል ለማድረስ እንዲሁም በፍራፍሬ ሰብሎች በ2015 በጀት አመት 166.90 ሺህ ሄ/ር ከተደረሰበት የመሬት ሽፋን በ2018 ወደ 168.69 ሺህ ሄ/ር ለማሳደግና ምርቱንም በመነሻዉ ዓመት ከነበረበት 27,139.14 ሺህ ኩ/ል ወደ 29,794.28 ሺህ ኩ/ል ለማድረስ ታቅዷል።

**የሆርቲካልቸር ኤክስፖርት ልማት**

በመካከለኛ ዘመን የሆርቲካልቸር ኤክስፖርት እቅድ በአበባ በ2015 በጀት አመት የተደረሰበት 2.5 ሺህ ሄ/ር መሬት እንዳለ በማስቀጠል አጠቃላይ ምርቱን በመነሻዉ ዓመት ከነበረበት 112.99 ሺህ ኩ/ል ዘመናዊ ቴክኖሎጅዎችና አሰራሮች በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ ምርቱን በማሳደግ በ2018 ወደ 1,516.30 ሺህ ኩ/ል ለማድረስ፣ በፍራፍሬ ሰብሎች በ2015 በጀት አመት ከነበረበት 0.46 ሺህ ሄ/ር መሬት በ2018 ወደ 0.8 ሺህ ሄ/ር (87 በመቶኛ ጭማሪ) አጠቃላይ ምርቱን በመነሻዉ ዓመት ከነበረበት 31.60 ሺህ ኩ/ል ምርቱን እንዲጨምር የተለያዩ ስራዎች እንዲከናወኑ በማድረግ በ2018 ምርት ዘመን ወደ 512.36 ሺህ ኩ/ል ለማሳደግ እንዲሁም የአትክልት ሰብሎችን ልማት በ2015 በጀት አመት ከተደረሰበት 2.28 ሺህ ሄ/ር የመሬት ሽፋን በ2018 ወደ 4.37 ሺህ ሄ/ር (92 በመቶኛ ጭማሪ) አጠቃላይ ምርቱን በመነሻዉ ዓመት ከነበረበት 141.68 ሺህ ኩ/ል ምርት እንዲያድግ የተለያዩ ቴክሎጅዎችንና አሰራሮችን እንዲተገበሩ በማድረግ ወደ 2,239.33 ሺህ ኩ/ል ለማሳደግ ታቅዷል።

በአጠቃላይ በ2016-18 በጀት ዓመት በሰብል በየዓመቱ ከሚሸፈነው መሬት ውስጥ በየዓመቱ 817,404 ሄ/ር ከበልግ ወደ መኸር የሚዞር፣ 272,409 ሄ/ር መሬት ከመኸር በቀሪ እርጥበት በዳግም ሰብል ልማት የሚለማ እና 2,853.239 ሄ/ር ከመኸር ወደ መስኖ ልማት የሚገባ ሲሆን በድምሩ 3,943,052 ሄ/ር የሚለማ ይሆናል። ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ ምክንያቶች ወደልማት ያልገባና ሳይታረስ የቆየ 1,722,404

ሄ/ር አዲስ መሬት ወደ ልማት የሚገባ ሲሆን በአጠቃላይ በምርት ዘመኑ 5,665,456 ሄ/ር መሬት በአዲስ መልክ ወደ ልማት ይገባል ተብሎ ይጠበቃል።

### 3.1.4. በአነስተኛ ይዞታ በመኸር ቡና፣ ሻይ እና ቅመማ ቅመም

በመካከለኛ ዘመን እቅድ በአነስተኛ አርሶ አደር በመኸር ቡና በ2015 በጀት አመት 1,062 ሺ.ህ ሄ/ር ከነበረበት በመሬት በ2018 ወደ 1,225.6 ሺ.ህ ሄ/ር አጠቃላይ ምርቱን በመነሻዉ ዓመት ከነበረበት 7,614.8 ሺ.ህ ኩ/ል ወደ 10,984.27 ሺ.ህ ኩ/ል ማድረስ፣ ሻይ በ2015 በጀት አመት 3.34 ሺ.ህ ሄ/ር ከነበረበት በመሬት በ2018 ወደ 3.93 ሺ.ህ ሄ/ር አጠቃላይ ምርቱን በመነሻዉ ዓመት ከነበረበት 0.093 ሺ.ህ ኩ/ል ወደ 0.1675 ሺ.ህ ኩ/ል ማድረስ፣ በቅመማ ቅመም በ2015 በጀት አመት 443.86 ሺ.ህ ሄ/ር ከነበረበት በመሬት በ2018 ወደ 455.98 ሺ.ህ ሄ/ር አጠቃላይ ምርቱን በመነሻዉ ዓመት ከነበረበት 79.02 ሺ.ህ ኩ/ል ወደ 9,083.1 ሺ.ህ ኩ/ል ለማድረስ ታቅዷል።

**የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ምርት ጥራት ማሻሻል**

የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም የምርት ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋትና በማጠናከር፣ ጥራቱን የጠበቀ ምርት በማዘጋጀት፣ በማከማቸት፣ በማሸግና በማጓጓዝ፣ በየደረጃው የምርት ጥራት ምርመራ ማዕከላትን በማጠናከርና በማስፋፋት፣ የሰርተፊኬሽንና የብቃት ማረጋገጫ አገልግሎትን በማስፋትና በማዘመን የጥራት ግቦችን ለማሳካት ታቅዷል። የቡና ምርት ጥራት ደረጃ (1ኛና 2ኛ) ካለበት 36.2 በመቶ ወደ 50 በመቶ ማሳደግ፣ በመጠን ከነበረበት 104 ሺ.ህ ቶን ወደ 208 ሺ.ህ ቶን ማድረስ፤ የሻይና ቅመማ ቅመም ጥራት ደረጃ ማሳደግ፣

### 3.1.5. እርሻና ሆርቲካልቸር ኤክስቴንሽን

በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት የግብርና ኤክስቴንሽን ስርዓቱ ለ17,846,000 አርሶ/አርብቶ/ከፊል አርብቶ አደሮች የኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚ ያደርጋል። ከኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ተጠቃሚዎች ውስጥ 11,213,000 የሙሉ ፓኬጅ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ይሆናሉ። ከኤክስቴንሽን ተጠቃሚዎች ውስጥ አዳዲስና የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን የሚቀበልና ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚተገብሩ እንዲሁም ለሌሎች አርሶ፣ አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሮች አርአያ ሊሆኑ የሚችሉ 4,538,700 ሞዴል አርሶ/አርብቶ አደሮችን መፍጠር ላይ ትኩረት ተደርጐ ይሰራል። ከኤክስቴንሽን ተጠቃሚዎች ውስጥ በግብርና ሥራ የተሰማሩ እማወራዎችን 100%፣ ባለትዳር ሴቶች 50%፣ እንዲሁም 10 በመቶ የሚሆኑትን ወጣቶች የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በትኩረት ይሠራል።

**የአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማእከላትን አቅም ብቃት ማሳደግ**

ግብርናችንን በማዘመን ሂደት አርሶ/አርብቶ አደሮችን ወደ አነስተኛ ኮሜርሻላይዜሽን ደረጃ ለማሸጋገር ለሚደረገው ጥረት አጋዥ የሆኑ ማሰልጠኛ ማእከላት መንግስት ከተለያ ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ የሚሰሩበትን የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል። አሁን ያሉትን የአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማእከላት አደረጃጀት የተቀመጠውን መስፈርት በሚሟላት ውጤታማ ማድረግ ያስፈልጋል። በዚህም መሰረት በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት በቅድመ መሰረታዊ (pre-basic) ደረጃ የሚገኙትን 3,140 ማሰልጠኛ

ማእከላት ሙሉ በሙሉ ወደ መሠረታዊ እንዲያድጉ የሚደረግ ይሆናል። በተመሳሳይ መልኩ በመሰረታዊ (basic) ደረጃ ከሚገኙት የአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማእከላት ውስጥ 50 በመቶውን ማለትም 2,646 ወደ መካከለኛ (intermediate) ደረጃ እንዲያድጉ ይደረጋል።

## የቀበሌና ወረዳ ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን አቅም መገንባት

ከዚህ በፊት በሥርዓተ ትምህርት ልማት እና በሥልጠና አሰጣጥ ውስጥ ትኩረት ማግኘት ሲገባቸው ያላገኙ ርዕሰ ጉዳዮች ማለትም የተግባቦት፣ የማመቻቸት፣ ገበያ ትስስር፣ የእሴት ሰንሰለት ልማት፣ የውል እርሻ አቀራረብ፣ የብዙ ተዋንያን የኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የሚስማማ ግብርና፣ የስራ-እድል ፈጠራ፣ ሥርዓተ-ምግብ እና ሥርዓተ-ፆታ የመሳሰሉት ላይ በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት ለ35,100 ማለትም 50 በመቶ የቀበሌ ግብርና ባለሙያዎች እና ለ10,000 ለወረዳ ባለሙያዎች ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የአጭር ጊዜ ስልጠና እንደያገኙ ይደረጋል። በተጨማሪም በተዘጋጀው የግብርና ኮሜርሻላይዜሽንና የአርሶ አደር ምርት ክላስተር ማእቀፍ ላይ እውቀትንና ክህሎትን ሊያሳድጉ የሚችሉ ሥልጠናዎች ይሰጣሉ።

## የግብርና ልማት አካላት ግንኙነት ማጠንከር

ሁሉም ባለድርሻ አካላት የግብርና ልማቱን በተልኳቸው መሰረት በውጤታማነት እንዲያግዙ የሚያስችል በመርህ ላይ የተመሰረተ ህጋዊ ማዕቀፍና ተቋማዊ ይዘት ያለው የግንኙነት መድረክ ማደራጀት ይገባል። ስለዚህ የግብርና ልማት አጋር አካላት ግንኙነት አማካሪ ካውንስል የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ በሁሉም ደረጃ በበጀትና በሰው ኃይል የተደራጀ ራሱን የቻለ መዋቅር እንዲኖረው ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል። በዚህም መሰረት በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት በክልል ደረጃ 13፣ በዞን ደረጃ 96 እና በወረዳ ደረጃ 972 የግብርና ልማት አካላት ግንኙነት መድረክ እንዲጠናከር እና እንዲቋቋም ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል።

### 3.1.6. እጽዋት ጥበቃ

በመካከለኛው የእቅድ ዘመን በተዛማች ወራሪና መደበኛ ተባዮች የአሰሳና መከላከል ስራ በመስራት በተባይ ምክንያት የሚደርሰውን የሰብል ምርት ብክነት በ2015 ከነበረበት 15 በመቶ በ2018 ወደ 11 በመቶ ለመቀነስ ታቅዷል። መደበኛ ተባይ አሰሳና ቁጥጥር ከነበረበት 553,649 ሄ/ር በ2018 ወደ 1,180,478 ሄ/ር፣ ተዛማጅ ተባዮች አሰሳና ቁጥጥር ከነበረበት 288,342 ሄ/ር በ2018 ወደ 495,809 ሄ/ር እና የመጤ አረም አሰሳና ቁጥጥር ከነበረበት 67,320 ሄ/ር በ2018 ወደ 257,250 ሄ/ር ለማድረስ ታቅዷል።

በአጠቃላይ ከ2016-2018 የመካከለኛ ዘመን እቅድ በዕፅዋት ጥበቃ መስክ በተዛማች ወራሪ ተባዮች፣ መደበኛ ተባዮችና መጤና ወራሪ አረሞች የሚደርሰውን የምርት ብክነት ለመቀነስ 4,811,375 ሄ/ር ላይ ወቅቱን የጠበቀ አሰሳ ስራ በማካሄድ የተባይ ክስተት በሚኖርበት ወቅት ጊዜውን የጠበቀ ሳይንሳዊ በሆነ ዘዴ የመከላከል ስራ በማከናወን የሚደርስውን የምርት ብክነት በየዓመቱ በ5% ለመቀነስ ይሰራል፣ በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን የተደገፈ የተባይ ትንበያና ቅድመ-ማስጠንቀቂያ ስርዓት በመዘርጋት መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን ለአርሶ አደሮች፣ አርብቶና ከፊል አርሶ አደሮች ትንበያና ቅድመ-ማስጠንቀቂያ ይሰጣል በCABI Plantwise የተቋቋሙ የማህበረሰብ ተኮር ክሊኒኮችን የማጠናከር ስራ መስራትና ወደ ሌሎች አካባቢዎች በማስፋት (Scalling up and scaling out) ስራ በማከናወን የተባይ

ልየታ እና መከላከል ምክረ-ሀሳብ በመስጠት ለአርሶ አደሮችን፣ ለከፊን አርሶ አደሮችንና ለአርብቶ አደሮችን በቅርበት አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፤ሦስት የተዛማች ወራሪ ተባዮች በተመረጡ ስትራቴክ ቦታዎች ላይ በማቋቋም የአሰሳና መከላከል አቅምን የማሳደግ ስራ ይሰራል፤ለባለሙያዎችና ለአርሶ አደሮች የአቅም ግንባታ ስልጠና በመስጠት ያለባቸውን የክህሎትና የዕውቀት ክፍተት ለመሙላት ይሰራል፤ ተደጋጋሚ የሚደረጉ ርጭቶችን በመቀነስ በሰው፣ በእንስሳትና በአካባቢ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ርጭት አገልግሎት ሰጪዎችን (Spray service providers) በማደራጀት ትክክለኛውን የርጭት ስልትና ጊዜ በመጠቀም የተከሰተውን ተባይ የመከላከል ስራና ለወጣቶች የስራ ዕድል እንዲፈጠር በማድረግ በተባዮች ምክንያት በሰብል ምርትና ምርታማነት ላይ ሊደርስ የሚችለውን የምርት ብክነትና ብክለት ለመቀነስ የሚከናወኑ ተግባራት ናቸው፡፡ የእርሻና ሆርቲካልቸር ልማት የቀጣይ ሶስት ዓመታት ዒላማዎች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡-

**ሀ) የአዝርዕት ሰብል ልማት**

ከ2016 እስከ 2018 ባለው የመካከለኛ ዘመን እቅድ አመታት የአገዳ፣ የብርዕ፣ የጥራጥሬና የቅባት ሰብሎች ሰብልን ምርት ለማሳደግ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፡- ለየስነ-ምሕዳሩ ተስማሚ የሆኑ ምርታማ ዝርያዎችንና የቅድመ እና ድህረ ምርት ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅና ማስፋፋት ትኩረት የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡ በየስነ-ምህዳሩ ተፈላጊ የሆኑ ምርጥ ዘሮችን፣ ማዳበሪያና ኬሚካሎችን አርሶአደሩ በሚፈልገው መጠን፣ ዓይነት ጥራትና በወቅት እንዲቀርቡ በማድረግ አጠቃቀሙ እንዲያድግ ይደረጋል፣ በዋና ዋና የጤፍ አምራች ስነ-ምህዳሮችን /ስፔሻላይዝ በሚያደርጉ አካባቢዎች/ በመለየትና በክላስተር በማደራጀት የተሻሻሉ የሰብል አመራረት ቴክኖሎጂዎች በተለይም ጉልበት ቆጣቢ የሆኑ መሳሪያዎች (የመዝሪያ መሳሪያዎችን ጨምሮ)፣ የሰብል ፈረቃና የዳግም ሰብል ልማት በተገቢው እንዲተገበሩ ይደረጋል፡፡

የስነምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ የሚያስችሉ በመካካለኛና በአጭር ጊዜ የሚደርሱ እና በፕሮቲን የበለፀጉ አማራጭ የበቆሎ፣ የቦሎቄ፣ ኪንዋ ወዘተ... ዝርያዎችን በምርምር በማላመድ፣ በማስተዋወቅ ለአርሶአደሮች እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡ የሰብል አመራረትን በተቀመጠው ምክረ-ሀሳብ መሰረት ተግባራዊ ማድረግ፤ በተለይም ምርጥ ዘር በአግባቡ መጠቀም፣ የድህረ ምርት አያያዝን ማሻሻል፣ የተቀናጀ የሰብል ጥበቃ ስርዓት እንዲተገበር ይደረጋል፡፡ ሀገራዊ የስንዴን ምርት መጠን በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ ከውጭ የሚገባውን ስንዴ ለማስቀረትና ስንዴን ፍላጎትን ማሟላት እንዲቻል ሰብሉ በመስኖ ሊለማ በሚችልባቸው አካባቢዎች ላይ ያተኮረ የስንዴ ልማት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡ ኢንዱስትሪው በሚፈልገው የጥራት መስፈርት ከፍተኛ የዘይትና ፕሮቲን መጠን፣ በሽታን የመቋቋም ብቃት ያላቸው የአኩሪ አተር፣ ሱፍና ሌሎች የቅባት ሰብል ዝርያዎች የማላመድና ስራ ይከናወናል፡፡ የሰብል የዘር ብዜት በመንግስትና በግል ዘር አባዥ ድርጅቶች ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ የኢንዱስትሪውን ፍላጎት የሚያሟሉ ከፍተኛ ምርታማ የሆኑ አማራጭ የተሻሻሉ የብቅል ገብስ ዝርያዎችን በማላመድ፣ ማስተዋወቅና ማስፋፋት ትኩረት ተሰጥቶት ይተገበራል፡፡

## ሰ) የሆርቲካልቸር ሰብል ልማት

ገበያ ተኮር፣ በንጥረ-ነገር የበለጸጉ እና ለአየር ንብረት ተስማሚ የሆኑ በምርምር የተለቀቁ ቴክኖሎጂዎች እና አዳዲስ የሆርቲካልቸር ዝርያዎችን ማስፋፋት፣ የኤክስፖርት ምርት ድርሻን ማሳደግ፣ የሆርቲካልቸር ልማት ቴክኖሎጅ ፓኬጅ ማዘጋጀት፣ ማሻሻልና እንዲሁም ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ለተጠቃሚዎች ማሠራጨት፣ የሆርቲካልቸር ሰብሎች ሀገራዊ የምርት መረጃ/ ቅድመ ምርት ግመታ እና ድህረ ምርት መረጃ ማሰባሰብ፣ መተንተን፣ የሆርቲካልቸር ልማት ፍኖተ-ካርታ፣ ስትራቴጅ፣ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች መቅረጽ መተግበርና የአፈፃፀም ክትትል ማድረግ፣ የሆርቲካልቸር ልማቱን የሚመለከቱ ልዩ ልዩ አዋጆችን፣ ስታንዳርዶች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መነሻ ሀሳብ ማመንጨት፣ ማዘጋጀት እና በሚመለከተው አካል ማፀደቅ፣ ተግባር ላይ እንዲዉል ማድረግ፣ በሆርቲካልቸር ልማት ስትራቴጅክ ዕቅድ ማዘጋጀት እና ለተፈፃሚነቱ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ተደራሽ የሆነ የሆርቲካልቸር መስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት ማስፋፋት፣ ተደራሽ ማድረግ፣ በሆርቲካልቸር ልማት ላይ ለተሰማሩ/ለሚሰማሩ የግል ባለሃብቶች የማበረታቻ ስርዓት መንደፍ እና ተግበራዊ ማድረግ፣ ብክነትን የሚቀንሱና ጥራትን የሚያሻሽሉ የምርት አሰባሰብ ቴክኖሎጂዎችን (ዘመናዊ ምርት መሰብሰቢያ፣ ማከማቻ፣ ማጓጓዣ) ማስተዋወቅ/ማስፋፋት፤ የሆርቲካልቸር ኮሞዲቲ ክላስተር/ኮሪደርን በጥናት መለየት፣ የሆርቲካልቸር ልማት የኮሞዲቲ ክላስተር መመስረት፣ አፈፃፀሙን መከታተል፣ መተግበር፣ የሆርቲካልቸር ድህረ ምርት እና የዘር ብዜት ባለሙያዎችን ማፍራትና ማብቃት፤ የቲሹ ካልቸር ማባዣ ቴክኖሎጂን/ማእከላት እንዲስፋፉ ማድረግ፣ መደገፍ፣ የዘር/ችግኝ/የቁርጥራጭ አመራረትና ስርጭት ስርዓት መዘርጋት (Certification)፣ የግብዓት አቅርቦት (የአፈር ማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘር፣ አነስተኛ የእርሻ መሳሪያዎችና ማሽነሪዎች) ተደራሽ እንዲሆኑ በቅንጅት መስራት፤ የባለድርሻ አካላትን ማለትም ከአምራቹ እስከ መጨረሻ ተጠቃሚው ድረስ ያሉትን ዋና ዋና ተዋናዮች ግንዛቤ ማሳደግ፤ የአሰራር ስርዓትን ማሻሻል፤ እምቅ አቅም ባላቸው ኮሪደሮች ላይ የገጠርና ከተማ አውት ግሮወርስ የአመራረት ስርዓት ተግባራዊ ማድረግ (ለምሳሌ ድሬዳዋ፣ ሀዋሳ፣ ጣና ዙሪያ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ አዲስ አበባ ዙሪያ)፣ አርሶ አደሩ ምርቱን የሚያስተዋውቅባቸውና የገበያ ትስስር የሚፈጥርበት መድረክ ማመቻቸት፣ በቅንጅት መስራት (ሲምፖዚየም፣ ኤግዚቢሽን፣ ባዛር፣ የሆርቲካልቸር ቀን ወዘተ...)፣ በፌደራልና በክልል በዘርፉ የተሰማሩ የምርምር ማዕከላትን አቅም መገንባት፤ የሆርቲካልቸር ሰብሎች የአመራረት ዘዴ፣ ማዘመን፣ ማሻሻል (በስልጠና፣ በቴክኖሎጅ ፣ በሠርቶ ማሳያ፣ በክትትልና ድጋፍ፣ የማበረታቻ ድጋፍ ወዘተ...)፣ በየደረጃው ያለውን የፈፃሚ አካል አቅም ማጎልበት፤ የመልካም እርሻ አሰራርን /Good Agricultural Practice (GAP)/ ደንቦችን ማስተዋወቅና እንዲተገበር ማድረግ ናቸዉ።

በጥጥ ልማት መስክ ለመሰማራት መሬትና ብድር ወስደው በሙሉ የማልማት አቅማቸው የማያለሙ ባለሃብቶች ያሉባቸውን መሰረታዊ ችግሮች በመቅረፍ ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ፣ በጥራት ላይ የተመሰረተ ቀልጣፋና ዘመናዊ የጥጥ ግብይት ሥርዓት፣ የኮንትራት እርሻ ስርዓትን በማስፋፋት እና የአነስተኛ አርሶ አደሮችን ተሳትፎ በማረጋገጥ የጥጥ ምርትን ማሳደግ፣ በፌደራልና በክልል ደረጃ ያሉ የግብርና ምርምር ማዕከላት የጥጥ ምርምር አቅማቸውን በማጎልበት የተሻሻሉ የጥጥ አመራረት ቴክኖሎጂዎች እንዲያወጡና ተደራሽ እንዲሆኑ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የጥጥ



አለ ዜና ሀ/ወልድ
የስትራቴጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

ግብዓቶችን በአገር ውስጥ በመተካት እና አዳዲስ የአቅርቦት አሰራሮችን በመዘርጋት የጥጥ ግብዓት አቅርቦትን ማሳደግ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተፈላጊነታቸው እያደገ የመጣው በዘላቂነት መርህ የተመረተ ጥጥ (Sustainable Cotton) ልማት ሀገሪቱ ካላት ፅምቅ ሀብት ጋር በማስተሳሰር ማስፋፋት ናቸው።

## 3.1.7. ግብርና ምርምር: ሰብልና ሆርቲካልቸር ልማት ምርምር

በቀጣይ ሦስት ዓመታት በምርምር የሚወጡት ቴክኖሎጂዎች (ዝርያዎች) በምርት ውስጥ ከሚገኙ አብዛኛው ዝርያዎች በምርታማነት በ10 ፐርሰንት ብልጫ ያላቸው ሲሆን እነዚህን በምርምር የመነጩትን ቴክኖሎጂዎችና መረጃዎችን በተገቢዉ መልኩ በመቀመርና የኤክስቴንሽን ፓኬጅ አካል ሆነው ወደ ምርት ስርዓት ውስጥ ሲገቡ ምርትና ምርታማነትን በማሻሻል ለምግብ ዋስትና፣ ለውጭ ገበያና ለአግሮ ኢንዱስትሪ ግብዓት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ይሆናሉ።

### ሀ) የቴክኖሎጂና መረጃ አቅርቦት

በመካከለኛው የልማት ዕቅድ ዘመን የቴክኖሎጂና መረጃ አቅርቦትን በተመለከተ በማላመድና በማፍለቅ እንድሁም በመሰረታዊ የምርምር አሰራሮች በመታገዝ በአጠቃላይ 192 አዳዲስ የግብርና ቴክኖሎጂዎች እንዲሁም 816 በመረጃና የአሰራር ዘዴዎች አቅርቦት በድምሩ 1008 ውጤቶችን እንደሚያቀርብ ይጠበቃል። እነዚህ ውጤቶች ሲገኙ ምርትና ምርታማነትን በማሻሻል ለምግብ ዋስትና፣ ለውጭ ገበያ፣ ለአግሮ ኢንዱስትሪ ግብዓት፣ ለአካባቢ ጥበቃ እና ለፖሊሲ ግብዓትነት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ናቸው።

### ለ) የቴክኖሎጂ ማስተዋወቅ

አዳዲስና የተሻሻሉ እንዲሁም አርሶ አደሩን፣ አርብቶ አደሩንና ባለሃብቱን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ቴክኖሎጂዎችን በስፋት ለማስተዋወቅና በፍጥነት ወደ ልማቱ እንዲገቡ ለማድረግ ኢንስቲትዩቱ በቴክኖሎጂ ሰርቶ ማሳያ፣ በሠፋፊ ክላስተር ማስፋት፣ በአነስተኛ የዘር ፓኬጅ፣ በቴክኖሎጂ ሰርቶ ማሳያ መንደር፣ በመስክ ቀንና በአርሶና አርብቶ አደር የልምድ ልውውጥ በቅንጅት የማስተዋወቅ ስራዎችን በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች በሦስት ዓመቱ ለ54,070 የቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች ወካይ ወረዳዎች ላይ ተደራሽ ይደረጋል።

### ሐ) የቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች ስልጠና

ስልጠና ከምርምር በወጡ ቴክኖሎጂዎች ዙሪያ ለተጠቃሚዎች ግንዛቤ በመስጠት የምርምር ውጤቱን በአግባቡ ስራ ላይ እንዲያውሉት ለማድረግ የሚያግዝ የአቅም ግንባታ ተግባር ነው። በቀጣይ ሦስት ዓመታት በተቋሙ ስር ባሉ የተለያዩ የምርምር ዳይሬክቶሬቶች /ንዑስ ፕሮግራሞች/ በድምሩ 41,339 የቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎችን ለማሰልጠን ታቅዷል።

### መ) የመነሻ ቴክኖሎጂ ብዜት

የመነሻ ቴክኖሎጂ ብዜት ጋር በተያያዘ ለቀጣይ ሦስት ዓመታት በሰብል፣ በእንስሳት፣ በተፈጥሮ ሀብትና በግብርና ሜካናይዜሽን ዘርፎች ሥር ይከናወናሉ። በዚህም መሠረት በሰብል ዘርፍ በአራቢ፣ በቅድመ-

መስራች እና በመስራች ዘር 59,326 ኩ/ል ዘር፣ 6.84 ሚ/ን ችግኝ/ ቁርጥራጭ/ቀንበጥ/ግንጣይ ለማባዛት ዕቅድ ተይዟል።

### ሠ) አገራዊ የግብርና ምርምር ሥርዓትን ማስተባበር እና ማጠናከር

በአገር አቀፍ ደረጃ የግብርና ምርምር ሥራዎችን በማቀናጀት ውጤታማነትን ለማሳደግ እና ምርምሩን ለማዘመን ማስተባበር፣ የምርምር ውጤቶች ተደራሽነትን ለማስፋት የአዋጪ ቴክኖሎጂዎችን ሽግግር ማስተባበር፣ አገራዊ የግብርና ምርምር ብቃትና አቅምን መገንባት፣ የግብርና ምርምርን በተመለከተ አገራዊና አለምአቀፋዊ ግንኙቶችን ማጠናከር፣ የተመረጡ የግብርና ምርምር ፕሮጀክቶችን መደገፍ እንዲሁም ከአግሮ ኢንዱስትሪ ልማት ጋር ያለውን ትስስር በማጠናከር የግብርና ልማቱ ትራንስፎርሜሽን እንዲሳካ ግንባር ቀደም አስተዋፅኦ ለማበርከት በመካከለኛው የዕቅድ ዘመን ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸው ሲሆኑ በቀጣይ ሦስት ዓመታት 2 የጥናት ሰነድ፣ 5 የአሰራር ስርዓት፣ 48 ህንጻዎችንና መሠረተ ልማቶችን መገንባት እና መጠገን፣ 6 የምክክር መድረኮችን ማዘጋጀት፣ 9,370 ተመራማሪዎችና ቴክኒሽያኖችን ለማሰልጠን በዕቅድ ተይዟል።

### የሰብልና ሆርቲካልቸር ዘርፉን ሊደግፉ የሚችሉ ኢንሼቲቮች

ከሁለተኛው ሀገር በቀል ኢኮኖሚክ ሪፎርም ከግብርና ዘርፍ የሪፎርም አጀንዳዎች ጋር የተያያዙ በሰብልና ሆርቲካልቸር ልማት የገቢ ምርትን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት፣ የኤክስፖርት ምርቶችን ለማስፋፋት እና የኢንዱስትሪ ግብዓት ፍላጎትን ለማሟላት በኢንሼቲቭ ተይዘው የሚተገበሩ ሀገራዊ የስንዴ ልማት ፕሮግራም፣ ሀገራዊ የቅባት ሰብሎች ልማት ፕሮግራም፣ የእንሰት ልማትን ማስፋፋት ፕሮግራም፣ የሆርቲካልቸር ኮሞዲቲ (አቮካዶ፣ ሙዝ፣ ቲማቲም እና ሽንኩርት) ፕሮግራም፣ ሀገራዊ የገበያ መር ኩታ ገጠም እርሻ ACC/FPC ማስፋፊያ ፕሮግራም፣ ሀገራዊ የባለብዙ ተዋንያን ኤክስቴንሽን ማስፋፊያ ፕሮግራም፣ የሀገር ውስጥ የግብርና ግብዓት አቅርቦት ማሻሻል (ሀገራዊ የሰብል ምርጥ ዘር ልማት ፕሮግራም) እና ሀገራዊ መደበኛ እና ተዛማች ተባዮች መከላከልና መቆጣጠር ፕሮግራሞች በትኩረት የሚተገበሩ ይሆናል።

## 3.2. ገበያ ተኮር የእንስሳትና ዓሳ ምርታማነት ማሻሻል

የግብርናው ዘርፍ ስትራቴጂክ ዓላማ አንዱ የሆነውን ገበያ ተኮር የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ምርትን ለማሳደግ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን የሚጠቀም አርሶና አርብቶ አደር በመገንባትና በገበያ የሚመራ የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ለማስፋፋት አቅጣጫ ተጠቀምጧል። በሚቀጥሉት ሶስት አመታት የእንስሳት እና ዓሳ ሀብት ልማት ሁለት የምርት እድገት አማራጮች ማለትም (1) ዝቅተኛ ምርታማነትን በዝርያ ማሻሻል፣ አያያዝ አመጋገብና እና ጤና አጠባበቅን ማሻሻል እና (2) የምርት ፍላጎት ማለትም ከኢንዱስትሪ መስፋፋት ጋር የሚፈጠሩ የግብዓት ፍላጎት፣ ለውጪ ምንዛሬ ግኝት እንዲሁም የኢኮኖሚ እድገት ጋር የሚመጣ የእንስሳት ምርት መጠንና አይነት ለውጥ ለሟሟላት ትኩረት ተደርጎ ይሰራል። በተለይም የወተት፣ ስጋ፣ እንቁላል፣ ዓሳ፣ ማርና የሐር ኩኩባ ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ አቅጣጫ ተቀምጧል። ይህም የአነስተኛ አርሶ/አርብቶ አደር እና ሰፋፊ እንስሳትና ዓሳ አመራረት ዘዴዎች ላይ ያተኮረ ይሆናል። ይህ

የእንስሳት እና ዓሳ ሀብት ልማት ምርት እድገት ለግብርና አጠቃላይ ምርት አሁን ያለውን 28 በመቶ ድርሻ በ2018 መጨረሻ ወደ 38 በመቶ ድርሻ እንዲኖረው የሚያስችል ኢላማ ተቀምጧል።

### 3.2.1. እንስሳት እና ዓሳ ምርት

#### ሀ) የወተት ምርትና ምርታማነት

የአነስተኛ እንስሳት እርባታ በወተት ምርት በዳልጋ ከብት፣ ፍየል እና ግመል ልማት ላይ ትኩረት ተደርጎ የሚሰራ ሲሆን የተለያዩ የአመራረት ስርዓቶችን ታሳቢ በማድረግ ከላም ከግመልና ፍየል አጠቃላይ የወተት ምርት በ2015 ከደረሰበት 8.69 ቢ/ን ሊትር በ2018 ዓ.ም መጨረሻ ላይ 11.93 ቢ/ን ሊትር ለማድረስ የሚያስችል ዒላማ ተቀምጧል። የዳልጋ ከብት (ላም) ወተት ልማት ሶስት የአመራረት ስርዓቶችን የሚከተል ሲሆን አብዛኛው (86 በመቶ) የሚሆነውን የወተት ምርት ሽፋን የሚይዝና በትኩረት የሚሰራ ይሆናል። የተሻሻለ የቤተሰብ ወተት ላም ልማት አንዱና ዋነኛው የአመራረት ስርዓት ሲሆን በአርሶና አርብቶ አደሩ ተይዘው የሚገኙትን የሀገር በቀል የወተት ላም ዝርያዎችን በመረጣ፣ በማዳቀልና አያያዝ በማሻሻል ምርታማነትን ማሳደግ ላይ ትኩረት በማድረግ ይሰራል። የአመራረት ስርዓቱም በአነስተኛ ስፔሻላይዝድ (Small Specialized Dairy Production System) ወተት ከብት እርባታ በአንድ ዕርባታ ጣቢያ ከ5 ያላነሱ የዲቃላና የውጪ ዝርያ ላሞች በመያዝ የሚሰራ ይሆናል።

ሁለተኛው የወተት ምንጭ የግመል ወተት ልማት ሲሆን ከአጠቃላይ የወተት ምርት የ12 በመቶ የምርት ድርሻ የሚሸፍንና በአርብቶ አደሩ ተይዘው የሚገኙትን የሀገረሰብ ዝርያዎችን በመረጣና በድቀላ በማሻሻል ላይ ትኩረት በማደረግ የሚሰራ ይሆናል። ሶስተኛው የወተት ምንጭ የፍየል ወተት ልማት ሲሆን ከአጠቃላይ የወተት ምርት አነስተኛ የምርት ድርሻ የሚሸፍን ሲሆን አርሶና አርብቶ አደሩ ተይዘው የሚገኙትን የሀገር በቀል የፍየል ዝርያዎችን በመረጣና ከውጪ ደም ካላቸው ጋር በማዳቀል ምርታማነትን ማሳደግ ትኩረት በማድረግ የሚሰራ ይሆናል።

#### ለ) የቀይ ሥጋ ምርትና ምርታማነት

የቀይ ስጋ ምርት ከዳልጋ ከብት፣ በግ፣ ፍየል እና ግመል ልማት ላይ ትኩረት ተደርጎ የሚሰራ ሲሆን የተለያዩ የአመራረት ስርዓቶችን ታሳቢ በማድረግ በ2015 መጨረሻ ከደረሰበት 491.35 ሺህ ቶን በ2018 መጨረሻ ላይ 861 ሺህ ቶን ለማድረስ የሚያስችል ኢላማ ተቀምጧል። ይህ ምርት በአብዛኛው ከአነስተኛ አርሶና አርብቶ አደር የእንስሳት ልማት ይሆናል። ስነ-ምህዳርን መሰረት በማድረግና የቀይ ስጋ ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በመጠቀም የዳልጋ ከብት፣ በግ፣ ፍየልና ግመል ሥጋ ምርታማነት የማሻሻል ሥራዎች ይሰራሉ።

#### ሐ) የቆዳና ሌጦ ምርት

ከስጋ ምርት ጋር በተያያዘ ቆዳና ሌጦ ዋነኛው ተዋፅዖ ሲሆን በ2015 ከተደረሰበት 19.02 ሚ/ን የቆዳ እና የሌጦ ምርት በ2018 ወደ 23.13 ሚ/ን ለማድረስ ዕቅድ ተይዟል።

#### መ) የዶሮ ስጋና እንቁላል ምርትና ምርታማነት

የዶሮ ሥጋና እንቁላል ምርት ከማሻሻል አንጻር የእንቁላል ምርትን በ2015 መጨረሻ ከነበረዉ 3,918 ሚ/ን እንቁላል በ2018 መጨረሻ ላይ ወደ 9,197 ሚ/ን እንቁላል የማሳደግ ስራ ይሰራል።

የዶሮ ስጋ ምርትን በ2015 መጨረሻ ከደረሰበት 112 ሺህ ቶን በ2018 መጨረሻ ላይ ወደ 239.87 ሺህ ቶን ለማሳደግ ይሰራል። የዶሮ ስጋና እንቁላል ምርትን ለማሳደግና የሀገር ውስጥ የምግብና ስነ-ምግብ ፍላጎትን በማሟላት የውጭ ኤክስፖርትን ለማስጀመር የሚያስችሉ የአካባቢ ዶሮች አያያዝን የማሻሻል፣ የተሻሻለ የቤተሰብ ዶሮ እርባታና የስፔሻላይዝድ ዶሮ እርባታ ተሳታፊዎችን እንዲሁም በየእርባታው የሚያዙትን የዶሮ ቁጥርን መጨመርና ምርታማነትን ለማድረስ የሚያስችል ሥራዎች በማከናወን የተቀመጠውን ዒላማ ለማሳከት ጥረት ይደረጋል።

#### ሠ) የዓሣ ምርት እና ምርታማነትን ማሳደግ

የዓሳ ምርትን ለማሳደግና የሀገር ውስጥ የምግብና ስነ-ምግብ ፍላጎትን ለማሟላት ከሀይቆች፣ ግድቦች፣ ወንዞችና ሌሎች ትንንሽ የውሃ አካላት እንዲሁም አኳካልቸር በ2015 መጨረሻ ከተደረሰበት ከ101.36 ሺህ ቶን በ2018 መጨረሻ ወደ 214.4 ሺህ ቶን ለማድረስ ይሰራል።

#### ረ) የማር ምርትና ምርታማነት

የማር ምርትን ለማሳደግና ለሀገር ውስጥ ፍላጎት እና ለኤክስፖርት የማር ምርት በ2015 መጨረሻ ከደረሰበት 194 ሺህ ቶን በ2018 መጨረሻ 333.41 ሺህ ቶን ለማድረስ ይሰራል። በተመሳሳይ በ2015 መጨረሻ ከደረሰበት የሰም ምርት 13.3 ሺህ ቶን በ2018 መጨረሻ 14.89 ሺህ ቶን ለማድረስ ይሰራል። ይህን ለማሳከት ስነምህዳርን መሰረት በማድረግ የማርና የሰም ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በመጠቀም ኢላማውን ለማሳከት ጥረት የደረጋል።

#### ሸ) የሐር ኩኩባ ምርትና ምርታማነት

የደረቅ የሐር ኩኩባ ምርት በ2015 መጨረሻ ከተደረሰበት 41 ቶን በ2018 መጨረሻ 47.94 ቶን ለማድረስ ይሰራል።

### 3.2.2. የእንስሳትና ዓሳ ኤክስቴንሽን አገልግሎት

የኤክስቴንሽን ተጠቃሚ ቁጥርን ማሳደግ: - አርሶ/አርብቶ/ከፊል አርብቶ አደሮች በወተት፣ በዶሮ፣ በሥጋ፣ ቆዳና ሌጦ፣ በማርና ሐር፣ በዓሳ እና በመኖ ልማት የኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ተጠቃሚ ይደረጋሉ። በዚህም በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት የእንስሳትና ዓሳ ኤክስቴንሽን ተጠቃሚ ቁጥር በ2015 ከተደረሰበት 5,004,000 በመካከለኛው ዘመን ዕቅድ መጨረሻ በ2018 ወደ 8,646,912 እንዲደርስ ይደረጋል። ከእነዚህ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚዎች ውስጥ 40 በመቶ (3,458,765) የሙሉ ፖኬጅ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ይሆናሉ። በተመሳሳይ መልኩ ካሉት የኤክስቴንሽን ተጠቃሚዎች ውስጥ አዳዲስና የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን የሚቀበልና ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚተገብሩ እንዲሁም ለሌሎች አርሶ፣ አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሮች አርአያ ሊሆኑ የሚችሉ 30 በመቶ (1,037,629) ሞዴል አርሶ/አርብቶ

ላከ ፀጋ ህ/ወልድ የስትራቴጂክ ጉዳዮች ሥራ አስፈጻሚ

አደሮችን መፍጠር ላይ ትኩረት ተደርጐ ይሰራል። ከተጠቃሚዎች ውስጥ በእንስሳት ልማት ሥራ የተሰማሩ እማወራዎችን 100%፣ ባለትዳር ሴቶች 50%፣ እንዲሁም 10 በመቶ የሚሆኑትን ወጣቶች የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚ ይደረጋሉ።

**የኤክስቴንሽን ተጠቃሚዎችን ቁጥር ለማሳደግ የሚከናወኑ የትግበራ መስኮች**

የእንስሳት እና ዓሳ ኤክስቴንሽን አደረጃጀትና መረጃ ፍሰትን ማሻሻል፣ አርሶ እና አርብቶ አደር ማዕከላትን ማሻሻል፣ የዲጂታል ኤክስቴንሽን የምክር አገልግሎትን ማጠናከር፣ የኤክስቴንሽን ሰራተኞች የሰው ኃይል ልማት ግንባታ በማከናወን የተሟላ የእንስሳትና ዓሳ ሃብት ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት በተለይም ገበያን መሠረት ያደረገ የእንስሳት እና ዓሳ ሀብት ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠት ከምርት ወደ ዘላቂ የገበያ ተኮር ኤክስቴንሽን አገልግሎት ማሸጋገር እንዲሁም የውል እርሻ አቀራረብ ላይ በትኩረት መስራት፣ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ሰጪ አካላት፣ የአገልግሎት ዓይነት እና አሰራር ስልቶች በብዛህነት መጠቀም የብዙ ተዋንያን (Pluralistic) የኤክስቴንሽን የምክር አገልግሎትን የማሳደግ ስራ በትኩረት ይሰራል።

### 3.2.3. የእንስሳት መኖ ልማት

በሁሉም የእንስሳት መኖ ምንጮች (የተፈጥሮ ግጦሽ፣ የሰብል ተረፈ ምርት፣ ከተሻሻለ የመኖ ዕፅዋት ልማት፣ ከኢንዱስትሪ መኖ ልማት፣ ከወልና ከግል የግጦሽ መሬት ልማት) በ2015 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 165.04 ሚ/ን ቶን ድርቆ መኖ ምርት በ2018 219.67 ሚ/ን ቶን ድርቆ መኖ ለማምረት ግብ ተጥሏል። የመኖ ዘር ምርት በ2015 መጨረሻ ከተደረሰበት 4.24 ሺህ ቶን በ2018 መጨረሻ 5.65 ሺህ ቶን ለማድረስ ይሰራል። በመስኖ መኖ የለማ መሬት በ2015 መጨረሻ ከተደረሰበት 34,658 ሄ/ር በ2018 መጨረሻ 46,128.50 ሄ/ር ለማድረስ ይሰራል።

ይህንንም ለማሳካት የተለያዩ የማሻሻያ ስትራቴጂዎችን በመተግበር የመኖ ማልሚያ ፓኬጆችን በማዘጋጀትና በመተግበር እንዲሁም ከለሙ የተሻሻሉ የመኖ ዓይነቶች ሰብል ተረፈ ምርትን በተገቢዉ ማሰባሰብና ማከማቸት፣ መጤ የግጦሽ ወራሪ አረም ባለባቸዉ የአርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ መሬት አረም በማስወገድና በማልማት በተወሰኑ ወካይ ቦታዎች በፓይለት ደረጃ በመተግበር ማስተማሪያ እንዲሆንና ተሞክሮ የማስፋፋት ሥራዎች በትኩረት ይሰራሉ።

### 3.2.4. የተሻሻለ የእንስሳት እና ዓሳ ዝርያ ማሻሻያ

በየዓመቱ የሚመረተው የተሻሻሉ ላሞች አባለዘር ምርት አሁን ካለበት 1.40 ሚ/ን ዶዝ ወደ 3 ሚ/ን ዶዝ ለማሳደግ ይሰራል። የፈሳሽ ናይትሮጂን ምርትን አሁን ከደረሰበት 0.37 ሚ/ን ወደ 0.78 ሚ/ን ለማድረስ፣ የተሻሻለ ሆርሞን በየአመቱ 70 ሺህ ዶዝ ወደሀገር ውስጥ እንዲገባ ይደረጋል፣ ለአባለዘር ምርት ተመርጠው የሚገቡ ታዳጊ ኮርማዎች ቁጥር አሁን ካለበት 35 ወደ 220 ለማሳደግ ታቅዷል። ከተሻሻሉ ዝርያዎች የሚወለዱ ዲቃላ ጥጆች ቁጥር 2015 ካለበት 272,855 ጥጆች ወደ 1.2 ሚ/ን ጥጆች ማሳደግ፣ ተመርጠው የተሰራጩ አውራ በጎችና ፍየሎች ቁጥር አሁን ካለበት 4,569 ወደ 9,000 ማድረስ፣

የተሰራጩ ዝርያቸው የተሻሻሉ ዶሮዎች አሁን ካላበት 29 ሚ/ን ወደ 55.75 ሚ/ን ለማሳደግ፣ የተሻሻሉ የዓሳ ብዜት በ2016፣ 2017 እና 2018 በተከታታይ 3.63፣ 4.72 እና 6 ሚ/ን ለማድረስ ይሰራል።

## 3.2.5. የተሻሻለ የእንስሳት ጤና አገልግሎት

የተሻሻለ የእንስሳት ጤና አገልግሎትን ለመፍጠር ከእንስሳት ሀብቱ 70 በመቶ የሚደርሱ የድንበር ዘለልና ድንበር ዘለል ያልሆኑ ምርትን የሚቀንሱ በሽታዎችን በመከተብ የእነዚህን በሽታ ክስተት በመቀነስ- እንስሳት ምርታማ እንዲሆኑ ይሠራል። ለበግና ፍየሎች ገዳይ የሆነ የበጎችና ፍየሎች ደስታ መሰል በሽታ (PPR) በታቀደለት ወቅት ከሀገራችን እንድጠፋ በቅንጅት ይሠራል። የሌማት ትሩፋት ሥራ ዕቅድ ግቡን እንዲመታ የጥጆችና ግልገሎች፣ ዶሮዎች ሞት ለመቀነስ የተዘጋጀውን ፓኬጅ ይተገበራል። የእንስሳት ጤና ክሊኒክ አገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ፣ ከሰው ወደ እንስሳት፣ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የተቀረፀውን የቁጥጥር ስርዓትና የእንስሳት ጤና ራሽናላይዜሽን ፍኖተ ካርታን መተግበር የግል ሴክተሩን ተሳትፎ ማሳደግ ስለሚቻል በቀጣይ ሶስት ዓመታት የሚሰሩ ዋና ዋናዎቹ ሥራዎች ናቸዉ። የክሊኒኮች ደረጃ እና ስታንዳርድ ማሳደግ፣ ተዘዋዋሪ የእንስሳት ጤና ፈንድ አሰራርን ማጠናከርና ማስፋት፣ የእንስሳት ጤና ራሽናላይዜሽን ፍኖተ ካርታን ማጸደቅና በመተግበር፣ የእንስሳት ጤና ደህንነት እንድጸድቅና ምክር ቤትን (Vet.Statutory Body) እንድቋቋም የእንስሳት ጤና አገልግሎት በመላዉ ሀገርቱ እንደ አርብቶና አረባብ ሁኔታዉ ተደራሽ ለማድረግና የሌማት ትሩፋት እንቅስቃሴ የተሳካ እንድሆን በተቀመጠዉ አቅጣጫ ሥራ ላይ እንዲዉል ይደረጋል።

የድንበር ዘለል እና ድንበር ዘለል ያልሆኑ በሽታን ክትባት ማስራጨትና መከተብን በተመለከተ በመከላከል ላይ ያተኮረ የእንስሳት ጤና ሥርዓትን በማጠናከር እንደ ሀገር 70 ከመቶ የሚደርሱ እንስሳትን መከተብ የሚያስችል የድንበር ዘለል እና ድንበር ዘለል ያልሆኑ በሽታዎች ክትባትን በማሰራጨት በ2015 በጀት አመት ከነበረበት 227 ሚ/ን እንስሳት በመከተብ በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት የድንበር ዘለል እና ድንበር ዘለል ያልሆኑ ክትባትን በማሰራጨት 787 ሚ/ን እንስሳት በመከተብ የበሽታ ክስተትን በመቀነስ የእንስሳት ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር በማድረግ የሌማት ትሩት ዕቅድ እንዲሳካ ይሰራል። ስኬታማ የሆነ የበሽታ መከላከል ስርዓትን ለማከናወን በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት የዋና ዋና የድንበር ዘለል እና ድንበር ዘለል ያልሆኑ በሽታዎች ሥርጭት የሚያሳይ ካርታ ይዘጋጃል። እንደ አመቺነቱ በእያንዳንዱ ክልል (ዞን/ወረዳ) የክትባት ካሌንዳር እንዲወጣ ይደረጋል። የሌማት ትሩፋት ለእንስሳት ሀብት ትልቅ እድል ስለሆነ ይህንን እድል በመጠቀም በቂ በጀት በማስመደብ የሚያስፈልገውን የክትባት ዓይነትና መጠን ከብሄራዊ እንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲቲዩት በኩል እንዲቀርብ ይደረጋል። በሌላ በኩል የመንግስት እና ግል ዘርፍን ትብብር በማጠናከር ዉጤታማ የሆነና በክትባት ላይ የተመሰረተ የድንበር ዘለል እና ድንበር ዘለል ያልሆኑ በሽታዎች መካላከል ለግል የእንስሳት ጤና አገልግሎት የሳኒተሪ ኮንትራት ዉል በመስጠት እንዲተገበር ይደረጋል። ይህን በHEARD ፕሮጀክት እየተሰሩ ያሉ የግልና የመንግት አጋርነት የሙከራ ሞደሎች ዉስጥ ስኬታማ የሆኑት በማስፋት የእንስሳት ጤና አገልግሎት የግሉ ዘርፍ በስፋት እንድገባና የመንግስትን የሌማት ትሩፋት ሥራ እንድደግፍ ይደረጋል።

ለአ ብርሀ ሀ/ወልድ
የስትራተጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

በክሊኒክ ላይ የተመሰረተ የእንስሳት ጤና አገልግሎት ሽፋንን ለማሳደግ በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት በመንግስትና በግል ዘርፍ በቅንጅት የሚተገበር ይሆናል። ይህም የግሉ ዘርፍ ወደ እንስሳት ጤና አገልግሎት በስፋት እንዲገቡ የተዘጋጁ ሰነዶች እንዲጸድቁ በማድረግ ምቹ ሁኔታን በመፍጠር ነዉ። በመሆኑም በክሊኒክ ላይ የተመሰረተ የእንስሳት ጤና አገልግሎት ተደራሽነትን በ2015 ከደረሰበት 86 በመቶ ወደ 90 በመቶ ለማሳደግ እቅድ ተቀምጧል። ከዚህም ውስጥ የግል ዘርፉ ድርሻ 35 በመቶ እንዲሸፍን ኢላማ የተቀመጠ ሲሆን የመንግስት 55 በመቶ የሚሸፍን ሲሆን ጥራት ማሻሻል ላይ ትኩረት ተደርጎ ይሰራል።

የበጎችና ፍየሎች ደስታ መሰል በሽታ (PPR) በታቀደለት ወቅት ከሀገራችን ማጥፋት፦ ይህ በሽታ ከሀገራችን ለማጥፋት የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እቅዱን ለማሳካት ትልቅ ሚና አለዉ። ስለሆነም በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት ከበሽታዉ ጋር ተያይዘዉ የሚሰሩ ምርመራዎች፣ የበሽታ ዳሰሳና የክትባት ሥራዎች ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ተጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን በድምሩ 26.7 ሚሊየን በጎችና ፍየሎች ይከተባሉ።

**የጥጆች፣ግልገሎችና ዶሮዎች ሞት ለመቀነስ የተዘጋጀውና ፓኬጅን መተግበር፦** በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት የተዘጋጁት የጥጆች ሞት ቅነሳ ፓኬጆችና የዶሮ ጤናና አያያዝ ፓኬጅ ለባለሞያዎችና ለአርቢዎች በስልጠና መልክ እንዲደርስ በማድረግ የጥጆችንና ግልገሎችን ሞት አሁን ካለበት የ25 በመቶ ድርሻ ወደ 10 በመቶ እንዲሁም የዶሮዎች ሞት አሁን ካለበት 50 ወደ 20 በመቶ ለመቀነስ ይሰራል።

የውሻ እብደት በሽታ ክትባት ዉሾችን መከተብ፦ በአለም አቀፍ ደረጃ እ.አ.አ በ2030 ይህን በሽታ ለመግታት ታቅዶ እየተሰራ ነዉ። ሀገራችንም በዉሻ ምክንያት የሚከሰተዉን የዉሻ እብደት በሽታ ለማጥፋት ዘመቻዉን መጀመሯ ይታወቃል። ይሄንንም ለማሳካት በሚቀጥሉት ዓመታት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበርና የአንድ ጤናን ተግባራዊ በማድረግ ሥራዉ ተጠናክሮ ይቀጥላል። የዉሻ እብደት በሽታ የዱር እንስሳትንም ስለሚያጠቃ በተለይ ቀበሮዎችን እንዲሁም ብርቅዬ እንስሳት (ቀይ ቀበሮን) ከሀገራችን እንዲጠፉ ምክንያት ሊሆን ስለሚችል ከኢትዮጵያ ዱር ዓራዊት ደህንነትና ጥበቃ እና ሌሎች ዱር አራዊት ላይ ከሚሰሩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ለሕብረተሰባችንና የእንስሳቶቻችን ጤና ለመጠበቅ አመታዊ የዉሾች ክትባት አሁን ከተደረሰበት 210 ሺ.ህ ወደ 360 ሺ.ህ ለማድረስ ተጠናክሮ ይሰራል።

ከሰው ወደ እንስሳት የሚተላለፉ በሽታዎችን የቁጥጥር ስርዓት በመተግበር በተመለከተ የእንስሳቱን ምርታማነት ከመጉዳት ባሻገር የሰዉን ጤናም ስለሚጎዱ ከማምረት ባሻገር ምርቱም ለተመጋቢዉ ሕብረተሰብ ሥጋት እንዳይሆን በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት ተጠናክሮ ይቀጥላል። ሌማታችን ከእነዚህ በሽታዎች በፀዱ ምግቦች እንዲሞላ ተመጋቢዎችም ያለስጋት እንዲመገቡት ከሌማቱ ሙላት የተረፈዉና ለገበያ የሚቀርበዉም እንደዚሁ እንዲሆን ይሰራል። በሀገራችን አምስት ከእንስሳት ወደ ሰዉ የሚተላለፉ ቅድሚያ የተሰጣቸዉ በሽታዎች አሉ። እነዚህም የዉሻ እብደት በሽታ (Rabies)፣ አባሰንጋ በሽታ (Anthrax) የዉርጃ በሽታ (Brucellosis)፣ የስምጥ ሸለቆ ትኩሳት (RVF) እና አደገኛ የወፍ ጉንፋን (HPAI) ሲሆኑ በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት ከእንስሳት ወደ ሰዉ ከሰዉ ወደ እንስሳት የሚተላለፉ በሽታ ጋር ተያይዞ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር እነሱ ላይ ትኩረት ተደርጎ ይሰራል።

የእንስሳት በሽታ ቅኝት፣ ዳሰሳና የስጋት ትንተና ማጠናከር በተመለከተ እንደ ሀገር በቂ የበሽታ አሰሳና ቅኝት መረጃ ያልተሰባሰበባቸውና ያልተደራጀባቸው የዓሣና የንብ በሽታዎችን በተመለከተ የቅኝትና ዳሰሳ ስራዎችን ለማከናወን የሚያግዝ ስርዓት በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት እንደሌሎች እንስሳት ሁሉ ሥርዓቱ ይዘረጋላቸዋል:: የዓሣ በሽታ ጥናትና ዳሰሳ በአለም አቀፍ የምግብና እርሻ ድርጅት (FAO) ጋር በመተባበር እየተሰራ ያለዉ የስትራቴጂክ ሰነድ ዝግጅት ተጠናቆ እንዲጸድቅ ይደረጋል:: ለንግድ የተመሰረቱ (Commercial Farms) እርባታዎች ዉስጥም በተመሳሳይ በተንቀሳቃሽ ስልክ (Mobile Phone) ላይ ተመስርቶ የተመዘገቡ በሽታዎችን (OIE Listed Notifiable Diseases) ሪፖርት እንዲያደርጉ ስልጠና በመስጠት ለእርባታዉ መስክ በቅርበት የተጠናከረ ድጋፍና ክትትል ይደረጋል::

በዶቫር-ll የእንስሳት በሽታ እና ክትባት አገልግሎትና በተንቀሳቃሽ ስልክ የበሽታ ሪፖርትን ማጠናከር በተመለከተ በዶቫር-ll የእንስሳት በሽታ እና ክትባት አገልግሎትና ሪፖርት በ2015 በጀት ዓመት ከደረሰበት 74 በመቶ በ2018 መጨረሻ ወደ 80 በመቶ እንዲደርስ ተጠናክሮ ይሰራል:: የተመዘገቡ በሽታዎችን በተንቀሳቃሽ ስልክ ላይ የተመሰረተ የበሽታ ሪፖርት ማድረግ አሰራር ተግባራዊ የተደረገባቸው ጣቢያዎችና አዳዲስ የሚጨመሩትን ጨምሮ በ2015 ከነበረዉ 25 በመቶ በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት ወደ 65 ከመቶ ለማድረስ ይሰራል::

ከበሽታ ነጻ የሆነ ቀጠና መፍጠር (Diseases Free Zone or Compartment) ፡- ለዉጭ ገበያ ብቁ የሆነ የእንስሳት ጤና ሥርዓትን ለመፍጠር የበሽታ ዳሰሳ፣ ቅኝትና የመከላከል ሥራዎችን በማጠናከር ከበሽታ የፀዳ አካባቢ ወይም ዞን (Diseases Free Zone or Compartment) ለመፍጠር ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር በሚቀጥሉተ ሶስት ዓመታት በጥንካሬ ይሰራል::

ደህንነታቸውና ጥራታቸው የተጠበቀ የእንስሳት ውጤቶች፣- በሌማት ትሩፋት የሚገኙት የእንስሳት ዉጤቶች ለሥጋት መንስኤ እንዳይሆኑ በሚቀጥሉት 3 ዓመታት ለሌማት ትሩፋት የተመረጡት የወተት ላሞች፣ ዶሮዎች፣ ዓሳና ንብ እርባታ መንደር ላይ ትኩረት ተደርጎ ይሰራል::

**አንድ ጤና አሰራር መዘርጋት:-** በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በአየር ለዉጥም ሆነ በሌላ ተያያዥ ሁኔታዎች የሚመጡትን በሽታዎች ለመቆጣጠር ይሰራል::

**የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ሽፋን ማሳደግ: -** የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ዳግም ወረራ ለመከላከል የተሸፈነ መሬት ስፋትን ማሳደግ፣ከቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የፀዳ መሬት ስፋትን ማሳደግ፣ መሠረታዊ መረጃ በማሰብሰብ አዳዲስ የቁጥጥር ሥራዎችን መጀመር፣ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ቅንጅታዊ አሰራርን ማስፈን፣ የተገነባ እንስሳት በሽታ ምርመራና ምርምር አቅም፣ የምርመራና ምርምር አሰራር ስርዓትን ማሻሻል፣ ለክልል እንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችና ሌሎች የምርመራ ሥራ ለሚሰሩ ተቋማት ድጋፍ ማድረግ፣ የተቋሙን የውስጥ ገቢ ማመንጨት ናቸው:: በመሆኑም በ2015 በጀት አመት የተደረሰበት የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ዳግም ወረራ ለመከላከል የተሸፈነ መሬት ስፋት ከ53,404 ወደ 75,000 ካ.ኪ..ሜ.

እንዲሁም ከቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የፀዳ መሬት ስፋትን ከ34,238 ወደ 55,000 ካ.ኪ..ሜ. ለማሳደግ ይሰራል።

### 3.2.6. ግብርና ምርምር: እንስሳትና ዓሳ ልማት ምርምር

በቀጣይ ሦስት ዓመታት በምርምር የሚወጡት ቴክኖሎጂዎች (ዝርያዎች) በምርት ውስጥ ከሚገኙ አብዛኛው ዝርያዎች በምርታማነት በ10 ፐርሰንት ብልጫ ያላቸው ሲሆን እነዚህን በምርምር የመነጩትን ቴክኖሎጂዎችና መረጃዎችን በተገቢዉ መልኩ በመቀመርና የኤክስቴንሽን ፓኬጅ አካል ሆነው ወደ ምርት ስርዓት ውስጥ ሲገቡ ምርትና ምርታማነትን በማሻሻል ለምግብ ዋስትና፣ ለውጭ ገበያና ለአግሮ ኢንዱስትሪ ግብዓት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ይሆናሉ።

#### ሀ) የቴክኖሎጂና መረጃ አቅርቦት

በመካከለኛው የልማት ዕቅድ ዘመን የቴክኖሎጂና መረጃ አቅርቦትን በተመለከተ በማላመድና በማፍለቅ እንድሁም በመሰረታዊ የምርምር አሰራሮች በመታገዝ በአጠቃላይ 103 አዳዲስ የግብርና ቴክኖሎጂዎች እንዲሁም 287 በመረጃና የአሰራር ዘዴዎች አቅርቦት በድምሩ 390 ውጤቶችን እንደሚያቀርብ ይጠበቃል። ይህ የልማት ዕቅድ ከቴክኖሎጂ እና መረጃ አቅርቦት አንጻር በአስር ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ ሦስቱ ዓመታት ላይ ተይዞ ከነበረው ዕቅድ ጋር ሲወዳደር 60 በመቶ የተሻለ ነው። እነዚህ ውጤቶች ሲገኙ ምርትና ምርታማነትን በማሻሻል ለምግብ ዋስትና፣ ለውጭ ገበያ፣ ለአግሮ ኢንዱስትሪ ግብዓት፣ ለአካባቢ ጥበቃ እና ለፖሊሲ ግብዓትነት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ናቸው።

#### ለ) የቴክኖሎጂ ማስተዋወቅ

አዳዲስና የተሻሻሉ እንዲሁም አርሶ አደሩን፣ አርብቶ አደሩንና ባለሃብቱን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ቴክኖሎጂዎችን በስፋት ለማስተዋወቅና በፍጥነት ወደ ልማቱ እንዲገቡ ለማድረግ ኢንስቲትዩቱ በቴክኖሎጂ ሰርቶ ማሳያ፣ በሠፋፊ ክላስተር ማስፋት፣ በአነስተኛ የዘር ፓኬጅ፣ በቴክኖሎጂ ሰርቶ ማሳያ መንደር፣ በመስክ ቀንና በአርሶና አርብቶ አደር የልምድ ልውውጥ በቅንጅት የማስተዋወቅ ስራዎችን በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች በሦስት ዓመቱ ለ20,994 የቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች ወካይ ወረዳዎች ላይ ተደራሽ ይደረጋል።

#### ሐ) የቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች ስልጠና

ስልጠና ከምርምር በወጡ ቴክኖሎጂዎች ዙሪያ ለተጠቃሚዎች ግንዛቤ በመስጠት የምርምር ውጤቱን በአግባቡ ስራ ላይ እንዲያውሉት ለማድረግ የሚያግዝ የአቅም ግንባታ ተግባር ነው። በቀጣይ ሦስት ዓመታት በተቋሙ ስር ባሉ የተለያዩ የምርምር ዳይሬክቶሬቶች /ንዑስ ፕሮግራሞች/ በድምሩ 17,898 የቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎችን ለማስልጠን ታቅዷል።

#### መ) የመነሻ ቴክኖሎጂ ብዜት

የመነሻ ቴክኖሎጂ ብዜት ጋር በተያያዘ ለቀጣይ ሦስት ዓመታት በሰብል፣ በእንስሳት፣ በተፈጥሮ ሀብትና በግብርና ሜካናይዜሽን ዘርፎች ሥር ይከናወናሉ። በዚህም መሠረት በእንስሳት ዘርፍ 5,050 እንቁላል ጣይ የሐር ቢራቢሮ፣ 240 እናት ንብ፣ 450 የንብ ጠላት ማጥመጃ ቀፎ፣ 2,199 የቀንድና የዳልጋ ከብቶች፣

729,716 የ1 ቀን የዶሮ ጫጩት፣ 5.3 ሚ/ን የዓሳ ጫጩት እንዲሁም በእንስሳት መኖ ብዜትም 1,857 ኩንታል የመኖ ዘር፣ 18.57 ሚ/ን ችግኝ/ቁርጥራጭ/ዝንጣይ ለማባዛት ዕቅድ ተይዟል።

### ሠ) አገራዊ የግብርና ምርምር ሥርዓትን ማስተባበር እና ማጠናከር

በአገር አቀፍ ደረጃ የግብርና ምርምር ሥራዎችን በማቀናጀት ውጤታማነትን ለማሳደግ እና ምርምሩን ለማዘመን ማስተባበር፣ የምርምር ውጤቶች ተደራሽነትን ለማስፋት የአዋጪ ቴክኖሎጂዎችን ሽግግር ማስተባበር፣ አገራዊ የግብርና ምርምር ብቃትና አቅምን መገንባት፣ የግብርና ምርምርን በተመለከተ አገራዊና አለምአቀፋዊ ግንኙቶችን ማጠናከር ስራ ይሰራል።

### የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ዘርፉን ሊደግፉ የሚችሉ ኢንሼቲቮች

ከሁለተኛው ሀገር በቀል ኢኮኖሚክ ሪፎርም ከግብርና ዘርፍ የሪፎርም አጀንዳዎች ጋር የተያያዙ በእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ሞዴል የገቢ ምርትን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት፣ የኤክስፖርት ምርቶችን ለማስፋፋት እና የኢንዱስትሪ ግብዓት ፍላጎትን ለማሟላት በኢንሼቲቭ ተይዘው የሚተገበሩ መንደርን መስራት፣ የዝርያ ማባዣ ራንቾችን ማስፋፋት፣ የዶሮ ግራንድ ፓረንት ስቶክ ማባዣ ማዕከላት ማቋቋም፣ ማህበረሰብ ተኮር የበግና ፍየል የዝርያ ማሻሻያ ማዕከል ማቋቋም ፕሮግራሞች በትኩረት የሚተገበሩ ይሆናል።

## 3.3. ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም

### 3.3.1. የተቀናጀ የተፋሰስ ልማትና አጠቃቀም

በመካከለኛ ዘመን ዕቅድ ለ3,750 የማኅበረሰብ ተፋሰሶች የተፋሰስ ልማት ስትራቴጂክ ዕቅድ እንዲሁም ለ3,000 የማኅበረሰብ ተፋሰሶች ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ማህበራት የሚቋቋም ይሆናል። በዚሁ መሰረት በ2016፣ 2017 እና በ2018 በተከታታይ 1,200፣ 1,250 እና 1,300 የማህበረሰብ ተፋሰሶች የተፋሰስ ልማት ስትራቴጂክ ዕቅድ የሚዘጋጅላቸው ሲሆን፣ በየአመቱ 1,000 የማህበረሰብ ተፋሰሶች ህጋዊ ሰውነት እንዲያገኙ ይደረጋል። የተፈጥሮ ሀብታችን ለማልማትና በዘላቂነት ለመጠቀም በስነ-አካላዊ የአፈርና ውሀ ጥበቃ ስራዎች የተሸፈነ መሬት በ2015 ከተደረሰበት 1,374.57 ሺህ ሄ/ር በየአመቱ 2 ሚ/ን ሄ/ር በመሸፈን በ2018 መጨረሻ 6 ሚ/ን ሄ/ር ለመሸፈን ታቅዷል። በሥነ-ህይወታዊ አፈርና ውሃ ጥበቃ የተካሄደባቸው የማህበረሰብ ተፋሰሶች ስፋት በየዓመቱ 471 ሺህ ሄ/ር የታቀደ ሲሆን በ2018 መጨረሻ ላይ 1,413 ሺህ ሄ/ር መሬት ለመሸፈን የታቀደ ሲሆን በተመሳሳ መልኩ ጥገናና ዕድሳት የሚደረግላቸው የማህበረሰብ ተፋሰሶች ስፋት በሶስት ዓመቱ መጨረሻ 1350 ሺህ ሄ/ር ለማድረስ ታቅዷል። በጥምር ደን የተሸፈነ መሬት ስፋት አሁን ካለበት 2.8 ወደ 4.3 ሚ/ን ሄ/ር ለማድረስ፣ ከእንስሳትና ከሰዉ ንክኪ ነጻ በማድረግ ተከልለው እንዲያገግሙ የተደረጉ ተፋሰሶች ስፋት አሁን ካለበት 707.30 ሺህ ሄር ወደ 1 ሚ/ን ሄ/ር ለማድረስ ዒላማ ተቀምጧል።

ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም የሚረጋገጠው አርሶ/አርብቶ አደሩ ለአገራችን ሥነ-ምህዳሮች ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በአግባቡ እንዲጠቀም በማድረግ፣ አርሶ/አርብቶ አደሩ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በአግባቡ ለመጠቀም በተጠቃሚዎች ተቀባይነት ያለው የተፈጥሮ ሀብት

ቴክኖሎጂዎች በማቅረብ፣ የአፈርና ውሃ ሃብቶችን ለመጠበቅ፣ የአፈር ጤንነትና ለምነት ለማሻሻል እና የመስኖ ውሃን በቁጠባ ለመጠቀም የሚያስችሉ አሳታፊ የተቀናጁና ተፋሰስን መሠረት ያደረጉ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችንና አዳዲስ አሰራሮች ላይ ዕውቀቱ፣ አመለካከቱና ክህሎቱ በማሳደግ እንዲሁም የተሻሻለ የተፈጥሮ ሀብት ግብዓትን በሚፈለገው መጠን እና ጥራት በማቅረብ ነው።

የአረንጓዴ አሻራ መርሐግብርን በተመለከተ 2015 በጀት ዓመት ከነበረበት በሚቀጥሉት ዓመታት በየዓመቱ 6.5 ቢ/ን ችግኞችን በመትከል እስከ 2018 በጀት ዓመት 19.5 ቢ/ን ለመትከል ታቅዷል። ከእነዚህ ዉስጥ በየዓመቱ ሳይንሳዊ ደረጃዉን በጠበቀ መልኩ 3 ቢ/ን በፖሊቲን ቱብ የተዘጋጀ የአገር በቀል የደን ዛፎችና የፍራፍሬ ዛፎች የሚተከሉ ሲሆን ቀሪዎቹ 3.5 ቢሊዮን ችግኞች በባሕላዊ መንገድ የሚፈሉ ይሆናሉ። በፖሊቲን ቱብ ከሚዘጋጁት 3 ቢ/ን መካካል 1.5 ቢሊዮኑ አገር በቀል የደን ዛፎች ሲሆኑ 1.5 ቢ/ን ደግሞ ዘርፈ-ብዙ ጥቅም ያላቸዉ የጥምር ደን እርሻ የሚተከሉ ይሆናሉ።

ከላይ የተቀመጡ ኢላማዎችን ለማሳከት ተፋሰሱ ያለውን ጸጋና ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ የልማት ስራ መተግበር፣ የተጎዱ ተፋሰሶችን ከንክኪ ነጻ በማድረግ ማልማት፣ ስነ-አካላዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች፣ ስነ-ሕይወታዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች፣ የተራሮች ልማት፣ የመጤ ወራሪ አረሞችን መስፋፋት መቀነስ፣ የማኅበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚ ማኅበራት በማደራጀት ድጋፍ እና የጥምር እርሻ-ደን ልማት ስራዎች የሚከናወኑ ይሆናል።

### 3.3.2. ዘላቂ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓት

ለአርሶ አደሮች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሚዘጋጅላቸው ማሳዎች በ2015 በጀት ጨረሻ 2.44 ሚ/ን የደረሰ ሲሆን በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት ለተጨማሪ 3.2 ሚ/ን ማሳዎች የይዞታ ማረጋገጫ ሠርተፍኬቶችን ለአርሶአደሮች ተዘጋጅቶ ለመስጠት ታቅዷል። በተመሳሳይ ሁኔታ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የተሰጣቸው አርሶ አደሮች ቁጥር በ2015 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 660 ሺህ በሚቀጥሉት ሶስት አመታት ማለትም በ2016 ለ343 ሺህ እንዲሁም በ2017 እና በ2018 በየዓመቱ ለ286 ሺህ አርሶ አደሮች ሰርተፍኬት በመስጠት በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ለ915 ሺህ የገጠር መሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠርተፍኬት ለመስጠት ታቅዷል። የገጠር መሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠርተፍኬት ያገኙ አርሶአደሮች የመሬት የመጠቀም መብታቸውን በማስያዝ ከፋይናንስ ተቋማት ብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ ሥራ በትኩረት ይሠራል። የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓት መሻሻልና መጠናከር ለአርሶአደሮች በተለይ ሴቶች የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን ተጠቅመው የተፈጥሮ ሀብትን በባለቤትነት ስሜት እንዲያለሙና እንዲንከባከቡ ያበረታታቸዋል፤ አስተማማኝ ዋስትናም ይሆናቸዋል።

ብሄራዊ የገጠር መሬት አስተዳደር የመረጃ ስርዓትን በተጠናከረ መንገድ በሀገሪቱ የማስፋፋትና ከገጠር መሬት ጋር በተያያዘ የሚከናወኑ ግብይቶች ወቅታዊ የማድረግ ስራ እና የመረጃ ስርዓቱ የሚያመነጫቸውን መረጃዎች ለተጠቃሚዎች በማሰራጨት ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ የማሳደግ ስራ ይከናወናል። ይህን የመረጃ ሥርዓት ወደ ተጨማሪ ወረዳዎች ለማስፋፋት በ2015 በጀት አመት 94 ወረዳዎች ላይ የተዘረጋው የመረጃ

ስርዓት በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት በየአመቱ 50 ወረዳዎች ላይ በአጠቃላይ 150 ወረዳዎች ላይ ለመዘርጋት ዒላማ ተደርጓል።

የገጠር መሬትን በእንክብካቤ ይዞ በዘላቂ መንገድ ለተሻለ ጠቀሜታ እንዲውል ለማድረግ የአሳታፊ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ዝግጅትና ትግበራን ያካተተ ዕቅድ ይዘጋጃል። ይህም አርሶአደሩ በየአካባቢው የተፈጥሮ ሀብትን በዘላቂነት ሊያስጠብቁ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን የአካባቢውን ሥነ-ምህዳርና መሬት አቀማመጥ መሠረት ያደረገ የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ ዝግጅትን በባለቤትነት መንፈስ በመስራት በማሳ ደረጃ እንዲተገብር ያስችላል። ይህን የአሳታፊ መሬት አጠቃቀም እቅድ በማሳ ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግና ትንተናውን ለማቀላጠፍ የሞባይል መተግበሪያ LandPKS app በመጠቀም የአርሶአደሩን እያንዳንዱን ማሳ ያለበትን የማምረት አቅም ደረጃ በማወቅ የመሬት ይዞታ ሠርተፍኬትን በመጠቀም ለተጀመረው የብድር እና የኪራይ አገልግሎት አጋዥ እንዲሆን ይደረጋል። አሳታፊ የመሬት አጠቃቃም እቅደ የተዘጋጀላቸው ቀበሌዎች ብዛት በ2015 በጀት ዓመት ከነበረበት 410 ቀበሌዎች በቀጣይ ሦስት ዓመታት በተለያዩ ድጋፎች በየዓመቱ ለ200 ቀበሌዎች በማዘጋጀት በሶስት ዓመቱ መድርሻ 600 ቀበሌዎችን በአሳታፊ መሬት አጠቃቀም ዕቅድ ለመሸፈንና ከዚህ ውስጥ በየዓመቱ 90 ቀበሌዎች ላይ በአጠቃላይ 270 ቀበሌዎች ላይ ለመተግበር በእቅድ ተይዟል።

የቀበሌ ማዕከል ግንባታ ዝግጅትም አሳታፊ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ዝግጅትን መሰረት ያደርጋል። የቀበሌ ማዕከላት ግንባታ የመሬት እምቅ አቅምን መሠረት በማድረግ መመስረት እንዲቻል የመሬት አጠቃቀምን መሠረት በማድረግ እንዲሰራ በ2015 ከነበረበት 135 ቀበሌ ማእከላት ግንባታ ዝግጁ የሆነ ሲሆን በቀጣይ ሶስት ዓመታት በየዓመቱ 60 ማእከላት ግንባታ በማከናወን በሦስት ዓመት 180 ቀበሌዎች ላይ ይከናወናል።

### 3.3.3. ዘላቂ የአፈር ጤንነትና ለምነት ማሻሻያ

ኢትዮጵያ በተለያዩ ሥነ-ምህዳሮች ውስጥ የሚገኝ ሰፊ የመሬት ሀብትና ለግብርና ልማት ሊውል የሚችል የተለያዩ የአፈር ዓይነቶች ያላት ቢሆንም በተለያዩ ተፈጥሯዊ እና ሰው ሰራሽ ምክንያቶች የአፈር ሀብታችን ጤንነቱና ለምነቱ የተጎዳ በመሆኑ የግብርናው ዘርፍ በከፍተኛ የምርታማነት ችግር ውስጥ ይገኛል።

ከነዚህም ችግሮች ዋናው የአፈር አሲዳማነት በመሆኑ በተለያየ ጊዜ በሀገሪቷ ውስጥ የተካሄዱ የዳሰሳ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደ/ብ/ብ/ህ/፣ ሲዳማ፣ደ/ም/ኢ/ሕ/ እና ቤ/ጉ/ ክልሎች ውስጥ በከፍተኛ ሁኔታ በአሲዳማነት የተጠቃ (pH <5.5) ከ4 ሚሊየን ሄ/ር በላይ የሚሆን የእርሻ መሬት እንደሚገኝ በጥናት ተመላክቷል። በሀገራችን ውስጥ ያለው ጠቅላላ የእርሻ መሬት 43% በአፈር አሲዳማነት የተጠቃ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ 28% በከፋ አሲዳማነት የተጎዳ ነው።

ስለዚህ አሁን በሀገሪቷ ውስጥ የሚገኘውን ከ3.88 ሚ/ን ሄ/ር በላይ የሚሆነውን በከፋ አሲዳማነት የተጠቃ የእርሻ መሬት በግብርና ኖራ ብናክም የአፈሩን ለምነት ከማሻሻሉም በላይ በመጀመሪያው አመት እንደ ጊዜ በግብርና ኖራ ባክምነው ብቻ በቀጣይ ከ4-5 አመታት ምርት በየአመቱ እንዲጨምር ማድረግ ይቻላል። ስለሆነም በ2015 በጀት ዓመት የታካመውን 130 ሺህ ሄ/ር መሬት መነሻ በማድረግ በቀጣይ ሶስት ዓመታት

በየዓመቱ 300 ሺህ ሄ/ር መሬት በኖራ በማከም በሶስተኛው ዓመት መጨረሻ 900 ሺህ ሄ/ር ለማከምና ወደ ምርት የመስገባት ሥራ ይሰራል::

ሌላው የአፈር ጨዋማነት ችግር ሲሆን በተፈጥሮ (Geological/Parent Material) ፣ ጨዋማነት ባለው የከርሰ-ምድር ውሃ ወደላይ መምጣት፣ ጨዋማነት ይዘት ባለው የመስኖ ውሃ በመጠቀምና ኋላቀርና ውሃ አባክኝ በሆነ የመስኖ ውሃ አጠቃቀም ምክንያት ሊፈጠር ይችላል:: በተለያዩ ጊዜያት የተጠኑ ጥናቶች እንዳሚያሳዩት ኢትዮጵያ ከ11 ሚሊየን ሄ/ር በላይ በጨዋማ አፈር በተሸፈነ መሬት ስፋት ከሰሃራ በታች ባለው የአፍሪካ ክፍል አንደኛ ደረጃ መያዝዋንና በቅርብ ጊዜ በአገሪቱ እየተደረገ ባለው የመስኖ ልማት ማስፋፋት ጋር ተያይዞ ችግሩ ከዚህም በላይ እንደሚሰፋ ይገመታል::

ይህንንም ችግር ለመቀነስ በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት 60 ሺህ ሄ/ር በጨዋማነት የተጠቃ አፈር ለማከም ታቅዷል:: የኮትቻ አፈርን በማንጣፈፍ ወደ ልማት ከማስገባት አንጻርም በ2015 በጀት ዓመት 660 ሺህ ሄ/ር መሬት ማንጧፈፍ የተቻለ ሲሆን በቀጣይ ሶስት ዓመታት 2.50 ሚ/ን ሄ/ር በማንጣፈፍ ወደ ልማት ለማስገባት ታቅዷል:: በተመሳሳይ ሁኔታ የአፈር ለምነትና ጤንነትን ለመጠበቅ የተፈጥሮ ማዳበሪያ (ኮምፖስት፣ቨርሚ ኮምፖስት፣ ባዮ ሳላሪ፣) በመጠቀም የአፈር ምርታማነትን በዘላቂነት የማሻሻል ሥራዎች በትኩረት ይሰራሉ::

ዘመናዊ የአፈር ሀብት መረጃ ዝርጋታን በተመለከተ በቀጣይ ሶስት ዓመታት ብሔራዊ የአፈር መረጃ ሥርዓት (NSIS - National Soil Information System) በማሻሻል እንዲሁም የአፈር መረጃ አያያዝና ልውውጥ መመሪያ ሰነድ እንዲፀድቅ በማድረግ ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል::

የአፈር ላቦራቶሪዎችን አቅምና የአሰራር ደረጃ ለማሻሻል አዲስ ደረጃውን የጠበቀ ብሄራዊ የአፈር ምርመራ ላቦራቶሪ ግንባታ ለማካሄድ ታቅዷል:: በተጨማሪም ሌሎች የክልል አፈር ምርመራ ላቦራቶሪዎችን በማጥናት የደረጃ መስፈርት በማዘጋጀት ደረጃ መስጠት፣ ደረጃቸውን በማሻሻል አስተማማኝ፣ ገበያ ተኮር እና ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ የማድረግ ስራ ይሰራል::

እንደዚሁም ከአጋር አካላት ጋር (በተለይ OCP) ጋር በመተባበር ጥራታቸውን የጠበቁ ተንቀሳቃሽ የአፈር ምርመራ ላብራቶሪዎችን በሙከራ ደረጃ ተግባራዊ በማድረግ እና በማስፋፋት ገበያ ተኮር የሆነ አገልግሎት እንዲሰጡ ማስቻል እና አገልግሎቱን በስፋት ተደራሽ የማድረግ ስራ ይሰራል::

የአፈር ሀብት ዓይነትና ባህርይ ልየታ ለአፈር ጤንነትና ለምነት ማሻሻያ ሥራዎች መነሻ በመሆኑ በቀጣይ ሶስት ዓመት በ400 ወረዳዎች የአፈር ሀብት ዓይነት ልየታና ካርታ የማዘጋጀት ሥራ ይከናወናል:: የአፈር ምርመራ ውጤትን፣ የሰብል የንጥረ-ነገር ፍላጎትንና ሥነ-ምህዳር መሰረት በማድረግ እንዲሁም ተንቀሳቃሽ የአፈር ላቦራቶሪዎችንና የጂኦ-ስፓሻል ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ በማዋል በቀጣይ ሶስት ዓመት ለ60 ሺህ ሄ/ር ማሳዎች የማዳበሪያ ዓይነት ምክረ-ሐሳብ ካርታ ይዘጋጃል::

### 3.3.4. ያደገ የመስኖ ሽፋንና አጠቃቀም

የመስኖ ውሃ በበቂ መጠን ማቅረብና አጠቃቀሙን ማሻሻል የግብርናውን ዘርፍ በዘላቂነት ለማሳደግ ወሳኝ ነው፡፡ ስለሆነም በአገራችን ዋነኛ የመስኖ ውሃ ምንጭ ከሆኑት የዝናብ፣ የከርሰ-ምድርና የገፀ-ምድር ውሃ የምናገኘውን ውሃ ዘመኑ የደረሰባቸውን ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም ግብርናውን ከዝናብ ጥገኝነት በማላቀቅ በዓመት ሁለትና ከዚያ በላይ ጊዜ በማምረት ምርትና ምርታማነትን በከፍተኛ ሁኔታ ማሳደግ ይቻላል፡፡ የመስኖ ውሃ አቅርቦትና አጠቃቀምን ማሻሻል ተገቢ ባልሆነ የመስኖ ውሃ አጠቃቀም ምክንያት የሚከሰተውን የአፈር ጨዋማነትና ተያያዥ ችግሮች ከመፍታት ባሻገር ተፋሰስን መሠረት በማድረግ ለሚሠሩ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም ሥራዎች ውጤታማነት ጉልህ አስተዋፅዖ ያደርጋል፡፡

ተፈጥሮ ሀብታችን በዘላቂነት ጥቅም ላይ ለማዋል በሶስት ዓመቱ በአዲስ 94.90 ሺህ ሄ/ር ለመስኖ ልማት ዝግጁ ይሆናል፡፡ ይህም 251.90 ሺህ አርሶ/ከፊል አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ያደርጋል፡፡ የመስኖ ውሃ አጠቃቀም ብቃት ያለበትን ደረጃ በጥናት ለማረጋገጥ የተጀመረው ስራ እንዲጠናቀቅ ይደረጋል፡፡ በተቀመጠው ምክረ-ሀሳብ መሰረትም የተለያዩ የውሀ አጠቃቀምን የሚያሻሽሉ አሰራሮች ተግባራዊ መደረግ ይጀምራሉ፡፡

የመስኖ መሠረተ ልማትን ማስፋፋት አስመልክቶ ከፍተኛ ሀብት የሚጠይቅ በመሆኑ በዘላቂነት ሀብት የሚገኝበትን ሥርዓት መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ በዚሁ መሰረት በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት 388 በማህበረሰብ የሚተዳደሩ የመስኖ ተቋማት ይዘጋጃሉ፡፡

የመስኖ አውታሮች እድሳትና ጥገናን በሚመለከት በተለያዩ ምክንያቶች ተበላሽተው አገልግሎት የማይሰጡ ወይንም ከአቅማቸው በታች አገልግሎት የሚሰጡ የመስኖ አውታሮችን እድሳትና ጥገና በማካሄድ በሙሉ አቅማቸው አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ የመስኖ ሽፋንን የማሳደግ ሥራ ይሠራል፡፡ በዚህም መሰረት በቀጣይ ሶስት ዓመታት 123 ነባር የመስኖ አውታሮች መልሶ የማቋቋም እና የማሻሻያ ሥራ ይሰራል፡፡

የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ እና የቅርብ ከርሰ-ምድረ ውሀ ለመስኖ አገልግሎት ለማዋል እንደ ሀገር ከፍተኛም ሆነ ዝቅተኛ አማካይ ዓመታዊ ዝናብ ባለባቸውም አካባቢዎች በትርፍነት ጎርፍ ሆኖ የሚባክነውን ውሃ በመያዝ ወደ ልማት መቀየር ቢቻል በዝናብ እጥረትና አለመስተካከል ምክንያት የሚመጣውን የምርታማነት ችግር በከፍተኛ ሁኔታ መፍታት ይቻላል፡፡ ለዚህም በቤተሰብ ደረጃ የሚተገበሩ የውሃ ማሰባሰብ ሥራዎችን ውሃ ከሚቆጥቡ አሰራሮች ጋር በማቀናጀት ይተገበራል፤ በማህበረሰብ ደረጃ አገልግሎት የሚሰጡ ኩሬዎችንና አነስተኛ ግድቦችን በመገንባት የመስኖ መሬቶች እንዲለሙ ይደረጋል፡፡

አማራጭ አቅርቦቶችንና ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የመስኖ ልማት ተደራሽነትን በሁሉም ስነ-ምህዳር ለማስፋፋትና ለማጠናከር በደጋማ አካባቢዎች የተራራ ላይ የመስኖ ልማትን በማጠናከር፣ በቆላማና በደጋማ አካባቢዎች የከርሰ-ምድር ውሃ አጠቃቀምና አስተዳዳር ሥርዓትን በማጠናከርና በከተሞች አካባቢ የፍሳሽ ውሃን አጣርቶ በመጠቀም የከተማ የመስኖ ልማት ማስፋፊያ ተክኖሎጂዎችን ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ እንዲሁም ሌሎች ውሃና ሃይል ቆጣቢ የሆኑ ቴክኖሎጆዎችን በማላማድና ተደራሽነትን በማስፋት የመስኖ ልማቱን እንዲፋጠን ይደረጋል፡፡



ለኔ ዘሪሁን ሀ/ወልድ
የስትራቴጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

የመስኖ አውታርና ውሀ አስተዳደርና አጠቃቀም ለማሻሻል በሚሰሩ ስራዎች በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት ለተደራጁ 225 የመስኖ ውሀ ተጠቃሚ ማህበራት የአቅም ግንባታ ስራዎች ይሰራሉ፤ የመስኖ ውሃ አጠቃቀም የተሻለ እንዲሆን የውሀ አጠቃቀም ብቃት ከተካሄደባቸው የመስኖ አውታሮች ውስጥ ምክረ-ሀሳቦችን በመተግበር 25% የተሻለ የውሀ አጠቃቀም እንዲኖራቸው ይደረጋል።

የመስኖ ልማት የመረጃ ስርዓትና እንደ ሀገር ከፍተኛ ክፍተት ያለበት መሆኑ ይታወቃል። በዚህም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በመጠቀም የመስኖ አውታርና ውሃ አያያዝና አጠቃቀም የመረጃ ሥርዓት ለመዘርጋት ባለፉት አመታት ተጀምሮ ወደ ትግበራ ተገብቷል። ይህንንም ከግብ ለማድረስ ከላይ እስከ ታች ላለው ባለሙያና አመራር ሰፊ የግንዛቤ ስራ በመፍጠር መረጃዎቹ በተዘጋጀው የመረጃ ስርዓት እንዲገቡና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል። ይኸውም በመረጃ ስርዓቱ የሚገቡ የመስኖ አውታሮችን ብዛትና የአጠቃቀም ሁኔታና አጠቃላይ ገጽታ የሚያሳይ፤ የሰብል ውሃ ፍላጎትና የመስኖ ውሃ ማጠጫ መርሃ-ግብርን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (ICT) የሚደግፍ የመስኖ አስተዳደር ኢንፎርሜሽን ሲስተም ይጠናከራል።

## 3.3.5. ግብርና ምርምር፡ ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም

በቀጣይ ሦስት ዓመታት በምርምር የሚወጡት ቴክኖሎጂዎች (ዝርያዎች)ከሚገኙ አብዛኛው ዝርያዎች በምርታማነት በ10 ፐርሰንት ብልጫ ያላቸው ሲሆን እነዚህን በምርምር የመነጩትን ቴክኖሎጂዎችና መረጃዎችን በተገቢዉ መልኩ በመቀመርና የኤክስቴንሽን ፓኬጅ አካል ሆነው ወደ ምርት ስርዓት ውስጥ ሲገቡ ምርትና ምርታማነትን በማሻሻል ለምግብ ዋስትና፣ ለውጭ ገበያና ለአግሮ ኢንዱስትሪ ግብዓት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ይሆናሉ።

### ሀ) የቴክኖሎጂና መረጃ አቅርቦት

በመካከለኛው የልማት ዕቅድ ዘመን የቴክኖሎጂና መረጃ አቅርቦትን በተመለከተ በማላመድና በማፍለቅ እንድሁም በመስረታዊ የምርምር አሰራሮች በመታገዝ በአጠቃላይ 49 አዳዲስ የግብርና ቴክኖሎጂዎች እንዲሁም 220 በመረጃና የአሰራር ዘዴዎች አቅርቦት በድምሩ 269 ውጤቶችን እንደሚያቀርብ ይጠበቃል። እነዚህ ውጤቶች ሲገኙ ምርትና ምርታማነትን በማሻሻል ለምግብ ዋስትና፣ ለውጭ ገበያ፣ ለአግሮ ኢንዱስትሪ ግብዓት፣ ለአካባቢ ጥበቃ እና ለፖሊሲ ግብዓትነት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ናቸው።

### ለ) የቴክኖሎጂ ማስተዋወቅ

አዳዲስና የተሻሻሉ እንዲሁም አርሶ አደሩን፣ አርብቶ አደሩንና ባለሃብቱን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ቴክኖሎጂዎችን በስፋት ለማስተዋወቅና በፍጥነት ወደ ልማቱ እንዲገቡ ለማድረግ ኢንስቲትዩቱ በቴክኖሎጂ በመስክ ቀንና በአርሶና አርብቶ አደር የልምድ ልውውጥ በቅንጅት የማስተዋወቅ ስራዎችን በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች በሦስት ዓመቱ ለ7195 የቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች ወካይ ወረዳዎች ላይ ተደራሽ ይደረጋል።

ከኩ ዜና ሀ/ወልድ የስትራቴጂክ ጉዳዮች ሥራ አስፈጻሚ

## ሐ) የቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች ስልጠና

ስልጠና ከምርምር በወጡ ቴክኖሎጂዎች ዙሪያ ለተጠቃሚዎች ግንዛቤ በመስጠት የምርምር ውጤቱን በአግባቡ ስራ ላይ እንዲያውሉት ለማድረግ የሚያግዝ የአቅም ግንባታ ተግባር ነው። በቀጣይ ሦስት ዓመታት በተቋሙ ስር ባሉ የተለያዩ የምርምር ዳይሬክቶሬቶች /ንዑስ ፕሮግራሞች/ በድምሩ 10748 የቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎችን ለማሰልጠን ታቅዷል።

## መ) የመነሻ ቴክኖሎጂ ብዜት

የመነሻ ቴክኖሎጂ ብዜት ጋር በተያያዘ ለቀጣይ ሦስት ዓመታት በተፈጥሮ ሀብትዘርፎች ሥር ይከናወናሉ። በዚህም መሠረት በተፈጥሮ ሃብት አያያዝ ልማት የአፈር ለምነትን ለመጠበቅ 64,211 ፓኬት የራይዞቢያ ሕየውማዳበሪያ (ባዮፈርቲላይዘር)፣ 294 ኩ/ል ቨርሚኮምፖስት ለማባዛት ታቅዷል። በተጨማሪም በግብርና ምህንድስና ዘርፍ 43 ልዩ ልዩ የቅድመ-ምርት፣ ምርት እና ድህረ-ምርት የእርሻ መሣሪያዎችን ለማባዛት ዕቅድ ተይዟል።

## ሠ) አገራዊ የግብርና ምርምር ሥርዓትን ማስተባበር እና ማጠናከር

በአገር አቀፍ ደረጃ የግብርና ምርምር ሥራዎችን በማቀናጀት ውጤታማነትን ለማሳደግ እና ምርምሩን ለማዘመን ማስተባበር፣ የምርምር ውጤቶች ተደራሽነትን ለማስፋት የአዋጪ ቴክኖሎጂዎችን ሽግግር ማስተባበር፣ አገራዊ የግብርና ምርምር ብቃትና አቅምን መገንባት፣ የግብርና ምርምርን በተመለከተ አገራዊና አለምአቀፋዊ ግንኙቶችን ማጠናከር፣ የተመረጡ የግብርና ምርምር ፕሮጀክቶችን መደገፍ እንዲሁም ከአግሮ ኢንዱስትሪ ልማት ጋር ያለውን ትስስር በማጠናከር ይሰራል።

### 3.3.6. የደን ልማት

### የመካከለኛ ዘመን (2016-2018) የልማት ዕቅድ እንድምታዎች እና የሚጠበቁ ውጤቶች

ለአየር ንብረት ለዉጥ የማይበገር አረንጓዴ ስትራቴጂ ለይቶ ካስቀመጣቸው አራት ዋና ዋና ምሰሶዎች መካከል አንዱና ዋነኛው የደኑ ዘርፍ ነው። የደኑ ዘርፍ ዋነኛ ምሰሶ የሆነበትም ምክንያት በሀገራችን በፈጣን ሁኔታ በማደግ ላይ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ልማት ደህንነትና ዘላቂነት ለማረጋገጥ መንግስት ከሁሉም ሴክተሮች ወደ አየር በሚለቀቁ በካይ ጋዞች ምክንያት የሚመጣውን የአየር ብክለት ለመቀነስ የደኑ ዘርፍ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው በመታመኑ ነው። በዚህም ምክንያት በሀገራችን ለደኑ ዘርፍ ልዩ ትኩረት በመስጠት ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ያላቸው በቢሊዮን የሚቆጠሩ የደን ችግኞች በየአመቱ እንዲተከሉ በማድረግ፣ ትኩረት የተሰጣቸውን የተፈጥሮ ደኖች በመንከባከብ እና በመጠበቅ፤ የተራቆቱ አካባቢዎች በተደራጀ የህዝብ ተሳትፎ እንዲያገግሙ በማድረግ የሀገራችንን የደን ሽፋን ለመጨመር የሚያስችሉ በርካታ ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል። በየክልሉ ተሳትፎአዊ የተፋሰስ ልማት ሥራዎች በተደራጀ የሕዝብ ንቅናቄ ርብርብ ተደርጎ በመሰራቱ ምክንያት በከፍተኛ ደረጃ ተራቁተው የነበሩ አካባቢዎች አፈራቸውና እርጥበታቸው በመመለሱ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያላቸው ዕፅዋቶች በማልማት ተራራዎች የሃብት ምንጭ መሆን ጀምረዋል።

ወደ አየር በሚለቀቁ በካይ ጋዞች ምክንያት የሚመጣውን የአየር ብክለት ከመቀነስ ባሻገር የሀገራችንን የደን ልማት በማስፋፋት የሕዝቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ፣ የሥርዓተ- ምህዳር ቀጠናዎችን ሚዛን እንዲጠበቅ ለማድረግና በሀገር ኢኮኖሚ እድገት ላይ የራሱን ድርሻ እንዲያበረክትና በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚደርሰውን የድርቅ እና የጎርፍ አደጋ በአስተማማኝ ደረጃ ለመቋቋም የደን ሃብት ቁልፍ ሚና እንዳለው በልማት ፖሊሲዎቻችንና ስልቶቻችን ላይ በግልጽ ተቀምጧል። የደኑ ዘርፍ በቤተሰብ እና በሀገር ኢኮኖሚ እድገት ላይ የራሱን ድርሻ እንዲያበረክት ከማድረግ አንጻር እያደገ የመጣውን የህብረተሰቡን የደን ምርት ውጤት ፍላጎትን ለሟሟላት፣ ለቤተሰብ ፍጆታ እና ተጨማሪ የጥሬ ገንዘብ ለማስገኘት፣ ከውጪ የሚገቡ የተለያዩ የደን ውጤቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች ለመተካት፣ በደን ልማት፣ ጥበቃ፣ አጠቃቀም እና በተለያየ ደረጃ ባሉ የደን ኢንዱስትሪዎች ለበርካታ ዜጎች የስራ ዕድል በመፍጠር እንዲሁም ወደ ውጪ የሚላኩ የደን ውጤቶችን በማምረት እና ወደ ውጪ በመላክ ሀገራችን የውጭ ምንዛሬ ከዘርፉ እንድታገኝ ሲደረግ ቆይታል። የደኑ ዘርፍ ለሃገራችን አጠቃላይ የሃገር ውስጥ ምርት (GDP) እስከ 12.8 ፐርሰንት ድርሻ እንዳለው ጥናቶች ያመላክታሉ። በተጨማሪም የደኑ ዘርፍ ለግብርና፣ ለኢነርጂ፣ ለውሃ፣ ለጤና፣ ለቱሪዝም ወዘተ እያበረከተ ያለው ግልጋሎት ከፍተኛ ነው። በአጠቃላይ በሀገራችን እየተሰሩ ያሉ የደን ልማት፣ እንክብካቤ እና ጥበቃ ስራዎች በአለም አቀፍ እና በአህጉር ደረጃ የሀገራችንን መልካም ገጽታና የተሰሚነት ደረጃ ከፍ እንዲል አስችሏል።

ከላይ የተጠቀሱትን ለማሳካትም በቀጣዩ የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ የአስር ዓመት የልማት መሪ ዕቅድ መሰረት የተለያዩ የደን ልማትና ምርምር ስራዎች ይከናወናሉ። በዚህም መሰረት በሚደረገው የደን ልማትና ጥበቃ ስራ ከደን ዘርፍ  የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት በ33 ሚ/ን ቶን ለመቀነስ፣በደን ጥበቃ እና አጠቃቀም ህጎች ዙሪያ ለ7.5 ሚ/ን ለተለያዩ ማህበረሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ለመስጠት፣ በደን የተሸፈነ መሬት ድርሻን 20 በመቶ ለማድረስ፣ በ2.4 ሚ/ን ሄ/ር መሬት ላይ ተከላ ለማካሄድ፣ 7.5 ቢ/ን ደረጃቸውን የጠበቁ ችግኞች ለማዘጋጀት፣ የቀርከሃ ደን ሽፋን 0.06 ሚ/ን ሄ/ር ለማድረስ፣ 3 ሚ/ን ሄ/ር የተራቆቱ የደን መሬቶችን በመለየት እንዲያገግሙ ለማድረግ፣በ22.24 ሚ/ን ሄ/ር መሬት ላይ ነባር የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ደኖችን ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብና በዘላቂነት ለመጠቀም የሚያስችል ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ፣ 0.6 ሚ/ን ሄ/ር ላይ የደን ማኔጅመንት ፕላን ለማዘጋጀት፣ ነባር የአሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓትን 3.06 ሚ/ን ሄ/ር ላይ እንዲታቀፉ ለማድረግ፣ አዲስ የአሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓትን በ1.19 ሄክታር መሬት ላይ ተግባራዊ ለማድረግ፣ ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ የቀረበ የደን ምርት መጠን 6 ሚ/ን ቶን ለማድረስ፣ ከደን ሮያሊቲ የተገኘ ሀብት መጠን 900 ሚ/ን ብር ለማድረስ፣ ከደን ምርት ኤክስፖርት የተገኘ እና በሃገር ውስጥ የደን ምርት ምክንያት የዳነ የውጭ ምንዛሪ መጠን 84 ሚ/ን ዶላር ለማግኘት እና ለ0.375 ሚ/ን ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር እቅድ ተይዟል።

በተመሳሳይ በቀጣዩ የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ የአስር ዓመት የልማት መሪ ዕቅድ መሰረት የልማቱን ፍላጎት የሚያሟላ በዓይነትና በጥራት በቂ የቴክኖሎጂ እና የመረጃ አቅርቦት ይኖር ዘንድ በሰው ሰራሽ ደን ምርምር 48 መረጃና ቴክኖሎጂ ለማዉጣት፣ በተፈጥሮ ደንና አየር ንብረት ለዉጥ ምርምር 23 መረጃና ቴክኖሎጂ ለማዉጣት፣ በደን ውጤቶች ኢኖቬሽን ምርምር 34 መረጃና ቴክኖሎጂ ለማዉጣት እና በፖሊሲና ሶሺዮ-ኢኮኖሚክስ ምርምር 18 መረጃ ለማዉጣት በእቅድ የተያዘ ሲሆን በድምሩ 123 የደን ምርምር ቴክኖሎጂዎች እና መረጃዎች ለማውጣት፣ እንዲሁም አዳዲስና ነባር ቴክኖሎጂዎችና መረጃዎችን ከተለያዩ አካላት ለተዉጣጡ ለ600 የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ የህብረተሰብ ክፍሎች ለማስተዋወቅ እና ስልጠና ለመስጠት በእቅድ ተይዟል።

### 3.3.6.1. የደን ሃብት ይዞታ እና ጥቅሞች

ሀገራችን የተለያዩ የመሬት አቀማመጥ፣ የአየር ንብረት እና በርካታ ተፈጥሮአዊ ስርዓተ ምህዳሮችን ያቀፈችና ይህንንም ተከትሎ የተለያየ የደን ሃብት፣ የዱር እንስሳትና የብዝሃ-ህይወት ባለቤት ስትሆን የደን ሽፋናችንም 19.2 ሚ/ን ሄ/ር (17.2%) ሆኖ በአራት የደን አይነቶች (Biomes) የተከፈለ ነው።

ይህ የደን ሃብታችን በቤተሰብ እና በሀገር ኢኮኖሚ እድገት ላይ የራሱን ድርሻ እያበረከተ ሲሆን እያደገ የመጣውን የህብረተሰቡን የደን ምርት ውጤት ፍላጎትን በሟሟላት፣ ለቤተሰብ ፍጆታ እና ተጨማሪ የጥሬ ገንዘብ በማስገኘት፤ ከውጪ የሚገቡ የተለያዩ የደን ውጤቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች በመተካት፣ በደን ልማት፣ ጥበቃ፣ አጠቃቀም እና በተለያየ ደረጃ ባሉ የደን ኢንዱስትሪዎች ለበርካታ ዜጎች የስራ ዕድል በመፍጠር እንዲሁም ወደ ውጪ የሚላኩ የደን ውጤቶችን በማምረት እና ወደ ውጪ በመላክ ሀገራችን የውጭ ምንዛሬ ከዘርፉ እንድታገኝ አስተዋፅኦ በማበርከት ላይ ይገኛል። የደኑ ዘርፉ ለሃገራችን አጠቃላይ የሃገር ውስጥ ምርት (GDP) እስከ 12.8 ፐርሰንት ድርሻ እንዳለውም ጥናቶች ያመላክታሉ። ከዚህ ባሻገር የደኑ ዘርፍ ለግብርና፣ ለኢነርጂ፣ ለውሃ፣ ለጤና፣ ለቱሪዝም ወዘተ እያበረከተ ያለው ግልጋሎት ከፍተኛ ሲሆን የደን ሃብታችን ወደ አየር በሚለቀቁ በካይ ጋዞች ምክንያት የሚመጣውን የአየር ብክለትን በመቀነስ እና የሥርዓተ- ምህዳር ሚዛን እንዲጠበቅ በማድረግ በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚደርሰውን የድርቅ እና የጎርፍ አደጋ ለመቋቋም ቁልፍ ሚና አለው።

ስለሆነም ከደን ሃብታችን የሚገኙትን ጥቅሞች በዘላቂነት ለማስቀጠል የተፈጥሮ ደኖቻችንን ለመጠበቅ፣ በሰው ሰራሽ መንገድ ተጨማሪ ደን ለማልማት፣ ሀገራችን ለአለም አቀፍ ማህበረሰብ ቃል የገባችበትን የተራቆተ እና የተመናመነውን የደን ሃብት መልሶ ለማልማት ማህበረሰቡን፣ የግል ሴክተሩን፣ የመንግስት ደን ኢንተርፕራይዞችን በማሳተፍና የአለም አቀፍ የልማት አጋሮችን ድጋፍ በማሳደግ በመካከለኛ ዘመን ዕቅድ በትኩረት ይሰራል። በአጠቃላይ የአረንጓዴ አሻራ ስራን ጨምሮ በሀገራችን እየተሰሩ ያሉ የደን ልማት፣ እንክብካቤ እና ጥበቃ ስራዎች በአለም አቀፍ እና በአህጉር ደረጃ የሀገራችንን መልካም ገጽታና የተሰሚነት ደረጃ ከፍ እያደረጉ ስለሆነ ከምንጊዜውም በላይ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

ዜና ሀብተወልድ
የስትራቴጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

### 3.3.7. ብዝሀ ሕይወት ጥበቃና አጠቃቀም

አሰሳና ቅኝት የተደረገባቸው ዝርያ/ቦታ/ በ2015 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 3/14/ ዝርያ/ቦታ (በ2018 በጀት ዓመት 595 ዝርያ 32 ቦታዎች አሰሳና ቅኝት ማድረግ፤ ለጥቅም ላይ የዋሉ ብዝሀ ህይወት እና ተያያዥ የማህበረሰብ ዕውቀቶች ዝርያዎች/ጥናቶች በቁጥር በ2015 በጀት ዓመት ያልነበረ ሲሆን ( በ2018 በጀት ዓመት 19/9 ዝርያ/ጥናት ማድረስ፤ ለቀጣይ ምርምር፣ልማትና መልሶ ለመተካት የተሰራጩ የብዝሀ ሕይወት ሀብት በ2015 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 470 ዝርያዎች 45,325 ናሙናዎችና 7,000 አባላዘር በቀሰም - በ2018 በጀት ዓመት 620 ዝርያዎች 75,925 ናሙናዎችና 10,000 አባላዘር በቀሰም ማድረስ፣ በብዝሀ ሕይወት እና ተያያዥ የማህበረሰብ ዕውቀቶች ላይ የተካሄደ ምርምርና ልማት በ2015 በጀት ዓመት ከተደረሰበት የምርምር ብዛት 3 ለማካሄድ ታቅዷል ወደ በ2018 በጀት ዓመት በቁጥር 85 ለማካሄድ ታቅዷል፤ በዘቦታና በኢዘቦታ የተነበሩ በ2015 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 245 ዝርያ፣ 1,242 ናሙናዎች እና 4,776 አባላዘር በቀሰም ወደ በ2018 በጀት ዓመት 9,155 ዝርያ፣ 11,886 ናሙናዎች እና 18,000 አባላዘር በቀሰም ማድረስ፣ በ2015 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 1,329 ለምርምር ዓላማ እና ጥቅም ተጋሪነት የአርክቦት ፈቃድ ወደ በ2018 በጀት ዓመት 3,318 ለምርምር ዓላማ እና ጥቅም ተጋሪነት የአርክቦት ፈቃድ ማድረስ፤ ከወራሪ መጤ ዝርያዎች ነፃ የተደረጉ ቦታዎች ሽፋን በ2015 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 233,111 ሄክታር መሬት - በ2018 በጀት ዓመት 160,000 ሄክታር መሬት ነፃ ለማድረግ ታቅዷል።

### የተፈጥሮ ሀብት ልማት ዘርፉን ሊደግፉ የሚችሉ ኢንሼቲቮች

አገራዊ የአፈር ጤንነትና ለምነት ንቅናቄ በአሲዳማ፤ ጨዋማ እና ኮትቻ አፈርን ማልማት እንዲሁም በተፈጥሮ ማዳበሪያ አጠቃቀምን ተግባራዊ በማድረግ የአፈር ጤንነትና ለምነት የማሻሻል ሥራዎችን ማከናወን የግብርና ምርትና ምርታማነትን በእጅጉ የሚያሳድግ በመሆኑ፤ የአራንጓዴ አሻራ መርሀ-ግብር የተተከሉ ችግኞችን በተፋሰስ ልማት ከተሠሩ ከአካላዊና ሥነ-ህይወታዊ አፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች ጋር አቀናጅቶ ማስኬድ፤ የተፋሰስ ተጠቃሚ አርሶ አደሮች የህ/ሰብ ደኖች ልማትን (Community Forestry Development) እንዲያሳልጥ የማድረግ ሥራ በትኩረት መፈፀም፤ በመጀመሪያ አራንጓዴ አሻራ መርሀ-ግብር የተተከሉ ችግኞችን እንክብካቤ የማድረግ ሥራዎች ላይ ትኩረት ይደረጋል፤

የሁለተኛ ዙር አረንጓዴ አሻራ ልማት መርሀ-ግብር ፕሮግራምን ከማሳለጥ አንፃር ነባር ችግኝ ጣቢያዎችን በማጠናከርና አዳዲስ ችግኝ ጣቢያዎችን ከማቋቋም ጎን ለጎን አገራዊ የንቅናቄ መድረክ በመፍጠር በህዝብ ንቅናቄ የታጀበ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ስራዎችን በማከናወን የአረንጓዴ ኢኮኖሚ የመገንባት አቅቅጫን ላይ ትኩረት ይደረጋል።

የመስኖ ውሃ አስተዳደርና አጠቃቀም አነሳሽ (Initiative) በተመለከተ ተቋማዊ አቅም ግንባታ ሥራዎችን እስከ መስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ህ/ሰብ ድረስ በመፈፀም የመስኖ ውሃ አስተዳደርና አጠቃቀም ክህሎትን ማሳደግ። ይኼውም የመስኖ ውሃን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ መጠቀም የአፈር ጨዋማነትን ከመቀነስም ባሻገር ምርትና ምርታማነትን እንዲጨምር የሚያደርግ መሆኑን፤ በየደረጃው ያሉ የግብርና ምርምር ማዕከላት ለመስኖ ውሃ አጠቃቀም የሚሆኑ ቴክኖሎጂዎችን እንዲያወጡ ከማድረግ አንፃር ከምርምር ማዕከላት ጋር ተቀናጅቶ በመሥራት የመስኖ ውሃ ቴክኖሎጂዎችን አርሶ/አርብቶ አደሩ በስፋት

እንዲጠቀሙ ማድረግ የውሃ አጠቃቀም ብቃት የሚያሳድግ በመሆኑ፤ የውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት የመስኖ ውሃ መለኪያ መሳሪያ እንዲጠቀሙ በማድረግ የውሃ አጠቃቀም ብቃት ደረጃውን ለመለየት ያስችላል። ይህ ከላይ የተጠቀሰ የመስኖ ውሃ አስተዳደርና አጠቃቀም የአሁናዊ የመስኖ ውሀ አጠቃም ችግሮችን የሚያስተካክልና በመስኖ የሚለማ የበጋ ስንዴ ያለባቸውን ማሳዎች የጨዋማነት ልኬት ቅኝት በማድረግ የአፈር ጨዋማነትን ለመቀነስና ለመከላከል ወሳኝ ጉዳይ በመሆኑ ነው።

አገራዊ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ (National Land Use Planning) በሚኒስትሮች ም/ቤት ለማስፀደቅ ቀርቦ በእንጥልጥል ላይ ያለውን አገራዊ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ እንዲፀድቅ በማስደረግ የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ በማዘጋጀት ለእርሻ መዋል የሚገባቸው መሬቶች ለእርሻ እንዲሁም ለሌሎች አገልግሎቶች መዋል ያለባቸው መሬት ለታለመለት ዓላማ እንዲውል በማድረግ በመሬት ላይ እየተፈፀመ ያለውን የተሳሳተ አጠቃቀም ተግዳሮቶች እልባት እንዲያገኝ ያደረጋል።

በተፈጥሮ ሀብት ልማት ዘርፍ ዘርፈ-ብዙ ጉዳዮች ተግባራትን በተመለከተ፡- የሴቶችንና ወጣቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ ረገድ በግብርና ኖራ እና በኮምፖስት ዝግጅትና ማምረት ተግባር ውስጥ የሥራ ዕድሎች እንዲፈጠር ይመቻቻል፤ የተለያዩ የፀረ-ኤችአይቪ መልእክት የያዙ መልእክቶችን በየሩብ አመቱ የተግባር አካል በማድረግ፣ በበራሪ ወረቀቶች የማስተላለፍ ሥራዎች ይከናወናሉ። ቫይረሱ በደማቸው ላለባቸው ሠራተኞች እና ወላጆቻቸውን በኤድስ ምክንያት ላጡ ህጻናት ድጋፍ የማድረግ ሥራ ይከናወናል፤ የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖዎችን የሚቀንሱ እንዲሁም ዝቅተኛ የካርቦን ልቀት ያላቸው ቴክኖሎጂዎችን በመተግበር የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀትን በመቀነስ ረገድ ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል።

## 3.4. የግብርና ኢንቨስትመንትና ግብይት

### 3.4.1. የግብርና ግብዓት አቅርቦት

የማዳበሪያ የአቅርቦት ሰንሰለትን ማሻሻልና ዘመናዊና ቀልጣፋ እንዲሆን ለማስቻል በማዳበሪያ አቅርቦት ሰንሰለት ማሻሻያ ጥናት የተቀመጡ ምክር ሃሳቦች ተግባራዊ ይደረጋሉ። እነዚህን የውሳኔ አቅጣጫዎች ተግባራዊ በማድረግ ማዳበሪያን ለአርሶ አደሩ በሚፈለገው ወቅት፣ መጠን፣ ጥራት፣ ዓይነት፣ ቦታ እና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ አስቻይ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ። በዚህም መሠረት በየዓመቱ የሚደረገውን የማዳበሪያ ግዢ አሠራር ወደ ተራዘመ ጊዜ አሰራር በመቀየር /ከ2-3 ዓመት/ የሚቆይ የግዢ ውል ከተለያዩ አምራቾች ወይም ከተመረጡ አቅራቢዎች ጋር ይፈጸማል። 2015/16 ምርት ዘመን አመታዊ የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት 1.62 ሚ/ን ሚ/ቶን ከተደረሰበት በቀጣይ ሶስት ዓመታት በ2016/17 ም/ዘመን 2.3 ሚ/ን ሚ/ቶን፣ በ2017/18 ም/ዘመን 3.1 ሚ/ሚ/ቶን፣ በ2018/19 ም/ዘመን 3.5 ሚ/ሚ/ቶን የአፈር ማዳበሪያ ለማቅረብ በትኩረት ይሰራል። ዕቅዱ ለሶስት የምርት ዘመናት ለበልግ፣ ለመኸር እና ለመስኖ ጥቅም ላይ የሚውል ታሳቢ የተደረገ ሲሆን በየዓመቱ ለአነስተኛ መሬታ ይዞታ ላላቸው አ/አደሮች እና በሰፋፊ ማሳ ላይ ለተሰማሩ ባለሃብቶች በሚል በዝርዝር ተለይቷል ።

ኣኣ ዜና ሀ/መልድ
የስትራቴጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

የአግሮ ኬሚካል አቅርቦትን በተመለከተ በ2015/16 ምርት ዘመን የቀረበው አግሮ ኬሚካል 1.32 ሚ/ን ሊ/ር ከተደረሰበት በቀጣይ ሶስት ዓመታት በ2016/17 ም/ዘመን 11.13 ሚ/ን ሊ/ር፣ በ2017/18 ም/ዘመን 11.44 ሚ/ን ሊ/ር እና በ2018/19 ም/ዘመን 11.58 ሚ/ን ሊ/ር ለማቅረብ ታቅዷል። በ2015 በጀት ዓመት የቀረበው ኬሚካል መረጃ ከግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን እና ከኦሮሚያ ፌዴሬሽን የተገኘ መረጃ ብቻን መሰረት ያደረገ ሲሆኑ ከ2016/17 ጀምሮ በሌሎች አቅራቢዎችን ታሰቢ ያደረገ በመሆኑ እቅዱ ተለጥጦ ታቅዷል።

በየምርት ዘመኑ ያስፈልጋሉ በሚል የታቀዱ ኬሚካሎች በሙያዊ ዕይታ የተቃኙ ፣ በየዓመቱ እየተከሰቱ ካሉ ክስተቶች በመነሳትና አጠቃላይ ሁኔታውን ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ነው። ታሳቢ ከተደረጉ ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል በየዓመቱ የበሽታ ፣ የነፍሳት እና የተባይ ክስተት መጨመር፣ የአየር ንብረት መቀያየር ለክስተቱ እንደ ምቹ ሁኔታ መጠቀም ፣ አካባቢን በመላመድ ቶሎ አለመሞት ማለትም በርካታ መጠን ያለው ኬሚካል መጠቀም የመሳሰሉት ዋና ዋናዎቹ ታሳቢ የተደረጉ ጉዳዮች ናቸው።

የግብርና ኖራ አቅርቦትን በተመለከተ ባለፉት ዓመታት ያልታከመ እና በጠንካራ አሲዳማነት ደረጃ ላይ ከሚገኘውን መሬት ውስጥ አቅም የፈቀደውን ያህል በየዓመቱ 300 ሺህ ሄ/ር ለማከም በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት 27 ሚ/ን ኩ/ል ኖራ ለማቅረብ የታቀደ ሲሆን በየዓመቱ 9 ሚ/ን ኩ/ል ኖራ እንደሚቀርብና አንድ ሄ/ር ለማከም 30 ኩ/ል እንደሚያስፈልግ ታሳቢ ተደርጓል።

የግብርና ብድር አቅርቦትን በተመለከተ በ2015/16 ም/ዘመን ለዋና ዋና ግብዓቶች መግዣ (የአፈር ማዳበሪያ፣ ለም/ዘር ፣ ለኖራ፣ ለኬሚካል እና ለትራንስፖርት) ጥቅም ላይ የዋለውን ብር 62.9 ሚ/ን ብር ታሳቢ በማድረግ ለሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት በአጠቃላይ 403.61 ቢ/ን ብር ለማቅረብ ታቅዷል። ይህም በየዓመቱ ሲተነተን በ2016/17 110.88 ቢ/ን፣ በ2017/18 133.06 ቢ/ን እና በ2018/19 159.67 ቢ/ን ብር እንደሚያስፈልግ ታሳቢ ተደርጓል።

የሰብል ምርጥ ዘር አቅርቦትን በሚመለከት በ2015/16 የተደረሰበት 1.5 ሚ/ን ኩ/ል ሲሆን በቀጣይ ሶስት በ2016/17 ም/ዘመን 2 ሚ/ን ኩ/ል፣ በ2017/18 ም/ዘመን 2 ሚ/ን ኩ/ል፣ በ2018/19 ም/ዘመን 2 ሚ/ን ኩ/ል የሰብል ም/ዘር ለማቅረብ ታቅዷል። ይህም የዋና ዋና ሰብል ዓይነቶች ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ነው። ይህን ለማሳካት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፣ ከመነሻ ዘር እስከ ስርጭት ያሉ ተግባራት በተዘረጋው የዘር ፍኖተ ካርታን መሰረት በማድረግ ይፈጸማል ፣ የፍላጎት ፣ የአቅርቦትና የስርጭት ስራዎችን ለማዘመን የተጀመረው የዘር ዲጅታላይዜሽን ስራ ተግባራዊ ይሆናል።

የእንስሳት ግብዓት አቅርቦትን በተመለከተ የአንድ ቀን የዶሮ ጫጩት አቅርቦት በ2015 በጀት አመት ከተደረሰበት 41 ሚ/ን አመታዊ የአንድ ቀን ጫጩት አቅርቦት በቀጣይ ሶስት ዓመታት በ2016 በጀት ዓመት 62 ሚ/ን፣ በ2017 በጀት ዓመት 82 ሚ/ን እና በ2018 በጀት ዓመት 124 ሚ/ን አንድ ቀን ጫጩት ለማቅረብ ታቅዷል። ይህን እቅድ የተቀመጠው ለሌማት ትሩፋት ኢኒሼትቭ ለማሳካት በሚያስችል መልኩ የተዘጋጀ ነው።

ዘመናዊ የንብ ቀፎ አቅርቦት ለማሳደግ በ2015 በጀት አመት ከተደረሰበት 291.7 ሺህ አመታዊ የዘመናዊ የንብ ቀፎ አቅርቦት በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት በ2016 በጀት ዓመት 1,100 ሺህ ፣ በ2017 በጀት ዓመት 1,210 ሺህ እና በ2018 በጀት ዓመት 1,331 ሺህ ዘመናዊ የንብ ቀፎ ለማቅረብ ታቅዷል።

የእንስሳት መኖ ዘር አቅርቦት በተመለከተ በ2015 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 2.83 ሺህ ቶን በ2016 በጀት አመት 2.98 ሺህ ቶን፣ በ2017 በጀት ዓመት 3.27 ሺህ ቶን እና በ2018 በጀት ዓመት 3.6 ሺህ ቶን የመኖ ዘር ለማቅረብ ታቅዷል በተመሳሰይ ሁኔታ የዓሳ ጫጩት አቅርቦት ለማሳደግ በ2015 በጀት አመት ከተደረሰበት 0.94 ሚ/ን አመታዊ የዓሳ ጫጩት አቅርቦት አቅም በማሳደግ በ2016 በጀት ዓመት 6.78 ሚ/ን፣ በ2017 በጀት ዓመት 7.46 ሚ/ን እና በ2018 በጀት ዓመት 8.2 ሚ/ን ለማቅረብ ታቅዷል።

## 3.4.2. የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት

የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት የአየር ንብረት ለውጥንና ስርዓተ ፆታን ባማከለና ከተፈጥሮ ሀብት ጋር ተስማሚ በሆነ መልኩ የሜካናይዜሽንና የመስኖ ልማት ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት፣ ስርጭትና፣ አጠቃቀም በማሳደግ ምርት፣ ምርታማነትና ጥራት ለማሳደግ ነው።

በዚሁ መሰረት በግብርና ሜካናይዜሽን የተደገፈ የሰብል ልማትና ጥበቃ ሥራን በተመለከተ በ2015 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 2.8 ሚ/ን ሄ/ር በ2018 9.7 ሚ/ን ለማድረስ ይሰራል። በዚሁ መሰረት ይህንን ለማሳከት የትራክተር አቅርቦት በ2015 ከነበረበት 15,000 በ2018 54,902 ለማድረስ ይሰራል። በተጨማሪም መስኖ እና አፈር ለምንት መጠበቂያ ማሺኖች፣የኬሚካል መርጫ ማሽን የሚቀርብ ይሆናል።

የሰብል መፈልፈያና መውቂያ ማሽን በ2015 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 14,145 በ2018 በጀት ዓመት 23,393 ለማድራስ የታቀደ ሲሆን የዘር ማበጠሪያ፣ደረጃ ማውጫ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ እሴት መጨመሪያ ማሽኖች ይቀርባሉ።

የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ሜካናይዜሽን መሳሪዎችን በተመለከተ የእንስሳት መኖ ማቀነባባር በመካከለኛ መኖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች ለማከናወን በ2015 ከተደረሰበት 617 የመኖ ማቀነባበሪያ ቴክኖሎጂዎች ቁጥር በማሳደግ በእቅድ ዘመኑ መጨረሻ ወደ 3,081 ለማድረስ ይሰራል። የመኖ ልማት በሜካናይዜሽን ለመደገፍ በ2015 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 250 የሞወር እና ቤለር (ለሳርና መኖ ማጨጃ እና ማሰሪያ) በማሳደግ በእቅድ ዘመኑ መጨረሻ 496 ለማድረስ ይሰራል።

የግብርና መካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎች ምርትና የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ለማረጋገጥ የፍተሻና የሰርቲፊኬሽን ማዕከል ማቋቋም እና የግብርና ሜካናይዜሽን ተቋማዊ አቅም መገንባትና ክህሎትን ማሳደግ ላይ በትኩረት ይሰራል።

ዜና ሀ/ወልድ
የስትራቴጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

የግብርና መካናይዜሽን አገልግሎት የአሰራር ስርዓትን ለማሻሻል በጥናት የተለየ ሀገራዊ የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ አቅርቦት፣ስርጭትና፣ አጠቃቀም አሰራር ይነደፋል፣ ሀገራዊ የግብርና ሜካናይዜሽን ስትራቴጂ/ፍኖተ ካርታ ይዘጋጃል።

የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን ቁጥር ማሳደግና አሰራሩን በኢ.ኮ. ቴ ከመደገፍ አንጻር በቁጥር ከ30-40 የሚሆን እያንዳንዱ የአገልግሎት መስጫ ማዕከል በጥሪ ማዕከል አገልግሎቱን ለመስጠት በኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ለዚሁ ተግባር በተለየ አፕሊኬሽን ይደገፋል። የማዕከሉ ንብረት የሆኑና ለሌሎች በማዕከሉ ዙሪያ በግል የተያዙ የሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎችን (ማረሻ፣ መከስካሻ፣ መዝሪያ፣ መውቂያ፣ መፈልፈያ ወዘተ) በመረጃ ቋቱ በመያዝና በእያንዳንዱ ቴክኖሎጂ በተለይም ትራክተሮችና ኮምባይነሮች ቦታን መጠቆሚያ መሳሪያን በመግጠም አገልግሎት ፈላጊዎችንና አገልግሎት ሰጪዎችን በሞባይል መረብ (ኔት ዎርክ) በማገናኘት ስምሪትንና አገልግሎት አሰጣጥ ይቀላጠፋል። በዚህ ስርዓት ውስጥም መሃልተኞች ይተካሉ። አሁን ያሉትን የግል ባለሀብት አገልግሎት ሰጪዎችን ቁጥር 40 በመቶ ማሳደግና አገልግሎቱን በኢ.ኮ. ቴ መደገፍ፤ መቶ የህብረት ሥራ ማሕበራት ለአባሎቻቸው ቢያንስ ሦስት ዓይነት የሜካናይዜሽን አገልግሎት እንዲሰጡ ማብቃት፤ በያንስ በየክልሉ በአማካይ 3 የግብርና ሜካናይሽን የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት እንዲቋቋሙ የሚያስችል ሥራ መስራትና አገለግሎት አሰጣጡን በኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ መደገፍ፤ በተደራጁ ወጣቶች ከ150-200 የሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ኢንተርፕራይዞችን መመስረት የሚያስችል ሥራ ይሠራል።

### 3.4.3. የግብርና ኢንቨስትመንት ማስፋፋት

#### ሀ) መሬት መለየትና ማስተላለፍ

በሰፋፊ ሰብል እርሻ ኢንቨስትመንት በሚመለከት በአስር ዓመቱ የግብርና መሪ ዕቅድ 1.05 ሚ/ን ሄ/ር መሬት በጥናት እንደሚለይ ተመላክቷል። በዚህ መሰረት በ2015 በጀት አመት 143.76 ሺህ ሄ/ር መሬት የተለየ ሲሆን በቀጣይ ሶስት ዓመታት 284.5 ሺህ ሄ/ር መሬት ከክልሎች ጋር በመሆን በጥናት ለመለየት ታቅዷል። በመሆኑም በ2016 በጀት አመት 105 ሺህ፣ በ2017 በጀት አመት 94.5 ሺህ እና በ2018 በጀት አመት 85 ሺህ ሄ/ር መሬት የሚለይ ይሆናል። መሬት ማስተላለፍን በተመለከተ በሰፋፊ ሰብል እርሻ ኢንቨስትመንት በ2015 ዓ.ም 94.6 ሺህ ሄ/ር መሬት ለባለሃብቶች የተላለፈ ሲሆን በ2016 በጀት አመት 100.8 ሺህ ሄ/ር፣ በ2017 በጀት አመት 92 ሺህ ሄ/ር እና በ2018 በጀት አመት ደግሞ 83 ሺህ ሄ/ር መሬት በማስተላለፍ በሶስቱ ዓመት መጨረሻ ላይ በድምሩ 275.8 ሺህ ሄ/ር መሬት ለባለሃብቶች ለማስተላለፍ ግብ ተጥሏል። በሌላ በኩል ቀደም ሲል በባለሃብቶች ይዞታ ስር ያለና ያልለማ መሬት ወደ ልማት እንዲገባ ለማድረግ በታቀደው መሰረት በ2015 የበጀት ዓመት በባለሃብቶች ይዞታ ስር ያለና ወደ ልማት ያልገባ 1.18 ሚ/ን ሄ/ር መሬት ውስጥ በ2016 በጀት አመት 118 ሺህ ሄ/ር፣ በ2017 በጀት አመት 106 ሺህ ሄ/ር እና በ2018 በጀት አመት 90 ሺህ ሄ/ር ሆኖ በቀጣይ ሶስት ዓመታት መጨረሻ ላይ 314 ሺህ ሄ/ር መሬት ወደ ልማት እንዲገባ ድጋፍ ይደረጋል።



ዜና ሀ/ወልድ
የስትራቴጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

የግብርና ምርቶች አምራችና አስመራች አዋጅን በመተግበር የገበያ ትስስርን ለማጠናከር የግብርና ምርቶች የኮንትራት ውል ትስስር የፈጠሩ አስመራቾች በ2015 ከተደረሰበት 234 በእቅድ ዘመኑ መጨረሻ 354 አስመራቾች ለማድረስ የታቀደ ሲሆን በግብርና ውል የኮንትራት ውል ትስስር የፈጠሩ አምራቾች/አርሶ አደሮች በ2015 ከተደረሰበት 585 ሺህ በእቅድ ዘመኑ መጨረሻ 891 ሺህ ለማድረስ ታቅዷል። በግብርና ምርቶች የኮንትራት ውል ትስስር የተሳተፉ ዩኒየኖች እና መሠረታዊ ማኅበራት ብዛት በ2015 ከተደረሰበት 704 ማኅበራት በእቅድ ዘመኑ መጨረሻ 1,077 ለማድረስ ታቅዷል። በግብርና ምርቶች የኮንትራት ውል ትስስር የሚሸፈን መሬት በ2015 ከተደረሰበት 772 ሺህ ሄ/ር ወደ 1,022,000 ሄ/ር ለማድረስ ታቅዷል።

በሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንት፡- ለአበባ ኢንቨስትመንት መሬት ተወስዶ ያልለማና በባለሃብት ይዞታ ስር ከሚገኝ እና በ2015 የበጀት ዓመት ከተመዘገበው 692 ሄ/ር ውስጥ በየዓመቱ በአማካይ 14 በመቶ ወደ ልማት እንዲገባ በማድረግ በ2018 ዓ.ም መጨረሻ 252 ሄ/ር መሬት ወደ ልማት እንዲገባ ድጋፍ ይደረጋል። በአትክልት ልማት መሬት ወስደው ካላለሙት ውስጥ በ2015 ዓ.ም ከተመዘገበው 1,050 ሄ/ር ውስጥ በየዓመቱ በአማካይ 46.2 በመቶ ወደ ልማት እንዲገባ በመደገፍ በ2018 ምርት ዘመን መጨረሻ ላይ በአትክልት ልማት 885 ሄ/ር መሬት እንዲለማ ይደረጋል። ለፍራፍሬ ልማት መሬት ወስደው ያላለሙትን 1,500 ሄ/ር መሬት ውስጥ በየዓመቱ በአማካይ 11.1 በመቶ ወደ ልማት እንዲገባ በማድረግ በቀጣይ ሶስት ዓመታት መጨረሻ 443 ሄ/ር መሬት እንዲለማ ድጋፍ ይመቻቻል። በሸርብስ ልማት መሬት ወስደው ያላለሙትን 220 ሄ/ር መሬት ውስጥ በየዓመቱ በአማካይ 11.13 በመቶ ወደ ልማት እንዲገባ በመደገፍ በ2018 በጀት ዓመት መጨረሻ 60 ሄ/ር መሬት ወደ ልማት እንዲገባ ይደረጋል። በሌላ በኩል ነባር ይዞታቸውን አሟጥጠው የተጠቀሙና የማስፋፊያ ጥያቄ ያቀረቡ አልሚ ባለሃብቶች እስከ 2018 የበጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ 43 ሄ/ር መሬት እንዲያገኙ ድጋፍ ይደረጋል። እንዲሁም ለሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንት ተስማሚነታቸው በጥናት ከተረጋገጠ የሆርቲ ቁንዝላ ፓርክ መሬት በ2015 በጀት ዓመት 399 ሄ/ር መሬት ለባለሃብቶች የተላለፈ ሲሆን እስከ 2018 የበጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ ተጨማሪ 40 ሄ/ር መሬት ለማስተላለፍ በዕቅድ ተይዟል።

በእንስሳት ኢንቨስትመንት፡- በእንስሳትና ዓሳ ኢንቨስትመንት ለሚሰማሩ ባለሃብቶች በተለያዩ የኢንቨስመንት የስራ መስኮች (ለዳልጋ ከብት ማድለብ፣ ለበግና ፍየል እርባታ/ማድለብ፣ ለዶሮ እርባታ፣ ለንብ እርባታ፣ ለመኖ ልማት፣ ለአኳካልቸር) በ2015 ከተደረሰበት 131.76 ሺህ ሄ/ር በእቅድ ዘመኑ መጨረሻ 200.24 ሺህ ሄ/ር መሬት ለባለሃብቶች እንደሚተላለፍ ዕቅድ ተይዟል። በዚሁ መሰረት በ2016 ዓ.ም 19.65 ሺህ ሄ/ር፣በ2017 ዓ.ም 22.71 ሺህ ሄ/ር እና በ2018 ዓ.ም 26.12 ሺህ ሄ/ር መሬት እንደሚተላለፍ ግብ ተጥሏል። እንዲሁም የራንች ልማት በ2015 ከደረሰበት 90 ሺህ ሄ/ር በየአመቱ 20 ሺህ ሄ/ር በማስተላለፍ በቀጣይ ሶስት ዓመታት 150 ሺህ ሄ/ር መሬት ለማድረስ ታቅዷል። በመሆኑም ከላይ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት በግብርና ኢንቨስትመንት የተሰማሩ ባለሃብቶች የሚኖራቸውን መሬት በአግባቡና ለወሰዱት ዓላማ እንዲውል ቀጣይነት ያለው ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል። የባለሃብቱን

ምርታማነት አቅም ማጥናት፣መሬት ከተላለፈ በኋላም ባለሃብቱ ለማምረት የሚያስፈልጉትን ድጋፍ በተጠናከረ መልኩ የሚሰጥ ይሆናል።

## ለ) ለግብርና ኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታን መፍጠር

በሰፋፊ ሰብል እርሻ ኢንቨስትመንት፡- በሰፋፊ ሰብል እርሻ ኢንቨስትመንት የሚስተዋለውን የመሰረተ ልማቶች አቅርቦት ችግር እንዲፈታ በማድረግ አልሚዎች በሙሉ አቅም ወደ ማልማት ተግባር እንዲገቡ ምቹ ሁኔታ የመፍጠር ሥራ ይሰራል። በዋናነትም ከዋና መንገዶች ጋር የሚያገናኙ መጋቢ መንገዶች እንዲሰሩ፣ የሃይል አቅርቦት ፍላጎት መለየትና እንዲመቻች ማድረግ፣ በተጨማሪም የእርሻ ልማት አካባቢዎች ደህንነትን ለማስጠበቅ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር መጠነ ሰፊ ውይይቶችን በማካሄድ ከአካባቢያቸው የግል እርሻ ልማት ዘርፍ ተጠቃሚዎች የሚሆኑበትና ባለቤትነት የሚያዳብሩበት ስርዓት በመዘርጋት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል። የኢንሹራንስ አገልግሎትና የብድር አቅርቦት እንዲሻሻል አልሚዎች ከአቅም በላይ የሆኑ ስጋቶችን በመቀነስ ወደ እርሻ ልማት ሥራ እንዲገቡ ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ማነቆዎችን በጥናት በመለየት እንደ አስፈላጊነቱ መንግስት የኢንሹራንስ ስርዓቱ ተግባራዊ እንዲሆን ድጋፍ ይሰጣል። ከዚህም ባሻገር የእርሻ ልማቱን የሚደግፍ የብድር አቅርቦት ስርዓትም ይጠናከራል። የውጭ ገበያ ትስስርና የመሬት አቅርቦት ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል መዋቅሮች ጋር በመቀናጀት ተከታታይ የሆነ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ማነቆዎቻቸው እንዲፈቱ ይደረጋል።

በዚህ መሰረት በ2015 የበጀት ዓመት የ20 ባለሃብቶች ዘርፈ ብዙ ማነቆ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የተፈታላቸው ሲሆን በ2016 የበጀት ዓመት ቁጥሩን በማሳደግ 40፣ በ2017 በጀት ዓመት 48 እና በ2018 በጀት ዓመት 67 በድምሩ በሶስት ዓመት መጨረሻ ላይ የ155 ባለሃብቶች ፈርጀ ብዙ ማነቆዎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ በመፍታት ወደ ልማት እንዲገቡ ይደረጋል።

በሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንት፡- ከሚለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንት የተለዩ ማነቆዎች ለመፍታት እንዲቻል በ2015 የበጀት ዓመት በተደረገው የጋራ ጥረት የ20 ኩባንያዎች ዘርፈ ብዙ ችግር የተቀረፈ ሲሆን በቀጣይም ቅንጅታዊ ስራን በማጠናከር እስከ 2018 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ የ17 ኩባንያዎች የተለዩ ማነቆዎች ለመፍታት በጋራ ጥረት ይደረጋል። ለአብነት፡- ከመሬት ሊዝ ውል፣ ከክፍያ መጠንና የሊዝ ጊዜ ጋር በተያያዘ ማነቆ ያለባቸውን 10 ኩባንያዎች ችግር ከተቋማት ጋር በመቀናጀት መፍታትና በሙሉ አቅማቸው እንዲንቀሳቀሱ መደገፍ፣ ይዞታቸውን አሟጠው ተጠቅመው የመሬት ማስፋፊያ ለሚጠይቁ አልሚ ባለሃብቶች የማስፋፊያ ድጋፍ ማድረግ፣ ቀደም ሲል የተጠኑ መሬቶችን እና አዳዲስ መሬቶችን ወደ ልማት ማስገባት፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት አዳዲስ አልሚ ባለሃብቶችን በመመልመል ወደ ልማት እንዲገቡ ድጋፍ ማድረግ፣ ከክልሎች ጋር በመቀናጀት ለሆርቲካልቸር ልማት ለባለሃብት የተላለፈውን መሬት አጠቃቀም በመከታተል በመገምገም፣ ለአልሚዎች የብድር አቅርቦት እንዲያገኙ እና መሰረተ ልማቶች ተሟልተው (የሃይል አቅርቦት፣ የቴሌኮምና ኢንተርኔት አገልግሎት፣ የጎርፍ ችግር) ወደ ስራ እንዲገቡ ይደረጋል።



አለ ዜና ሀ/ወልድ
የስትራተጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

የሰፋ የገበያ መዳረሻ ከመፍጠር አንጻር የተለያዩ ሲምፖዚየሞች፣ ባዛሮችና ሌሎች የፕሮሞሽን ስራዎችን ማካሄድ፣ የግብይት የአሰራር ማነቆዎችን ሊፈቱ የሚችሉ የህግ ማዕቀፎች (ደንቦች፣ መመሪያዎች ወዘተ) በማዘጋጀት ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል። በሌላ በኩል ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት በሆርቲካልቸር ኢንዱስትሪ በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ የሆኑና አቅም ያላቸውን ባለሀብቶችን እንዲለዩ ማድረግ፣ በተቀናጀ አሰራር የሀገራችንን እምቅ ሀብት እና ምርቶች በማስተዋወቅና የምልመላ ስራ በማከናወን በስፋት እንዲሳቡ መስራት፣ በኢንዱስትሪው ውስጥ የባንክ ብድር ሳይፈልጉ በራሳቸው አቅም ለማልማት የሚፈልጉ ኩባንያዎችን በተለየ ሁኔታ እንዲስተናገዱ በጋራ መስራት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ተስበው ለመጡና ለነባር ኩባንያዎች ምርታቸውን ወደ ውጭ ኤክስፖርት ለማድረግ የሚያስፈልጋቸውን ሁለገብ ድጋፍ የመስጠት ስራ ይሰራል።

የመሰረተ ልማትና ሎጀስቲክስ አገልግሎት ምቹ ሁኔታ ከመፍጠር አንጻር ከብሔራዊ ኤክስፖርት ካውንስል በተሰጠው መመሪያና አቅጣጫ መሰረት ክክልሎችና ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል ተቋማት ጋር በተሻለ አግባብና ቅንጅታዊ አሰራር መንቀሳቀስ፣ ለኢትዮጵያ አትክልትና ፍራፍሬ ምርት ዋና መዳረሻ ገበያ የመካከለኛው ምስራቅ ሲሆን የተወዳዳሪ ሃገሮችን አሰራር በመከተል በተቀራራቢ አቅም ገበያው ውስጥ ለመገኘትና በሂደት የገበያውን ድርሻ ለማስፋት አሁን ያለውን የባህር ሎጀስቲክስ አገልግሎት ማጐልበት አስፈላጊ በመሆኑ የተጀመሩ ዓበይት ስራዎችን ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀትና ተግባራዊ ይደረጋል። በሌላ በኩል በአትክልትና ፍራፍሬ አቅርቦት የኬንያን ጨምሮ የሰሜን አፍሪካና የመካከለኛ ምስራቅ ሃገሮችን አሰራር በዳሰሰ መልኩ ተወዳዳሪ የአየር፣ የባህርና የየብስ (ባቡር፣ ሪፈር ኮንቴይነር) ሎጂስቲክስ አገልግሎት እንዲመቻቸች በጋራ መስራት ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው።

የፋይናንስ አቅርቦት ምቹ ሁኔታ ከመፍጠር አኳያ በኢንቨስትመንት ፈቃድ መሬት ለወሰዱ ባለሃብቶች በባንኩ አሰራር መሰረትና በሚያቀርቡት ቢዝነስ ፕላን መሰረት በተፋጠነ መልኩ ከልማት ባንክ ብድር ማመቻቸት፣ ለአርሻ ልማት ግንባታ የፈሰሰውን መዋዕለ ንዋይ ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ብድር ማመቻቸት ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው።

የገበያ ስርዓቱን በማሻሻል ረገድ በቀጥታ ተደራሽ ለሆኑ ገበያዎች ተፈላጊውን የግብይት ስርዓት (የኮንሶሊዴሽን ዩኒትን ጨምሮ) መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ፣ ከየሰብሉ ባህሪ አንፃር መሟላት በሚገባቸው የኩልቼይን አሰራሮች ላይ የሚታዩ ጉድለቶችን ነቅሶ በማውጣት በችግሩ አፈታት ላይ ከምርት እስከ መዳረሻ ገበያ ድረስ ለስኬቱ ወሳኝ የሆኑ ባለድርሻ አካላትን ማሳተፍ፣ ተቀባዮች የሚፈልጓቸውን መስፈርቶችን (Global GAP፣ BRC) በማሟላት የወልና የተናጠል የስራ ድርሻና ኃላፊነቶችን ለይቶ መተግበር፣ መቆጣጠር፣ መከታተልና መገምገም፣ የትራንስፖርት ዋጋ ተወዳዳሪ ሊሆን የሚቻልበትን አግባብ መፈተሽና በሥራ ላይ ማዋል፣ የሆርቲካልቸር ሰብሎች የነፍስ ወከፍ ፍጆታ ከፍተኛ በሆነበት የመዳረሻ ገበያዎች ላይ የሚገኙ ዋና ዋና ተቀባዮችን መለየት፣ አዋጪ የሎጀስቲክስና ትራንስፖርት እንደዚሁም የኮንሶሊዴሽን አሰራሮችን በማመቻቸት ነባር ገበያዎችን ማጠናከርና አዳዲስ ገበያዎችን ማስፋት በዕቅድ ዘመኑ ትኩረት ይሰጠዋል።

የዓለም አቀፍ ገበያ ህጎችንና መስፈርቶችን በስራ ላይ እንዲውሉ ከማድረግ አኳያ የሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንት ምርቶች በኤክስፖርት ገበያ ላይ ተፈላጊነት እንዲኖራቸው በአቅርቦት፤ በጥራትና በዋጋ ደረጃ ያሉትን ክፍተቶች ከማሻሻል ጎን ለጎን በገበያ ውስጥ ለመግባት የአለምአቀፍ የአመራረት፤ የአካባቢና ህብረተሰብ ጥበቃ መስፈርቶችን ማማሏትና ዕውቅና (Certification) ለማግኘት ሁኔታዎችን የማመቻቸት ስራ ትኩረት ተሰጥቶት የሚከናወን ይሆናል። በመሆኑም ሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንት ረገድ ያሉ ፕሮጀክቶች፤ ድጋፍ ሰጪ ተቋማትና ባለሙያዎች ስለ መልካም እርሻ (GAP-Good Agricutural Practices) አተገባበር፣ የተለያዩ የአለም አቀፍ የገበያ ጥራት መስፈርት ሰርተፍኬቶች (Global GAP, BRC, BSI, ETI, TESCO እና የምርት ሀገር ስሪት የHs code) ገበያው የሚፈልጋቸው ደረጃዎችን እንዲያሟሉ የግንዛቤ ማሳደግ ስራ በቀጣይ የዕቅድ ዓመታት በተከታታይ የሚከናወን ተግባር ይሆናል።

ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ማጠናከር ሌላው ምቹ ሁኔታ የሚፈጠርበት ዓውድ ሲሆን በዘርፉ ወሳኝ ድርሻ ካላቸው የመንግስት አካላት ጋር የተጀመረውን የተቀናጀ አሰራር (የአየር ትራንስፖርት፣ የሪፈሪ ኮንቴይነር፣ ገቢዎች እና ጉምሩክ፣ ባለሃብቶች ምልመላ እና የውጭ ገበያ ማፈላለግ፣ የባንክ ብድር አስተዳደር፣ ወዘተ) በማጠናከር በየኮሪደሩ የጋራ ዕቅድ እና ባለቤት በመሰየም ተጠያቂነት ያለው አሰራር መዘርጋት ያልተፈቱ ችግሮችን በወሳኝነት እንዲፈቱ በጋራ መስራት፣ በዘርፉ አሰራር ላይ ልምድ ያካበቱና Enterprenual ክህሎቱን የጨበጡ ኢትዮጵያውያን ወደ ዘርፉ እንዲገቡ በመንግሥት በጀት በሃገራችን የhirelease የአበባ የግንባታ ሥራዎችን ማከናወን፣ የክልሎችን የተመጣጠነ የሆርቲካልቸር ልማት ዕድገት የሚያስገኝ የኢንቨስትመንት ማትጊያ መቀየስና ተግባራዊ ማድረግ በትኩረት የሚተገበር ነው። በዚህም መሰረት በ2014 የበጀት ዓመት የተጀመረውና አሁን ላይ ከ15 በላይ አጋር አካላትን እያሳተፈ ያለው የሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንት ስትራቴጂክ አጋር አካላት የቅንጅት መድረክ በማጠናከር በየወሩ የሚደረገውን የአፈጻጸም ግምገማ መነሻ በማድረግ የኩባንያዎች ማነቆ በተቀናጀ አግባብ እየተፈታ ያለበትን ሁኔታ አጠናክሮ ማስቀጠል ይገባል።

በዚህ መሰረት በ2015 የበጀት ዓመት የ20 ባለሃብቶች ዘርፈ ብዙ ማነቆ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የተፈታላቸው ሲሆን በ2016 የበጀት ዓመት ቁጥሩን በማሳደግ 40፣ በ2017 በጀት ዓመት 48 እና በ2018 በጀት ዓመት 67 በድምሩ በሶስት ዓመት መጨረሻ ላይ የ155 ባለሃብቶች ፈርጀ ብዙ ማነቆዎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ በመፍታት ወደ ልማት እንዲገቡ ይደረጋል።

በእንስሳትና ዓሳ ኢንቨስትመንት፡- የእንስሳትና ዓሳ ሃብት ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ምቹ ሁኔታ ከመፍጠር አንጻር መሬት መለየትና ማስተላለፍ፣ መሰረት ልማትና አገልግሎት አቅርቦት ማሻሻል፣ በመልማት ላይ ያሉ የእንስሳት ኢንቨስትመንት ማዕከላትን ማጠናከር፣ በተሰጠ ኢንቨስትመንት ፈቃድ መሰረት እያለሙ ያሉ የእንስሳት እርባታ ማዕከላት ሁሉን አቀፍ ድጋፍ በማድረግ የባለሀብቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ ይሰራል። በዘርፉ መሰማራት የሚፈልጉ ባለሃብቶችን ለመሳብ የመንግስት አቅም በፈቀደ መጠን መሰረተ ልማቶችን (የኃይል፤ የመንገድ፣ የውሃ፣ የቴሌኮም) ለማማሏት የተለያዩ ጥረቶችና እንቅስቃሴዎች ሲደረጉ መቆየታቸውና አሁንም በመደረግ ላይ መሆናቸው ይታወቃል። ይሁን እንጂ የኢንቨስትመንቱን

የስራ ባህሪ ግምት ውስጥ በማስገባት ለኢንቨስትመንት የሚውሉ አካባቢዎችን በመለየትና ቅድሚያ በመስጠት ረገድ ባለው የአፈጻጸም ችግር፣ በአንድ ጊዜ ሁሉም አካባቢ ለማሟላት ካለው የመንግስት አቅም ውስንነት አኳያ መሰረተ ልማት ባለመሟላቱ ለኢንቨስትመንቱ ዋና ማነቆ ሆኖ ይታያል። በመሆኑም በጥናት ላይ ተመስርቶ ለኢንቨስትመንት የሚውሉ አካባቢዎችን በመለየትና ቅድሚያ በመስጠት በሚመለከታቸው ተቋማት በኩል መሰረተ ልማት እንዲሟሉ የማድረግ ስራ እንዲከናወን የክትትልና ድጋፍ እንዲሁም ቅንጅታዊ አሰራር የሚጠናከር ይሆናል።

በዚህ መሰረት በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በእንስሳትና ዓሳ ኢንቨስትመንት የሚሰማሩ ባለሃብቶች የሚያጋጥሟቸውን ፈርጀ ብዙ ማነቆዎች (የመሬት፣ የመሰረተ ልማት፣ የብድር አቅርቦት ወዘተ) ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ችግሮችን ደረጃ በደረጃ ለመፍታት ጥረት ይደረጋል። በዚህም መሰረት በቀጣይ ሶስት ዓመታት የ47 በዘርፉ የተሰማሩ ባለሃብቶች ማነቆዎች በቅንጅት በመፍታት ምቹ የኢንቨስትመንት ሁኔታ ለመፍጠር ይሰራል።

## ሐ) የባለሃብቶች ማህበራትን ማጠናከርና ማቋቋም

በዕቅድ ዘመኑ በሰፋፊ ሰብል ኢንቨስትመንት መስክ የተሰማሩ ባለሃብቶች በየጊዜው የሚያጋጥማቸውን የልማትና የመልካም አስተዳደር ችግሮች በተናጠል ለመፍታት ከመንቀሳቀስ ይልቅ ሊወክላቸው የሚችል ማህበር በማቋቋም የጋራ ችግራቸውን በጋራ መፍታት ይገባቸዋል። በመሆኑም ነባር ማህበራትን ከማጠናከር አንጻር ቀደም ሲል የተቋቋመው የፌዴራል የባለሃብቶች ማህበር እንደተጠበቀ ሆኖ እስከ 2018 የበጀት ዓመት መጨረሻ በ3 ክልሎች ማለትም ኦሮሚያ፣ ጋምቤላ እና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች የባለሃብቶች ማህበራትን የማጠናከር ስራ ይሰራል። አዳዲስ ማህበራት ማቋቋም በተመለከተ በ2015 የበጀት ዓመት በአማራ ክልል አንድ አዲስ የባለሃብቶች ማህበር የተመሰረተ ሲሆን እስከ 2018 ዓ.ም ድረስ በሲዳማ እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልሎች 2 አዳዲስ ማህበራት እንዲቋቋሙ ድጋፍ ይደረጋል።

## መ) የመረጃ ስርዓት ማጠናከር

በግብርና ኢንቨስትመንት ዘርፍ የሚስተዋለውን የመረጃ ችግር በመቅረፍ ወጥነትና ጥራት ያለው መረጃ በማደራጀት ለተጠቃሚ ተደራሽ ለማድረግ በቀጣይ ሶስት ዓመታት በትኩረት ይሰራል። በዚህ መሰረት በሰፋፊ ሰብል እርሻ፣ በሆርቲካልቸር፣ እንስሳትና ዓሳ ኢንቨስትመንት የሚስተዋለውን የመረጃ ውሱንነት ለመቅረፍ እንዲቻል እና አሰራሩን በማሳለጥ ዘርፉን ውጤታማ ለማድረግ በመስኩ የተሰማሩ ባለሃብቶችን በመለየት በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ዘዴ /ኮቦ ቱል ቦክስ/ ዳታ ቤዝ የማደራጀትና ለተጠቃሚዎች ተደራሽ የማድረግ ስራ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል።

ኣለ ዜና ሀ/ወልድ
የስትራቴጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

በሌላ በኩል የግብርና ምርት ግብይት መረጃ ሥርዓት ወቅታዊ፣ ታዓማኒነት ተደራሽ በሆነ መልኩ እንዲቀርብ ጥረት የሚደረግ ሲሆን በዚህም መሰረት በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ የግብርና ምርቶች ወቅታዊ የገበያ ዋጋ፣ የምርት አቅርቦት፣ ምርቱ ያለበት አካባቢና ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በመተንተንና ለተጠቃሚው በማሰራጨት በተለይ አርሶ/አርብቶ አደሮች ገበያው የሚፈልገውን ምርት በማምረትና ከገበያው የተሻለ ተጠቃሚ የሚሆኑበት አሰራር ለመፍጠር ታቅዷል።

## ሠ) የአሰራር ስርዓት መዘርጋት

በቀጣይ የዕቅድ ዘመን በግብርና ኢንቨስትመንት ትኩረት ከሚሰጣቸው ስራዎች መካከል የአሰራር ስርዓት መዘርጋት አንዱ ነው። በዚህ መሰረት የግብርና ኢንቨስትመንቱን አሰራር በማሳለጥ ዘርፉን ለማሳደግና ውጤታማ ለማድረግ ሃላፊነት የተሞላበት የግብርና ኢንቨስትመንት የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋት በትኩረት ይሰራል።

በዚህ ማዕቀፍ ስር እንደ የኢንቨስትመንቱ ባህርይ በመነሳት የተለያዩ የአሰራር ስርዓት ማሻሻያ እና አዳዲስ የአሰራር ሰነዶች የሚዘጋጁ ይሆናል። በዚህ መሰረት በሰፋፊ ሰብል እርሻና ሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንት በቀጣይ ሶስት ዓመታት አምስት የአሰራር ሰነዶች ማለትም የአትክልትና ፍራፍሬ የግብይት መመሪያ፣ የሆርካልቸር ምርቶች አቀናጅቶ የማቅረብ (የኮንሶሊዴሽን) አፈጻጸም መመሪያ፣ የግብርና ኢንቨስትመንት የመሬት ማስተላለፍ ማኑዋል እና የክትትል እና ድጋፍ ማኑዋል እንዲሁም የኩባንያዎች የኤክስፖርት አፈጻጸምና ያሉባቸውን ችግሮች ለመከታተል የሚያስችል ዲጂታላይዝ የመረጃ ስርዓት የሚዘጋጅና የሚተገበር ይሆናል።

በእንስሳትና ዓሳ ኢንቨስትመንት የዶሮ ምርቶች ልማትና ግብይት አዋጅ፣ የእንስሳት መኖ ግብይት መመሪያ፣ የወተትና ወተት ተዋጽኦ የግብይት አዋጅ፣ የራንች ልማት ማኑዋል እና የንብና ሀብረ-ንብ ውጤቶች ግብይት አዋጅ በድምሩ አምስት የአሰራር ሰነዶች የሚዘጋጁ ይሆናል።

በግብርና ምርት ውል ሶስት የአሰራር ስርዓት ማስተግበሪያ ሰነዶች የግብርና ምርት ውል አሰራርን ሊያሳልጡ የሚችሉ የአሰራር ስርዓቶች የሚዘጋጁ ሲሆን የግብርና ምርት ውል አዋጅ፣ የግብርና ምርት ውል አዋጅ ማስፈጸሚያ መመሪያ እና የግብርና ምርት ውል ጋይድላይን የሚዘጋጁ ይሆናል። እንዲሁም የግብርና ምርት ግብይትን ለማሳለጥ በቀጣይ ሶስት ዓመታት የዕቅድ ዘመን የአትክልትና ፍራፍሬ ግብይት የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋት ግብ ተጥሏል።

የአሰራር ስርዓት ማሻሻያ ሰነድ ዝግጅትን በሚመለከት የአትክልትና ፍራፍሬ ወለል ዋጋ ተመን ማሻሻያ፣ የአበባ ወለል ዋጋ ተመን ክለሳ እንዲሁም የቫውቸር ስርዓትን ለማስፈጸም የግብዓት ምርት ጥመርታ ስታንዳርድ ሰነድ የተጣለን ግብ ለማሳካት ከፍተኛ አቅም የሚፈጥሩ የአሰራር ስርዓቶች ሲሆኑ እነዚህ የአሰራር ስርዓቶች ባለቤት ተፈጥሮላቸው ደረጃ በደረጃ እንደሚተገበሩ በቀጣይ የዕቅድ ዘመኑ ታሳቢ ተደርጓል።

## የግብርና ምርት ውል ስራዎች ማስፋፋት

አዳዲስ በግብርና ምርት ውል የሚተሳሰሩ ኒውክለስ እርሻዎችን እና አርሶ/አርብቶ አደሮች፣ ሴቶችና ወጣቶችን መለየትና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፤ አውትግሮወርስ ሰርቲፋይድ እንዲሆኑ የአቅም ግንባታ መስጠት፣ አርሶ/አርብቶ አደሮችን፣ ወጣቶችንና ሴቶችን በኮንትራት እርሻና በአውትግሮወርስ አምራችነት ከኒውክለስ እርሻዎች ጋር ማስተሳሰር፣ በኮንትራት እርሻና አውትግሮወርስ አምራችነት የተሳሰሩ ኩባንያዎችን፣ አርሶ አደሮችን፣ ወጣቶችና ሴቶችን አፈጻጸም መደገፍ፣ የአውትግሮወርስና ኮንትራት እርሻ ትስስር በህግ ማዕቀፍ እንዲደገፍና አቅም ያላቸው በዘርፉ በስፋት እንዲሰማሩ ማድረግ የቀጣይ ሶስት ዓመታት የዕቅዱ የትኩረት አቅጣጫ ሆኖ ተቀምጧል።

ገበያ መር የግብርና ልማት ለማረጋገጥና አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ/አርብቶአደሮች የአመራረት ሥርዓት በመቀየር ከፍጆታ ማምረት፣ በገበያ የሚፈለግና የተሻለ ዋጋ የሚያስገኝ ምርት ወደ ማምረት ለማሸጋገር ከሰፋፊ እርሻዎች፣ የግብርና ምርት ከሚቀበሉ ኢንዱስትሪዎች፣ ከላኪዎችና የገበያ ማዕከላት ጋር እንዲሁም የምርጥ ዘር አምራች ኩባንያዎችንና ተጠቃሚዎችን በግብርና ምርት ውል ላይ የተመሰረተ ግብይት ትስስር የሚፈጠር ሲሆን በዚህ ሂደት አምራችና አስመራችን ህጋዊ በሆነ መልኩ በማገናኘት አስተማማኝና ዘላቂነት ያለው የገበያ ትሥሥር ለመፍጠር የሚሰራ ሲሆን የግብርና ምርት እንደ ግብዓት የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች የሚፈልጉትን ምርት በሚፈልጉት ጥራት፣ መጠንና ጊዜ እንዲመረትላቸው ለአልሚ አርሶ/አርብቶ አደርና ባለሃብቶች እውቀት፣ ክህሎት እና ቴክኖሎጂ በማቅረብ ምርትን በመጨመርና ብክነትን በመቀነስ እንዲሁም የምርት ጥራትን በማሻሻል የልማትና ግብይት ትስስር በትኩረት ይሰራል።

## ሀ) የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራት ማከናወን

በግብርና ኢንቨስትመንት (በሰፋፊ እርሻ፣ በሆርቲካልቸርና በእንስሳት) ልማት አካባቢ ያሉ አርሶ/አርብቶ አደሮችን በግብርና ምርት ውል ስርዓት ከባለሃብቶች ጋር በስፋት እንዲተሳሰሩና ውጤታማ ስራ እንዲከናወን ለማስቻል የግብርና ምርት ውል ጠቀሜታና አሰራርን በስፋት ማስተዋወቅና አቅም ያላቸው በዘርፉ በስፋት እንዲሰማሩ ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚህም ሰፋፊ የማስተዋወቂያና የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች የሚፈጸሙ ይሆናል። በዚህ መሰረት በ2015 ዓ.ም የተካሄዱ 10 የማስተዋወቂያና የግንዛቤ መድረኮችን በቀጣይ ሶስት ዓመታት ወደ 48 የማድረስ ሥራ ይሰራል። የመሬት ተደራሽነትንና የአርሶ/አርብቶ አደሩን ተጠቃሚነት እንዲሁም የኢንዱስትሪውን ሰላም በመጠበቅ የግብርና ልማት ውል አዋጅን ወደ ተግባር እንዲገባ መጠነ ሰፊ የማስተዋወቅ ሥራ ይሰራል። በመሆኑም በመካከለኛ እና ሰፋፊ እርሻዎች፣ በሆርቲካልቸር እና የእንስሳት ኢንቨስትመንት አካባቢ የሚገኙ አርሶ/አርብቶ አደሮች በውል ግብርና ስርዓት በማስተሳሰር ከልማቱ ተጠቃሚ በማድረግ የዘርፉን ምርት የማሳደግ ስራ ይሰራል።

## ለ) የግብርና ምርት አስመራቾችን ከአምራቾች ጋር እንዲተሳሰሩ መደገፍ

በሰፋፊ ሰብል እርሻና ሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንት ልማቱ አካባቢ ያሉ አርሶ/አርብቶ አደሮች እና ወጣቶች እንዲበቁና በማህበር ሰርቲፋይ እንዲሆኑ በመደገፍ ከኒውክለስ እርሻዎች/ባለሀብቶች ጋር በግብርና ምርት ውል ስርዓት ማስተሳሰር፤ አነስተኛ አርሶና አርብቶ አደሮችን ከእንስሳትና ዓሳ ኢንቨስትመንት ጋር የምርት ትስስር በመፍጠር የሚገኘውን የሁለትዮሽ ጠቀሜታ በአግባቡ ለመጠቀም በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት በትኩረት ለመስራት ግብ ተቀምጧል።

በዚህም መሰረት በሚካሄዱ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች እና በሚሰጡ የድጋፍ አግባቦች መሰረት በግብርና ምርት ውል ትስስር የሚፈጥሩ አካላት በተመለከተ የአስመራቾች ቁጥር በ2015 በጀት አመት ከነበረበት 50 በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 193 ለማድረስ እንዲሁም በግብርና ምርት ውጤቶች በውል ግብርና ትስስር የሚፈጠሩ የአምራቾች ቁጥር በ2015 ከነበረበት 200 ሺህ በቀጣይ ሶስት ዓመታት መጨረሻ 963 ሺህ ለማድረስ በትኩረት ይሰራል። በዚህ የትስስር ሂደት በስድስት ዓይነት የግብርና ምርቶች እነርሱም የብርዕ ሰብሎች፣ የቅባት ሰብሎች፣ የእንስሳትና እንስሳት ምርት ተዋጽዖ፣ የአትክልና ፍራፍሬ እና የጥጥ የውል ዓይነቶች ትስስር እንዲፈጠር የማስተባበርና የድጋፍ ስራ የሚከናወን ይሆናል።

## የግብርና ምርት ግብይት ስራዎችን ማስፋፋት

## ሀ) የግብይት ምክር አገልግሎት መስጠት

የአርሶ/አርብቶ አደሮች በዕውቀት ላይ የተመሠረተ የማምረትና ግብይት ውሳኔዎችን መወሰን የሚያስችላቸው ክህሎት መዳበር ውጤታማ እንደሚያደርጋቸው ዕዉን ነው። ስለሆነም አርሶ/አርብቶ አደሮች በገበያ ተፈላጊና የተሻለ ገቢ በሚያስገኙ ምርቶች ላይ እንዲያተኩሩ ምክረ ሃሳብ ማቅረብ እንዲሁም በሀገር ውስጥና በዓለም ገበያ ተፈላጊነት ያላቸውን ምርቶች በመለየት በአርሶ/አርብቶ አደሩ እንዲለመዱ ይሠራል። በግብርናው ዘርፍ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት ለማምጣት ከተለመዱ ምርቶች ከፍተኛ ዋጋ ወዳላቸው ምርቶች (High Value Commodities) እንዲሸጋገር አስፈላጊው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እንዲሁም ድጋፍና ክትትል ይደረጋል። በዚህ መሰረት በቀጣይ ሶስት ዓመታት የዕቅድ ዘመን ለ4,215 የግብርና ምርት አምራቾች የግብይት ምክር አገልግሎት ለመስጠት ዕቅድ ተይዟል።

## ለ) የግብይት መሠረተ ልማት መገንባት

የግብርና ምርት የግብይት ስርዓቱን ዘመናዊ፣ በውድድር ላይ የተመሰረተ አርሶ/አርብቶ አርሶ አደሩንና ባለሃብቱን ከግብይቱ ተጠቃሚ የሚያደርግ ዘመናዊ የግብይት መሰረተ ልማትን ማስፋፋት መሰረታዊ ጉዳይ ነው።

ከላ ቤና ሀ/ወልድ የስትራተጂክ ጉዳዮች ሥራ አስፈጻሚ



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ግብርና ሚኒስቴር The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

በሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንት ምርቶች (አትክልት፣ ፍራፍሬ) ፣ የሎጀስቲክስ አገልግሎት አቅርቦትና ዋጋ ውድነት ምክንያት የሚመረተው ምርት በዓለም አቀፍ በተወዳዳሪ ዋጋ እንዳይቀርብ ማነቆ የሆኑትን የጥራትና መሰረተ ልማት ችግሮች በመቅረፍ በተለያዩ ቦታዎች በአምራቾች የሚመረተውን የአትክልትና ፍራፍሬ ልምዱና በገበያ መዳረሻዎች ዕውቅና ካላቸው ኒውክለስ እርሻዎች ከማስተሳሰር ባሻገር ምርቱ ተሰባስቦ ሊላክ የሚችልበትን የሎጂስቲክስና ተያያዥነት ያላቸውን ፋሲሊቲዎች የማመቻቸት ተግባር በዕቅድ ዘመኑ ትኩረት ተሰጥቶት የሚከናወን ይሆናል።

የቅዝቃዜ መጠበቂያ መጋዘን እና ሎጂስቲክስ ከማመቻቸት አንጻር የሆርቲካልቸር ምርቶች ጥራታቸው በአግባቡ ተጠብቆ ወደ መዳረሻ ገበያ እንዲደርሱ ለማድረግ ከምርት አካባቢዎች ወደ ወደቦችና ኤርፖርቶች ለማድረስ ኩል ቼይን ሎጂስቲክስ /Cool Chain Logistics/ አገልግሎት አስፈላጊ በመሆኑ በዕቅድ ዘመኑ ከፍተኛ ፍራፍሬ በሚመረትባቸውና ግብይት በሚካሄድባቸው አርባ ምንጭና ድሬዳዋ የልማት ኮሪደሮች 2 የምርት ማዳራጃና ማከማቻና ማደራጃ ማዕከላት እንዲገነቡ በዕቅድ ተይዟል።

በሌላ በኩል በወተት ምርት ግብይት ከአርሶ አደሮች የሚቀርበው ወተት በማዕከላት ተሰባስበው ለኢንዱስትሪውና ለተጠቃሚው ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲደርሱ በዕቅድ ዘመኑ 6 የወተት ምርት ማሰባሰቢያና መሸጫ ማዕከላት እና ከማር ምርት ግብይት አንጻር በተመሳሳይ 6 የማር ማሰባሰቢያና መሸጫ ማዕከላት እንዲገነቡ ጥረት ይደረጋል።

## ሐ) የግብይት ፋይናንስ አቅርቦት ማሻሻል

የግብርና ምርት ግብይት እሴት ሰንሰለቱን የተከተለ በቂና የተሟላ የፋይናንስ አቅርቦት አገልግሎት የሌለው በመሆኑ በተለይም የብድር እና ኢንሹራንስ አገልግሎት አሰጣጥ፣ አቅርቦትና ተደራሽነት ዙሪያ ያለው የአሰራር ስርዓት ምቹ እንዲሆን መሥራት ያስፈልጋል። ስለሆነም በዘርፉ የሚታየውን ደካማ የፋይናንስ አቅርቦትና የተደራሽነት ክፍተት ለመሙላትና የሃገራችንን የግብርና ግብዓትና ምርት ግብይት በሚፈለገው ልክ ለማድረስ እንዲረዳ በጥናትና ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የግብርና ፋይናንስ አቅርቦት ሥርዓት መዘርጋት ለዕቅዱ መሳካት ቁልፍ ሚና የሚጫወት በመሆኑ በቀጣይ የዕቅድ ዘመን በትኩረት የሚሰራ ሥራ ይሆናል።

## መ) የገበያ ትስስር ስራዎች ማከናወን

የግብርና ምርቶች የኤክስፖርት መዳረሻ ገበያዎችን በጥናት በመለየት በፍላጎትና በአቅርቦት መካከል የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ውጤታማ የሚያደርጉ የአሰራር ስልቶች ይቀየሳሉ። የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በውጭ ሃገራትና በሃገር ውስጥ በሚካሄዱ የንግድ ትርዒቶች ላይ በመሳተፍ ምርቶቻቸውን እንዲያስተዋውቁ መደገፍና አዳዲስ የኤክስፖርት መዳረሻ ሃገራት ገበያዎችን የማስፋፋት ተግባራት ይከናወናሉ። የሃገሪቱን የሆርቲካልቸር ምርቶች በአገር ውስጥና በዓለም

ለሐ ዜና ሀ/ወልድ
የስትራቴጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

አቀፍ ገበያ ላይ የማስተዋወቅ ስራ ማጠናከር እንዲሁም የዓለም ገበያ መስፈርቶችን በማሟላትና ተወዳዳሪ ለመሆን በጥራትና ብዛት ላይ ያተኮረ ስራ በዕቅድ ዘመኑ በትኩረት ይሰራል።

አርሶ/አርብቶ አደሩን አግሮ-ኢንዱስትሪያል ፓርኮች፣ ከምርት አቀነባባሪዎች፣ ላኪዎች፣ የግብይት ትስስር፡ አነስተኛ አርሶ/አርብቶ አደሮች ላመረቷቸው ምርቶች ዘላቂና አስተማማኝ የገበያ ትስስር ሲፈጠርላቸው ምርታቸውን ያለስጋት እንዲያመርቱና የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ጥራትን መሰረት ያደረገ ምርት እንዲያመርቱ ይበረታታሉ። አነስተኛ አርሶ/አርብቶ አደሮችን ከህ/ሥራ ማህበራት፣ ከነጋዴዎች፣ ከአቀነባባሪዎች እንዲሁም ከላኪዎች ጋር በማስተሳሰር የየምርቶቻቸው ተቀባዮች የሚፈልጉትን መጠን፣ በሚፈልጉት ጥራትና ወቅት እንዲያገኙ በማስቻል በሙሉ አቅማቸው እንዲሰሩ ያስችላቸዋል። በተጨማሪም አርሶ/አርብቶ አደሮችን በሀገራችን በመስፋፋት ላይ ካሉት አግሮ-እንዱስትሪያል ፓርኮችና ከምርት አቀነባባሪዎች ጋር የማስተሳሰር ተግባራት ይከናወናሉ። ትስስሩ የግብርና ምርትን ጥራት፣ የአመራረት ቅልጥፍናና ተወዳዳሪነት እንዲሁም የግብርና እና አግሮ- ኢንዱስትሪ ተመጋጋቢነት በማሳደግ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር እውን ለማድረግ አጋዥ ሚና ይኖረዋል።

በዚህ መሰረት በቀጣይ የዕቅድ ዘመን መጨረሻ በቁጥር ለ50 ባለሃብቶች የመኖ ምርት የገበያ ትስስር የመፍጠር ስራ የሚሰራ ይሆናል። እንዲሁም 3,365 አምራቾች ከአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ አቀነባባሪዎች፣ ላኪዎች ወዘተ ጋር የቀጥታ ገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው ለማድረግ ታቅዷል። በተጨማሪም ለሃገር ውስጥ ገበያ ተቀነባብሮ የሚቀርብ የእንስሳት ምርትና መኖ ለማሻሻል ተቀነባብሮ ለሃገር ውስጥ ገበያ የሚቀርብ ወተት ምርት መጠን አሁን ካለበት 125.2 ሚ/ን ሊትር ወደ 158.26 ሚ/ን ሊትር የማድረስ፤ ተቀነባብሮ ለሃገር ውስጥ ገበያ የቀረበ የመኖ ምርት መጠን ዕድገት አሁን ካለበት 170,162. ቶን ወደ 215,310 ቶን ለማሳደግ እና ተቀነባብሮ ለሃገር ውስጥ ገበያ የቀረበ የዶሮ ሥጋ ምርት መጠን ዕድገት አሁን ካለበት 1,187 ቶን ወደ 2,700 ቶን ለማሳደግ ታቅዷል።

### 3.4.4. የግብርና ምርቶች የወጪ ንግድ

#### የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም የወጪ ንግድ በመጠንና በገቢ ማሳደግ

ዘመናዊና ፍትሀዊ የግብይት ስርአት በመገንባት የግብይት የህግ ማዕቀፎችንና መመሪያዎችን በማጠናከር፣ የግብይት ማዕከላትንና አማራጮችን በማስፋፋት፣ ዘመናዊ የገበያ መረጃ ስርዓት በመዘርጋት፣ የክምችትና የኮንትራት አስተዳደር አሰራርን በማዘመን፣ የገበያ ጥናትና ፕሮሞሽን ተግባራትን በማከናወን፣ የነባርና አዳዲስ መዳረሻ ገበያዎች ድርሻን በማስፋት የላኪዎችን ምርት ግገር፣ ዝግጅት፣ ሽያጭ እና የመላክ ዕውቀትና ክህሎት እንዲሁም የፋይናንስ አቅም በማሳደግ የወጪ ንግድ በመጠንና በገቢ ለማሳደግ ታቅዷል።

የቡና ወጪ ንግድ ከነበረበት 240.37 ሺህ ቶን ወደ 416 ሺህ ቶን ማድረስ እና የወጪ ምንዛሪ ገቢ ግኝትን ከነበረበት 1,331 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ወደ 2,390 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ማድረስ፣ በዋናነት

ባለ ልዩ ጣዕም ቡና (1ኛና 2ኛ) ደረጃ በመጠን 50 በመቶ በማድረስ የገቢ መጠኑን ከነበረበት 689.63 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ወደ 1,466 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ማሳደግ፣ ዕሴት የተጨመረበት የቡና የወጪ ንግድ ድርሻ ከነበረበት 1 በመቶ ወደ 5 በመቶ ማድረስ፤ የሻይ ቅጠል የወጪ ንግድ ከነበረበት 0.90 ሺህ ቶን ወደ 3.75 ሺህ ቶን ማድረስ እና የወጪ ምንዛሪ ግኝት ከነበረበት 2.02 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ወደ 9.1 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ማድረስ፣ የቅመማ ቅመማ የወጪ ንግድ በመጠን ከደረሰበት 6.32 ሺህ ቶን ወደ 19.31 ሺህ ቶን ለማድረስ እና የወጪ ምንዛሪ ግኝትን ከነበረበት 10.48 ሚ/ን አሜሪካን ዶላር ወደ 38.61 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ለማድረስ በመካከለኛ ዘመን ዕቅድ ተይዟል።

## የሆርቲካልቸር የወጪ ንግድ

ለሆርቲካልቸር አምራች ኩባንያዎች የተቀናጀ ድጋፍ በማድረግ በ2015 በጀት ዓመት የተደረሰበትን የኤክስፖርት ምርት መጠን በየዓመቱ ማሳደግ። በቀጣይ ሶስት ዓመታት መጨረሻ ለወጪ ንግድ የሚቀርብ የሆርቲካልቸር (የአበባ፣ አትክልት እና ፍራፍሬ) ምርት በ2015 በጀት አመት ከነበረት 289.55 ሺህ ቶን በእቅድ ዘመኑ መጨረሻ 505.07 ሺህ ቶን ለማድረስ ታቅዷል። የአበባ የኤክስፖርት ምርት በ2015 በጀት አመት ከነበረት 113 ሺህ ቶን በ2018 192.33 ሺህ ቶን ማድረስ፣ የአትክልት ምርት በ2015 በጀት አመት ከነበረት 141 ሺህ ቶን በ2018 248.58 ሺህ ቶን ማድረስ እና የፍራፍሬ ምርት በ2015 በጀት አመት ከነበረት 35.00 ሺህ ቶን በ2018 64.16 ሺህ ቶን ለማድረስ ታቅዷል።

ምርታቸውን ለወጭ ገበያ የሚያቀርቡ ኩባንያዎች ማነቆ በመፍታት፣ ለኤክስፖርትና ለልማት የሚያስፈልጋቸው ግብዓት፣ አገልግሎት ድጋፍ በመስጠትና የውጭ ምንዛሪ ግኝትን በ2015 ከነበረበት 658.30 ሚ/ን ዶላር በእቅድ ዘመኑ መጨረሻ 897.33 ሚ/ን ዶላር ማሳደግ፤ የአበባ የኤክስፖርት ገቢን በ2015 ከነበረበት 566 ሚ/ን ዶላር በ2018 ወደ 745.91 ሚ/ን ዶላር ማሳደግ፤ ከአትክልት ኤክስፖርት በ2015 ከነበረበት 69 ሚ/ን ዶላር በ2018 ወደ 114.86 ሚ/ን ዶላር ማሳደግ እና ፍራፍሬ ኤክስፖርት በ2015 ከነበረበት 23.3 ሚ/ን ዶላር በ2018 ወደ 36.56 ሚ/ን ዶላር ማሳደግ በእቅድ ተይዟል።

## የእንስሳትና ዓሳ የወጪ ንግድ

የተቀነባበሩ የእንስሳት ምርት ወደ ወጪ በመላክ የዶላር ግኝትን ለማሻሻል ተቀነባብሮ ለዉጪ ገበያ የቀረበ የስጋ ምርት (የበግና ፍየል ሥጋ ፣ የዳልጋ ከብ እና የአሳ ስጋ) ምርት በ2015 ከነበረበት 10.72 ሺህ ቶን ወደ 21.24 ሺህ ቶን በማድረስ በ2018 ወደ 123.04 ሚ/ን ዶላር ገቢ ለማግኘት፤ ተቀነባብሮ ለዉጪ ገበያ የቀረበ የእርድ ተረፈ ምርት አሁን ካለበት 4.46 ሺህ ቶን በ2018 ወደ 6.24 ሺህ ቶን በማድረስ 16.57 ሚ/ን ዶላር ገቢ ለማግኘት፤ ተቀነባብሮ ለውጪ ለገበያ የቀረበ የማር ምርት አሁን ካለበት 0.04 ሺህ ቶን በ2018 ወደ 0.9 ሺህ ቶን በማድረስ 2.16 ሚ/ን ዶላር ገቢ ለማግኘት፤ ለዉጪ ገበያ የቀረበ የሰም ምርት አሁን ካለበት 0.139 ሺህ ቶን በ2018 ወደ 0.35 ሺህ ቶን በማድረስ 2.62 ሚ/ን ዶላር ለማግኘት፤ ለውጭ ገበያ የሚቀርብ የተቀነባበረ ወተትና የወተት ተዋጽኦ አሁን ካለበት 1056.2 በሺ ሊ/ር በ2018

ወደ 4719.6 በሺ. ሊ/ር በማድረስ 0.39 ሚ/ን ዶላር ገቢ ለማግኘት በአጠቃላይ በሶስት ዓመቱ 427.43 አሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዷል፡፡

## 3.4.5. የአግሪ ቢዝነስና የከተማ ግብርና ልማት

### የአግሪ ቢዝነስ ስራዎችን ማስፋፋት

የገበያ ተኮር የግብርና ሥርዓትን በመገንባት ሰፊውን ማህብረሰብ የኢኮኖሚው ተጠቃሚ እንዲሆኑ የግብርና ዘርፍ ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ ነው፡፡ አስቻይ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የአግሪቢዝነስ ስራዎች እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም የአግሪቢዝነስ ስራዎች የሴቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት የሚያሳድጉ፣ የስርአተ-ምግብና የአካባቢ ደህንነትን በሚያረጋግጡ ሁኔታ ተቀርፀው የሚተገበሩ ይሆናል፡፡ ስለዚህ አካታች የአግሪቢዝነስ ስራዎች እንዲስፋፋ ለማድረግ በበጀት አመቱ ዘላቂ፣ ፍላጎትንና አቅምን መሠረት ያደረገ የአግሪቢዝነስ ስራዎች እንድስፋፉ በማድረግ የተሳታፊዎች ገቢ ከማሳደግ ባሻገር የግብርና ምርትና ምርታማነትን እንዲሁም የዘርፉን ተወዳዳሪነት ማሳደግና ሰፊ የሥራ እድል የመፍጠር ስራዎች ይከናወናሉ፡፡ በዚህ መሰረት ከዚህ በፊት ታቅደው የተከናወኑ ተግባራት ባይኖሩም በሚቀጥለው ሦስት በጀት አመት የእሴት ሰንሰለት ትንተና በማካሄድ በድምሩ 22 አዋጭነታቸው የተረጋገጠ የአግሪቢዝነስ ስራዎች ተለይተው እንዲከናወኑ ይደረጋል፡፡

አዋጭነታቸው የተረጋገጠ በአግሪቢዝነስ ስራዎች ላይ በ2015 በጀት አመት የተሰማሩ 154,066 የነበሩት ተሳታፊዎች በተለያዩ የአግሪቢዝነስ መስኮች ላይ የሚሳተፉትን በየአመቱ 10% በማሳደግ በ2018 ዓ.ም መጨረሻ ላይ 207,132 እንዲደርስ በማድረግ የሚቀጥሉት ሦስት የበጀት አመታት በድምሩ ወደ 566,618 እንዲደርሱ ይደረጋል፡፡ በ2015 በጀት አመት የአግሪቢዝነስ ልማት አገልግሎት (ABDS) ድጋፍ ያገኙ 155,250 ተጠቃሚዎች የማማከር፣ የሙያ ድጋፍ፣ የህግ ጉዳዮች፣ የሂሳብ አያያዝ፣ ወዘተ ዙሪያ ድጋፍ ያገኙትን በየአመቱ በ10% በማሳደግ በ2018 በጀት አመት ወደ 208,730 በማድረስ በሦስት በጀት አመታት በድምሩ ወደ 570,980 እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም በ2015 በጀት አመት በስራቸው ውጤታማ የሆኑ 800 ሞዴል አነስተኛ አርሶ/አርብቶ አደሮች ድጋፍ በመስጠት በየአመቱ 10% እድገት በማስመዝገብ በ2018 ዓ.ም መጨረሻ ላይ 1,065 እንዲደርሱ በማድረግ በሦስት አመት በድምሩ 2,913 የሚሆኑት ደረጃ በደረጃ ወደ ኢንቨስትመንት እንዲሸጋገሩ ይደረጋል፡፡ ከላይ የተቀመጠውን እቅድ ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

### ሀ) እሴት ሰንሰለት መሰረት ያደረገ የአግሪቢዝነስ ስራዎች ማስፋፋት

የአግሪቢዝነስ ስራዎች በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ ለትርፍ የሚሰሩ ሁሉንም የግብርና ስራዎች ያጠቃልላል፡፡ አካታች የአግሪቢዝነስ ልማትን እውን ለማድረግ ዘላቂ፣ ፍላጎትንና አቅምን መሠረት ያደረገ ወጣቶችን እና ሴቶችን እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት ያሳተፈ ውጤት ተኮር የአግሪቢዝነስ ስራዎች የማስፋፋት ስራዎች ይከናወናሉ፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ የእሴት ሰንሰለት ትንተና

በማካሄድ አዋጭነታቸው በጥናት የተለዩ የአግሪቢዝነስ ስራዎችን መለየት፣ ማስተዋወቅ፣ የተለዩት ስራዎች በህግ ማዕቀፍ እንዲደገፉ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት እና የቴክኖሎጂ አጠቃቀማቸውን በማሻሻል ዜጎችን በማሳተፍ የአግሪቢዝነስ ሥራዎችን የማስፋፋት ስራ በትኩረት ይሰራል፡፡ በተጨማሪም በመንግስትና ባለድርሻ አካላት መካከል ጠንካራ የግንኙነት ስርአት በመዘርጋት ቅንጅታዊ አሰራርን የማጎልበት ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

## ለ) የአግሪቢዝነስ ግንዛቤና የአቅም ግንባታ ስራዎች ማጎልበት

የአግሪቢዝነስ ስራዎችን ለማስፋፋት አገልግሎት ሰጪ አካላት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አስተዳደራዊ መዋቅሮች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት እንዲሁም ተፅዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች ጋር በመቀናጀትና ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠር የአግሪቢዝነስ ልማት አስፈላጊነት ለዘርፉ ተዋንያን የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራዎች ላይ በትኩረት ይሰራል፡፡ የአግሪቢዝነስ ልማት ጠቀሜታ እንዲሰርፅ እና የአሰራር ክፍተቶችንና ማነቆዎችን እንዲለዩ በማድረግና በተለይም አሉታዊ አመለካከቶችና አስተሳሰቦች በማስወገድ ህብረተሰቡ ለለውጥ እንዲነሳሱ እና በስፋት በስራው እንዲሰማሩ የማነቃቃት ስራዎች ይከናወናሉ፡፡ በተለይም የስራዎቹን ባሕሪያት ካለመገንዘብ የተነሳ የግብርና ስራ ሁሉን አቃፊነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገቡ አካላትና የጉልበት ስራ ስለሚበዛበት ለሴቶችና ለሌሎች ልዩ ድጋፍ ለሚሹ አካላት አመቺ እንዳልሆነ የሚያስቡ አካላት ግንዛቤ አግኝተው ቀና አስተሳሰብ እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና የቢዝነስ ሀሳቦች የሚፈልቁበት የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች በአግሪቢዝነስ ስራዎች ላይ የማሳተፍ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

በሌላ በኩል የአግሪቢዝነስ ተዋንያን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ክፍተት በመለየት፣ የተለዩት ክፍተቶች ላይ ቀጣይነትና ተከታታይነት ያለው የክህሎት ሥልጠና በመስጠት አቅማቸው እንዲጎለብት ይደረጋል፡፡ በዚህ መሰረት ተግባር ተኮር በሆኑ የአግሪቢዝነስ ልማትና አስተዳደር፣ የእሴት ሰንሰለት ትንተና፣ የአዋጭነት ጥናትና የንግድ ስራ ዕቅድ ዝግጅትና ተግባራዊነት፣ አግሪፕሩኔርሽፕ ልማት እና የፋይናንስ ክህሎት ማሳደግ ዙሪያ የአቅም ግንባታ ስልጠናና የልምድ ልውውጥ መድረክ ይመቻቻሉ፡፡

## ሐ) የአግሪቢዝነስ ስራዎች ለማስፋፋት የሚያግዙ የግብዓት አቅርቦት ማሻሻል

የአግሪቢዝነስ ልማት በበቂ ደረጃ ለማሳደግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የፋይናንስና የመሬት አቅርቦትን ማሻሻልና የንግድ ስራ እቅድ መሰረት ለታለመለት አላማ እንዲውል ቀጣይነት ያለው ክትትና ድጋፍ ማድረግ እንዲሁም የፋይናንስ ምንጮችን ማስፋት የሚያስችል አካታች የፋይናንስ አቅርቦት ማመቻቸትና ጅምር ላይ ያሉ ስራዎችን የማጠናከር ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

## መ) የአግሪቢዝነስ ተቋማዊ የማስፈፀም አቅም መገንባት

የአግሪቢዝነስ ስራዎች በበቂ ጥናት የተደገፈ፣ ተናባቢና ተደጋጋፊ የሆነ አደረጃጀት እንዲኖር ማድረግ፣ የህግና አሰራር ስርዓት ክፍተቶችን መለየት፣ ተቋማዊና ሙያዊ አቅም ውስንነት እንዲሁም የቴክኖሎጂ

አቅርቦትና አጠቃቀም ስርአት እንዲዳብር በማድረግ ተልዕኮውን በሚገባ እንዳይወጣ ይደረጋል፡፡ ዘርፉ የሚመራበት ፖሊሲና ስትራቴጂዎች የተዘጋጁ ቢሆንም የህግ ማዕቀፍ እና አሰራር ክፍተቶች በዝርዝር በመለየት የማስፈፀም አቅም እንዲሁም ለገበያ ተኮር የግብርና ዕድገት እንዲፋጠን ይደረጋል፡፡

### ሠ) በስራቸው ውጤታማ የሆኑ አርሶ/አርብቶ አደሮች ወደ ኢንቨስትመንት ማሸጋገር

በግብርና ፖሊሲ ማሻሻያ እና በ10 አመት መሪ እቅዱ የተቀመጠ የገበያ ተኮር የግብርና ልማት አቅጣጫ ለመከተል የተቀመጡ ግቦችን እያሳኩ ለመንዝ ሞዴል የሆኑ አነስተኛ አርሶ/አርብቶ አደሮች በገበያ ተፈላጊ የሆኑ የግብርና ምርቶች ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡ ለዚህም የዓለምን ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብና የወደፊት አዝማሚያውንም አስቀድሞ ለመተንበይ የሚያስችል በየወቅቱ የዳሰሳ ጥናቶችን በማካሄድ ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ይሆናል፡፡ በመሰረታዊ የአግሪቢዝነስ ልማትና አስተዳደር ክህሎት ዙሪያ የስልጠና አገልግሎት እንዲያገኙ፣ ስራዎቻቸውን በንግድ ስራ እቅድ (Business Plan) እንዲመሩ ድጋፍ በመስጠት፣ የቁጠባ ባህላቸው እንዲያድግ የምክር አገልግሎት በመስጠትና ከፋይናንስ ተቋማት ጋር ትስስር እንዲፈጠርላቸው በማመቻቸት ደረጃ በደረጃ ወደ ኢንቨስትመንት እንዲሸጋገሩ ይደረጋል፡፡

### 3.4.6. የከተማ ግብርና ልማት

የከተማ ግብርና ልማት በቤተሰብ ደረጃ የምግብ ፍላጎትን ከማሟላት ባሻገር ገቢ በማስገኘት ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ አስተዋጽዖ እንዳለዉ ይታወቃል፡፡ በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸዉ የከተማ ነዋሪዎች በአነስተኛ የከተማ ግብርና ልማት ሥራዎች ላይ በመሰማራት የምግብ ፍላጎታቸዉን ከመሸፈን አልፈዉ የገቢ ምንጭና ሰፊ የስራ ዕድል መፍጠር ያስችላል፡፡ በሀገር ደረጃ በራስ አቅም የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው፣ ለዜጎች ገቢ ማስገኛ እና የቤተሰብ የምግብ ዋስትና ማረጋገጫ፣ ለሥራ አጥ ወጣቶች፣ ሴቶች እና ልዩ ድጋፍ የሚሹ አካላት የሥራ እድል መፍጠሪያ እንዲሁም ለዘርፉ ግብዓት አቅራቢዎች በተጨባጭ የገበያ አማራጭ እንዲሆን በበጀት አመቱ በስፋት ይሰራል፡፡ የከተማ ግብርና ልማት ስራዎች ለአካባቢ ደህንነት ምቹ በሆነ መንገድ የሚተገበሩ ይሆናል፡፡

በዚህም መሠረት በከተማ ግብርና ልማት ስራዎች ላይ ግንዛቤን በማሳደግ በከተማ የሚኖሩ ዜጎች እንዲሳተፉ ለማድረግ በ2015 በጀት አመት 74,880 (ወንድ 52,200 እና ሴቶች 22,680) ዜጎች የከተማ ግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ያገኙ ሲሆን በ2018 በጀት አመት ደግሞ 221,686 (ወንድ 169,524 እና ሴት 52,162) አገልግሎቱን እንዲያገኙ በማድረግ በቀጣይ ሶስት አመት በድምር3 506,419 (ወንድ 381,637 እና ሴቶች 124,782) እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

ኦሎ ዜና ሀ/ወልድ
የስትራተጂክ ጉዳዮ
ሥራ አስፈጻ

### የከተማ ግብርና ሰብል ልማት

ሀ) እህል ሰብል

በከተማ ግብርና በብርዕና አገዳ ሰብሎች የሚለማ መሬት በ2015 በጀት አመት ከነበረበት 1.5 ሺህ ሄ/ር በእቅድ ዘመኑ መጨረሻ 44.01 ሺህ ሄ/ር ለማድረስና በምርት 46.59 ሺህ ኩ/ል ከነበረበት በ2018 ወደ 1,364.30 ሺህ ኩ/ል ለማድረስ ታቅዷል፤ የጥራጥሬ ሰብሎች በ2015 በጀት አመት ከነበረበት 0.46 ሺህ ሄ/ር ወደ 3.93 ሺህ ሄ/ር ለማድረስና በምርት ከነበረበት 8.32 ሺህ ኩ/ል ወደ 70.74 ሺህ ኩ/ል ማድረስ፣ የቅባት ሰብሎች በ2015 በጀት አመት ከነበረበት 0.69 ሺህ ሄ/ር በ2018 ወደ 1.31 ሺህ ሄ/ር ለማረስና በምርት 5.55 ሺህ ኩ/ል ከነበረበት በ2018 ምርት ዘመን ወደ 10.48 ሺህ ኩ/ል ለማድረስ ታቅዷል።

### ለ) ሆርቲካልቸር

በመካከለኛ ዘመን እቅድ የአትክልት ሰብሎች በ2015 በጀት አመት በመሬት ከነበረበት 0.21 ሺህ ሄ/ር በ2018 ምርት ዘመን ወደ 14.18 ሺህ ሄ/ር ለማድረስና በምርት 63.43 ሺህ ኩ/ል ከነበረበት በ2018 ምርት ዘመን 4,254 ሺህ ኩ/ል እና በፍራፍሬ ሰብሎች በ2015 በጀት አመት በመሬት ከነበረበት 0.08 ሄ/ር ወደ 1.89 ሺህ ሄ/ር በምርት ከነበረበት 16.06 ሺህ ኩ/ል ወደ 378.0 ሺህ ኩ/ል ለማድረስ ታቅዷል።

### ሐ) የእንስሳት ምርት ማሳደግ

በከተማ ግብርና የእንስሳት ምርት ለማሳደግ በ2015 ዓ.ም የደረሰበት የምርት መጠን በሚቀጥሉት ሦስት አመታት ለማሻሻል እቅድ ተይዟል። በዚህ መሰረት በ2015 ከተደረሰበት የወተት ምርት ከ230 ሚ/ን ሊ/ር ወደ በእቅድ ዘመኑ መጨረሻ 781 ሚ/ን ሊ/ር፣ የበሬ ስጋ ምርት ከ31 ሺህ ቶን ወደ 114.40 ሺህ ቶን፣ የበግና ፍየል ስጋ ምርት ከ36 ሺህ ቶን ወደ 55 ሺህ ቶን፣ የዶሮ ስጋ ምርት ከ25.9 ሺህ ቶን ወደ 42.35 ሺህ ቶን፣ ቆዳና ሌጦ 1.10 ሚ/ን ወደ 2.53 ሚ/ን፣ የማር ምርት ከ500 ቶን ወደ 22,000 ቶን፣ የአሳ ምርት ከ10,150 ቶን ወደ 7,865 ቶን፣ የእንቁላል ምርት ከ768 ሚ/ን ወደ 3,564.2 ሚ/ን እና ከእንስሳት መኖ ማቀነባበር የሚገኝ ምርት ከ100 ቶን ወደ 38,500 ቶን ለማድረስ እቅድ ተይዟል። የከተማ ግብርና ልማት የምርት እቅድ ውጤታማነት ማረጋገጥ የሚቻለው ከዚህ በታች የተገለጹትን ዋና ዋና ተግባራት በማከናወን ነው።

### መ) የከተማውን ማህበረሰብ ማነሳሳትና ማደራጀት

የከተማ ግብርና ልማት የአሰራር ጥንካሬዎችና ክፍተቶች በመለየት ነዋሪዎች በከተማ ግብርና ላይ በስፋት እንዲሰማሩ የከተማ ግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት የሚሰጠው ባለሙያዎችና በማህበረሰብ ዘንድ ተሰሚነትና ተቀባይነት ባላቸው ግለሰቦች በመጠቀም በአዳዲስ የከተማ ግብርና አሰራሮች ላይ ለመሳተፍ እንዲችል የማነቃቃት ስራ ይከናወናል። ፍላጎትን መሰረት ባደረገ መልኩ በልማት ቡድንና በፓኬጅ በማደራጀት የከተማ ግብርና ልማት ላይ እንዲሰማሩ ይደረጋል።

## ሠ) የከተማ ግብርና ልማት ዙሪያ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት

የከተማ ግብርና ልማት ዙሪያ የአመለካከት፣ የግንዛቤና የአቅም ክፍተቶችን መለየት፣ ሙያዊ የአቅም ውስንነት እና የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ክፍተቶችን እና የአሰራር ክፍተቶች በጥናት በመለየት የአመለካከት ለውጥ፣ የግንዛቤ መፍጠሪያና የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፡፡

## ረ) ተስማሚ የከተማ ግብርና ቴክኖሎጂዎች እና ግብዓቶች ማመቻቸት

ለተለያየ ስነ ምህዳር እና የግብርና ስራ ዘርፎች ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችንና ግብዓቶች አቅርቦት የሚያሰልጥ አሰራር ስርዓት የመዘርጋት፣ ፍላጎት በመለየት የቴክኖሎጂዎቹንና ግብዓቶቹን ብዜትና ስርጭት በመደገፍ የከተማ ግብርና ላይ የሚሰማሩ አካላት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

## ሰ) ለከተማ ግብርና ልማት ምርጥ ተሞክሮ ፓኬጆችን ማስፋት

በሀገር አቀፍ እና በአለም አቀፍ ደረጃ በከተማ ግብርና ተጠቃሚዎች ተሞክረው ውጤታማ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን እና አሰራሮችን በተሟላ ሁኔታ በመሰብሰብና በመቀመር እንዲሁም በተቀመሩ የከተማ ግብርና ምርጥ ተሞክሮዎች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በማመቻቸት ተመሳሳይ ስነ-ምህዳር ወዳላቸው ከተሞች እንዲስፋፉ በማድረግ የከተማ ግብርና አርሶ/አርብቶ አደሮች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

## ሸ) የከተማ ግብርና የኤክስቴንሽን አገልግሎትን ተደረሽ ማድረግ

ለከተማ ግብርና ልማት የኤክስቴንሽን አገልግሎትን ተደራሽ ከማድረግ አኳያ በሚቀጥለው ሦስት በጀት አመታት ትኩረት ተሰጥቶት ይሰራል፡፡ በዚህም መሰረት ለከተማ ግብርና የኤክስቴንሽን አገልግሎትን ለመስጠት ይቻል ዘንድ የተቀረጸው የከተማ ግብርና የኤክስቴንሽን ስርዓት የማስፈፀሚያ ሰነድ ይዘጋጃል፤ እንዲሁም የኤክስቴንሽን ፓኬጅ በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት የግንዛቤ መፍጠሪያ ስልጠና ለሁሉም ተጠቃሚዎች ይሰጣል፡፡

## ቀ) የከተማ ግብር ልማት ባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ አሰራር ማጠናከር

በየደረጃው የሚገኙ የከተማ ግብርና መዋቅሮችና ሌሎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለከተማ ግብርና ልማት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት መካከል ቅንጅታዊ አሰራር እንዲኖር በማድረግ የተያዘው የከተማ ግብርና ልማት ትኩረት ግቡን እንዲመታ ይደረጋል፡፡

ዜና ሀ/ወልድ
የስትራቴጂክ ጉዳዮች ሥራ አስፈጻሚ

በ) የከተማ ግብርና ልማት የክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ ስርዓት ይዘረጋል

በየጊዜው እያደገ ከሚመጣው የከተማ ግብርና ልማት ድጋፍ ፍላጎትና ተለዋዋጭ ሁኔታ ክትትል በማድረግ እየተገመገመ የሚሻሻል ሲሆን በሚደረገው የግምገማ ውጤት መሠረት የከተማ ግብርና አፈፃፀምን በብቃት ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል ዝርዝር የድርጊት መርሀ ግብሮችን በቅንጅት የክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት በውጤት ላይ የተመሰረተ ከፌዴራል እስከታችኛው መዋቅር ድረስ አካታች ክትትል፣ ድጋፍ እና ግምገማ ስራዎችን ይካሄዳል።

የግብርና ስራ ዕድል ፈጠራና የከተማ ግብርና የፕሮጀክቶች እቅድ ሃሳቦች

በቀጣይ ሦስት አመታት በንኡስ ዘርፉ የተያዙትን እቅዶች ለማሳካት በመደበኛ ፋይናንስ ብቻ አዳጋች ይሆናል። በመሆኑ ከታች የተዘረዘሩ ስራዎች ማስፈጸሚያ የሚውል ፕሮጀክቶች መቅረጽ እና አዋጭነታቸው ተጠንተው ከተረጋገጠ እና ከጸደቀ በኃላ ወደ ስራ ማስገባት ያስፈልጋል፡-

የስራ ፈጠራ ማበልጸግያ ማዕከላት (Incubation Centres) በማስፋፋት የግብርና ስራ ፈጠራ ሀሳብ ያላቸው አካላት ፍላጎት መሰረት ያደረገ የአግሪቢዝነስ ስራዎች ላይ እንዲሰማሩ የሚያግዝ እና የዲጂታል አግሪቢዝነስ ስራዎች ለማስፋፋት የሚደግፍ ፕሮጀክት፤

በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ የምርት ግብይትና ስርጭት አንዱ ቢዝነስ የሚሰራበት የስራ ዘርፍ በመሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መግቢያ በሮች እና የመንገድ ዳር የግብርና ምርት ሽያጭ ቢዝነስ የሚሰራበት ማዕከላት የመገንባት ፕሮጀክት፤

የከተማ ግብርና ሞደል ሰርቶ ማሳያ ማዕከላት (Smart Urban Agriculture Demonstration Centres) በአዲስ አበባ እና በዋና ዋናዎች የክልል ከተሞች በመገንባት የከተማ ግብርና ለማስፋፋት የሚደግፍ ፕሮጀክት።

### 3.4.7. ህብረት ስራ ማህበራት

የኅብረት ሥራ ማህበራትን የማጠናከርና የማደራጀት አገልግሎት በመስጠት የማጠናከር አገልግሎት በየዓመቱ በድግግሞሽ በመስጠት የ2015 አፈፃፀማችንን መነሻ በማድረግ የመሰረታዊ ማህበራትን 184,370 ወደ 239,367 በመድረስ እንዲሁም ዩኒየኖችን በተመሳሳይ ከ1,485 ወደ 2,010 በማድረስ በተጨማሪም የአካባቢ ሀብትን መሠረት አደርጎ በተለያዩ ዓይነትና ደረጃ ማህበራትን ማደራጀት የ2015 አፈፃፀማችንን መነሻ በማድረግ የመሰረታዊ ማህበራትን 110,584 ወደ 114,389 በማድረስ እንዲሁም ዩኒየኖችን በተመሳሳይ ከ403 ወደ 414 በማድረስ የአባላትን ቁጥር በማሳደግ የ2015 አፈፃፀማችንን መነሻ በማድረግ 28,582,005 (ወንድ 18,898,771 ሴት 9,683,234 ) ወደ 31,164,304 (ወንድ 20,295,602 ሴት 10,866,551) ማሳደግን ትኩረት በማደረግ አባላቱ የሚያመነጩትን የካፒታል መጠናቸውን በ2015 ዓ.ም

ከደረሰበት 48.7 ቢሊዮን ብር ወደ 56.3 ቢሊዮን ብር በማሳደግ ዉጤት ማምጣት ላይ ትኩረት ያደረገ አንድ ፕሮግራም ነው።

በሌላ በኩል በጥናት ላይ የተመሰረተ እና ወቅታዊ የሆነ ስልጠና ለሁሉም የኅብረት ሥራ ፈጻሚና አስፈጻሚ አካላት በየዓመቱ በማዘጋጀት እና የተጀመረውን የሥራ ላይ ስልጠና አጠናክሮ በማስቀጠል የአቅም ግንባታ ሥራዎችን የ2015 ዓ.ም አፈፃፀም መነሻ 67,435 የኅብረት ሥራ ማስፋፊያ ባለሙያዎችን፣ 671,552 የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራሮችን፣ 84,907 የኅብረት ሥራ ማህበራት ቅጥር ሰራተኞችን በድምሩም 823,894 በማድረግ በ2018 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 108,865 የኅብረት ሥራ ማስፋፊያ ባለሙያዎችን፣ 1,249,815 የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራሮችን፣ 155,398 የኅብረት ሥራ ማህበራት ቅጥር ሰራተኞችን በድምሩም 1,514,078 በማሳደግ የዘርፉን ተዋንያን በማብቃት እና የስልጠናውን ውጤታማነት ማሳደግን ትኩረት ያደረገ አንድ ፕሮግራም ነው።

የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሀገር ውስጥ የግብርና ምርቶች የግብይት ድርሻቸውን በ2015 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት 18 በመቶ ወደ 23 በመቶ እንዲሁም የውጭ ግብይት ድርሻቸውን በ2015 ዓም መጨረሻ ከደረሰበት 7 በመቶ ወደ 12 በመቶ በማድረስ አባላት ከምርቶቻቸው ቀጥተኛ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻልና በኅ/ሥራ ማህበራት ምርጥ ዘር አባዝተው የሚያቀርቡ የኅ/ሥራ ማህበራት ቁ/ር 35 ከነበረበት ወደ 62 ማድረስ ዉጤት ማምጣት ላይ ትኩረት ያደረገ ሌላ ፕሮግራም ነው።

እንዲሁም የማዳበሪያ እና የኬሚካል/ ፀረ-ተባይና ፀረ-ፈንገስ / አቅርቦትና ስርጭትን ድርሻ በ2015 ዓም መጨረሻ ከደረሰበት 92 በመቶ ወደ 96 በመቶ ማድረስ የቅድመ እና ድህረ ምርት የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት የሚሰጡ የግብርና ኅብረት ሥራ ማህበራትን ቁጥር በ2015 ዓ.ም መጨረሻ ከተደረሰበት 377 ወደ 400 በማሳደግ፣ የግብርና ኅብረት ሥራ ማህበራት የአካባቢያቸውን ፀጋ መሠረት አድርገው የሚያቋቁሟቸውን የግብርና ምርት ማቀነባበሪያዎችንና ኢንዱስትሪዎች ቁጥር በ2015 ዓ.ም መጨረሻ ከተደረሰበት 1,914 ወደ 1,989 በማድረስና ለምርቶቻቸው እሴት ጨምረው በገበያው ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ከማድረግም አልፎ ለዜጎች የስራ እድል መፍጠሪያ ማእከላት መሆን እንዲችሉ በኅ/ሥራ ማህበራት በስራ እድል ፈጠራ የቋሚ ቅጥር ሰራተኞች ወደ 177,207 በማድረስ ላይ ትኩረት ያደረገ ሌላ ፕሮግራም ነው።

የተለያዩ የፋይናንስ አገልግሎቶችን በማስፋፋትና የቁጠባ ባህልን በማጎልበት የአባላትንና የህብረተሰቡን ገቢ እያሳደጉና የሥራ እድሎችን እየፈጠሩ ኢንቨስትመንትን እንዲሁም የአባላትን የብድር ፍላጎት ለሟሟላት የቁጠባ መጠን በ2015 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት ብር 49.7 ቢ/ን ወደ ብር 75.4 ቢ/ን በማድረስ በፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባላት የሚቀርበውን የብድር መጠን በ2015 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት ብር 58.4 ቢ/ን ወደ ብር 89 ቢ/ን በማሳደግ የአምራቹን የፋይናንስ አቅርቦት ችግር በመፍታት ውጤታማ እንዲሆኑ በማስቻል ላይ ትኩረት ያደረገ ሌላ ፕሮግራም ሲሆን በአጠቃላይ የአባላትን መሪነት፣ ባለቤትነት፣ ተጠቃሚነት እንዲሁም እምነት በማሳደግ የኅ/ሥራ ማህበራት በሀገር ኢኮኖሚ ግንባታ ላይ ያላቸውን ሚና እንዲያሳድጉ ማድረግ ነው።

የኅብረት ሥራ ማህበራትን የኢንስፔክሽን ሽፋን በ2015 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት ከ50.7 በመቶ በ2018 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 58 በመቶ ማድረስ፤ የኅብረት ሥራ ማህበራትን የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ አገልግሎትን በ2015 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት 25,323 ማህበራት በ2018 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 39,573 ማህበራት ማሳደግ እንዲሁም ለማስቻል የኅበረት ሥራ ማህበራት ኦዲት አገልግሎት ሽፋን በ2015 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት 38.03 በመቶ በ2018 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 50 በመቶ በማሳደግ የኅብረት ሥራ ማህበራት መርሆዎቻቸውንና እሴቶቻቸውን ጠብቀው በመሥራት የአባላትን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ የሚችሉበት ቁመና እንዲኖራቸው እና ህግን አክብረው መስራታቸውን ኢንስፔክት ብቁና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በተቀመጠው መመዘኛ መሥፈርት መሠረት ተመዝነው በሚያገኙት የአፈፃፀም ብቃት ደረጃቸውን በመለየት ለአቅም ግንባታና ለሌሎች ድጋፍ አሰጣጥ ዝግጁ እንዲሆኑ በማድረግ የታዩ የአሰራር ግድፈቶች ላይ የእርምት እርምጃ ተግባር ማበከናወን ጠንካራ የቁጥጥር ስርአት ዘርግቶ በመተግበር ከብልሹ አሰራር፤ ከብክነት፤ ከሌብነትና ከውድመት ማህበራትን በመታደግ ውጤታማነታቸውን በማሳደግ በሀገር ኢኮኖሚ ግንባታ ላይ ያላቸውን ሚና ያደገና ቀጣይነት ያለው እንዲሆን ለማድረግ ነው።

የማዳበሪያ የአቅርቦት ሰንሰለትን ማሻሻልና ዘመናዊና ቀልጣፋ እንዲሆን ለማስቻል በማዳበሪያ አቅርቦት ሰንሰለት ማሻሻያ ጥናት የተቀመጡ ምክር ሃሳቦች ተግባራዊ ይደረጋሉ። እነዚህን የውሳኔ አቅጣጫዎች ተግባራዊ በማድረግ ማዳበሪያን ለአርሶ አደሩ በሚፈለገው ወቅት፣ መጠን፣ ጥራት፣ ዓይነት፣ ቦታ እና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ አስቻይ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ። በዚህም መሠረት በየዓመቱ የሚደረገውን የማዳበሪያ ግዢ አሠራር ወደ ተራዘመ ጊዜ አሰራር በመቀየር /ከ2-3 ዓመት/ የሚቆይ የግዢ ውል ከተለያዩ አምራቾች ወይም ከተመረጡ አቅራቢዎች ጋር ይፈጸማል። 2015/16 ምርት ዘመን አመታዊ የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት 1.62 ሚ/ን ሜ/ቶን ከተደረሰበት በቀጣይ ሶስት ዓመታት በ2016/17 ም/ዘመን 2.3 ሚ/ን ሜ/ቶን፣ በ2017/18 ም/ዘመን 3.1 ሚ/ሜ/ቶን፣ በ2018/19 ም/ዘመን 3.5 ሚ/ሜ/ቶን የአፈር ማዳበሪያ ለማቅረብ በትኩረት ይሰራል። ዕቅዱ ለሶስት የምርት ዘመናት ለበልግ፣ ለመኸር እና ለመስኖ ጥቅም ላይ የሚውል ታሳቢ የተደረገ ሲሆን በየዓመቱ ለአነስተኛ መሬታ ይዞታ ላላቸው አ/አደሮች እና በሰፋፊ ማሳ ላይ ለተሰማሩ ባለሃብቶች በሚል በዝርዝር ተለይቷል ።

**የአግሮ ኬሚካል አቅርቦትን በተመለከተ** በ2015/16 ምርት ዘመን የቀረበው አግሮ ኬሚካል 1.32 ሚ/ን ሊ/ር ከተደረሰበት በቀጣይ ሶስት ዓመታት በ2016/17 ም/ዘመን 11.13 ሚ/ን ሊ/ር፣ በ2017/18 ም/ዘመን 11.44 ሚ/ን ሊ/ር እና በ2018/19 ም/ዘመን 11.58 ሚ/ን ሊ/ር ለማቅረብ ታቅዷል። በ2015 በጀት ዓመት የቀረበው ኬሚካል መረጃ ከግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን እና ከኦሮሚያ ፌዴሬሽን የተገኘ መረጃ ብቻን መሰረት ያደረገ ሲሆኑ ከ2016/17 ጀምሮ በሌሎች አቅራቢዎችን ታሰቢ ያደረገ በመሆኑ እቅዱ ተለጥጦ ታቅዷል።

በየምርት ዘመኑ ያስፈልጋሉ በሚል የታቀዱ ኬሚካሎች በሙያዊ ዕይታ የተቃኙ ፣ በየዓመቱ እየተከሰቱ ካሉ ክስተቶች በመነሳትና አጠቃላይ ሁኔታውን ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ነው። ታሳቢ ከተደረጉ ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል በየዓመቱ የበሽታ ፣ የነፍሳት እና የተባይ ክስተት መጨመር፣ የአየር ንብረት

መቀያየር ለክስተቱ እንደ ምቹ ሁኔታ መጠቀም ፣ አካባቢን በመላመድ ቶሎ አለመሞት ማለትም በርካታ መጠን ያለው ኬሚካል መጠቀም የመሳሰሉት ዋና ዋናዎቹ ታሳቢ የተደረጉ ጉዳዮች ናቸው።

**የግብርና ኖራ አቅርቦትን በተመለከተ** ባለፉት ዓመታት ያልታከመ እና በጠንካራ አሲዳማነት ደረጃ ላይ ከሚገኘውን መሬት ውስጥ አቅም የፈቀደውን ያህል በየዓመቱ 300 ሺህ ሄ/ር ለማከም በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት 27 ሚ/ን ኩ/ል ኖራ ለማቅረብ የታቀደ ሲሆን በየዓመቱ 9 ሚ/ን ኩ/ል ኖራ እንደሚቀርብና አንድ ሄ/ር ለማከም 30 ኩ/ል እንደሚያስፈልግ ታሳቢ ተደርጓል።

የግብርና ብድር አቅርቦትን በተመለከተ በ2015/16 ም/ዘመን ለዋና ዋና ግብዓቶች መግዣ (የአፈር ማዳበሪያ፣ ለም/ዘር ፣ ለኬሚካል እና ለትራንስፖርት) ጥቅም ላይ የዋለውን ብር 62.95 ሚሊዮን ብር ታሳቢ በማድረግ ለሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት በአጠቃላይ 478.27 ቢ/ን ብር ለማቅረብ ታቅዷል። ይህም በየዓመቱ ሲተነተን በ2016/17 110.88 ቢ/ን፣ በ2017/18 133.06 ቢ/ን እና በ2018/19 159.67 ቢ/ን ብር እንደሚያስፈልግ ታሳቢ ተደርጓል።

የሰብል ምርጥ ዘር አቅርቦትን በሚመለከት በ2015/16 የተደረሰበት 1.5 ሚ/ን ኩ/ል ሲሆን በቀጣይ ሶስት በ2016/17 ም/ዘመን 2 ሚ/ን ኩ/ል፣ በ2017/18 ም/ዘመን 2 ሚ/ን ኩ/ል፣ በ2018/19 ም/ዘመን 2 ሚ/ን ኩ/ል የሰብል ም/ዘር ለማቅረብ ታቅዷል። ይህም የዋና ዋና ሰብል ዓይነቶች ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ነው።

**የእንስሳት ግብዓት አቅርቦትን በተመለከተ የአንድ ቀን የዶሮ ጫጩት አቅርቦት** በ2015 በጀት አመት ከተደረሰበት 41 ሚ/ን አመታዊ የአንድ ቀን ጫጩት አቅርቦት በቀጣይ ሶስት ዓመታት በ2016 በጀት ዓመት 62 ሚ/ን ፣ በ2017 በጀት ዓመት 82 ሚ/ን እና በ2018 በጀት ዓመት 124 ሚ/ን አንድ ቀን ጫጩት ለማቅረብ ታቅዷል።

**ዘመናዊ የንብ ቀፎ አቅርቦት ለማሰድግ** በ2015 በጀት አመት ከተደረሰበት 291.7 ሺህ አመታዊ የዘመናዊ የንብ ቀፎ አቅርቦት በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት በ2016 በጀት ዓመት 1,100 ሺህ ፣ በ2017 በጀት ዓመት 1,210 ሺህ እና በ2018 በጀት ዓመት 1,331 ሺህ ዘመናዊ የንብ ቀፎ ለማቅረብ ታቅዷል።

**የተቀናባበረ እንስሳት መኖ ዘር አቅርቦት በተመለከተ** በ2015 ከተደረሰበት 2.83 ሺህ ቶን በ2016 በጀት አመት 2.98 ሺህ ቶን፣ በ2017 በጀት ዓመት 3.27 ሺህ ቶን እና በ2018 በጀት ዓመት 3.6 ሺህ ቶን የመኖ ዘር ለማቅረብ ታቅዷል ።

**በተመሳሰይ ሁኔታ የዓሳ ጫጩት አቅርቦት ለማሳደግ** በ2015 በጀት አመት ከተደረሰበት 0.94 ሚ/ን አመታዊ የዓሳ ጫጩት አቅርቦት አቅም በማሳደግ በ2016 በጀት ዓመት 6.78 ሚ/ን ፣ በ2017 በጀት ዓመት 7.46 ሚ/ን እና በ2018 በጀት ዓመት 8.2 ሚ/ን ለማቅረብ ታቅዷል።

## 3.5. የግብርና ቁጥጥር

### የዕጽዋት ሬጉላቶሪ የግብዓት ቴክኖሎጅ አገልግሎትና ምርት ጥራት ቁጥጥር

በዚህ ፕሮግራም ውስጥ በቁልፍ አመልካችነት የተያዙ ሶስት ሲሆኑ እነዚህም በግብዓት ቁጥጥር ፣ በምርትና ቴክኖሎጂ የትኩረት መስኮች የታቀፉ ናቸው። እነዚህን ወደ ስኬት ለማድረስ በርካታ ዝርዝር ተግባራት የሚከናወኑ ሲሆን በዚህ የሶስት ዓመታት ዕቅድ ቁልፍ የሆኑ አመልካቾችን ብቻ መሠረት ያደረገ ሆኖ እንደሚከተለው ቀርቧል።

### ውጤታማ ጥራቱና ህንነቱ የተጠበቀ ፀረተባይና ማዳበሪያ

ለሙከራ ምርምር ፈቃድ የተሰጣቸው ፀረ-ተባይና ማዳበሪያዎች በሶስት ዓመቱ ለ350 የሚሠጥ ሲሆን የዚህ ቁልፍ አመልካች በአማካይ በየዓመቱ በቁጥር 118 በመጨመር የሶስት ዓመት አፈጻጸም ልዩነት 30% ለማድረስ የሚሠራ ይሆናል፡፡ ተገምግመው የተመዘገቡ በሶስት ዓመት ውስጥ 750 የፀረ-ተባይ እና የአፈር ማዳበሪያዎችን ሰነድ በመገምገም ለመመዝገብ የታቀደ ሲሆን ይህንንም በአማካይ በየዓመቱ 250 ሰነዶችን ገምግሞ በመመዝገብ የሚከናወን ሆኖ የ2015 ዓ.ም አፈጻጸምን እንደ መነሻ በመውሰድ በሶስት ዓመት ውስጥ 14.7% የአፈጻጸም ልዩነት ለማምጣት ይሠራል፡፡ የቅድመ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገቢያ ፈቃድ የተሰጣቸው ፀረ-ተባይ እና ማዳበሪያዎች ብዛት በ2015 1,873 ለማድረስ የተቻለ ሲሆን በ2018 በጀት ዓመት መጨረሻ በድምሩ 6,000 ለማድረስ የሚሠራ ሲሆን ይህንንም በአማካይ በየዓመቱ 2,000 ክንውን በመፈጸም የሚከናወን ይሆናል፡፡ ድንገተኛ ፍተሻ የተደረገባቸው የፀረ-ተባይ እና የአፈር ማዳበሪያ ተቋማት ብዛት በአማካይ በየአመቱ 6 ድንገተኛ ፍተሻ በማከናወን በ2018 በጀት ዓመት መጨረሻ 18 ጊዜ ለማከናወን የሚሠራ ይሆናል፡፡

### ወደ ውጭ ለሚላኩና ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ የእጽዋት ምርቶች የተሰጠ የጤና ማረጋገጫ

በ2018 በጀት ዓመት መጨረሻ በድምሩ 1,687,721 ሜትሪክ ቶን የእጽዋት ምርቶች የጤናና የጥራት ምርመራ ተደርጎላቸው ወደ ውጭ የሚላኩ ሲሆን ይህንንም በየዓመቱ በአማካይ 562,573.81 ሜትሪክ ቶን በማከናወን የሚፈጸም ሆኖ በ2015 ከነበረው ጋር በንጽጽር የአፈጻጸሙን ልዩነት 21.6% በቀጣዮቹ ሶስት ዓመታት ለማድረስ የሚሠራ ይሆናል፡፡ በድምሩ 128,878 የእጽዋት ምርቶች የጤና ማረጋገጫ ሰርተፊኬቶችን ወደ ውጭ ለሚላኩ የእጽዋት ምርቶች የሚሰጥ ሲሆን ይህንንም በየዓመቱ በአማካይ 42,626 ሰርተፊኬቶችን በመስጠት የሚፈጸም ይሆናል፡፡ በ2018 በጀት ዓመት መጨረሻ በድምሩ 258,830 ሜትሪክ ቶን ለውጭ ገበያ በሚቀርቡ በተመረጡ የዕጽዋት ምርቶች ላይ የማዕጠንት /Fumigation/ የሚደረግ ሲሆን በ2015 የነበረው እንደ መነሻ ተወስዶ በየዓመቱ በአማካይ 86,276.67 ሜትሪክ ቶን በማከናወን የሚፈጸም ይሆናል፡፡ በ2018 በጀት ዓመት መጨረሻ በድምሩ ለ6,160 ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕፅዋትና የዕፅዋት ዉጤቶች ደህንነታቸዉን ጠብቀዉ እንዲገቡ በላብራቶሪ የተደገፈ ምርመራ የሚከናወን ሲሆን በአማካይ በየዓመቱ ለ2.053 ምርቶች የምርመራ ስራው የሚከናወን ይሆናል፡፡

### በቁጥጥር ሰንሰለት ውስጥ ያለፈ ጥራት ያለው ዘር

በ2018 በጀት ዓመት ማጠናቀቂያ በድምሩ ለ340 ከተለያዩ የምርምር ተቋም ዩኒቨርስቲዎች የግል ኩባንያዎች የቀረቡ ዝርያዎችን በመስክ እንዲገመገሙ የማስተባበር እና የመገምገም የመከታተል ስራ የሚከናወን ሲሆን የ2015 በጀት ዓመት አፈጻምን እንደ መነሻ በመውሰድ በየዓመቱ በአማካይ የ113 ጭማሪ በማሳየት የሚከናወን ይሆናል፡፡ በ2015 መጨረሻ ለ85 ጥያቄ ለሚያቀርቡ ዘር አስመጪዎች አምራቾችና አዘጋጅዎች የብቃት ማረጋገጫ መስጠትና ለማደስ የታቀደ ሲሆን የ2015 በጀት ዓመት አፈጻጸምን እንደ መነሻ በመውሰድ በየዓመቱ በአማካይ 28 በማከናወን የሚፈጸም ይሆናል፡፡ በ2018 ዓ.ም መጨረሻ በድምሩ ለ750 የዘር ናሙናዎች በላቦራቶር የዘር ጥራት ፍተሻ የሚደረግባቸው የሚከናወን

ሲሆን የ2015 በጀት ዓመት አፈጻጸምን እንደ መነሻ በመውሰድ በየዓመቱ በአማካይ 250 በማከናወን የሚፈጸም ይሆናል።

### የእንስሳትና ዓሳ የግብዓት ቴክኖሎጅ አገልግሎትና ምርት ጥራት ቁጥጥር

### ደህንነቱና ጥራቱ ተረጋግጦ ለውጭ ገበያ የተላከ የእንስሳት ምርትና የቁም እንስሳት

በ2018 መጨረሻ ለ5,766,000.00 እንስሳት (በግ ዳልጋ ከብት) የቅድመ ዕርድ ምርመራ ለማድረግ የታቀደ ሲሆን የ2015ን እንደ መነሻ ተወስዶ በየዓመቱ በአማካይ ለ1,922,000 እንስሳት ምርመራው የሚደረግ ይሆናል። በ2018 መጨረሻ ለ5,614,430 እንስሳት ስጋ በግ ፍየልና ዳልጋ ከብት) የድህረ ዕርድ ምርመራ ለማድረግ የታቀደ ሲሆን የ2015ን እንደ መነሻ ተወስዶ በየዓመቱ በአማካይ ለ1,871,476.67 እንስሳት ስጋ ምርመራው የሚደረግ ይሆናል። በቀጣዮቹ ሶስት ዓመታት በድምሩ 29,200 ዓለም ዓቀፍ የጤና ማረጋገጫ ሰርፊኬት የሚሰጥ ሆኖ የ2015 ክንውን እንደ መነሻ ተወስዶ በየዓመቱ በአማካይ 9,773 ሰርተፊኬት መስጠት የሚከናወን ይሆናል። በ2018 በጀት ዓመት ማጠናቀቂያ በድምሩ ለ412,000 የቁም እንስሳት የኳራንቲን አገልግሎት ተሰጥቷቸው ወደ ውጭ የሚላኩ ሲሆን የ2015 ክንውን እንደ መነሻ ተወስዶ በየዓመቱ በአማካይ ለ137,333.33 የቁም እንስሳት አገልግሎቱ የሚሰጥ ይሆናል። በኳራንቲን የቁጥጥር ስርአት ውስጥ አልፎ የቨተርነሪ ሳኒተሪ ሰተፍኬት የሚሰጠው ማር በ2018 በጀት ዓመት መጨረሻ 690 ቶን ለማድረስ የሚሰራ ይሆናል። በተመሳሳይ ለ690 ቶን ሰም አገልግሎቱ የሚሰጥ ይሆናል። በ2018 ማጠናቀቂያ በድምሩ ለ4,000,000 የአንድ ቀን ጫጩቶችና ለ1,639,000 የለማ እንቁላል በኳራንቲን የቁጥጥር ስርአት ውስጥ አልፎ የቨተርነሪ ሳኒተሪ ሰተፍኬት የሚሰጣቸው ይሆናል። እስከ 2018 መጨረሻ በድምሩ ለ1,810 የእንስሳት ውጤቶች (ስጋ ማር፣እና ወተት) ናሙናዎች የላቦራቶሪ ምርመራ በማድረግ ጥራትና ደህንታቸውን የማረጋገጥ ስራ የሚከናወን ይሆናል።

### ጥራቱ ፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድሃኒት

በ2018 ማገባደጃ በድምሩ ለ548 የእንስሳት መድኃኒትና የህክምና መሳሪያዎች ምዝገባ ሰነዶች የሚገመገሙ ሲሆን የ2015 ክንውን እንደ መነሻ ተወስዶ በየዓመቱ በአማካይ የ182 የእንስሳት መድኃኒትና የህክምና መሳሪያዎች ምዝገባ ሰነዶች በመገምገም የሚሠራ ይሆናል። በተመሳሳይ በድምሩ የ27 የክትባት ሰነዶች ግምገማ የሚደረግ ይሆናል። በቀጣዮቹ ሶስት በድምሩ 1,152 የእንስሳት መድኃኒት ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጣቸው ወይም የሚታደስላቸው ሲሆን የ2015 በጀት ዓመት ክንውን እንደመነሻ ተወስዶ በየዓመቱ በአማካይ ለ384 የእንስሳት መድኃኒት ተቋማት የብቃት ማረጋጋጫ የሚሰጣቸው ወይም የሚታደስላቸው ይሆናል። በቀጣዮቹ ሶስት ዓመታት በድምሩ ለ1,530 የእንስሳት መድሃኒቶች የቅድመ ማስገቢያ ፈቃድ የሚሰጥ ሲሆን በ2015 የነበረው ክንውን እንደ መነሻ ተወስዶ በየዓመቱ 510 በመጨመር የሚከናወን ይሆናል። እስከ 2018 ዓ.ም ማጠናቀቂያ በድምሩ 1,891 ኢንስፔክሽን የሚሰራ ይሆናል። ይህም በአማካይ 631 ሲሆን በተመሳሳይ 907 በየዓመቱ በአማካይ 301 ናሙናዎች ተሰብስበው ለቅድመ ምዝገባ፣ ከኮንሳይንመንት እና ከድህረ ገበያ ለምርመራ ይላካሉ። እስከ 2018 ማገባደጃ በድምሩ 918

በየዓመቱ በአማካይ 318 የእንስሳት መድሃኒትና የክትባት ናሙናዎች በላቦራቶሪ ምርመራ ጥራትና ደህንታቸውን የማረጋገጥ ስራ የሚከናወን ይሆናል።

**ጥራቱ ደህንነቱና የተረጋገጠ የእንስሳት መኖ**

በ2018 መጨረሻ በድምሩ ለ1,179 የእንስሳት መኖ ንግድ ተቋማትና ባለሙያዎች የብቃት ማረጋገጫ የመስጠትና የማደስ ስራ የሚሠራ ሲሆን ይህም በአማካይ በየዓመቱ 379 ተቋማትና ባለሙያዎች ላይ የሚከናወን ይሆናል። በድምሩ ለ9,000 ቶን የመኖና መኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮች የግዥና ማስገቢያ ፈቃድ በአንድ መስኮት አገልግሎት እስከ 2018 ማጠናቀቂያ ለመስጠት የታቀደ ሲሆን በየዓመቱ በአማካይ 3,000 ቶን በማከናወን የሚፈጸም ይሆናል። እስከ 2018 ማጠናቀቂያ በድምሩ 420 የመኖ ናሙናዎችን በላቦራቶሪ ምርመራ ጥራትና ደህንታቸው ለማረጋገጥ በዕቅድ የተያዘ ሲሆን ይህንንም በየዓመቱ 140 በማከናወን የሚሠራ ይሆናል።

## 3.6. የግብርና ትራንስፎርሜሽን ማሳለጥ

### የግብርና ሴክተር ላይ ያሉ ሥርዓታዊ ተግዳሮቶች እና የፖሊሲ ክፍተቶችን መለየትና የመፍትሄ ሀሳቦችን መጠቆም

በቀጣይ ሶስት አመታት የሚዘጋጁት የፖሊሲ ሰነዶች ውስጥ የሚካተቱት ነጥቦች በግብርና ምርምር ውስጥ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ማሻሻል፣ የግብርና ግብዓት አቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ማሻሻል፣ የግብዓት ፍላጎት፣ ምርት እና አቅርቦት መከታተያ ሥርዓት፣ አካታች የኤክስቴንሽና ምክር አገልግሎት እና ገለልተኛ የቁጥጥር ሥርዓት ማቋቋም ላይ ያተኩሩ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ እንደ የግብርና ንግድ ኢንቨስትመንት፣ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ማዘመን፣ በግብርና ውስጥ ፋይናንስ እና ኢንሹራንስ ማስፋፋት እና በግብርና ውስጥ ፋይናንስ እና ኢንሹራንስ ማስፋፋት አይነት ያሉ በጠቅላላው 8 የሚሆኑ የግብርና ፖሊሲ ጥናቶችን ለማዘጋጀት ታቅዷል። ከፖሊሲ ጥናት ባሻገርም የተለያዩ የሴክተሩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ ጥራታቸውን የጠበቁ እና በፈጠራ የታገዙ ጥናቶችን ለማካሄድ ታቅዷል።

### ሥርዓታዊ ችግሮችን የሚፈቱ አዳዲስ ፕሮጀክቶችን መንደፍ፤ ሰርቶ ማሳየትና ማስረከብ

በቀጣዮቹ ሶስት አመታት ግ.ት.ኢ. የተለያዩ የአሰራር ተግዳሮቶችን ለመፍታት ያለሙ አጠቃላይ 19 ፕሮጀክቶችን ለመተግበር ዕቅድ ይዟል። ከነዚህ መካከል ሦስቱ ፕሮጀክቶች በሙከራ ጊዜቸው ጥሩ ውጤት አሳይተው ለሴክተር ተቋማት እንደሚተላለፉ የሚጠበቁ ፕሮጀክቶች ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ 7 አዳዲስ ፕሮጀክቶች ለሰርቶ ማሳያነት ይቀርባሉ ተብሎ ታቅዷል።

### በፈጠራ የታገዙ አዳዲስ ሰርቶ ማሳያ ፕሮጀክቶች ብዛት

**የእንስሳት መኖ የተሻሻለ** ጥራት ያለው መኖ ለአርብቶአደሮች በተመጣጣኝ ዋጋ ተደራሽ እንዲሆን በማስቻል በዘርፉ ምርትና ምርታማነትን መጨመር ላይ ያተኮረ ፕሮጀክት ነው። **የዶሮ እርባታ የዘመናዊ** የዶሮ እርባታን በማስፋፋት አርሶአደሮችን በተለይም ሴት አርሶአደሮችን ተጠቃሚነት ማድግና የአመጋገብ ስርዓት ማሻሻል ላይ ያተኮረ ፕሮጀክት ነው። **ግብርና ተኮር አመራረት የስራ እድል ለወጣቱ** (ADEY) በግብርና

ሴክተር ላይ በተቀናጀ መልኩ ለወጣቶች በተለይም ለሴቶች የስራ እድል መፍጠር ላይ ያተኮረ ፕሮጀክት ነው። ምግብ ዋስትና ማስጠበቅ እና የግብርና መልሶ ማቋቋም እርምጃዎች (FARM) በጦርነቱ ለተጎዱ አርሶአደሮችና አርብቶአደሮች መልሶ የማቋቋም ድጋፍ መስጠትና ወደ ምርት እንዲገቡ ማስቻል ላይ ያተኮረ ፕሮጀክት ነው።

## በሙከራ ጊዜቸው ጥሩ ውጤት አሳይተው ለሴክተር ተቋማት የሚተላለፉ ፕሮጀክቶች

**የኢትዮጵያ የዘር ስርዓት ተቋማዊ ድጋፍ ፕሮጀክት** (ISSSE) 2,579 ኩንታል ጥራት ያለው መስራች ዘር ለአርሶ አደሩ ተደራሽ ማድረግ፤ በፌደራል ደረጃ የዕፅዋት ቁጥጥር ተቋምን ማጠናከር የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ፕሮጀክት የእንስሳት ልማት ዘርፍ የኤክስቴንሽንና የምክር አገልግሎት ስትራቴጂ እና ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀት፤ 94 ተጨማሪ የእንስሳትና የአሳ ሀብት አምራቾች የመስክ ትምህርት ቤቶች ብዛት ማቋቋም፤

**የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ማዕከላት የሙከራ ፕሮጀክት** በቀጣዩ ዓመት ሞዴል የአርሶ አደር ክላስተሮችን መሰረት ያደረገ ስራ በመስራት ትራክተሮችን፣ አጭዶ-መውቂያዎችን፣ መውቂያና መፈልፈያዎችን ጨምሮ በርካታ ዘመናዊ ማሽነሪዎችን በማቅረብ የአርሶአደሩን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፤ ካለፉት የሜካናይዜሽን ማዕከላት ግንባታ አተገባበር ልምድ በመውሰድ ተጨማሪ የአገልግሎት ማዕከላትን በተሻሻለ ዲዛይን ማስገንባት እና ለተጠቃሚዎች የመካናይዜሽ አገልግሎት ለመስጠት፤ይህንንም ለማከናወን ይረዳ ዘንድ ተከታታይነት ያላቸው የድጋፍና ክትትል ስራዎችን፣ ስልጠናዎችንና የምክክር መድረኮችን ማከናወን።

## ትግበራ ላይ የሚቆዩ ነባር ፕሮጀክቶች

**የአርሶ አደር ምርት ክላስተር-በሰብል** ምርት አኩሪ አተርን በመጨመር ዋና ዋና ሰብሎችን 6 ማድረስ፤ መሬት ሽፋንን እና የአባል አርሶ አደሮችን ቁጥር መጨመር፣ አርሶ አደሮች የተሻሻለ ዘር፣ ማዳበሪያ እና ኬሚካሎች፣ የብድር፣ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት፣ የገበያ ትስስር፣ የምክር አገልግሎት እና የተሻሻለ የድህረ ምርት አገልግሎት አቅርቦት እና አጠቃቀም እንዲሻሻል ማድረግ፣ በክላስተር አፈፃፀም ውስጥ የተከሰቱ ውሱንነቶች ላይ በማተኮር ጥራት ያለው የአሠራር ሂደት በመከተል ምርትና ምርታማነት በበለጠ እንዲጨምር፣ የአርሶ አደሩ የኑሮ ሁኔታ እንዲሻሻልና በተጠቃሚ በኩል ያለውን የግብርና ምርት ፍላጎት እና አቅርቦት ክፍተት ማጥበብ፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በማሻሻል አርሶ አደሩን ተጠቃሚ ለማድረግ ከሚደረገው ጥረት ጎን ለጎን የተሸጋገሩ ክላስተሮችን በመደገፍ ወደ ተቋም /ካምፓኒ/ ማድረስ፣ በሥራ ዕድል ፈጠራዎች ላይ በስፋት መስራት፣ አካባቢ ጥበቃን ማዕከል ያደረጉ አሰራሮችን ማስፋፋት፤

**የአርሶ አደር ምርት ክላስተር፡-** በአትክልትና ፍራፍሬ ምርት የመሬት ሽፋንን እና የአባል አርሶ አደሮችን ቁጥር መጨመር፣ አርሶ አደሮች የተሻሻለ ዘር፣ ማዳበሪያ እና ኬሚካሎች፣ የብድር፣ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት፣ የገበያ ትስስር፣ የምክር አገልግሎት እና የተሻሻለ የድህረ ምርት አገልግሎት አቅርቦት እና አጠቃቀም እንዲሻሻል ማድረግ፣ በክላስተር አፈፃፀም ውስጥ የተከሰቱ ውሱንነቶች ላይ በማተኮር ጥራት

ያለው የአሠራር ሂደት በመከተል ምርትና ምርታማነት በበለጠ እንዲጨምር፣ የአርሶ አደሩ የኑሮ ሁኔታ እንዲሻሻልና በተጠቃሚ በኩል ያለውን የግብርና ምርት ፍላጎት እና አቅርቦት ክፍተት ማጥበብ፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በማሻሻል አርሶ አደሩን ተጠቃሚ ለማድረግ ከሚደረገው ጥረት ጎን ለጎን የተሸጋገሩ ክላስተሮችን በመደገፍ ወደ ተቋም /ካምፓኒ/ ማድረስ፣ በሥራ ዕድል ፈጠራዎች ላይ በስፋት መስራት፣ አካባቢ ጥበቃን ማዕከል ያደረጉ አሰራሮችን ማስፋፋት፤

**የግብርና ግብዓትና አገልግሎት ፕሮጀክት** በመጭው ሶስት አመታት በራሳቸው ገንዘብ የሚቋቋሙ የግብዐትና አገልግሎት መስጫ ማእከላትን በማቋቋምና በቅርበት ክትትልና ድገፍ በማድረግ የግብዐት አቅርቦትን ለማሻሻል፣ ቋሚ የስራ እድል ለመፍጠር የኅብረት ስራ ማህበራት አቀፍ ዘር ብዜት ፕሮጀክት በቀጣይ ሶስት አመታት ፕሮጀክቱ አሁን እየሰራው ካለበት የአሰራር ሞዳሊት በተጨማሪ የግል ዘር አባገሮችን በመለየትና በመደገፍ ዩንዬኖችና የግል ዘር አባዥ ድርጅቶችን በማቋቋም ምርጥ ዘር በመሰብሰብና አበጥሮ ለማሰራጨት፣ አርሶ አደሮች ምርጥ ዘርን በመጠቀም ምርትና ምርታማነታቸውን እንዲያሳድጉ በዚህም ኑሮአቸው እንዲሻሻል ማድረግና ለተጨማሪ የአካባቢው ነዋሪዎች ቋሚ እና ጊዜያዊ የስራ እድል መፍጠር፤

**የታዳሽ ኃይል መስኖና ዘርፈ-ብዙ ልማት (DREAM Irrigation) ፕሮጀክት** በ9 የሙከራ ቦታዎች ዘመናዊ የመስኖ አውታር ጥልቅ ጥናትና ዲዛይን በማካሄድ፣ የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮና የመስኖ አውታር ግንባታ በማካሄድ፣ የመስኖ ቴክኖሎጂዎች አቅርቦትና ተከላ በማካሄድ፣ የአርሶ አደር፣ የግብርና ባለሙያዎች፣ የቴክንሺያን አቅም ግንባታ ስልጠና በማካሄድ እንዲሁም የፕሮጀክት ክትትልና ግምገማ በማካሄድ የፕሮጀክቱን ዋና ግብ የአርሶ አደሩ ምርትና ምርታማነት ማሳደግ፤ የስነ-ምግብ ዋስትና መሻሻል የአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭነትን ታዳሽ ሃይልን በመጠቀም መቀነስና የቤተሰብ ገቢን ማሳደግ፤

**የተቀናጀና ጥልቅ ያልሆነ የከርሰ ምድር ውኃ መስኖ ልማት ፕሮጀክት** በፀሀይ ሀይል የሚሰራ የዉሀ ፓምፕ ለአርሶአደሮች ድጋፍ ማድረግና የቴክኖሎጅው አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከተ ለተጠቃሚዎች ስልጠና መስጠት፣ የፓምፕ ተከላና ጥገና ለሚሰጡ ቴክኒሻኖችና ለተደራጁ ወጣቶች ስልጠና መስጠት የእጅ ጉድጓድ መቆፈሪያ ቴክኖሎጅ ድጋፍና ተያያዥ ስልጠናዎች መስጠት እና በከፊል ሞተራይዝድ የውሀ ጉድጓድ መቆፈሪያ ቴክኖሎጅውን የማስተዋወቅ ስራም ማከናወን፣ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው የአትክልት ሰብሎች ለማምረትና ቴክኖሎጂዎችንና የተሻሻሉ የመስኖ አሰራር ዘዴዎችን በመጠቀም እሴት ሰንሰለቶች ውስጥ ለሚሰሩ አካላት የንግድ ክህሎት በማጎልበት እና የፋይናንስ አቅርቦትን በማመቻቸት በቤተሰብ ደረጃ ገቢን ማሳደግና የኑሮ ሁኔታን ማሻሻል፤

**አግራ-ሃብ የኢንተርፕራይዞች አቅም ማሳድግ** ተወዳዳሪ ምርትና አገልግሎት እንዲያቀርቡ ያስችል ዘንድ ለተጨማሪ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የንግድ ክህሎት ስልጠና። ለተመረጡ ኢንተርፕራይዞች የንግድ የምክር አገልግሎት ይሰጣል። የብድር ፋይናንስ ትስስር ለማግኘት የተለያዩ የፋይናንስ ተቋማት ከኢንተርፕራይዞች ጋር ግንኙነት እንዲፈጥሩ ድጋፍ ይደረጋል።

**የንግድ እና ኢንቨስትመንት ማስፋፍያ ፕሮጀክት** በግብርና ኮሜርሻላይዜሽን ፕሮግራም ማዕቀፍ ውስጥ፣ የግብርና ምርት ማቀነባበርያ ኢንቨስትመንት ዕድሎችን፣ ቢያንስ በሁለት ከፍተኛ የኢንቨስተር ትውውቅ ኩነቶች ማስተዋወቅ፣ ከግብርና ሚኒስቴር እና ከንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር በመቀናጀት፣ ቢያንስ አንድ አገር-አቀፍ የአትክልትና ፍራፍሬ ኤክስፖ (Horticulture Expo) ማዘጋጀት፤

**የ8028 የድምፅ ቅብብሎሽ ምላሽ ፕሮጀክት** በ8028 ሲስተም ላይ የተመዘገቡ የክልሉን የአርሶ አደሮችን ቁጥር ማሳደግ፣ የአገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል፣ ለባለሙያዎች እና ለሞዴል አርሶአደሮች ስልጠና መስጠት፣ ባለድርሻ አካላትን ማሳተፍ፤

**ሀገር አቀፍ የገበያ መረጃ ስርዓት ፕሮጀክት** አነስተኛ ገበሬዎችን ጨምሮ ለሁሉም የእሴት ሰንሰለት ተዋናዮች ትክክለኛ፣ ወቅታዊ እና ተገቢ የገበያ መረጃ ማቅረብ፣ ለባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማሳደጊያ ስልጠና መስጠት፣ የፕሮጀክቱ ቀጣይነት እንዲረጋገጥ ፕሮጀክቱን ለንግድ ሚንስቴር ለማስተላለፍ ከንግድ ሚኒስቴርና በተዋረድ ካሉት ባለድርሻ አካላት ጋር በተለይ የክልል ንግድ ቢሮዎችን በቅርበት በመደገፍና በቅርበት በመስራት ቀጣይነቱን ማረጋገጥ፤

**የግብርና ግብዓት የኩፖን ሽያጭ ሥርዓት ፕሮጀክት** አርሶ አደሮች በዚህ የግብዓት ኩፖን ስርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል፣ ከጠቅላላው የግብአት ተጠቃሚ አርሶአደሮች ውስጥ የብድር ተደራሽነቱን እና የብድር ክፍያ መጠኑን ወደ ለመሳደግ፣ አርሶ አደሮች የግብዓት መግዣ ብድር በኩፖን ሥርዓት እንዲያገኙ ማድረግ እና የእፅዋት ኢንዴክስ የሰብል መድን (Vegetation Index Crop Insurance) እና የእንስሳት መድን (Livestock Insurance) ለአርሶ አደሮች ማስተዋወቅና ማዳረስ

**የገ/ቁ/ብ/ኀ/ሥ/ማ የዓቅም ግንባታ ፕሮጀክት** በቀጣይ ሶስት አመታት የዲያግኖስቲክ መሳሪያን በመጠቀም የህብረት ስራ ማህበራትን የአቅም ክፍተት ልየታና ምዘና ማካሄድ፣ ለክልል ማህበራት ኤጀንሲ፣ ለዞንና ለወረዳ ባለሙያዎች እና የገጠር ገንዘብ ብድርና ቁጠባ ዩኒየን ሰራተኞች በጥናት በተለዩ ክፍተቶች ዙሪያ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፤ ለገጠር ገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራት የቦርድ አባላትም በአመራርና በአስተዳደር ክህሎት ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፤ አሰራራቸዉን ለማዘመን በሦስቱም ክልል ለሚገኙ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ሕብረት ሥራ ዩኒየኖች እንዲሁም ለተወሰኑ በሥራቸዉ ለሚገኙ ማህበረት የዴስክቶፕ ኮምፒውተሮች ድጋፍ ማድረግ፤ የብድር ፋይናንስ ትስስር ለማግኘት የተለያዩ የፋይናንስ ተቋማት ከኢንተርፕራይዞች ጋር ግንኙነት እንዲፈጥሩ ማድረግ እና እንዱሁም የሴቶችና ወጣቶችን ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፤

**የማስፈፀም (የትግበራ) ድጋፍ** በ2016 የዴሊቨሪ ዩኒት አፈፃፀም ድጋፍ ከማድረግ አንፃር በግብርና ሚኒስቴር ድጋፍ የሚሰጥ የትንተና ቡድን ማቋቋምና ማብቃት በእቅድ ተይዟል።

**የትስስር እና ቅንጅት** በኢትዮጵያ የምግብ ስርዓት ፕሮግራም እና ዲጂታል ግብርና የኤክስቴንሽን እና ምክር አገልግሎት ፕሮግራም ውጤታማነትን ለማረጋገጥ ባለፉት አመታት የተጀመሩትን የማስተባበር ተግባራት በቀጣይም ሶስት አመታት ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ታቅዷል። በተጨማሪም በቀጣይ ሦስት አመታት የአየር ንብረት ለውጥ ላይ ያተኮረ የሀገር አቀፍ ምክክር መድረክ በአመት ሁለት ጊዜ ለማካሄድ ታቅዷል።



ለካ ዜና ሀ/ወልድ
የስትራተጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

የአደጋ ስጋት ግምገማ እና ስጋቶችን ለመቀነስ የሚተገበሩ ስትራቴጂዎች የግ.ት.ኢ. የሶስት አመት እቅድ ዝግጅትና አተገባበርን ለመምራት የበርካታ ባለድርሻ አካላት ግብአት በማግኘት የዕቅድ አተገባበር ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ስጋቶች የሚዳስስ ጥልቅ ትንተና ተዘጋጅቷል። የተለዩት ስጋቶችና የመከላከያ እርምጃዎች እንደሚመለከተው ቀርበዋል።

## 3.7. ዘርፈ-ብዙ ጉዳዮች

### 3.7.1. ምግብ ዋስትና

**ሀ) የማህበረሰብ ልማት ስራዎች የፕሮግራሙን ተጠቃሚዎችን ኑሮ በሚያሻሽል መልኩ እንዲሁም ለአደጋ ስጋት ቅነሳና አየር ንብረት ለውጥ አስተዋፅኦ ማበርከት**

በፕሮግራሙ የታቀፉ 6.8 ሚሊየን የሚሆኑ የማህበረሰብ ልማት ተጠቃሚዎችን በልማት ስራዎች ላይ በማሰማራት፤ የሰው ጉልበትን በስፋት የሚጠቀሙና በሕብረተሰቡ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የሚሰሩ የማህበረሰብ የልማት ስራዎችን ተሳትፋዊ የተፋሰስ ልማት እቅድ ዝግጅት መርህ መሰረት በተዘጋጀ እቅድ የሚመራ የወል ጥሪት ግንባታ የሚካሄድ ሲሆን ይህውም የሚካሄዱት የማህበረሰብ የልማት ስራዎች ተጠቃሚዎች በቅርብ ርቀት የሚደርሱበት ቦታ መሆን እና የወረዳው የልማት እቅድ አካል መሆን ይኖርባቸዋል። በመካከለኛ የእቅድ ዘመኑ ውስጥ ከሚተገበሩት የማህበረሰብ የልማት ስራዎች ዋና ዋናዎቹ ለመጥቀስ ያህል የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች፣ የአነስተኛ መስኖ ልማት ስራዎች ፣ ውሃ የማሰባሰብ እና ምንጭ የማጎልበት፣ የእጅ ጉድጓድ ቁፋሮ፣ የፍራፍሬና ደን ችግኝ ዝግጅት እና ልማት፣ የገጠር የመሰረተ ልማት ግንባታና ጥገና፣የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ግንባታና ጥገና ወዘተ ሆነው ፕሮግራሙ የጋጠመዉን የበጀት እጥረት ከግምት ውስጥ በማስገባት በሚገኘው በጀት መሰረት ቅደም ተከተል በማስያዝ (Prioritization) የሚከናወኑ ይሆናል።

**ለ) አቅምን ያገናዘበ እና ተገቢ የሆነ የቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ አገልግሎት በፍላጎታቸውና ባላቸው ዕምቅ አቅም ለተመረጡ የማህበረሰብ ስራ ተሳታፊ ቤተሰቦች ማቅረብ**

የቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ አገልግሎት ዓላማ በፍላጎታቸውና ባላቸው አቅም መሰረት የሚመረጡ የማህበረሰብ ስራ ተሳታፊዎችን የኑሮ መሰረት (Livelihoods) በማሻሻል የተረጋጋና ዘላቂ የገቢ ምንጭና ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሮአዊ አደጋ ተጽእኖ ፈጥነው የሚያገግም አቅም ያላቸው እንዲሆኑ ማስቻል ነው። በተጨማሪም በቤተሰብ ደረጃ ለስርዓተ ምግብ መሻሻል አስተዋጽኦ ያደርጋል። ለዚህም ስኬት በጊዜ የተገደበና የተሟላ ድጋፍ የሚሰጥ ሲሆን ስታንዳርዳቸውን ጠብቀው የተዘጋጁ ልዩ ልዩ ሥልጠናዎች እና የፋይናንስ አገልግሎት ቅደም ተከተል በጠበቀ መልኩ የሚቀርብበት የድጋፍ አቅርቦት ስርዓት ተገንብቶለታል።

በዚህ መሰረት የኑሮ ክህሎት (Life Skill) ፣ የገንዘብ አያያዝ፣ አጠቃቀምና ቁጠባ (Financial Literacy) ፣ የቢዝነስና ግብይት ክህሎት (Business Skill and Marketing) ፣ የገቢ ማስገኛ ስራ ዕቅድ አዘገጃጀት እና ለስራ ዕቅድ ትግበራ የሚያስፈልግ የቴክኒክ ስልጠናዎች ወዘተ ለተጠቃሚዎች ይሰጣሉ። በመቀጠልም በአንጻራዊነት ሻል ያለ አቅም ላላቸው ተጠቃሚዎች ብድር፣ የደሃ ደሃ ለሆኑ (Ultra Poor Clients) የአንድ ጊዜ ጥሪት መፍጠሪያ የፋይናንስ ድጋፍ (Livelihood Transfer) በማመቻቸት ውጤታማ

በሚሆኑባቸው የገቢ ማስገኛ ስራዎች ላይ ባዘጋጁት የስራ እቅድ መሰረት ወደ ትግበራ እንዲገቡ ይደረጋል። በተጨማሪም የምርት ግብዓቶች፣ የምርት እና አገልግሎት ገበያ ትስስር በመፍጠር፣ ለተጠቃሚ ቤተሰቦች በቡድን እና በተናጠል ክትትል እና ድጋፍ (Group and Individual Coaching) በወረዳ ባለሙያዎች፣ በልማት ሰራተኞች እና በማህበረሰብ አመቻቾች እንዲያገኙ በማድረግ በተሰማሩበት ገቢ ማስገኛ ስራ ውጤታማ ሆነው የገቢ አማራጮቻቸውን እንዲያሰፉ ይደረጋል።

በአጠቃላይ በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ንዑስ ፕሮግራሞች መካካል እና ከሌሎች መደበኛ የልማት ፕሮግራሞች እና የመንግስት የማነሳሻ ፕሮግራሞች (Government Initiatives) ጋር በተቀናጀ መልኩ በየትግበራ መስኮች የታቀዱ ዋና ዋና ተግባራት ሲከናወኑ በተለይ የቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም ተጠቃሚ ቤተሰቦችን የገቢ ምንጭ ለማስፋት፣ የምግብ ዋስትናቸውን እና የኑሮ ደረጃቸውን ለማሻሻል ብሎም ከተረጂነት እንዲወጡ ጉልህ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። ከምግብ ዋስትና ከፕሮግራም ማስወጣት (Program Exit) በሁለት ደረጃ የሚታይ ነው። የመጀመሪያው ምዕራፍ በጽኑ ድህነት ውስጥ ያሉና ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ስራ ተጠቃሚ ቤተሰቦች በሴፍቲኔት ፕሮግራም እየታገዙ የምግብ ጉድለታቸውን በማሟላትና ያላቸውን ጥሪት (Asset) እንዲጠብቁ ከማድረግ በተጨማሪ በቤተሰብ የኑሮ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም በሚቀርብላቸው የክህሎት ስልጠናና የፋይናንስ አገልግሎት ትስስር (Saving and Micro Credit) እና ድጋፍ (Livelihood Transfer/Grant) ታግዘው ገቢያቸውን አሻሽለው፣ ጥሪት ገንብተውና ዓመታዊ የምግብ ፍላጎታቸውን በራሳቸው የመሸፈን አቅም ፈጥረው ከሴፍቲኔት ፕሮግራም ማሰናበት (Recertification and Exit) ሲሆን ይህም በሶስት ዓመታት ውስጥ ሊደረስበት የሚቻልና በምግብ ዋስትና ፕሮግራም ቅድሚያ ትኩረት የተሰጠው ተግባር ነው።

የሁለተኛ ምዕራፍ ከሴፍቲኔት ፕሮግራም የተሰናበቱ ቤተሰቦችን የድህረ ስንብት የኑሮ ማሻሻያ ድጋፍ እና ክትትል እንዲሁም በመደበኛው የግብርና የኤክስቴንሽን ፕሮግራም በሚያገኙት ድጋፍ የገቢ አማራጮቻቸውን ይበልጥ በማስፋት በሚያገኙት ገቢ በአስተማማኝ ሁኔታ በቤተሰብ ደረጃ የምግብ እና የስርዓት ምግብ ዋስትናቸውን እንዲያረጋግጡ፣ ሰው ሰራሽ እና የተፈጥሮ አደጋዎች በሚከሰቱበት ወቅት ከተጽእኖው ፈጥነው ማገገም የሚችሉበት ደረጃ ላይ ማድረስን የሚጠይቅና ከልማታዊ ሴፍቲኔት ኃላፊነት በላይ የሆነ የተቀናጀ ጥረት የሚሻ ውጤት ነው። በዚህ መሰረት ለሶስት ተከታታይ ዓመታት የሴፍቲኔት ኮር ትራንስፈር፣ የቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ አገልግሎት እና ተጓዳኝ ድጋፎች የተደረጉላቸው ተጠቃሚዎች ያመጡትን ለውጥ ክትትል በማድረግ በመረጃ ላይ የተደገፈ ተአማኒነት ያለው የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ስንብት ወይም ከተረጂነት መውጣት (Program Exit Through Recertification) ስርዓት በመዘርጋት፣ ከፕሮግራሙ እንዲሰናበቱና የድህረ ስንብት ክትትል እና ድጋፍ እንዲያገኙ ይደረጋል።

### ሐ) የልማት እቅድ ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች

**ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚዎች በቂ እና ወቅቱን የጠበቀ ክፍያ በመክፈል የምግብ ክፍተት መሙላት**

በዕነ ድህነት ውስጥ የሚገኙ የፕሮግራሙን ተጠቃሚዎች ማለትም የማህበረሰብ ልማት ስራ ሰርተው እንዲሁም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ተከፋይ ለሆኑ የቋሚ ቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚዎቸ በቂ እንዲሁም ወቅቱን የጠበቀ ክፍያ በመክፈል የምግብ ክፍተት በመሙላት የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች ጥሪት እንዳይመናመን ያደርጋል፡፡ በዚህም ግብ ስር ሁለት ቁልፍ የውጤት አመላካች ሲኖሩት የእያንዳንዳቸው ዝርዝር እቅድ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**የልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራም ተጠቃሚዎች ቁጥር**

በመካከለኛ ዘመን እቅድ ትግበራ ጊዜ ውስጥ በሀገራችን በአስር ክልሎች ማለትም (አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ትግራይ፣ደቡብ ብ/ብ/ህ/ክ፣ ሲዳማ፣ደቡብ ምዕራብ፣አፋር፣ ሶማሌ ፣ ሀረሪና ድሬዳዋ) የምግብ ዋስትና መታጣት ችግር ባለባቸው 485 ወረዳዎች ውስጥ የሚገኙ 7.9 ሚ/ን ዕነ ደሃ እና ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን በፕሮግራሙ ደንበኝነት ይዞ የሚሰራ ይሆናል፡፡ የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች በአምስት ዓመት አንድ ጊዜ በሚደረግ የተጠቃሚዎች ምልመላ (Mass Targeting) መሰረት የሚለዩ ሲሆን በየአመቱ ደግሞ የስነ-ቤተሰብ (Demography Change due to Birth, Death and Displacement) አወቃቀር ለውጥን መሰረት በማድረግ አመታዊ የተጠቃሚዎች ክለሳ (Annual Update) ይደረጋል፡፡

ፕሮግራሙ በሚተገብርባቸው ወረዳዎች ውስጥ የሚገኙ ቤተሰቦች መጠነኛ አደጋ/ድርቅ (Modest Shock) በሚከሰትበት ወቅት የመኸር እና የበልግ ምርት ጥናት ውጤትን መሰረት በማድረግ በፕሮግራሙ የአደጋ ምላሽ ኮምፖነንት አማካኝነት የሩብ ዓመት የድርቅ ምላሽና ድጋፍ እቅድ በማዘጋጀት የምግብ ክፍተት ለማጥበብ ታቅዷል፡፡ በዚህም መሰረት የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ለሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ተጨማሪ ወራት ድጋፍ (Vertical Expansion) እንዲሁም በፕሮግራሙ ያልተካተቱ አዲስ የማህበረሰብ ክፍሎችን በጊዜአዊነት ድጋፍ (Horizontal Expansion) ድጋፍ ይደረጋል፡፡

**ክፍያቸውን በፕሮግራሙ የክፍያ ስታንዳርድ መሰረት ያገኙ ተጠቃሚዎች ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚዎች በቂ እና ወቅቱን የጠበቀ ክፍያ በመክፈል የምግብ ክፍተት መሙላት** በዕነ ድህነት ውስጥ ላሉና ለአደጋ ተጋላጭ የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች በቂ እና ወቅቱን የጠበቀ ክፍያ በመክፈል የምግብ ክፍተት መሙላት እንዲችሉና ያላቸውን ውስን የቤተሰብ ጥሪት እንዳይመናመን ማድረግ ፕሮግራሙ በትኩረት የሚያከናው ነው፡፡ በዚህ መሰረት ወቅቱን የጠበቀ ክፍያ አፈጻጸምን በ2015 በጀት ዓመት ከነበረበት 55 በመቶ በመካከለኛ ዘመን ዕቅዱ የመጨረሻዓመት ማለትም ወደ 80 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል፡፡

አከ ዜና ህ/ወልድ የስትራቴጂክ ጉዳዮች ሥራ አስፈጻሚ

ለሴፍቲኔት ፕሮግራም የገንዘብ ክፍያ ተጠቃሚዎች ክፍያ የሚውል ገንዘብ ለክልሎች እንዲተላለፍ ለገንዘብ ሚ/ር ጥያቄ በማቅረብ እና እንዲተላለፍ በማድረግ ገንዘቡ ወደ ወረዳዎቹ ደርሶ ለታለመለት ዓላማ መዋሉ ክትትል ይደረጋል። በተመሳሳይ ከብሔራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ጋር በመቀናጀት የሚቀርበው ምግብ በወቅቱ እስከ ምግብ ማሰራጫ ጣቢያዎች እንዲደርስና ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ጥብቅና የተቀናጀ ክትትል ይደረጋል።

**የማህበረሰብ ልማት ስራዎች የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎችን ኑሮ በሚያሻሽል መልኩ እንዲሁም የአደጋ ስጋት ቅነሳና ለአየር ንብረት ለውጥ አስተዋፅኦ ማበርከት** ባገገሙና በለሙ የወል መሬቶች፣ ከፍተኛ ዋጋ ባላቸው ፍራፍሬዎች ችግኝ አቅርቦት እና በአነስተኛ መስኖ ልማት ትስስር ተጠቃሚ የሆኑ ቤተሰቦች የማህበረሰብ ስራዎች ንዑስ ፕሮግራም ፕሮግራሙን ተጠቃሚዎች ገቢና የኑሮ ሁኔታ የሚያሻሽሉ፣ የተፈጥሮ አደጋዎ ስጋቶችን ለሚቀንሱ እና የአየር ንብረት ለውጥን የመቋቋም አቅምን የሚያጎለብቱ የማህበረሰብ ጥሪቶችን መገንባት ላይ ትኩረት አድርጎ ይተገበራል። በተጓዳኝም በራሰቸው መሬት ላይ የመሬት ምርታማነት የማሻሻል፣ የጓሮ አትክልት ልማት (perm-garden) ፣ ውሃ ማሰባሰብ እና የመሳሰሉትን ስራዎች መተግበር ለሚፈልጉ ቤተሰቦች የሙያና የምክር ድጋፍ ይደረጋል።

በዚህ መሰረት የ2014 በጀት ዓመት 163,746 ቤተሰቦችን ተጠቃሚ ለማድረግ ተይዞ የነበረውን ዕቅድ ታሳቢ በማድረግ በመካከለኛ ዕቅድ ዘመኑ ውስጥ 540,362 ቤተሰቦች ወይም 2,701,809 ተጠቃሚዎች በማህበረሰብ ስራ በለሙ የወል መሬቶች፣ በአነስተኛ መስኖ አውታሮች፣ ከፍተኛ ዋጋ ባላቸው ፍራፍሬዎች እና የእንስሳት መኖ ልማት (ችግኞች አቅርቦት) ፣በአነስተኛ የጓሮ አትክልት ልማት የምክር እና ሙያ ድጋፍ፣ የመሬት ምርታማነት በማሻሻል (Compost Preparation) እና በመሳሰሉት ከማህበረሰብ ስራዎች ንዑስ ፕሮግራም ጋር በማስተሳሰር (Public Works and Livelihood Linkage) በግብርና ነክ የገቢ ማስገኛ ስራዎች የገቢ ምንጫቸውን እንዲያሰፉ ይደረጋል።

**አቅምን ያገናዘበ እና ተገቢ የሆነ የቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ አገልግሎት ለቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ ተጠቃሚዎች ማቅረብ** የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም የማህበረሰብ ስራ ተጠቃሚዎች ውስጥ ለቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም የተጠቃሚ ልየታ መመሪያ መሰረት ለሚመረጡ ቤተሰቦች የገንዘብ አያያዝ፣ አጠቃቀምና ቁጠባ፣ የገቢ ማስገኛ ስራዎች ዕቅድ ዝግጅት፣ የቴክኒክ ክህሎት ፣ የስርዓተ ምግብ እና ስርዓተ ጾታ ስልጠናዎች በመስጠት ቁጠባን፣ አነስተኛ ብድር (Micro Credit) እና የአንድ ጊዜ ጥሪት መፍጠሪያ ድጋፍን (Livelihood Transfer) ያካተተ የፋይናንስ አገልግሎት፣ የምርት ግብዓቶች፣ የምርት እና አገልግሎት ገበያ እንዲሁም ቅጥር ስራ ትስስር ተፈጥሮላቸው የገቢ መሰረታቸውን እና የገቢ ምንጫቸውን እንዲያሰፉ እና የኑሮ ሁኔታቸውን እንዲያሻሻሉ ይደረጋል። በዚህ መሰረት በመካከለኛ ዕቅድ ዘመኑ 445,991 የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚ ቤተሰቦች በቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም ታቅፈው ልዩ ልዩ ደረጃቸውን ጠብቀው በተዘጋጁ የክህሎት እና የቴክኒክ ስልጠናዎች በመስጠት እና በቁጠባ እንዲሳተፉ የሚደረግ ሲሆን የውጤት አመልካቾች ዕቅድ ቀጥሎ ቀርቧል።

ዜና ሀብተወልድ
የስትራቴጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

### የብድር አቅርቦት ያገኙ የሴፍትኔት ተጠቃሚዎች

356,793 ተጠቃሚዎች ከአነስተኛ ብድር ተቋማት (MFIs) እና የገጠር ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት (RuSaCCOs) ጋር በሚደረግ ትስስር ብድር እንዲያገኙ ይደረጋል። በመካከለኛ ዘመኑ የብድር አቅርቦት ዕቅድ የሴቶች እና የወጣቶች ተሳትፎ ምጣኔ 50 በመቶ እና 42 በመቶ ነው። ከUSAID ጋር ትስስር ያላቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (CRS, WV and FH/E) እና ሌሎች አጋር አካላት በዚህ የውጤት አመልካቾች ትግበራ እና ስኬት ድርሻ ይኖራቸዋል።

### የአንድ ጊዜ ጥሪት መፍጠሪያ ድጋፍ ያገኙ የሴፍትኔት ተጠቃሚዎች

በፕሮግራሙ ዲዛይን መሰረት ፍላጎታቸውንና አቅማቸውን ታሳቢ አድርጎ በተዘጋጀ መስፈርት መሰረት ለቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም ከሚመረጡ ተጠቃሚዎች ውስጥ የመጨረሻው የድህነት ወለል ላይ ለሚገኙ (bottom-poor) 20 በመቶ ተጠቃሚዎች የአንድ ጊዜ ጥሪት መፍጠሪያ ድጋፍ እና በተጠናከረ የቅርብ ክትትል እና ድጋፍ ይደረግላቸዋል። በዚህ መሰረት ለቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም ከሚመረጡት ቤተሰቦች ውስጥ በአንጻራዊነት የድሃ ድሃ ለሆኑና ብድር የመውሰድ ልምድ ለሌላቸው 89,198 ቤተሰቦች የአንድ ጊዜ ጥሪት መፍጠሪያ ድጋፍ (Livelihood Transfer/grant) ይደረግላቸዋል። በመካከለኛ ዘመኑ የጥሪት መፍጠሪያ ድጋፍ አቅርቦት ዕቅድ የሴቶች እና የወጣቶች ተሳትፎ ምጣኔ 50 በመቶ እና 42 በመቶ ሲሆን ከUSAID ጋር ትስስር ያላቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (CRS, WV and FH/E) እና ሌሎች አጋር አካላት በዚህ የውጤት አመልካች ትግበራ እና ስኬት ድርሻ ይኖራቸዋል።

### አመልካች 3፡ ጥሪት ፈጥረው ከፕሮግራሙ የተሰናበቱ የሴፍትኔት ተጠቃሚዎች

በ2016-2018 የመካከለኛ ዘመን እቅድ መሰረት በቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም የሚሰጡ ድጋፎችን ከሌሎች የልማታዊ ሴፍቲኔት ንዑስ ፕሮግራሞች እና በመንግስት የተጀመሩ የማነሳሻ ፕሮግራሞች (Government Initiatives) ጋር በመቀናጀት በሶስት አመት ዉስጥ 151,800 የቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም ተጠቃሚ ቤተሰቦችን (759,000 ተጠቃሚዎች) የገቢ ምንጭ በማስፈት፣ የምግብ ዋስትናቸውን እና የኑሮ ደረጃቸውን አሻሽለው ከተረጂነት እንዲወጡ ይደርጋል። ከፕሮግራሙ የሚሰናበቱ ቤተሰቦች ልየታም ለሶስት ተከታታይ ዓመታት የሴፍቲኔት ኮር ትራንስፈር፣ የቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ አገልግሎት እና ተጓዳኝ ድጋፎች የተደረጉላቸው ተጠቃሚዎች ያመጡትን ለውጥ ክትትል በማድረግ በመረጃ ላይ የተደገፈ እና ታአማኒነት ያለው የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ስንበት ወይም ከተረጂነት መውጣት (Program Exit Through Recertification) ስርዓት የተከተለ ይሆናል።

### 3.7.2. ምግብና ስርዓተ ምግብ

የተሻሻለ የቤተሰብ የተሰባጠረ አመጋገብ ስኮር ለማሻሻል በሚቀጥለው የመካከለኛ የዕቅድ ዘመን እንደ ሀገር በቤተሰብ ደረጃ የተሰባጠረ አመጋገብን ወደ 70% ከፍ የማድረግ ግብ ተይዟል። ለዚህ ግብ መሳካት ሁሉም የግብርና ፕሮግራሞች አስተዋጸኦ የሚያደርጉ ቢሆንም የምግብና ሥርዓተ ምግብ ጽ/ቤት እንደ ዋና ግቡ አስቀምጦታል። በምግብ ንጥረ ነገር ይዘታቸው የበለፀጉ የግብርና ምርቶችን ለማሳደግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በምግብ ንጥረ ይዘት የበለጸጉ የእጽዋት ዝርያዎች ወደ ሌማት ቅርጫት ለማስገባት ሦስት

ጊዜ አውደ ጥናት ለማካሄድ ታቅዷል። በማህረሰቡ ውስጥ የሚታይ የምግብ ንጥረ ነገር ይዘት ክፍተቶችን (Nutrient Gap) አዋጭ እና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ለመተግበር በድምሩ ስምንት ምግብን መሰረት ያደረጉ ቴክኖሎጂዎችን ለማስተዋወቅ ታቅዷል። በምርምር ተሞክረው ውጤታማ የሆኑ የእሴት መጨመርና እና ድህረ ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን በድምሩ 9 ለማስተዋወቅ ታቅዷል። በምግብ ንጥረ ነገር ይዘታቸው የበለፀጉ ሰብሎች ቴክኖሎጂ ፍላጎት እና ግንዛቤ ለመፍጠር በየአመቱ አንድ አንድ አውደ ጥናት በድምሩ ሦስት ይካሄዳል። የባዮፎርቲፋይድ ሰብሎችን እሴት ጭመራ ለሁሉም የእሴት ሰንሰለት ተዋናዮች ግንዛቤ ለመፍጠር አራት ጊዜ አውደ ጥናት ይካሄዳል። ለሥርዓተ ምግብ ተኮር የኢንቨስትመንት ተዋናዮች በሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ኢንቨስትመንት ዙሪያ ግንዛቤያቸውን ለማሳደግ ዘጠኝ ጊዜ የግንዛቤ ስራ ይሰራል።

## የምግብና ሥርዓተ ምግብ የመፈፀም አቅምን ማሳደግ

በግብርናው ዘርፍ እስከታችኛው መዋቅር ድረስ ያሉ ባለሙያዎች እና ባለድርሻ አካላት የመፈጸም አቅማቸውን ለማሳደግ የተለያዩ ስልጠናዎችን መስጠት ተገቢ በመሆኑ በሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና፣ በምግብ ንጥረ ነገረ ይዘቱ የበለፀጉ ምርቶች ድህረ ምርት አያያዝ፣ በምግብ ደህንነትና ጥራት፣ የእሴት መጨመር፣ በሥርዓተ ምግብ ተኮር መሰረታዊ የንግድ ክህሎት፣ በአድቮኬሲ እና ሎቢንግ፣ በምግብ አዘገጃጀት መመሪያ፣ ለክፍሉ ባለሙያዎች የተለያዩ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ስልጠና ፣ ከምግብና ሥርዓተ ምግብ አንጻር የበይነ መረብ ስልጠና እና በምግብ ሥርዓት በድምሩ ለ3,231 ሰልጣኞች ስልጠና ለመስጠት ታቅዷል።

## የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ሥርዓትን ማጠናከር

### የተለያዩ የዳሰሳ ጥናቶችን ማካሄድ

መረጃን መሰረት ያደረገ የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርናን ተግባራዊ ለማድረግ እና ለተዘጋጁ ስትራቴጅዎች መነሻ የሚሆኑ ጥናቶችን ለመስራት ታቅዷል። እነዚህም ጥናቶች የተሰባጠረ አመጋገብ ዳሰሳ ጥናት፣ የምግብና ሥርዓተ ምግብ የሰው ሀይል ፍላጎት ጥናት፣ የድህረ ምርት አያያዝ ስትራቴጂ መነሻ ጥናት፣ የተቀዳሚ የግብርና ምርቶች ምግብ ደህንነትና ጥራት ስትራቴጂ መነሻ ጥናት፣ ድህረ ስልጠና የዳሰሳ ጥናት፣ የምግብ አዘገጃጀት መመሪያ ዝግጅት ጥናት፣ የስብጥር አመራረትና አመጋገብ መልካም ተሞክሮዎችን እና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ጥናት፣ የምግብ ንጥረ ይዘት ክፍተት ጥናት፣ በስርዓተ-ምግብ ዋስትና መሻሻል አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ሀገር በቀል ምርቶች (Indigenous Foods) ልየታ፣ እና የኩታ ገጠም አመራረት ላይ የእሴት መጨመርና ድህረ ምርት አያያዝ ችግሮች ጥናት በድምሩ በሦስት ዓመቱ 13 ጥናቶችን ለማካሄድ ታቅዷል።

### ሰነዶችን ማዘጋጀት

የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ሥርዓትን ማጠናከር በሚለው ዓላማ ስር ከተያዙት መካከል የተለያዩ ሰነዶችን ማዘጋጀት አንዱ ነው። እነዚህም ሰነዶች የክልሎች የምግብ ሥርዓት ፍኖተ ካርታ፣ የኢትዮጵያ ምግብ ሥርዓት ፍኖተ ካርታን ከ10 ዓመቱ ዕቅድ፣ከኢኒሼቲቮች፣ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ጋር



ዜና ሀ/ወልድ
የስትራቴጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

ማናበብ፣ ላለፉት አምስት ዓመታት በስራ ላይ የነበረውን የሥ/ም/ተ ግብርና ስትራቴጂን መከለስ፣ ከሥርዓተ ምግብ አንጻር ስምንት ፓኬጆችን መከለስ፣ የምግብ አዘገጃጀት መመሪያ ማዘጋጀት፣ የሥ/ም/ተ ግብርና ስትራቴጂ የትግበራ ማኑዋል፣ የድህረ ምርት አያያዝ ስትራቴጂ የትግበራ ማኑዋል፣ የምግብ ደህንነትና ጥራት ስትራቴጂ የትግበራ ማኑዋል፣ የድህረ ምርት አያያዝ ማሰልጠኛ ማኑዋል፣ የምግብ ደህንነትና ጥራት ማሰልጠኛ ማኑዋል፣ በምግብ ንጥረ ነገር ይዘታቸው የበለጸጉ ምርቶች ምርትና ምርታማነት ለማሻሻል የሚረዳ የማበረታቻ ስርዓት እና የምግብ ሥርዓት የሥልጠና ማኑዋል በድምሩ 32 ሰነዶችን ለማዘጋጀትና ለመከለስ ዕቅድ ተይዟል።

## በተለያዩ ቋንቋዎች ሰነዶችን መተርጎም

የተዘጋጁ ሰነዶችን በተለያየ ቋንቋዎች መተርጎም በሦስት ዓመቱ ዕቅድ ተይዟል። እነዚህን ሰነዶች በተለይም ደግሞ በአማርኛ፣ በኦሮምኛ፣ ሶማልኛ ትግረኛ እና አፋርኛ ቋንቋዎች ለመተርጎም ታስቧል። የሚተረጎሙ ሰነዶች የስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ስትራቴጂ እና የምግብ ሰርቶ ማሳያ መመሪያ ናቸው።

## የምግብና ሥርዓተ ምግብ አደረጃጀት መፍጠር/ማጠናከር

በሦስት ዓመቱ የልማት ዕቅድ በፌደራል ደረጃ ያለውን የምግብና ሥርዓተ ምግብ ጽ/ቤት ወደ ዘርፍ ለማሳደግ እና በሰባት ክልሎች የምግብና ሥርዓተ ምግብ አደረጃጀት በዳይሬክቶሬት ደረጃ እንዲፈጠር ለማድረግ ታቅዷል። የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ተግባራትን በተደራጀ እና በተቀናጀ መንገድ ለመስራት እንዲሁም ለሌሎች አካባቢዎች ተሞክሮዎችን ለማስፋት የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ሞዴል መንደር መፍጠር በሚል ሰባት ሞዴል መንደሮችን ለመፍጠር ታቅዷል። በዚህ ዓላማ ስር ከተያዙት ዕቅድ ውስጥ ሌላው የምግብና ሥርዓተ ምግብ ማስፈጸሚያ ፕሮግራም/ፕሮጀክቶችን መቅረጽ የሚል ነው። በሦስት ዓመቱ የዕቅድ ዘመን ውስጥ ሦስት ፕሮግራሞችን/ፕሮጀክቶችን ለመቅረጽ ዕቅድ ተይዟል። የምግብና ሥርዓተ ምግብ ሰርቶ ማሳያ ማዕከል መገንባትን በተመለከተ በየዓመቱ ሁለት ሁለት በድምሩ ስድስት ማዕከል ይገነባል። የኢትዮጵያ የምግብ ሥርዓት ፍኖተ ካርታን (EFS Road Map) በአስሩ ክልሎች ለማስተዋወቅ አውደ ጥናቶች ይካሄዳሉ።

## የባህሪ ለውጥ አምጪ ተግባርን ማካሄድ

የማህበረሰቡን የተሰባጠረ አመጋገብን ለማሻሻል እና የሥርዓተ ምግብ ግንዛቤን ለማሳደግ የተለያዩ የባህሪ ለውጥ አምጪ ተግባራትን ለማከናወን ዕቅድ ተይዟል። በሚመሰረቱት የሥ/ም/ተ ግብርና ሞዴል መንደሮች በየዓመቱ ሦስት በድምሩ ዘጠኝ የተሰባጠረ አመጋገብ ሰርቶ ማሳያ እና ባዮፎርቲፋይድ የሆኑ ሰብሎች አመጋገብ ሰርቶ ማሳያ ይካሄዳል። በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች አስራ ሁለት የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና መልእክት ለማስተላለፍ እና አስራ ሁለት መልእክቶችን በበራሪ ጽሑፎች፣ ፖስተር እና ባነር ለማስተላለፍ ታቅዷል። ሌላው በማህበረሰቡ ዘንድ ተሰሚነት ያላቸው እና ለማህበረሰቡ ወሳኝ መልእክቶችን የሚያስተላልፉ የምግብና ሥርዓተ ምግብ አምባሳደሮች በአምስት ክልሎች ለመሾም ታቅዷል።

### ምግብን መሰረት ያደረገ የአመጋገብ መመሪያን መተግበር

ምግብን መሰረት ያደረገ የአመጋገብ መመሪያን በተመረጡ ሦስት ክልሎች ወስጥ በሚገኙ ሦስት መንደሮች ለመተግበር የታቀደ ሲሆን በሦስቱም መንደሮች ለ215 ሰልጣኞች ስልጠና ለመስጠት፣ የተለያዩ የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ግብዓቶችን ለማሰራጨት እንዲሁም ስድስት ጊዜ የምግብ ሰርቶ ለማካሄድ እና የጋራ የአፈጻጸም ግምገማ ለማካሄድ ዕቅድ ተይዟል።

### ቅንጅታዊ አሰራርን ማሻሻል

በሰቆጣ ስምምነት ወረዳዎች የሚተገበሩ የሥ/ተ/ግብርና ተግባራት በየአመቱ በ10 ወረዳዎች ለመተግበር እና ከልማታዊ ሴፍቲኔት ጋር በመተባበር የሚከናወኑ የሥ/ም/ተ ግብርና ተግባራትን በየዓመቱ በ100 የተለዩ ተጠቃሚዎች ላይ ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዷል። ቅንጅታዊ አሰራርን ለማሳደግ በሰባት ክልሎች የምግብና የስርዓተ-ምግብ አጋር አካላት የጋራ መድረክ (Platform) ለማቋቋምና ለማጠናከር ታስቧል። በምግብ ንጥረ ነገር ይዘት የበለፀጉ የጓሮ አትክልት ዘር አቅርቦት በዘር ሥርዓት ውስጥ ለማካተት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር አውደ ጥናት ይካሄዳል። በት/ት ቤት ምገባ ፕሮግራም የሥ/ም/ተ ግብርና ተግባራትን በስድስት ትምህርት ቤቶች ለማካተት ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር ለመስራት ታቅዷል። የክትትልና ግምገማ ሥርዓቱን ለማሻሻል እና የክልሎችን የመፈጸም አቅም ለማሳደግ በአስር ክልሎች በየዓአመቱ የሥ/ም/ተ ግብርና ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል። ክልሎች፣ ምርምሮች ዩኒቨርሲቲዎች እና አጋር አካላት በተገኙበት የሥ/ም/ተኮር ግብርና አፈጻጸምን ለመገምገም በአመት ሁለት ጊዜ አውደ ጥናት ይካሄዳል። የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና የመረጃ ሥርዓትን ለማሳደግ እና የሥ/ም/ተ ግብርና መረጃን ለውሳኔ ለመጠቀም በአስር ወረዳዎች የግብርና የዲጂታል የመረጃ ሥርዓትን በመጠቀም ለመተግበር ታቅዷል። በየአመቱ አንድ አንድ የሥ/ም/ተ ግብርና ልምድ ልውውጥ በሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር በቁጥር ለማካሄድ እቅድ ተይዟል። በዚህ አላማ ስር ሌላው የተያዘው ዕቅድ በየአመቱ አንድ አንድ ውጤታማ የሆኑ የሥ/ም/ተ ግብርና ተሞክሮዎችን ለመቅረጽ ነው።

### 3.7.3. አየር ንብረት ለውጥ

ኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ በመገንባት በ2017 ዓ.ም መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ የሚያስችላትን ርዕይ በማዘጋጀት ወደ ተግባር መግባቷ ይታወቃል። ከዚህም ጋር በተያያዘ የግብርና ዘርፍ በተለያዩ ጊዜያት በአየር ንብረት ለውጥ ሳቢያ ከሚደረሱ አሉታዊ ተጽዕኖዎች ለመታደግ ከሴክተሩ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስልት ምሶሶዎች አንጻር ማለትም በተቀናጀ የተፈጥሮ ሀብት አያያዝ ላይ የተመሰረተ ውጤታማ የግብርና ልማት እና የመሬት አጠቃቀም በማከናወን እንዲሁም የሰብልና የእንስሳት ምርታማነትን በማሳደግ የምግብ ዋስትናን በተሻለ ሁኔታ በማረጋገጥ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን በተቀናጀ አግባብ ለመተግበር ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

ከዚህም ጋር ተያይዞ እየተከናወኑ ያሉ የግብርና ልማት ስራዎች የአካባቢና ማህበራዊ ሃብቶችን ከብክነትና ከብክለት በመጠበቅ እንዲሁም የአየር ንብረት ተፅዕኖን መቋቋም የሚችል ግብርናን ከመፍጠር አንጻር



ለካ ዜና ሀ/ወልደ
የስትራቴጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

የተለያዩ ስራዎች እየተተገበሩ ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በሁሉም ዘርፎች ስር የሚገኙ የስራ ክፍሎች በተቋሙ የአካባቢ ደህንነትና የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣምያ ስልት ውስጥ ቅድሚያ ተሰጥቶዋቸው እንዲተገበሩ የተለዩ ስራዎችና አሰራሮችን በተዘጋጀው የማካተቻ ቼክሊስት እና የዓስር አመቱን መሪ ዕቅድ መስረት ዓመታዊ የስራ ክፍሎች መደበኛ እቅድ ውስጥ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣምያና ማስተሰርያ ስራዎችን በማካተት (Mainstream) እንዲተገብሩ በቂ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

የተዘጋጀ እና የተተገበረ ለአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ መቀነሻ ስራዎች በመተግበር የቀነሰ ሙቀት አማቂ ጋዝ በሚ/ን ሜ/ቶን በመሆኑም ከሰብል ልማት ዘርፍ እስከ 2015 ዓ.ም ከተደረሰበት 14.34 ሚ/ን ሜ/ቶን Co2e በሚቀጥሉት ሦስት አመታ 13.71 ሚ/ን ሜ/ቶን Co2e በመቀነስ በ2018 ዓ.ም 28.05 ሚ/ን ሜ/ቶን Co2e ማድረስ፤ ከተፈጥሮ ሀብት ልማት ዘርፍ 2015 ዓ.ም ከተደረሰበት 22.8 ሚ/ን ሜ/ቶን Co2e በሚቀጥሉት ሦስት አመታት 10.05 ሚ/ን ሜ/ቶን Co2e በመቀነስ በ2018 ዓ.ም 32.85 ሚ/ን ሜ/ቶን Co2e ማድረስ፤ ከእንስሳት ሀብት ልማት ዘርፍ 2015 ዓ.ም ከተደረሰበት 20.40 ሚ/ን ሜ/ቶን Co2e በሚቀጥሉት ሦስት አመታት 16.11 Co2e በመቀነስ በ2018 ዓ.ም 36.51 ሚ/ን ሜ/ቶን Co2e ማድረስ ሲሆን በአጠቃላይ የግብርና ሴክተርን የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ቅነሳ 2015 ዓ.ም ከተደረሰበት 57.54 ሚ/ን ሜ/ቶን Co2e በሚቀጥሉት ሦስት አመታት 39.87 ሚ/ን ሜ/ቶን Co2e በመቀነስ በ2018 ዓ.ም 97.41 ሚ/ን ሜ/ቶን Co2e ይደርሳል፡፡

ይህንን ውጤት ለማምጣት በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት ከ2016-2018 ዓ.ም በስራ ክፍሉ የሚተገበሩ ተግባራት ዕቅድ እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርቧል፡-

በተቋሙ ስር የሚገኙ የተለያዩ የስራ ክፍሎች፣ ፕሮግራሞችና ተጠሪ ተቋማቶች የCRGE ስራዎችን የዓመታዊ ዕቅዳቸው በማካተት (Mainstream) እንዲተገብሩ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፤ ከአየር ንብረት ጋር የተስተጋበረ የግብርና ልማትን (Climate Smart Agriculture) እየተገበሩ ላሉ አርሶ/አርብቶ አደሮች ማበረታቻ ስርዓት (Incentive Mechanism) ለመዘርጋት የሚያግዝ የህግ ማዕቀፍ ይዘጋጃል፤ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተስተጋበረ የግብርና ልማት ስትራቴጂ ሰነድ ለመከለስ ተሞክሮዎችንና መረጃ ማሰባሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን ክፍተቶችን የመለየትና የመከለስ ስራዎች ይከናወናሉ፤ ከአየር ንብርት ለውጥ ጋር የተስማማ "CSA Taskforce" እና በየስራ ክፍሉ የሚገኙ ፎካሎችን በማጠናከር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ስራን የመደገፍ ስራ ይሰራል፤ የግብርና ዘርፍን የረጅም ዘመን ዝቅተኛ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳ ስትራቴጂን (Agricultural Sector Long Term - Low Emission Development Strategy) በሚፈለገው ደረጃ እንዲተገበር ለማስቻል ለባለድርሻ አካላት የማስተዋወቂያና ወደ ተግባር ማስገቢያ መድረክ ይዘጋጃል፤ በተጠሪ ተቋማትና ክልሎች ያለውን የአደረጃጀት ክፍተት ለማሻሻልና የመረጃና ትስስር ስርዓት ለመፍጠር የሚያስችል ከቁልፍ የባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ የምክክር መድረክ ይዘጋጃል፣ የአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ስቲሪንግ ኮሚቴ የውይይት መድረክ ወቅታቸውን ጠብቀው ይካሄዳሉ፤ የግብርና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ስራ የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት እንዲያረጋግጡና ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተጣጥሞ እንዲተገበር ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፤ የአበባ እርሻ ልማትን የአካባቢ አያያዝ ሥርዓት ውጤታማነት ለማሻሻል የሚያስችል የድጋፍና

ክትትል ስራ ይሰራል፤ በግብርና ሚኒስቴር የሚተገበሩ የልማት ፕሮጀክቶችን/ፕሮግራሞችን የስራ እንቅስቃሴ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተጣጥሞ እንዲተገበርና የአካባቢና ማህበራዊ አያያዝ ፍሬምዎርክ በመተግበር የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት እንዲያረጋግጡ ክትትልና ድጋፎች በስፋት ይደረጋሉ፤ የግብርናን CRGE ትግበራ የአፈፃጸም ኦዲት የተመለከተ የመስክ ዳሰሳ በክልሎች ይካሄዳል፤ የአካባቢ ደህንነትና የአረንጓዴ ልማት ስራዎች በጥራት እንዲተገበሩ በየደረጃው ላሉ አመራርና ፈጻሚ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች በስፋት ይሰጣሉ።

### 3.7.4. የስርዓተ ፆታ

በግብርናዉ ዘርፍ ሴቶችና ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች (አካል ጉዳተኞች ፣ አረጋዉያንና ሌሎችም) ለሀገር እድገትና ብልፅግና የሚያበረክቱትን የማይተካ ሚናና ድርሻ በማጉላት በህብረተሰቡ ውስጥ ተንሰራፍቶ የሚገኘውን ስር የሰደደ የተዛባ አመለካከትና አስተሳሰብ በመቀየር ፍትሀዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ ነው።

#### ሀ) የአቅም ግንባታ ስራዎች

የስርዓተ ፆታና ማህበራዊ ጉዳይን አካቶ ከመስራት አኳያ (Gender and Social Inclusion) በየደረጃዉ የሚስተዋሉ የአመለካከትና የክህሎት ክፍተቶችን ለመቅረፍ በ2015 ዓ.ም ከፌደራል ፣ ከክልሎች እስከ ቀበሌ ለተዉጣጡ 2,067 ፈፃሚዎችና አስፈፃሚዎች ፣ ለፕሮጀክቶች/ፕሮግራም ፈፃሚዎችና አስተባባሪዎችና ባለድርሻ አካላት የአቅም ግንባታ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን በቀጣይ ሶስት ዓመታት ለ6,935 አካላት ለመስጠት ታቅዷል።

#### ለ) የክትትል ፣ ድጋፍና የዳሰሳ ጥናት ስራዎችን ማጠናከር

በተቋሙ የሚገኙ ሁሉም የስራ ክፍሎችና ፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞች ስርዓተ-ጾታና ማህበራዊ ጉዳይን አካቶ እንዲሰሩ (Mainstreaming) ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ በተቋሙ ስር በሚገኙ በሁሉም ተጠሪ ተቋማት ሥርአት ጾታና ማህበራዊ ጉዳይን አካቶ እንዲሰሩ (Mainstreaming) ክትትልና ድጋፍ። በ2015 ዓ.ም በስምንት ክልሎች በተመረጡ 16 ወረዳዎችና 16 ቀበሌዎች እንዲሁም በሁለት ከተማ አስተዳደሮች የክትትልና ድጋፍና የዳሰሳ ጥናት ስራዎች የተሰራ ሲሆን በሁሉም ክልሎች በተመረጡ 66 ወረዳዎችና 66 ቀበሌዎች በዋናነት በእንስሳት ሀብትና የሰብል ልማት ስራዎች፣ በግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ፣ በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ስራዎች ፣ በመስኖ አጠቃቀም፣ በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ስራዎች ፣ በግብይት ግብዓት አቅርቦትና ተደራሽነት፣ በገጠር ስራ ዕድል ፈጠራ ስራዎች ፣ በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ስራዎች ሴቶችና ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ፍትሀዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነታቸዉን በተመለከተ የክትትልና ድጋፍና የዳሰሳ ጥናት ስራዎችን መስራት ፣ እንዲሁም ወቅታዊና ችግር ፈቺ ግብረ-መልስ መስጠት፤ በግብርና ሴክተር ውስጥ የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች Social Safeguarding and Gender Based Violence አካቶ ከመተግበር አኳያ ክትትልና ድጋፍ ማደረግ።

የሰቆጣ የቃልኪዳን ስምምነት (Sekota Declaration) በተደረገባቸው ወረዳዎች የህጻናት፤ ሴቶችና የወጣቶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ዙሪያ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤ በተመረጡ ወረዳዎች እና

መንደሮች የማህበረሰብ ውይይት ማካሄድና አፈፃፀሙን የመከታተል ስራ መስራት፤ ሴት አርሶ አደሮች የአየር ንብረት ለውጥን ያማከለ ዘመናዊ ግብርና ላይ ተሳታፊነትና ተጠቃሚ መሆናቸውን በተመለከተ መከታተልና መደገፍ፣ ሴት አርሶ አደሮች የአየር ንብረት ለውጥን ያማከለ በዘመናዊ የግብርና ስራዎች ላይ ተጠቃሚ መሆናቸዉን መከታተልና መደገፍ፤ እንዲሁም በተለያዩ የግብርና ስራዎች የህፃናት ጉልበት ብዝበዛን ለመከላከልና ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናት የወላጆቻቸውን መሬት ለማስተዳደርና ለመጠቀም ያላቸውን መሰረታዊ መብት ከማስጠበቅ አኳያ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራትን መከታተል፤ ወቅታዊና ችግር ፈቺ ግብረ-መልስ መስጠት በዋናነት የሚከናወኑ ተግባራት ናቸው።

### ሐ) የግብርና ቴክኖሎጂዎች አቅርቦትና ዉጤታማነት ስርዓትን ማሻሻል

በግብርናዉ ሴክተር የሚወጡ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ልየታ፣ የማቅረብና የማላመድ ሂደት ለሴቶች ምቹ ፣ ጊዜና ጉልበት ቆጣቢ ፣ አቅምና ዕዉቀታቸዉን እንዲሁም ምርታማነታቸዉን የሚጨምሩ መሆናቸዉን በመከታተል ወቅታዊና ችግር ፈቺ ግብረ-መልስ መስጠት፣ በግብርናዉ ሴክተር የሚወጡ የግብርና ቴክኖሎጂዎች ለወጣቶች በጊዜ ፣ በጥራትና አቅማቸዉን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ተደራሽ መሆኑን በመከታተል ወቅታዊና ችግር ፈቺ ግብረ-መልስ መስጠት በተጨማሪም በግብርናዉ ሴክተር የሚወጡ የግብርና ቴክኖሎጂዎች በአስቸጋሪ ሁኔታ ዉስጥ ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች (አካል ጉዳተኞች) ምቹ፣ ዕዉቀታቸዉን፣ አቅማቸዉንና ነባራዊ ሁኔታዎችን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ተደራሽ መሆኑን በመከታተል ወቅታዊና ችግር ፈቺ ግብረ-መልስ መስጠት።

### መ) የአሰራር ስርዓትን ማሳደግ

የማህበራዊ ጉዳይ አካቶ ትግበራ ስትራቴጂና የስልጠና ማንዋል ማዘጋጀት፣ የግብርና የስርዓተ ፆታ የስራ አካባቢ የዉስጥ መመሪያ ሰነድ ማዘጋጀት፣ የተሻሻለዉ የኤድስ ፈንድ አስተዳደርና አጠቃቀም መመሪያን ቀሪ ስራዎችን ማጠናቀቅና ወደ ተግባር መቀየር፣ በረቂቅ ደረጃ ያለውን የስርአተ-ጾታ ማካተቻ መመሪያ (Gender Mainstreaming Guideline) ማጠናቀቅና ማስተዋወቅ እንዲሁም ተፈጻሚነቱን መከታተል፣ በረቂቅ ደረጃ የለውን የስርዓተ-ጾታ ማካተቻ (Gender Mainstreaming) ማስልጠኛ ማንዋል በማጠናቀቅ ተግባራዊ ማድረግ እንዲሁም በሴክተሩ የሚዘጋጁ ስትራቴጂዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ህጎችና ልዩ ልዩ የሰነድ ዝግጅቶች ከሴቶች፣ ወጣቶች እና ይበልጥ ተገላጭ ከሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ተሳትፎና ተጠቃሚነት አኳያ በመገምገም ተገቢውን ግብዓት በመስጠት፤ ተግባራዊነታችውን የመከታተል ስራ መስራት፣ የማህበረሰብ ውይይት ማንዋል ማዘጋጀት፣ የሥርዓተ-ፆታ ሞዴል ቤተሰብን (ጂኤምኤፍ) ማቋቋም (Establishing Gender Model Family (GMF) in Order to Transform Inter and Into Household Gender Issues)፣ የጂኤምኤፍ (Gender Model Family) ማሰልጠኛ ማኑዋል ማዘጋጀት በዋናነት በእቅድ ተይዘዉ የሚከናወኑ ተግባራት ናቸው።

### ሠ) ኩነቶችን ማክበር

በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ጋር ተያይዞ ያሉትን አለማቀፍ ኩነቶችን በሀገር አቀፍ ደረጃ ማክበር (የሴቶች ቀን /March 8/, የህፃናት ፣ የወጣቶች ፣ የኤች.አይ.ቪ. ቀኖችንና ሌሎችንም ኩነቶች)

### ረ) የበጎ አድራጎት እና የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎችን ማከናወን

HIV በደማቸዉ ዉስጥ ለሚገኝ የመስሪያ ቤቱ ሰራተኞችና ወላጆቻቸውን በኤደስ ምክንያት ያጡ ህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ ማድረግ ፣ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በተቋም ደረጃ የደም ልገሳን ማሰባሰብ ፣ በ2015 ዓ.ም የተለያዩ አጋር አካላትን በማስተባበር ብር 80,000 የሚያወጡ አልባሳትና የምግብ ድጋፎችን ማድረግ የተቻለ ሲሆን በቀጣይ ዓመታት ለተለያዩ ማህበራዊ ቀውሶች ለተዳረጉ የህብረተሰብ ክፍሎች ብር 291,280 የሚያወጡ አልባሳት ፣ የምግብና ሌሎች ድጋፎችን ማድረግ ፣ በ2015 ዓ.ም አምስት የአቅመ ደካማ ማህበረሰቦች የመኖሪያ ቤቶች መገንባት የተቻለ ሲሆን በቀጣይ ሶስት ዓመታት 15 ቤቶች የሚገነቡ ይሆናል፡፡

## 3.8. ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት

የሚ/ር መ/ቤቱን አቅም የማጎልበት፣ የሀብት አጠቃቀምን እና አገልግሎት አሰጣጥን ከማሻሻል አንጻር የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር አሰራርና ውጤታማነት ለማሻሻል ግልጽነት የሰፈነበት የሰው ኃይል ስምሪት ማካሄድ፣ ለአመራር እና ለሰራተኞች የሚሰጡ ሥልጠናዎችን የመስጠት፣ የውስጥ የማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት፣ የሰራተኛ እርካታን በማሳደግ ፍልሰትን የመቀነስ ሥራዎች በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት በትኩረት ይከናወናሉ፡፡

የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር አሰራርንና ውጤታማነትን ለማሻሻል የተመደበ በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል፣ ነቀፌታ ያለበትን የኦዲት ግኝት የመቀነስ፣ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ክፍያን ድርሻ የማሳደግ፣ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዢን ድርሻ የማሳደግ፣መሰረታዊ አገልግሎትን በቅልጥፍና በመስጠት የደንበኞችን እርካታ የማሻሻል ሥራዎች በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት በትኩረት የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አሰራርንና ለውጤታማነትን ለማሻሻል መረጃ ቋት የማደራጀት በተቋሙ ወረቀት አልባ አሰራርን የመተግበር፣ በተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎቶችን አቶሜት የማድረግ የተገልጋዮችን እርካታ ደረጃ የማሳደግ ሥራዎች በመካከኛ እቅድ ዘመኑ ሶስት ዓመታት ይሰራሉ፡፡

የአጋርነት እና የህዝብ ግንኙነት አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል ለተቋም አቅም ግንባታ በሀገር ውስጥ የፋይናንስ ድጋፍ የማፈላለግ፣ ለተቋም አቅም ግንባታ በውጭ ሀገር አጋርነት የተገኘ ድጋፍ ለማሳደግ ፕሮግራም በንድፍ ፋይናንስ የማፈላለግ ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡መረጃዎችን በተለያዩ የተግባቦት ዘዴዎች ተደራሽ ለማድረግም የግብርና ዘርፍ የአፈጻጸም ውጤቶች፣ ስኬቶች መልካም ተሞክሮዎች እንዲሁም በፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች አፈጻጸም ላይ መረጃ በማደራጀት አመቺ በሆኑ የኮሚዩኒኬሽን ሚዲያዎች ለባላድርሻ አካለትና ህዝብ በየወቅት ተደራሽ ለማድረግ በሶስት ዓመቱ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል፡፡

ለተጠሪ ተቋማት እና ለክልሎች የሚደረገውን ድጋፍና ክትትልና ድጋፍ ለማሻሻል የተጠሪ ተቋማት ዕቅድን ከዘርፍ ዕቅድ ጋር ማናበብና የማጣጣም፣ የየሩብ ዓመት የተጠሪ ተቋማት ሪፖርት መገምገም፣ የክልሎችን ዕቅድ ከዘርፍ ዕቅድ ጋር ማናበብና ማጣጣም፣ በየሩብ ዓመት ከክልሎች ጋር የዘርፍ አፈጻጸም በጋራ በግብርና ልማት አመራር የጋራ መድረክ የመገምገምና ግብረመልስ የመስጠት፣ እንዲሁም ለክልሎች ወቅታዊ የአቅም ግንባታ ድጋፍ የመስጠት ሥራዎች በቅንጅት ይሰራሉ፡፡ በሁሉም ዘርፎች የተቀናጀ የመስክ



ዜና ሀ/ወልድ
የስትራቴጂክ ጉዳዮች
ሥራ አስፈጻሚ

ፕሮግራም በማዘጋጀት የክልሎች የክትትል ድጋፍ እና ግብረ-መልስ የመስጠት ሥራ በየዓመቱ ተጠናክሮ የሚከናወን ይሆናል።

የስነ-ምግባርና ፀረ ሙስና የክትትል ሥራዎችን ማሻሻል፣ በብልሹ አሰራር ዙርያ ጥቆማ በማሰባሰብ ወቅታዊ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ይደረጋል ፣ ለብልሹ አሰራር የተጋለጡ አሰራሮች በጥናት በመለየት የማሻሻያ ሀሳብ በማቅረብ ማስተካከያ እንዲደረግ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፣ የመ/ቤቱ ሰራተኞች የሀብት ምዝገባ የማከሄድ ስራ በሶስቱ ዓመታት በትኩረት ይከናወናል።

የሴቶችና ማሕበራዊ ተሳታፊነትንና ተጠቃሚነትን ማሻሻል፣ የበጎ አድራጎት እና የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎችን ለማሻሻል በሚ/ር መ/ቤቱ ሴቶች የህጻናት ማቆያ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ ሥራ፣ ወደ አመራር የመጡ ሴት ሰራተኞች ብዛት የማሳደግ፣ ሥልጠና ያገኙ ሴት ሰራተኞች ድርሻን የማሳደግ፣ ለአካል ጉዳተኛ ሰራተኞችና ተገልጋዮች ምቹ የስራ ሁኔታና ቦታ የመፍጠር ፣ የአቅመ ደካማ ማህበረሰቦች የመኖሪያ ቤቶች ግንባታን የማጠናቀቅ እንዲሁም ለማህበራዊ ቀውሶች ድጋፍ የማድረግ ሥራዎች በየዓመቱ በትኩረት የሚሰሩ ይሆናል።

## V. የግብርና ዘርፍ የመካከለኛ ዘመን ኢንቨስትመንት

